DANIEL FIKADU LAW OFFICE



# የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በ2016 ዓ.ም. የተሰጡ ያልታተሙ አስገዳጅ የህግ ትርጉሞች

**የ2016 ሁለተኛ ስብስብ ቅጽ - 2**

**በዳንኤል ፍቃዱ /ጠበቃ/**

**2016**

# DANIEL FIKADU LAW OFFICE

ዳንኤል ፍቃዱ ተስፋዬ።

danielfikadulawoffice@yahoo.com

Ethiopian Law by Daniel Fikadu

https://facebook.com/groups/1607340246185508/.https://t.me/joinchat/TDlwVN4QoPeK894b
https://t.me/joinchat/VHW6uiw5vqk6mgeZ
https://m.facebook.com/groups/1928323943874057/?ref=bookmarks
https://wordpress.com/home/lawethiopiacomment.wordpress.com
https://chat.whatsapp.com/CG7ELRZwtqV3srhBSOjgmf

መልካም ንባብ።

#Daniel Fikadu/ዳንኤል ፍቃዱ/ጠበቃና የህግ አማካሪ/

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

??/? /? ? ? 223254

ጥቅምት 05 ቀን 2016 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ረታ ቶሎሳ

በእወቀት በላይ

ቀነዓ ቂጣታ

ኑረዲን ከድር

አመልካቾች፡-1ኛ. አቶ አበባው ታደሰ ጠበቃ በረከት ቡሽራ ቀረቡ

2ኛ. አቶ ጌታሁን አበባው

ተጠሪዎች፡- 1ኛ. ወ/ሮ ሃና ወልደገብርኤል ------------------ አልቀረበም

2. አቶ ቴዎድሮስ ወልደገብርኤል --------------- ቀረበ

3. ወ/ሮ መአዛ ወልደገብርኤል --------------------- አልቀረበም

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን በዚሁ አግባብ መዝገቡ በዳኞች የእረፍት ጊዜ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች መጋቢት 12 ቀን 2014 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ. 31835 በቀን 02/03/2014 ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ

የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 382913 በቀን 17/06/2014 ዓ.ም በማጽናት መወሰኑ መሰረታዊ የህግ አተረጓጎም ስህተት የተፈጸመበት ነው በማለት እንዲታረምላቸው በመጠየቃቸው ሲሆን ተጠሪዎች በስር ፍ/ቤት ከሳሾች የነበሩ ሲሆን በዚህ ሰበር ክርክር ያልተካተቱ ግለሰብ 1ኛ ተከሳሽ፣ አመልካቾች ደግሞ እንደ ቅደም ተከተላቸው 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሽ ሆነው በውል ጉዳይ ተከራክረዋል፡፡

በስር ፍ/ቤት ተጠሪዎች በቀን 30/05/2011 ዓ.ም ባቀረቡት ክስ የተጠሪዎች እናትና አባት በህይወት የሌሉ መሆኑን፣ የአባታቸው ወራሾች መሆናቸውን በአዳማ ወረዳ ፍ/ቤት ያረጋገጡ መሆኑን፤ እናትና አባታቸው በህይወት እያሉ በአዳማ ከተማ በድሮው አጠራር ቀበሌ 20 ውስጥ በእናታችው ስም የተመዘገበ 513 ካ.ሜ የሆነ የመኖሪያ ቤት ስፋቱ 212 ካ.ሜ የሆነ ትርፍ መሬት የነበራቸው መሆኑን እንዲሁም ስፋቱ 539 ካ.ሜ የሆነ የቤት ቁጥር 201 የሆነውን በአባታችው ስም የተመዘገበውን ቤት በ1991 ዓ.ም ወደ ኤርትራ ሲሸኙ በዚህ የሰበር አቤቱታ ላልተካተተው በስር ፍ/ቤት 1ኛ ተከሳሽ ለነበረው ሰው በአደራ ሰጥተውት የሄዱ መሆኑን በመግለጽ ይሁን እንጂ 1ኛ ተከሳሽ በዚሁ ቤት ላይ ካርታ ካወጣ በኋላ በሀሰተኛ ውክልና ለ1ኛ አመልካች የሸጠው በመሆኑና 1ኛ አመልካችም ስመ ሃብቱን ልጁ ወደ ሆነው ወደ 2ኛ አመልካች በማዞር ካርታውንም አስለውጦ የያዘ በመሆኑ የሽያጭ ውሉ ህገወጥ ነው ተብሎ በ359 ካ.ሜ ላይ የተሰራው ቤት ፈርሶ አመልካቾች የእናትና የአባታችንን ይዞታ እንዲያስረክቡን ይወሰንልን በማለት ጠይቀዋል፡፡

የስር 1ኛ ተከሳሽም ስፋቱ 359 ካ.ሜ የሆነ ይዞታ የሸጥኩ ስለመሆኑ ማስረጃ ስላልቀረበና ሽያጭ የፈጸምኩትም የተጠሪዎች እናት የሆኑት ወ/ሮ ወለተ ሀይማኖት አላዘር በሰጡኝ ውክልና በመሆኑ ክሱ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡

አመልካቾችም በጋራ ሆነው ባቀረቡት መልስ የተጠሪዎች እናት ወ/ሮ ወለተ ሀይማኖት አላዘር ለስር 1ኛ ተከሳሽ በሰጡት ውክልና መሰረት ቤቱን ለ1ኛ አመልካች የሸጠ በመሆኑ በሀሰተኛ ውክልና የተሸጠ በማስመሰል ያቀረቡት ክስ ተገቢነት የለውም፡፡ ውክልናው ሀሰተኛ ስለመሆኑም ሆነ ተጠሪዎች የወ/ሮ ወለተ ሀይማኖት አላዘር ወራሾች ስለመሆናቸው ያቀረቡት ማስረጃ የለም፡፡ በሽያጭ ውሉ የተሸጠው ቤት ስፋት 765 ካ.ሜ ሲሆን ይህም በተጠሪዎች እናት ስም የካርታ ቁጥር 967/93 በሆነ የተካተተ ሆኖ እያለ ስፋቱ 359 ካ.ሜ የሆነ ይዞታ በአባታቸው ስም እንደሚገኝ አስመስለው ማቅረባቸው ተገቢነት የሌለው በመሆኑ ውሉ ጉድለት የለበትም፡፡ ጉድለት አለበት ቢባል እንኳ በቀን 05/03/1993 ዓ.ም በተደረገው ውል የተሸጠው ቤት በጭቃ የተሰራ ግምቱ 60,000.00( ስልሳ ሺህ ብር) የሆነው ፈርሶ ዘመናዊ ቤት ብር 10,000,000.00 (አስር ሚሊዮን) በሚሆን የተገነባበት ስለሆነ ተጠሪዎች ተገቢ ያልሆነ ብልጽግና ለማግኘት ያቀረቡት ክስ በመሆኑ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአመልካቾች የቀረበውን መቃወሚያ ተቀብሎ ውሉ እንዲፈርስ የቀረበው ክስ በይርጋ የታገደ ነው በማለት የተጠሪዎችን ክስ ውድቅ በማድረግ ብይን የሰጠ ቢሆንም ተጠሪዎች በዚህ ብይን ቅር ተሰኝተው ይግባኛቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት

ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው ፍርድ ቤቱም በተጠሪዎች የቀረበው ክስ የመፋለም ክርክርን መሰረት ያደረገ በመሆኑ ክሱ በይርጋ የሚታገድ አይደለም በማለት የስር ፍርድ ቤትን ብይን ሽሮ ጉዳዩን ወደ ስር ፍርድ ቤት የመለሰው ሲሆን የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም በቀሪ መቃወሚያዎች ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ ውድቅ አድርጎ በፍሬ ጉዳዩ ላይም የተጠሪዎችን ክስ ተቀብሎ የስር 1ኛ ተከሳሽ ሽያጩን ያከናወነው ቤቱን ለመሸጥ ውክልና ሳይሰጠው ስልጣን ሳይኖረው መሆኑን በመጥቀስ የሽያጭ ውሉን በማፍረስ አመልካቾች አከራካሪውን ቤትና ቦታ ለተጠሪዎች እንዲያስረክቡ ውሳኔ የሰጠ ቢሆንም አመልካቾች በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝተው ይግባኛቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ውሳኔውን ሽሮ ጭብጦች መስርቶ ጉዳዩ በድጋሚ እንዲታይ በሰጠው መመሪያ መሰረት ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን አከራክር ማስረጃዎቻቸውን መርምሮ የተጠሪዎች እናትና አባት በድምሩ አሁን ክስ የቀረበበት 1124 ካ.ሜ የጋራ ይዞታ የነበራቸው መሆኑን ከምስክሮች ቃል መረዳት የተቻለ ሲሆን የተጠሪዎች ወላጆች ድርሻቸውን ያልተከፋፈሉ እንዲሁም የተጠሪዎች አባት ለተጠሪዎች እናት የሰጠው ውክልና የሌለ በመሆኑ እንዲሁም የተጠሪዎች እናት ለስር 1ኛ ተከሳሽ ሰጠች የተባለውን ውክልና በተመለከተም የምስራቅ ሸዋ ዞን በላከው ማስረጃ በፕሮቶኮል ላይ ከመመዝገቡ በቀር የውክልና ሰነዱ በመዝገቡ ያልተገኘ መሆኑን የገለጸ በመሆኑ የተጠሪዎች እናት ለስር 1ኛ ተከሳሽ ውክልና ሰጥታው ቢሆን እንኳ የጋራ ንብረቱን በግሏ መሸጥ መለወጥ የማትችል በመሆኑ ውክልናው ህጋዊ ውክልና አይደለም፡፡ በመሆኑም ይህን ውክልና መሰረት አድርጎ የተደረገው የሽያጭ ውል ንብረቱን ለመሸጥ ህጋዊ ስልጣን ከሌለው ሰው ጋር የተደረገ ውል በመሆኑ ውሉ ህገ ወጥ ነው፡፡1ኛ አመልካች ክርክር ባስነሳው ይዞታ ላይ ባለይዞታዎቹ ሳይቃወሙት የገነባው ቤት አጠቃላይ ግምት ብር 3,604,045.53 (ሶስት ሚልየን ስድስት መቶ አራት ሺህ አርባ አምስት ብር ከአምሳ ሶስት ሳንቲም) መሆኑን በኦሮሚያ የከተማ እና ቤቶች ልማት ቢሮ የሚመራ ኮሚቴ ካቀረበው ሪፖርት መረዳት የተቻለ በመሆኑ ተጠሪዎች በፍ/ብ/ህ/ቁ.1179 መሰረት ይህንኑ ግምት ለአመልካቾች ከፍለው ቤቱን መውሰድ ይችላሉ፡፡ 1ኛ አመልካች ክርክር ያስነሳውን ቤትና ቦታ የገዛበትን ዋጋ እና በክርክሩ ያወጣውን ወጪ ከስር 1ኛ ተከሳሽ የመጠየቅ መብቱ ተጠብቋል በማለት ወስኗል፡፡

አመልካቾችም በዚህ ውሳኔ ቅሬታ አድሮብናል በማለት ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በተለያየ መዝገብ የይግባኝ አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱም ከመረመረ በኋላ የስር ፍ/ቤት ውሳኔን በማፅናት ወስኗል፡፡

አመልካቾችም የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት መጋቢት 12 ቀን 2014 ዓ.ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ለዚህ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም፦ ከአመልካቾች ጋር የተደረገው የሽያጭ ውል ህዳር 5 ቀን 1993 ዓ.ም የተደረገ በመሆኑና የተጠሪዎች ክስ በ2011 ዓ.ም ከ18 አመት በኋላ የቀረበ በመሆኑ ክሱ በይርጋ ይታገዳል በሚል ያቀረብነውን መቃወሚያ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ 308422 ውድቅ ያደረገው ክሱ የመፋለም ክስ ነው

በማለት ሲሆን መጨረሻ ላይ የተሰጠው ውሳኔ ከሽያጭ ውል ህጋዊነት ጋር ተያይዞ በመሆኑ ይርጋውን ውድቅ ማድረጉ ስህተት ያለበት ነው፡፡ የስር ከፍተኛ ፍ/ቤት 1ኛ ተከሳሽ ንብረቱን ያገኘው በውክልና መሆኑን አረጋግጦ ከተቀበለ በኋላ የተጠሪዎች ክስ እናታችን በሰጠችው ውክልና የአባታችን ድርሻም አብሮ ለ3ኛ ወገን ተላልፎብናልና የሽያጭ ውሉ ይፍረስልን የሚል ባልሆነበት የተጠሪዎች እናት ውክልና የሰጠችው ስልጣን በሌላት ንብረት ላይ በመሆኑ ውክልናውም ሆነ ሽያጩ ህገወጥ ነው በማለት ከቀረበው ክስ ውጭ መወሰኑ ልናቀርብ የምንችለውን መከላከያ እንዳናቀርብ በማድረግ የመከላከል መብታችንን ያጣበበ አግባብነት የሌለው ነው፡፡

የተጠሪዎች አባት በ1984 ዓ.ም ሞተው ተጠሪዎችም የአባታቸው ወራሽነታቸውን በዚሁ አመት ያረጋገጡ ሲሆን ተጠሪዎች ያቀረቡት የወራሽነት ማስረጃ የአባታቸው ልጆች መሆናቸውን እንጂ ሊወርሱ የሚገባው ንብረት ተጣርቶ የተገለጸበት አይደለም፡፡ የቤቱ ካርታም ለተጠሪዎች እናት የተሰጠው አባታቸው ከሞቱና ወራሽነት ከተረጋገጠ ከ9 አመት በኋላ በመሆኑ እንዲሁም ቤቱ ወደ አመልካቾች የተላለፈው ህዳር 05 ቀን 1993 ዓ.ም በመሆኑ የተጠሪዎች አባት ከዚህ ቤት ድርሻ እንዳላቸው ለመገመት የሚያስችል መሰረት የሌለ በመሆኑ የተሸጠው ንብረት የባልና የሚስት የጋራ ንብረት ነው ለማለት የሚቻልበት የህግ መሰረት ሳይኖር የስር ፍ/ቤቱ የጋራ ነው በሚል መደምደሙ አግባብ አይደለም፤ አመልካች ቤቱ የተጠሪዎች እናት የግል ንብረት መሆኑን የሚያሳዩ የሰነድ ማስረጃዎችን አይቼ በጥንቃቄና በቅን ልቦና የገዛሁ በመሆኑ እንዲሁም ድርሻዬ ተሸጦብኛል የሚለው ወገን ከሻጩ ከሚጠይቅ በቀር ንብረቱ ለ3ኛ ወገን በሽያጭ ከተላለፈና ስመ ሀብት ከተላለፈ በኋላ የሽያጭ ውሉ ሊፈርስ እንደማይገባ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 41857፣ 46527 እና በሌሎችም አስገዳጅ ውሳኔ የሠጠበት ሆኖ እያለ የስር ፍ/ቤት ሽያጭ ውሉ ህገወጥ ነው በማለት መወሰኑ ተገቢነት የለውም፤ አሁን እንድለቅ የተወሰነው ቦታ ከሌሎች ሰዎች የገዛሁትን ጨምሮ ይዞታው በሙሉ 1169.25 ካ.ሜ በስሜ ተመዝግቦ እኔም ለ2ኛ አመልካች በስጦታ ያስተላለፍኩ በመሆኑ እና በቦታው ላይም ከ20 ክፍል ቤቶች በላይ ተገንብቶ የሚገኝ በመሆኑ የሽያጭ ውሉ በተደረገበት ጊዜ ወደ ነበርንበት ሁኔታ መመለስ አስቸጋሪ ሆኖ እያለ የተገነቡትን ቤቶች ግምት በመቀበል ለተጠሪዎች እንድንለቅ መወሰኑ ከህገ መንግስቱ አንቀጽ 40(3) የሚቃረን ስለመሆኑ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 105125፣30101፣36638 እና ሌሎችም ላይ አስገዳጅ ትርጉም የሠጠበት በመሆኑ፤ ተጠሪዎች ዜግነታቸው ኤርትራዊ በመሆኑ በፍ/ህግ/ቁ. 390 በኢትዮጵያ ውስጥ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤት መሆን እንደማይችሉ የተደነገገ በመሆኑ እና ግንቦት 07 ቀን 2001 ዓ.ም በሚኒስትሮች ምክር ቤት በወጣው ደንብ አንቀጽ 3 የቀድሞ ንብረታቸው ሊመለስላቸው የሚችለው ንብረቱ ያልተሸጠ ከሆነና በወኪሎቻቸው እጅ የሚገኝ ከሆነ ብቻ መሆኑ የተደነገገ ሆኖ እያለ በተያዘው ጉዳይ ንብረቱ ለ3ኛ ወገን የተላለፈ በመሆኑ የስር ፍ/ቤቶች ይዞታው ለተጠሪዎች ይመለስላቸው በማለት የሰጡት ውሳኔ እነዚህን ህጎች የጣሰ ነው፡፡

በተጠሪዎች አባት ስም የተመዘገበ 359 ካ.ሜ በተመለከተ በ1956 ዓ.ም የተደረገ የግዥ ውል እንጂ ከአዋጅ ቁጥር47/67 በኋላ በተጠሪዎች አባት ስም የተመዘገበ ይዞታ ስለመኖሩ ምንም አይነት የሰነድ ማስረጃ የሌለ በመሆኑና የቤቶች ግምት በባለሙያ ሳይሆን በወቅቱ የዋጋ ግምት ሊተመን እንደሚገባው የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 35003 አስገዳጅ ትርጉም ሰጥቶበት እያለ የስር ፍ/ቤት ከ20 ሚልየን ብር በላይ የሚያወጣውን ቤት በብር 3,604,045.53 (ሶስት ሚልየን ስድስት መቶ አራት ሺህ አርባ አምስት ብር ከአምሳ ሶስት ሳንቲም) ብቻ ገምቶ ውሳኔ መስጠቱ መሰረታዊ የህግ አተረጓጎም ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ተሽሮ በአማራጭ ክሱ በይርጋ የታገደ ነው፣ ውሉ ፈራሽ ነው የሚባል ከሆኑ አመልካች የወቅቱን የቤቶቹን ግምት ብር 293,410.00 (ሁለት መቶ ዘጠና ሶስት ሺህ አራት መቶ አስር ብር) ለተጠሪ በመክፈል ቤቱን ማስቀረት ይችላል እንዲባል፣ ተጠሪዎች ግምቱን ለአመልካች ይክፈሉ የሚባል ከሆነ በመሃንዲስ የቀረበው የግንባታ እቃ ግምት ሳይሆን ቤቱ በአሁኑ ወቅት ሊያወጣ የሚችለው የገበያ ዋጋ ተገምቶ ሊከፈል ይገባል ተብሎ ይወሰንልን የሚል ነው፡፡

አቤቱታው የቀረበለት የሰበር አጣሪ ችሎትም ተጠሪዎች በስር ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ አቤቱታ ከወላጆቻቸው ጋር ወደ ኤርትራ ሲሸኙ ለክርክር ምክንያት የሆነውን ቤት የእህታቸው ባለቤት ለሆነው 1ኛ ተከሳሽ በውክልና ሳይሆን በአደራ ሰጥተው የሄዱ መሆኑን በመጥቀስ የተከራከሩ ሲሆን የስር ፍ/ቤት ባደረገው ማጣራት የአመልካች ወላጅ እናት ለ1ኛ ተጠሪ ቤቱን የሰጡት በውክልና መሆኑን ባረጋገጠበት ሁኔታ የተጠሪዎች አባት ለተጠሪዎች እናት ውክልና የሰጡ ስለመሆኑ አልተረጋገጠም ለ1ኛ ተከሳሽ የተሰጠው ውክልና ህጋዊ አይደለም አመልካቾች ቀድሞ የነበረውን ቤት አፍርሰው ሲሰሩ ተጠሪዎች ስላልተቃወሙ አሁን ያለውን የቤቱን ዋጋ ለአመልካች ከፍለው ቤቱን እንዲረከቡ በማለት የወሰነበትን አግባብነት ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 246፣ 247 እንዲሁም የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1179(2) እና 1180 ለጉዳዩ ያለውን አግባብነት ከመሰረታዊ የክርክር አመራር እና ማስረጃ ምዘና መርህ እና ሌሎች ተያያዥ ነጥቦች ጋር በማገናዘብ መጣራት ያለበት በመሆኑ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ይቅረብ ግራ ቀኙም የጽሁፍ ክርክር ይለዋወጡ በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ትዕዛዝ መሰረት ተጠሪዎች ግንቦት 23 ቀን 2014 ዓ.ም የተጻፈ መልስ ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም፡- የተጠሪዎች እናት በ1992 ዓ.ም ከዚህ አለም በሞት ተለይተው ባለበት በሽያጭ ውሉ ላይ ለስር 1ኛ ተከሳሽ ውክልና ተሠጠ የተባለው በ1996 ዓ.ም ነው፡፡ አመልካች ቤቱን በውክልና ከተሰጠው ከዚሁ ሰው ገዛሁ የሚሉት በ1993 ዓ.ም ነው፡፡ በኋላ ላይ በ1989 ዓ.ም ተሠጠ የተባለው ውክልናም ቢሆን በባህር መዝገብ ከመመዝገቡ በቀር የሌለ መሆኑ የተረጋገጠ ሲሆን በ1989 ዓ.ም በኢትዮጵያና በኤርትራ መካከል አለመግባባት አልነበረምና የጋራ በሆነው ንብረት ላይ የተጠሪዎች እናት ውክልና ሊሰጡ የሚችሉበት ሁኔታ የሌለ በመሆኑ ውክልናው በሃሰት የቀረበ ነው፡፡ ውክልና አለ ቢባል እንኳ በሽያጭ የተላለፈው ቤት ካርታ ቁጥር 967/93 ካርታ የወጣለት በ1993 ዓ.ም በመሆኑ በ1989 ዓ.ም ካርታ ቁጥሩ ተጠቅሶ ውክልና ሊሰጥ አይችልም፡፡ የሰበር አጣሪ ችሎቱ በያዘው ጭብጥ የስር ፍ/ቤት ውክልና ለ1ኛ ተከሳሽ መሰጠቱ በተረጋገጠበት... ይበል እንጂ የስር ፍ/ቤቱ ውክልናው ህገ ወጥ ነው በማለት

ያልተቀበለው በመሆኑ ይህ ጭብጥ ተገቢነት የለውም፡፡ አመልካቾች ቀድሞ የነበረውን ቤት አፍርሰው ሲገነቡ ተጠሪዎች ስላልተቃወሙ በሚል ከፍ/ብ/ህ/ቁ.1179 አንጻር ለማጣራት በሚል የተያዘው ጭብጥም ቢሆን ቤቱ ሰተላለፍም ሆነ ግንባታው ሲገነባ ተጠሪዎች በአገር ያልነበሩ እና የማያውቁ በመሆኑ ከውጤት አንጻር ይህ ድንጋጌ የሚቀይረው ነገር አይኖርም፡፡

አመልካቾች የይርጋ መቃዎሚያቸውን እና የውጭ ዜጎች በኢትዮጵያ ውስጥ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤት መሆን አይችሉም የሚለው መቃወሚያቸውን በተመለከተ ብይን ተሰጥቶበት የታለፈ በመሆኑ ለቀጣይ ፍ/ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይገባቸዋል እንጂ በመመሪያ በተመለሰ መዝገብ ላይ በተደረገ ክርክር ሊያነሱ እይችሉም፡፡  በጭብጥ አያያዝ ረገድ ቅሬታ ያለው ወገን ለቀጣይ ፍ/ቤት ይግባኝ ማለት ይችላል እንጂ የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ጭብጥ ተይዞ በተመራለት መሰረት በሰጠው ውሳኔ ላይ ሊቀርብ አይችልም፡፡ አመልካቾች በጭብጥ ረገድ ያቀረቡት ክርክርም የሌለ በመሆኑ ይህ ክርክር ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የሚገባው አይደለም፡፡ የተጠሪዎች የወራሽነት ማስረጃ በተሸጠው ንብረት ማህደር ውስጥ እስካሁንም ያለ በመሆኑ ንብረቱ የተጠሪዎች እናት ብቻ አለመሆኑን አመልካች እያወቁ የገዙት በመሆኑ የቅን ልቦና ገዥ ሊባሉ አይችሉም፡፡

ከቅን ልቦና ውጭ በህገ ወጥ መንገድ ግንባታ የገነቡ በመሆኑም ከተጠሪዎች የተሻለ መብት አልመሰረቱም፡፡ የውል ህግ አንቀጽ 1817 ተፈጻሚነት የሚኖረው በተዋዋዩች መካካል እንጂ የ3ኛ ወገኖች መብት ጎድቶ በተደረገ ውል ላይ አይደለም፡፡ የአዳማ ከተማ መሬት ልማትና ማኔጅመንት ጽ/ቤት በተጠሪዎች አባት ስም የተመዘገበ 359 ካ.ሜ ስፋት ያለው ቦታ ባልታወቀ አግባብ ወደ አመልካች የዞረ መሆኑን ገልጸው ማህደሩም በችሎት ቀርቦ ውሳኔ የተሰጠበት በመሆኑና አመልካቾችም ክደው ያልተከራከሩ በመሆኑ በዚህ ችሎት ያቀረቡት ሙግት ተገቢነት የለውም፡፡ በስር ፍ/ቤት የተጣራው የንብረቱ ግምት አሁን ያለው የገበያ ዋጋ በመሆኑ በግምት ረገድ የቀረበው ቅሬታ ተገቢነት የሌለው በመሆኑ የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ስህተት የለበትም ተብሎ እንዲጸና እንጠይቃለን የሚል ነው፡፡

አመልካቾችም ሰኔ 8 ቀን 2014 ዓ.ም የተጻፈ የመልስ መልስ በማቅረብ አቤቱታቸውን አጠናክረዋል፡፡

ከዚህ በላይ አጠር ባለመልኩ የተገለጸዉ የግራ ቀኙ ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት የሚመለከት ሲሆን እኛም የሰበር አጣሪ ችሎት የያዘዉን ማስቀረቢያ ጭብጥ መሰረት በማድረግ በውሳኔው ላይ በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡በመሰረቱ የተከራካሪ ወገኖች ክርክር በፍሬ ጉዳይ ላይ ብቻ የተወሰነ ከሆነ ወይም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ቀርቦ ከሆነ በዚሁ መቃወሚያ ላይ ተገቢው ብይን ከተሰጠ በኋላ ፍርድ ቤቱ ባለጉዳዮቹን የሚያከራክረው የተለያዩበት የህግ ወይም የፍሬ ነገር አግባብ ምን እንደሆነ በማረጋገጥ ለጉዳዩ ትክክለኛ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችለውን ጭብጥ በመያዝ  መሆኑን የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ.246(1) የሚደነግግ ሲሆን ለሚያዘው

ጭብጥ መነሻው በከሳሹ የሚቀርበው ክስ መሆኑ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.248(ሀ) መመልከቱም አንድ ፍርድ ቤት ክርክሩን በአግባቡ ለመምራት መሰረት የሚያደርገውና በመጨረሻም እልባት የሚሰጠው በክሱ የተጠየቀውን ዳኝነት መሰረት በማድረግ መሆኑን ያሳያል፡፡(የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.182(2) ን ይመለከቷል፡፡) የተያዙትን ጭብጦች መሰረት በማድረግ የሚሰጠው ውሳኔ የተያዘው ጭብጥ እንዴት እንደተወሰነና የተወሰነበት ምክንያት መገለፅ ያለበት መሆኑን የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ.182(1) የሚያሳይ ሲሆን ስለ እየአንዳንዱ ጭብጥ አወሳሰን የተሰጠው ምክንያት ሁሉ በትችት ላይ መገለፅ ያለበት መሆኑ በቁጥር 182(3) መመልከቱ ፍርድ ቤቱ ለጉዳዩ እልባት ሲሰጥ የግራ ቀኙን ክርክር እንዲሁም ማስረጃ የመዘነበትን ፤የመረመረበትንና ውድቅ ያደረገበትን አግባብ በዝርዝር ማመልከት ያለበት መሆኑን ያሳያል፡፡

አሁን በያዝነው ጉዳይ በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ በግልፅ እንደተመለከተው ተጠሪዎች በስር ፍርድ ቤት በአመልካቾች ላይ ክሱን ያቀረቡት የቤት ቁጥር 201 እና በዚሁ የቤት ቁጥር ውስጥ የተካተተውን በድምሩ 765 ካሜ ይዞታ በተመለከተ በእናታቸው ወ/ሮ ወለተሀይማኖት አላዛር ስም የተመዘገበውን እናታቸው ከአባታቸው ጋር ጋብቻ መስርተው ሲኖሩ ያፈሩትን ቤትና ቦታ እናታቸው ኤርትራዊ በመሆናቸው በ14/04/1991 ዓም በመንግስት ተገደው ከሀገር ሲወጡ ለአቶ ገብረማሪያም ብስራት በአደራ የሰጡ ቢሆንም እኚህ የስር 1ኛ ተከሳሽ በሀሰተኛ ውክልና ተጠቅመው ለ1ኛ አመልካች የሸጠው መሆኑን በአባታቸው ስም ተመዘገበ ያሉትን 359 ካሜ ይዞታ በተመለከተም 1ኛ አመልካች ከወ/ሮ አልማዝ ላቀው ይዞታ ጋር በመቀላቀል 539.45 ካሜ በማድረግ ካርታ በስማቸው አውጥተው ለ2ኛ አመልካች ማስተላለፋቸውን በመጥቀስ የሽያጭ ውሉ ፈርሶ በ359 ካሜ ይዞታ ላይ የተሰራው ቤት ፈርሶ የእናታቸውንና አባታቸውን ይዞታ እንዲረከቡ እንዲወሰንላቸው በመጠየቅ ነው፡፡ተጠሪዎች ከላይ እንደተመለከተው 765 ካሜ ይዞታና ቤትን አስመልክቶ ለስር 1ኛ ተከሳሽ ያስተላለፉት በአደራ መሆኑን ከመግለፅ ውጪ ለስር 1ኛ ተከሳሽ የተሰጠው ውክልና በወ/ሮ ሀይማኖት ድርሻ ላይ ብቻ የተሰጠ ተደርጎ የሚወሰድ መሆኑን በማመልከት በአባታቸው ድርሻ ላይ ጭምር የተደረገው የሽያጭ ውል እንዲፈርስላቸው በዚህ አግባብ የሽያጭ ውሉ ሲፈርስም አጠቃላይ በእናታቸው ስም ያለውን ይዞታና ቤት እንዲረከቡ በመጠየቅ ክስ ማቅረባቸውን የስር ፍርድ ቤት መዝገብ አያሳይም፡፡

1ኛ አመልካች አከራካሪውን በተጠሪዎች እናት ስም ተመዝግቦ ይገኝ የነበረውን የተጠሪዎች አባት ይዞታ የሆነውን በማካተት 765 ካሜ ሆኖ በወ/ሮ ወለተሀይማኖት አላዛር ስም ካርታ የተሰራለትን ቤትና ቦታ የወ/ሮ ወለተሀይማኖት ወኪል ከሆነው የስር 1ኛ ተከሳሽ ጋር በ05/03/1993 ዓም በተደረገ የግዢ እና ሽያጭ ውል በህጉ አግባብ ገዝተው ግምቱ ብር 10,000,000.00 የሚያወጣ ግንባታ ያከናወኑበትና አሁንም ድረስ ይዘውት የሚገኙት መሆኑን ጠቅሰው የተከራከሩ ሲሆን ተጠሪዎች ይህ ውክልና በሀሰት የተዘጋጀ መሆኑን፤እናታቸው ለስር 1ኛ ተከሳሽ የሰጡት ውክልና አለመኖሩን ይዞታውና ቤቱ በስር 1ኛ ተከሳሽ እጅ የገባው በአደራ እንዲጠብቁት መሆኑን ገልፀው የተከራከሩ ቢሆንም 2ኛ እና 3ኛ የተጠሪዎች ምስክሮች እናታቸው ለስር 1ኛ ተከሳሽ የሰጡት ውክልና መኖር አለመኖሩን የማያውቁ መሆኑን ሲያስረዱ 1ኛ የተጠሪዎች ምስክር ብቻ (ለተጠሪዎች ምስክር ሆነው የቀረቡት ተጠሪዎች

መሆናቸውን ልብ ይሏል) እናታቸው ለስር 1ኛ ተከሳሽ የሰጡት ውክልና የሌለ መሆኑን በመጥቀስ ያስረዱ ቢሆንም የስር ፍርድ ቤት ለምስራቅ ሸዋ ዞን ዐቃቤ ህግ ፅ/ቤት ተገቢውን ትዕዛዝ ሰጥቶ ባደረገው ማጣራት በፕሮቶኮል መዝገቡ ላይ ወ/ሮ ወለተህይማኖት አላዛር ለውክልና ተቀባይ አቶ ገብረማሪያም ብስራት (የስር 1ኛ ተከሳሽ) ውክልና መስጠታቸውን የሚያሳይ ተመዝግቦ መገኘቱን መጥቀሱ ከተጠሪዎች ክስና ክርክር ይልቅ የአመልካቾች ክርክር በአስተዳደር መስሪያ ቤቱ ምላሽ የተደገፈ መሆኑን ያሳያል፡፡

ማስረጃን የመስማት፣የመመርመርና የመመዘን ስልጣን ያላቸው የስር ፍርድ ቤቶች በዋነኝነትም የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተጠሪዎች እናት ለአቶ ገብረማሪያ ብስራት ተገቢውን ውክልና መስጠታቸውን "ከዚህ ላይ ለመረዳት የሚቻለው የከሳሾች እናት ለ1ኛ ተከሳሽ ውክልና የሰጠች ሲሆን …" የሚል ሀረግ በውሳኔው ላይ በማካተት አረጋግጦ የሽያጭ ውሉ ፈርሶ አከራካሪውን ቤትና ቦታ አመልካቾች ለተጠሪዎች እንዲያስረክቡ የወሰነው እንደ ተጠሪዎች ክስ አቀራረብ ውክልናው በሀሰት የተዘጋጀ መሆኑን በማረጋገጥ ሳይሆን ከተጠሪዎች ክስና የዳኝነት ጥያቄ ውጪ የሽያጭ ውሉ ውክልና ከተሰጠበት ድርሻ በማለፍ በተጠሪዎች አባት ድርሻ ላይ ጭምር መደረጉን መሰረት በማድረግ ነው፡፡ይህም የስር ፍርድ ቤቶችየፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.182(2)፣246(1) እና 248(ሀ) ድንጋጌ ውጪ ከተጠየቀው ዳኝነት ውጪ፣ከግራ ቀኙ ክርክር ውጪ ጭብጥ በመያዝ ለግራ ቀኙ ክርክር እልባት መስጠቱን ያሳያል፡፡

የስር ፍርድ ቤቶች ተጠሪዎች ለክሳቸው መሰረት ካደረጉት የዳኝነት ጥያቄ ውጪ በመውጣት ፍርድ ማሳረፋቸው እንደተጠበቀ ሆኖ አከራካሪው ቤትና ቦታ ለ1ኛ አመልካች የተላለፈው በወ/ሮ ወለተህይማኖት ስም ካርታ ተዘጋጅቶለት መሆኑ በስር ፍርድ ቤት ከመረጋገጡ አንፃር በሰበር መዝገብ ቁጥር 41857፣46527 እና በተመሳሳይ መዝገቦች የውርስ ንብረት በሆነ ቤትና ቦታ ላይ ድርሻ አለን የሚሉ ወገኖች ንብረቱን ህጋዊ የሆነ የባለቤትነት ማረጋጫ ይዞ ከነበረ ሰው በመግዛት ስመ ሀብቱን ወደራሱ አዛውሮ የሚገኝን ሰው ለመጠየቅ የማይችሉ መሆኑን በማመልከት የሠጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም ከግምት ውስጥ ያላስገባበትን የህግ አግባብ በውሳኔው ላይ አላመለከተም፡፡

1ኛ አመልካች አከራካሪውን ቤትና ቦታ በሽያጭ ውል በእጃቸው ያስገቡት ወ/ሮ ወለተህይማኖት ብስራት ለስር 1ኛ ተከሳሽ በሰጡት ውክልና መሰረት በወ/ሮ ወለተህይማኖት ብስራት ስም በይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መመዝገቡን መሰረት አድርገው በመሆኑ ከላይ በተመለከቱት አስገዳጅ የህግ ትርጉሞች አግባብ ተጠሪዎች ቤቱንና ይዞታውን አስመልክቶ በ1ኛ አመልካች ላይ ክሱን ከማቅረብ የሚያግዳቸው መሆኑን፣ ከዚህ ይልቅ ከሽያጩ ገንዘብ ላይ ድርሻቸውን የመጠየቅ መብትን የሚሰጣቸው መሆኑን ከላይ የተመለከቱት አስገዳጅ የህግ ትርጉሞች የሚያመለክቱ ሆነው እያለ የስር ፍርድ ቤቶች በ1ኛ አመልካች ላይ የቀረበውን ክስ ተቀብሎ የሽያጭ ውሉ እንዲፈርስና አመልካቾች አከራካሪውን ቤትና ቦታ ለተጠሪዎች እንዲያስረክቡ መወሰናቸው ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን አስገዳጅ የህግ ትርጉሞች መሰረት ያላደረገ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት መሆኑን ያሳያል፡፡

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ከዚህም በተጨማሪ ተጠሪዎች በአባታቸው ስም የሚታወቅ ቀሪ ይዞታ መኖሩን ጠቅሰው ክሱን ሲያቀርቡ አመልካቾች የአባታቸው ይዞታ ተጠቃልሎ በወ/ሮ ወለተሀይማኖት ብስራት ስም ካርታ የተሰራበት መሆኑን፣መኖሪያ ቤት የሰሩበትን ቦታ አቶ አወል ከተባለ ሰው በገዙትና ቀሪውን የስር 1ኛ ተከሳሽ በውክልና በሸጠው ከፊል ይዞታ ላይ የሰሩት መሆኑን ገልፀው ከመከራከራቸው አንፃር በፍትሐ ብሄር ክርክር አንድ መብት አለ ብሎ የሚከራከር ወገን መብቱ መኖሩን የማስረዳት ሸክም ያለበት መሆኑን ይህ መብት መኖሩን ካላስረዳ ፍርድ ቤቱ ጥያቄውን ውድቅ ሊያደርገው የሚገባ መሆኑን፣ አንድ ንብረት ይገባኛል በማለት የሚከራከር ወገን ንብረቱ መኖሩን የርሱም መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ካላቀረበ ጥያቄው ውድቅ ሊደረግ የሚገባ መሆኑን በማመልከት በሰበር መዝገብ ቁጥር 44364 እና በሌሎች አግባብነት ባላቸው መዝገቦች አስገዳጅ የህግ ትርጉም ተሰጥቶ እያለ 1ኛ ተጠሪ "በአባታችን ስም የተመዘገበው ይዞታ ጀርባ የእናታችን መሬት ያለው አንድ ቦታ ውስጥ ነው፡፡" በማለት የእናትና አባታቸው ይዞታ በአንደነት የሚገኙ መሆኑን በማመልከት በአመልካቾች ክርክር አግባብ አስረድተው እያለ ከዚህ በተለየ መልኩ ሁለቱ ይዞታዎች መለያ ተደርጎላቸው የሚገኙ መሆኑን በሚያሳይ መልኩ ማረጋገጫ ባልቀረበበት የሽያጭ ውሉ ውክልና ባልተሰጠበትም ንብረት ላይ የተደረገ ነው በማለት መደምደሙ ከማስረጃ ምዘና መሰረታዊ መርህ አንፃር መሰረታዊ የህግ ስህተት መፈፀማቸውን ያሳያል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የስር ፍርድ ቤት ውሉ ሊፈርስ ይገባል የሚል መደምደሚያ ላይ መድረሱ የግራ ቀኙን ክርክር ከውል ህግ መሰረታዊ መርሆች አንፃር በመመርመር ለጉዳዩ ተገቢውን እልባት መስጠቱን እያሳያ ይህ ከሆነ ደግሞ ከውል ህግ መሰረታዊ ድንጋጌዎች የፍ/ብ/ህ/ቁ.1815 እና 1817 አንፃር ግራ ቀኙ ከውሉ መፈፀም በፊት ወደነበሩበት ሊመለሱ ይችላሉ ወይስ አይችሉም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ለግራ ቀኙ ክርክር እልባት ሊሰጥ ሲገባ ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን ድንጋጌ የፍ/ብ/ህ/ቁ.1179 በመጥቀስ፣በይዞታው ላይ ተገንብተው የነበሩት ግምታቸው ብር 293,410.00 የነበረው ቤቶች ሙሉ ለሙሉ ፈርሰው በድምሩ ዋጋቸው ብር 3,604,045.53 የሚያወጡ ቤቶች በአመልካቾች መገንባታቸውን የምስክሮቹ ቃልና የሰነድ ማስረጃዎቹ እያሳዩ ይህም ግራ ቀኙን ወደነበሩበት መመለስ በፍ/ብ/ህ/ቁ.1817(1) መሰረት ከፍ ያለ መሰናክልን የሚያስከትል መሆኑን እያሳየ፣ተጠሪዎች ይዞታውንና ቤቱን እንዲረከቡ ማድረግ የሚቻለው በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ምክንያት ከሀገር እንዲወጡ ተደርገው የነበሩ ኤርትራዊያን በኢትዮጲያ ውስጥ ያላቸውን ንብረት ማግኘት እንዲችሉ ለማድረግ በሚኒስትሮች ምክር ቤት በወጣው መመሪያ አንቀፅ 3 መሰረት ንብረቶቹ ካልተሸጡ ወይም ካልፈረሱ ብቻ ሆኖ እያለ አሁን በያዝነው ጉዳይ ግን የተጠሪዎች ወላጆች በይዞታው ላይ ያከናወኑት ግንባታ ለ1ኛ አመልካች በሽያጭ ተላልፎ ግንባታው ሙሉ ለሙሉ ፈርሶ በአመልካቾች ግንባታ የተተካ መሆኑ ማስረጃን የመስማት የመመርመርና የመመዘን ስልጣን ባላቸው የስር ፍርድ ቤቶች ተረጋግጦ እያለ የተጠሪዎች የዳኝነት ጥያቄ በይዞታው ላይ አመልካቾች ያከናወኑት ግንባታ ፈርሶ ቤቱን ለመረከብ የሚጠይቅ ሆኖ እያለ የስር ፍርድ ቤቶች ከዚህ በማለፍ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የቤቶቹን የግንባታ ዋጋ ተጠሪዎች ለአመልካቾች ከፍለው፣ ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ደግሞ የቤቱን የገበያ ዋጋ ተጠሪዎች ለአመልካቾች

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በመክፈል ይዞታውንና ቤቱን እንዲረከቡ መወሰናቸው ከላይ የተመለከቱትን ድንጋጌዎችና በሰ/መ/ቁ.39336፤47617 እና በተመሳሳይ መዝገቦች የተሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም መሰረት ያላደረገ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላገኘነው ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ውሳኔ

1. የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ. 31835 በቀን 02/03/2014 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔና ይህንን ውሳኔ በማፅናት የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 382913 በቀን 17/06/2014 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ.348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. በአዳማ ከተማ ከፍተኛ 2 ቀበሌ 20 ውስጥ የሚገኘውን አከራካሪውን ቤትና ቦታ 1ኛ አመልካች የተጠሪዎች ወላጅ እናት ለአቶ ገ/ማሪያም ብስራት በሰጡት ውክልና መነሻነት በሽያጭ ውል ያገኙት በመሆኑ የሽያጭ ውሉ ፈርሶ አመልካቾች ለተጠሪዎች የሚያስረክቡበት የህግ አግባብ የለም ብለናል፡፡

3. ይህ ውሳኔ ተጠሪዎች የሽያጩን ገንዘብ ቤቱንና ቦታውን በሽያጭ ባስተላለፉት አቶ ገ/ማሪያም ብስራት ላይ ክስ አቅርበው ከመጠየቅ የሚያግዳቸው አይደለም ብለናል፡፡

4.ግራ ቀኙ በሰበር ክርክሩ ምክንያት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

**<u>ጉዳዩ ውሳኔ ስላገኘ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ይመለስ፡፡</u>**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ማ/ተ

*ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

**በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**
**የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት**

የሰ.መ.ቁ.245483

ጥቅምት 5 ቀን 2016 ዓ.ም

ዳኞች፡- 1. ብርሃኑ አመነዉ

2. ረታ ቶለሳ

3. በዕዉቀት በላይ

4. ቀነዓ ቂጣታ

5. ኑረዲን ከድር

አመልካች.....ኢትዮ ጃፓን ናይለን ጨርቃጨርቅ አ.ማ ተወካይ ብዙነሽ ጌዲወን ቀረቡ

ተጠሪ..........

1. አቶ ፍቃድ ቡና
2. አቶ ይሳኮር መላኩ
3. አቶ ቴዎድሮስ አበራ
4. አቶ ፍቅሬ አለሙ
5. አቶ ንጉሴ ቶሌራ
6. አቶ ዘዉዱ መንገሻ
7. አቶ ጫላ ባይሳ
8. አቶ ድሪባ ተሾመ
9. አቶ ጎሳ ገመቹ
10. አቶ ጀመረ አደበ

31. ወ/ሮ ትርንጎ አለማየሁ
32. አቶ አማረ ናደዉ
33. ወ/ሮ ቅድስት ደበበ
34. አቶ መስፍን በቀለ
35. ወ/ሮ ተዋበች ወ/ሰማየት
36. ወ/ሮ ወርቅነሽ ካሱ
37. አቶ እየሱስ ንጉሴ
38. ወ/ሮ ባንቺአምላክ ጣሰዉ
39. ወ/ሮ ታደሉ አበራ
40. ወ/ሮ አለምወርቅ የሻነዉ

*ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

11. አቶ ከፈኒ ዳባ
12. ወ/ሮ መስታወት ተገኝ
13. አቶ ታሪኩ ደሳለኝ
14. ወ/ሮ ትዕግስት አስማማዉ
15. አቶ አረጋሽ ራጎ
16. ወ/ሮ አሱናዋድ ፈይሳ
18. አቶ ሐጎስ ዳሩ
19. አቶ ዘማጅ ገብሩ
20. አቶ ደረጀ ነጋሽ
21. አቶ ፋንታሁን ምትኩ
22. አቶ አሰግድ አለማየሁ
23. አቶ ዳንኤል ዳምጤ
24. አቶ ገ/ኪዳን ገ/እግዚ
25. ወ/ሮ ገነት ተፈራ
26. ወ/ሮ እመቤት አለማየሁ
27. ወ/ሮ እመቤት እንዳለ
28. ወ/ሮ መሰረት ሞጆ
29. ወ/ሮ ትዝታ ተፈራ
30. ወ/ሮ ጥሩወርቅ ረጋሳ
41. አቶ ብሩክ ፋንታሁን
42. ወ/ሮ ቦጌ አበራ
43. ወ/ሮ ሸዋዬ ገላሶ
44. አቶ መሐመድ ካሶ
45. አቶ መንገሻ ለማ
46. አቶ ንጉሴ ተኮላ
47. አቶ ማሙሽ አዱኛ
48. አቶ ፍሬዉ በቀለ
49. አቶ አስፋዉ አስመራ
50. አቶ ትንሳዬ ተስፋዉ
51. አቶ ደስታ ታመነ
52. አቶ ብዙነህ ተፈራ
53. አቶ ኤልያስ ጉልላት
54. አቶ ብርሃኑ ሃይሌ
55. ወ//ሮ ፍሬህይወት ሸመልስ
56. ወ/ሮ አዲስ ብርሃኑ
57. አቶ ነጋ ጫኔ

ወ/ሮ ስነወርቅ ደገፉ

ነ/ፈጅ ተስፋዬ አበበ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

ይህ የሥራ ስንብት ክርክር የተጀመረው በኦሮሚያ ክልል በሉሜ ወረዳ ፍ/ቤት ሲሆን፣ የአሁን አመልካች የሥር ተከሳሽ፣ የአሁን ተጠሪ የሥር ከሳሾች ሆኖ ሲከራከሩ ነበር፡፡ ይህ ጉዳይ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ አመልካች

የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.422649 በ19/07/2014 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልን በማለት በማመልከቱ ነዉ፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ ከሳሾች በሥር ፍ/ቤት ባቀረቡት የክስ አቤቱታ ከሳሾች በተከሳሽ ድርጅት በተለያዩ ቀናትና የሥራ መደቦች ተቀጥረን እየሰራን እያለን የሞጆ ከተማ ሰራተኛና ማህበራዊ ጽ/ቤት ለሁለት ወር እንዲታገድ ጠይቆ ጽ/ቤቱም ከሕግ ዉጭ ሥራችን እንዲታገድ ያደረገ ሲሆን የእገዳዉ ጊዜ ሲያበቃ ተከሳሽ ሰራተኞችን ሥራቸዉን ማስጀመር ሲገባዉ፣ ተከሳሽ ከስሬአሁ በማለት ለሞጆ ከተማ ሰራተኛና ማህበራዊ ጽ/ቤት ጥያቄ በማቅረቡ ጽ/ቤቱ የ2011 ዓ.ም የኦዲት ዉጤትን ሳይመለከተዉ የአሠሪዉን ፍላጎት ብቻ መሰረት በማድረግ ሕገወጥ ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡ ተከሳሽ የዚህን ጽ/ቤት ዉሳኔ መሰረት በማድረግ የሥራ ዉላችን አቋረጧል፡፡ ተከሳሽ ምርታማነትን ለመጨመር ማሽኖችን እያስገባ ነዉ፤ ጽ/ቤቱ ተከሳሽ ስለመክሰሩ በ2011 ዓ.ም የኦዲት ዉጤት አልተረጋገጠም፤ ተከሳሽ ከስሮ ሙሉ ለሙሉ አልተዘጋም አርባ የሚሆኑ ሰራተኞችን አስቀርቶ ሌሎች ሰራተኞችን የቅነሳ ሥርዓትን አልተከተለም፡፡ ተከሳሽ እኛ በዚህ የተስማመን በማስመሰል የአገልግሎት ክፍያ በማስመሰል በባንክ ገቢ ያደረገዉ የሕግ መሰረት የለዉም፡፡ በመሆኑም ተከሳሽ ከሳሾችን ከሕግ ዉጭ የሥራ ዉላችን በማቋረጥ ያሰናበትን ስለሆነ በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 መሰረት ተገቢ ክፍያዎችን እንዲከፍለን በማለት እያንዳንዳችን ይገባናል የሚሉትን ክፍያዎች ዘርዝረዉ በአጠቃለይ ብር 2,318,361 (ሁለት ሚሊዮን ሶስት መቶ አስራ ስምንት ሺህ ሶስት መቶ ስልሳ አንድ) እንዲከፍለን፤ የሥራ ልምዳችንን እንዲሰጠን በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

ተከሳሽ በዚህ ክስ ላይ ባቀረበዉ መልስ ተከሳሽ ከአቅም በላይ የሆነ ጉዳይ ደመወዝ ለመክፈል የማይችል ሁኔታ ላይ መድረሱን ለሞጆ ከተማ ሰራተኞች እና ማህበራዊ ጉዳይ ጽ/ቤት አመልክተን ከሳሾች ሁለት ወር እንዲታገዱ የተወሰነልን ቢሆንም የተከሳሽ ድርጅት ሥራ ለመጀመር የጥሬ ዕቃ አቅርቦት እና የገንዘብ ጉድለት ችግር የተነሳ ሥራዉን ለመቀጠል ስላልተቻለ የሠራተኞችን የቅጥር ዉል ለመቋረጥ ተገድጀላሁ፡፡ ጽ/ቤቱም የድርጅቱን የኦዲት ዉጤት በማየትና በማጣራት ተከሳሽን ሥራ ለመጀመር እንደማይችል በማረጋገጥ በአዋጁ መሰረት ሙብት ማግኘት ያለባቸዉን የሥራ ልምዳቸዉ እንዲሰጣቸዉ በወሰነዉ መሰረት ለከሳሾች ክፍያዎችን ሁሉ ከፍለን አሰናብተነቸዋል፡፡ ከሳሾች ተከሳሽ ማሽን እያስገበ ነዉ ይበሉ እንጂ ሥራ እየሰራ መሆኑን አልገለጹም፣ አዲስ ማሽን ማቆም ሥራ መስራት አይደለም፡፡ የከሳሾች የሥራ ዉል የተቋረጠዉ በሕጋዊ መንገድ ስለሆነ ከሳሾች የሥራ ዉል በሕገወጥ መንገድ ነዉ በማለት ያቀረቡት ተቀባይነት የለዉም በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በኋላ የሥር የወረዳ ፍ/ቤት የሰዉ ምስክሮችን በመስማት ተከሳሽ ድርጅቱ ስለመክሰሩና በዚህ ምክንያት ስለመዘጋቱ በዉጭ ኦዲት አልተረጋገጠም፤ እንዲሁም 40 ሰራተኞችን ያስቀረ እና አዲስ ማሽኖችን እያስገባ መሆኑ በማስረጃ ስለተረጋገጠ፣ የኪሳራ መስፈርትን የማያሟላ በመሆኑ ከሳሾች ከሥራቸዉ የተሰናበቱት በሕገወጥ መንገድ ነዉ፣ ተከሳሽ በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 መሰረት ለከሳሾች ለእያንዳንዳቸዉ ሊከፈላቸዉ የሚገባዉን ክፍያዎች በማስላት በአጠቃላይ ብር 1,511,457.00 እንዲከፈላቸዉ ወስኗል፡፡

የሥር ተከሳሽ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን በማከራከር ባሳለፈዉ ዉሳኔ ለሥር 16ኛ ተከሳሽ እንዲከፍል የተወሰነዉን ክፍያ በማሻሻል በዚህ አግባብ የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ በማሻሻል ወስኗል፡፡

*ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

የሥር ከሳሽ አሁን በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታ ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበ ሲሆን ችሎቱም ቅሬታዉን በትዕዛዝ ዉድቅ በማድረግ የሥር ፍ/ቤትን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል። የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ነዉ።

የአሁን አመልካች ሚያዚያ 5 ቀን 2015 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ፡ አመልካች ከአንድ አመት ከስድስት ወራት በላይ የግብዓት እጥረት በማጋጠሙ ይህን ሁኔታ ለሞጆ ከተማ አስተዳደር ሰራተኛና ማህበራዊጉዳይ ጽ/ቤት ጥያቄ አቅርበን ጽ/ቤቱ ለሁለት ወራት ሰራተኞቹ እንዲታገዱ ፈቃደ የሰጠ ሲሆን፣ የእገዳዉ ጊዜ ከተጠናቀቀ በኋላ አመልካች ሰራተኞቹን ወደ ሥራ በመመለስ ሥራዉን ለማስቀጠል የሚያስችል ሁኔታ ባለመኖሩ የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ጽ/በተት፣ የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ እና የመሰረታዊ ሰራተኞች ማህበር ሥራ አስፈጻሚዎች በተገኙበት ዉይይት ተደርጎ ሰራተኞቹ ተገቢዉ የስንብት ክፍያ ተከፍሏቸዉ የሥራ ዉላቸዉ እንዲቋረጥ ስምምነተ ላይ በተደረሰበት አግባብ ሊቋረጥ ችሏል። ተጠሪዎች በእገድም ሆነ በስንብቱ ላይ ቅሬታ ከነበራቸዉ በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 20 (3) መመሰረት ቅሬታቸዉን ስልጣን ላለዉ ፍ/ቤት ማቅረብ እየቻሉ ያላቀረቡ በመሆኑ፣ ስንበቱ ሕጋዊ ሆኖ ሳለ የሥር ፍ/ቤቶች አመልካች ስለመክሰሩም ሆነ ለዘለቄታዉ ስለመዘጋቱ በዉጭ ኦዲተር አላረጋገጠም በማለት በሕግ ያልተመለከተዉን ጉዳይ መነሻ በማድረግ የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ። ተጠሪዎች የስድስት ወር ካሳ ተከፍሏቸዋል። በመሆኑም የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ እንዲሻርልን፣ የካሳ ጥያቄአቸዉ ዉድቅ እንዲደረግልን በማለት አመልክቷል።

የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን በማየት የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ ባዘዘዉ መሰረት በ9/10/2015 ዓ.ም የተጻፈ መልስ አቅርቧል። የመልሱም ይዘት ባጭሩ፡ አመልካች አዳዲስ ማሽኖችን እያስገበ በመሆኑ መክሰሩንና ለዘለቄታዉ መዘጋቱን በዉጭ ኦድት ማረጋገጥ በማስረፈለጉ በዚህ አግባብ ያቀረበዉ የዉጭ ኦድት ሪፖርት የለም። የሥር ፍ/ቤት ስንብቱ ሕገወጥ ነዉ ያለዉ ድርጅቱ አዳድስ ማሽን እያስገበ በመሆኑ ተጣርቶ፣ ድርጅቱ መክሰሩን የሚያመለክት ማስረጃ አለመኖሩን እና የ2011 ዓ.ም የኦዲት ሪፖርት በማቅረብ ስንብቱ ሕገወጥ ነዉ በማለት የተከፈላቸዉ ክፍያ በመቀነስ የተሰጠዉ ዉሳኔ ትክክል ነዉ። የሥር ፍ/ቤት ለተጠሪዎች ካሳ እንዲከፍል መወሰናቸዉ ተገቢ ነዉ። በመሆኑም የሥር ፍ/ቤት አመልካች የተጠሪዎችን የሥራ ዉል ያቋረጠዉ ሕገወጥ ነዉ በማለት የተጠሪዎችን የካሳ ክፍያ ጥያቄ በመቀበል የሰጡት ዉሳኔ እንዲጸናልን በማለት በዝርዝር ተከራክሯል። አመልካች ሰኔ 27 ቀን 2015 ዓ.ም በተጻፈ የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታዉን በማጠናከር ተከራክሯል።

የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል። እንደመረመርነዉ በዚህ ጉዳይ ምላሽ ማግኘት ያለበት ፣የአሁን ተጠሪዎች በሚመለከተዉ አካል በተሰጠዉ የእገዳ ዉሳኔ ላይ ቅሬታ ካላቸዉ ለሥራ ክርክር ሰሚ ፍ/ቤት ይግባኝ ማቅረብ ነበረባቸዉ ወይስ ቀጥታ ክስ ፍ/ቤት ማቅረብ ነበረባቸዉ? የሚለዉ ነጥብ መሆኑን ተገንዝበናል። በዚህ መሰረት ተጠሪዎች የአመልካች ድርጅት ሰራተኞች መሆናቸዉን እና አመልካች የተጠሪዎችን የሥራ ዉል በማቋረጥ ያሰናበታቸዉ መሆኑን ግራ ቀኙን ያላከራከረ ጉዳይ ነዉ። ነገር ግን የሥር ፍ/ቤቶች አመልካች የተጠሪዎችን የሥራ ዉል በማቋረጥ ያሰናበታቸዉ በሕገወጥ መንገድ ነዉ ወይስ አይደለም? የሚል

ጭብጥ በመያዝ አጣርተዉ ተገቢ ነዉ ያሉትን ዉሳኔ ከማሳለፍ ዉጭ የጉዳዩን አመጣጥ ሂደት በሕግ አግባብ የተመለከቱበት አግባብ የለም፡፡

ከግራ ቀኙ ክርክር እና በሥር ፍ/ቤት ከተረጋገጠዉ ፍሬ ነገር መረዳት እንደሚቻለዉ አመልካች ከጥሬ ዕቃ እጥረትና ከገንዘብ ችግር ጋር በተያያዘ የድርጅቱን ሥራ የሚያቋርጥ ከአቅም በላይ የሆነ ጉዳይ የገጠመዉ መሆኑን በመጥቀስ ለሞጆ ከተማ ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ጽ/ቤት አቤቱታ አቅርቦ፣ ጽ/ቤቱም ጉዳዩን በማጣራት ለሁለት ወራት የእገዳ ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡ የእገዳ ጊዜዉ እንዳበቀ ጽ/ቤቱ አመልካች ሥራዉን ለማስቀጠል የሚያስችል ሁኔታ የለም በማለት ለተጠሪዎች በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 መሰረት ተገቢ ክፍያዎችን በመክፈል እንዲያሰናብት ዉሳኔ መስጠቱን መዝገቡ ያሳያል፡፡ በዚህ መሰረት አመልካች ክፍያዎችን ለተጠሪዎች መፈጸሙን የሥር ፍ/ቤት የዉሳኔ ግልባጭ ያስገነዝባል፡፡ እንግዲህ አመልካች የተጠሪዎችን የሥራ ዉል በማቋረጥ ከሥራ ያሰናበታቸዉ በዚህ ጽ/ቤት የተሰጠዉን የእገዳ ዉሳኔ መነሻ በማደረግ መሆኑን የሥር ፍ/ቤት የዉሳኔ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ ይህ ከሆነ የእገዳ ዉሳኔዉን በተመለከተ ቅሬታ ያለዉ አካል በምን አግባብ ይስተናገዳል የሚለዉ ነጥብ በሕግ አግባብ መታየት ያለበት ጉዳይ ነዉ፡፡

እንደሚታወቀዉ አሠሪዉ የድርጅቱን ሥራ የሚያቋርጥ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 18 (5) እና (6) መሰረት ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ወይም ያልታሰበ የገንዘብ ችግር መከሰቱን፣ በአዋጁ አንቀጽ 19 መሰረት አሠሪዉ ለእገዳዉ ምክንያት መከሰቱን ሁኔታዉ ባጋጠመዉ በሶስት የሥራ ቀናት ዉስጥ ለሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ላለዉ ባለስልጣን በጽሑፍ ማስታወቅ እንዳለበት ያመለክታል፡፡ ሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያለዉ ባለስልጣን ይህን የጽሑፍ ማስተወቂያ በደረሰዉ ሶስት የሥራ ቀናት ዉስጥ ለእገዳ በቂ ምክንያት መኖሩን ይወስናል፤ በዚህ ጊዜ ዉስጥ የእገዳ ዉሳኔዉን ካላሳወቀ እገዳ እንደፈቀደ እንደሚቆጠር የአዋጁ አንቀጽ 19 (1) ሥር የተመለከተ ሲሆን፣ ሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያለዉ ባለስልጣን ለእገዳዉ በቂ ምክንያት የሌለ መሆኑን የወሰነ እንደሆነ ሥራዉ እንዲጀመርና ታግዶ ለነበረበትም ጊዜ ክፍያ እንዲደረግ መዘዝ እንደሚችል በአንቀጽ 19 (2) ሥር ተደንግጓል፡፡ በዚህ ዉሳኔ ቅሬታ ያደረበት ወገን ዉሳኔዉ በተሰጠ በአምስት የሥራ ቀናት ዉስጥ ስልጣን ላለዉ የሥራ ክርክር ሰሚ ፍ/ቤት ይግባኝ ማቅረብ እንደሚችል በአዋጁ አንቀጽ 19 (3) ሥር ተመልክቷል፡፡ አሠሪዉ ሥራዉን ለመቀጠል የማይችል መሆኑን ሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያለዉ ባለስልጣን ካመነ ሰራተኛዉ የቅጥር ዉሉ ተቋርጦ በአዋጁ አንቀጽ 39 እና 44 መሰረት ጥቅሞች ማግኘት መብት እንዳለዉ እንደሚያመልክት በአንቀጽ 21 (2) ሥር ተመልክቷል፡፡

በዚህ መሰረት አሁን ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ የአሁን አመልካች ያቀረበዉን የእገዳ ጥያቄ ለሞጆ ከተማ ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ጽ/ቤት ያቀረበ ሲሆን፣ ጽ/ቤቱም የቀረበዉን ምክንያት ለእገዳ በቂ ምክንያት መሆኑን በማረጋገጥ ወይም በማጽደቅ ከመወሰኑ በላይ አመልካች ሥራዉን መቀጠል እንደማይችል በማረጋገጥ የተጠሪዎችን የሥራ ዉል በማቋረጥ በአዋጁ አንቀጽ 39 እና 44 መሰረት ክፍያዎች እንዲከፈለዉ በወሰነዉ መሰረት አመልካች ለተጠሪዎች ክፍያ መክፈሉን የሥር ፍ/ቤት የዉሳኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡

ከፍ ሲል እንደተጠቀሰዉ የሞጆ ከተማ አስተዳደር ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ጽ/ቤት የሰጠዉን ዉሳኔ ላይ ቅሬታ ያላቸዉ እንደሆነ በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 19 (3) መሰረት ስልጣን ላለዉ የሥራ ክርክር ሰሚ ፍ/ቤት ይግባኝ ከሚያቀርቡ በስተቀር ይህን ሕጉ የዘረጋዉን ሥርዓት በመተዉ አመልካች የሥራ ዉላችን

በሕገወጥ መንገድ በማቋረጥ ከሥራ ስላሰናበተን፣ ስንብቱ ሕገወጥ ነዉ እንዲባልልን ተገቢ ክፍያዎች እንዲከፈለን በማለት ቀጥታ ክስ ለሥር ለወረዳ ፍ/ቤት የሚያቀርቡበት የህግ አግባብ የለም፡፡ የሥር የወረዳ ፍ/ቤትም ቢሆን ይህን የተጠሪዎች የክስ አቤቱታ የመቀበል ስልጣን አልነበረዉም፡፡ በመሆኑም የሥር የወረዳዉ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.9 (1) እና 231 መሰረት የክስ አቤቱታዉ ተቀባይነት የለዉም በማለት መመለስ ይገባዉ ነበር፣ ካልሆነ ደግሞ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 9 (2)፣ 244 (2) (ሀ) እና 245 (2) መሰረት ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለዉም በማለት የክስ አቤቱታዉን ዉድቅ በማድረግ መዝገቡን መዝጋት ይገባዉ ነበር፡፡ የሥር የወረዳ ፍ/ቤት የተጠሪዎችን ቀጥታ የክስ አቤቱታ ለመቀበል ስልጣን የለንም በማለት ዉድቅ ማድረግ ሲገባዉ በፍሬ ነገር ላይ ግራ ቀኙን በማከራከር ዉሳኔ ለመስጠት ስልጣን በሌላዉ ጉዳይ ላይ ዉሳኔ መስጠቱ የህግ ድጋፍ የሌለዉ ሆኖ ሳለ፣ በየደረጃዉ ያሉት ቅሬታ ሰሚ ፍ/ቤቶችም ይህን ዉሳኔ ማረም ሲገባቸዉ የሥር ፍ/ቤትን ዉሳኔ በማጽናት መወሰናቸዉ ተቀባይነት የለዉም ብለናል፡፡

ሲጠቃለል የሥር ፍ/ቤቶች በዚህ ጉዳይ ቀጥታ ክስ ተቀብለዉ ለመወሰን ስልጣን በሌላቸዉ ጉዳይ ግራ ቀኙን በፍሬ ነገር በማከራከር የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ተከታዩን ወስነናል፡፡

**<u>ዉሳኔ</u>**

1. የሉሜ ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ.95657 በ26/5/2015 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.71135 በ8/7/2015 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.422649 በ19/7/2015 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸወ በመሆናቸዉ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 (1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፤
3. ግራ ቀኙ በሰበር ክርክሩ የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡
4. ይህ ችሎት በ1/9/2015 ዓ.ም የሰጠዉ የእግድ ትዕዛዝ በዚህ ዉሳኔ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ማ/ተ

*ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁጥር---240697
ቀን- ጥቅምት 09 ቀን 2016 ዓ.ም

**ዳኞች፦** ብርሃኑ አመነዉ

ረታ ቶሎሳ

በዕዉቀት በላይ

ቀነዓ ቂጣታ

ኑረዲን ከድር

**አመልካች፦** ዲ አር ሲ/ዳኒሽ ሪፊዉጂ ካዉንስል/

**ተጠሪ፦** አቶ ዘላለም ሲሳይ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ለዚህ ሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ የሥራ ክርክር ሲሆን የተጀመረው በዲማ ወረዳ ፍ/ቤት ነው፡፡ በዚህ ፍ/ቤት ተጠሪ ከሳሽ ሲሆን የአሁን አመልካች ደግሞ ተከሳሽ ነበሩ፡፡ የሰበር አቤቱታዉ የቀረበዉ በዲማ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ 0028/2014 ጥቅምት 14 ቀን 2014 ዓ.ም ተሰጥቶ በአኝዋ ብሔረሰብ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት እና በጋምቤላ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በተሰጡ ዉሳኔዎች የጸናዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በሚል ነዉ፡፡

*ማ ስታወሻ፦ ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

ተጠሪ ሚያዚያ 28 ቀን 2014 ዓ/ም በተጻፈ የክስ አቤቱታ ያቀረቡት ክስ ይዘት፡- አመልካች ከሕግ ዉጪ ከሥራ ስላሰናበታቸዉ ወደ ሥራ እንዲመለሱ፤ የተቆረጠ ደመወዝ እና ለደረሰባቸዉ የሞራል ዉድቀት ካሣ እንዲከፈላቸዉ የሚጠይቅ ነዉ፡፡

አመልካችም በጽሁፍ በሰጠዉ ምላሽ፡- የሥራ ዉሉ የተቋረጠዉ በህጋዊ መንገድ ነዉ፤ ተጠሪ የስቶር ኪፐር ሠራተኛ ሆነዉ በሚሰሩበት ወቅት በሥራዉ ላይ የማታለል ተግባር ፈጽመዉ በመገኘታቸዉ እንዲሁም የራሳቸዉን ወይም የሌላዉን ብልጽግና በመሻት የፈጸሙ በመሆኑ በአዋጅ ቁ.1156/2011 አንቀጽ 27/1/ሐ፣ አንቀጽ 27/1/መ እና አንቀጽ 14/2/ለ መሰረት ያለማስጠንቀቂያ የሥራ ዉሉን ማቋረጥ የሚቻል በመሆኑ፤ ከዚህ ህግ በተጨማሪም የድርጅቱ የሥራ ደንብ/ማኑዋል/ በተራ ቁ.9.3 ላይም ይህንኑ ድርጊት የፈጸመ ሠራተኛ ከሥራ ያለማስጠንቀቂያ ሊሰናበት እንደሚችል በመደንገጉ የሥራ ዉሉ ሊቋረጥ እንደቻለ፤ በሌላ በኩልም የሥራ ዉሉ በሠራተኛዉ/በተጠሪ/ ጥፋት የተቋረጠ በመሆኑ የሚከፈል ክፍያ አለመኖሩን ገልጸዉ በአጠቃላይ የቀረበዉ ክስ አግባብነት የሌለዉ በመሆኑ ዉድቅ እንዲደረግ በመጠየቅ ተከራክሯል፡፡

የዲማ ወረዳ ፍ/ቤት ጉዳዩን አጣርቶና መርምሮ፡- የተጠሪ የሥራ ስንብት ህገ ወጥ ነዉ በማለት የወር ደመወዛቸዉ ከቆመበት ቀን ጀምሮ ተከፍሏቸዉ ወደ ሥራ ይመለሱ በማለት ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡ በዉሳኔዉ ላይ ቅር በመሰኘት የአሁን አመልካች የይግባኝ አቤቱታቸዉን ለአኝዋሃ ብሔር/ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱም የስር ፍ/ቤት ዉሳኔ በከፊል በማሻሻል አመልካች ለአሁን ተጠሪ ከሚያዚያ ወር 2014 ዓ/ም ጀምሮ እስከ ጥቅምት ወር 2015 ዓ/ም ድረስ ያለዉ የወር ደመወዝ ብር 17,566 x 7= ብር 122,962 ተከፍሏቸዉ ወደ ሥራ ይመለሱ በማለት ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ዉሳኔ ላይም ቅር በመሰኘት ወይም መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት የአሁን አመልካች አቤቱታቸዉን ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም የስር ፍ/ቤቶች የሰጡትን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የሰበር አቤቱታዉም ሊቀርብ የቻለዉ ይህ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በሚል ነዉ፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም፡- ተጠሪ ባላቸዉ የሥራ ኃላፊነት መሰረት ከተረከቡት ቆርቆሮዎች ዉስጥ ብዛቱ 1144 የሆነ በድምሩ 888,113.20 ብር የሚያወጣ ኃላፊነታቸዉን ባለመወጣታቸዉ እንዲጠፋ ማድረጋቸዉን/ከተጠሪ እጅ መጥፋቱን/ ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ ሲደረግ መጋቢት 30 ቀን 2014 ዓ/ም በቀረበዉ የዉስጥ ኦዲት ሪፖርት እና በሰዉ ምስክሮች በስር ፍ/ቤት አስረድተናል፡፡ ነገር ግን የዲማ ወረዳ ፍ/ቤት በፍርድ ሐተታዉ ከተጠሪ የጠፉ ቆርቆሮ ስለመኖር አለመኖሩ ለማስረዳት ፍ/ቤት መቅረብ የሚገባዉ የማስረጃ አይነት ኦዲት የማድረግ ሥልጣን ከተሰጠዉ አካል የተረጋገጠ የኦዲት ሪፖርት መሆን አለበት በማለት ዉሳኔ መስጠቱ እና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎትም ዉሳኔዉን ማጽናቱ በማስረጃ የማስረዳት ሸክምን በተመለከተ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.47551 ላይ የሰጠዉን አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሚጻረር ነዉ፡፡ በሌላ በኩል የስር ፍ/ቤቶች በጉዳዩ ተገቢዉን ዉሳኔ ለመስጠት የሚያስችል ጭብጥ ሳይመሰርቱ ዉሳኔ ሰጥተዉ ባሉበት ሁኔታ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በስር ፍ/ቤቶች የተፈጸመዉን የሕግ አካሄድ ጥሰት ሳያርም የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ

በአግባቡ ነዉ ወይስ አይደለም የሚል ጭብጥ ይዞ በምክኒያትነት/በዉጤት የስር ፍ/ቤቶችን ትንታኔ በመደገፍ በራሱ አመልካች መ/ሰጪን ከሥራ ያባረረዉ/ያሰናበተዉ/ በህገ ወጥ መንገድ ነዉ በማለት ዉሳኔዉን ማጽናቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነዉ፡፡ በአጠቃላይ ተጠሪ የሥራ ኃላፊነቱን በአግባቡ ባለመወጣቱ ብዛቱ 1144 ቆርቆሮ መጥፋቱን በማስረጃ አረጋግጠን ባለበት፤ በአንጻሩ ተጠሪ የኦዲት ሪፖርቱ በገለልተኛ ወገን ያልተረጋገጠ ነዉ ከማለት ዉጭ ንብረቱን ያላጠፉ ለመሆናቸዉ የማስረዳት ሸክም ያልተወጡ ሆኖ እያለ የስር ፍ/ቤቶች የሥራ ስንብቱ ህጋዊ መሆን አለመሆኑን ከአዋጅ ቁ.1156/2011 ዓ/ም እና ከሥራ ደንብ/ማኑዋል/ ተራ ቁ.9.3 አኳያ ጭብጥ በመያዝ መመርመር ሲገባቸዉ እንዲሁም የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.37391 ላይ ጭብጥ አመሰራረትን በሚመለከት የሰጠዉን አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሚሸር በመሆኑ የስራ ስንብቱ ህጋዊ ነዉ ተብሎ እንዲወሰንልንና ወደ ሥራ ይመለሱ፤ ዉዝፍ ደሞዝም ይከፈል የተባለዉ ዉሳኔ እንዲሻርልን የሚል ነዉ፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ተጠሪ ንብረት ስለማጉደሉ አመልካች ማስረጃ አቅርቦ እያለ ዉድቅ ሆኖበት ስንብቱ ህገወጥ ነዉ የመባሉን ተገቢነቱን ለማጣራት ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ግራ ቀኙ በጽሁፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የተጠሪ መልስ ይዘት በአጭሩ፡- አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ የማስረጃ ምዘናን የሚመመለከት በመሆኑ በሰበር ሰሚ ችሎት ሊታይ የሚችል መሰረታዊ የሕግ ስህተት አይደለም፡፡ የስር ፍ/ቤቶች በሕግ በተሰጣቸዉ ሥልጣን መሰረት ከቀረቡት ማስረጃዎች በተለይም አመልካች ያቀረቧቸዉን ማስረጃዎች አግባብነት፣ ተቀባይነት እና ያስረዱትን ፍሬ-ነገር በመመዘን እንጂ ዉሳኔ የሰጡት የተለየ ማስረጃን በመፈለግ ወይም አመልካች ያቀረቡትን ማስረጃ አልቀበልም በማለት አይደለም፡፡ በስር ፍ/ቤቶች የተሰጡት ዉሳኔዎች የኦዲት ሪፖርቱን በተመለከተ በአግባቡ የተደረገ ስላልሆነ እንደማስረጃ ሊቀርብ አይገባውም፡፡ የገቢ ደረሰኝ ገቢን እንጂ ዕቃ ለመጥፋቱ ደምዳሚ ማስረጃ አይደለም፡፡ የሰው ማስረጃዎችም እንደ ክሱ አግባቡ አላስረዱም፡፡ ንብረት ስለ መጥፋቱ የማስረዳት ሸክም ያለበት አመልካች ነዉ፡፡ ንብረት አለማጥፋቱን ባላስረዳበት ሁኔታ ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው መባሉ አግባብ አይደለም በማለት ያቀረበው ክርክር የማስረጃ ምዘና ጉዳይ ከመሆኑም በላይ ማን ምን ማስረዳት አለበት የሚለውን የማስረዳት ሸክም ፅንሰ ሀሳብን ያላገናዘበ ነው፡፡ አመልካች ባቀረበዉ አቤቱታ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.47551 የሰጠውን የሕግ ትርጉም የተጠቀመው ከአውድ ውጭ ነው፡፡ በሕግ በአስገዳጅ እስካልተቀመጠ ድረስ ፍ/ቤት የቀረበን ጉዳይ በማንኛውም ማስረጃ ማስረዳት ይቻላል ከማለት ውጭ ፍ/ቤቶች ማስረጃን ሲመዝኑ የቀረቡላቸውን ማስረጃዎች አግባብነት መመርመር የለባቸውም የሚል አይደለም፡፡ በሌላ በኩል የስር ፍ/ቤቶች ለቀረበዉ ጉዳይ አግባብነት ያለዉ ጭብጥ በመያዝ ዉሳኔ ሰጥተዋል፡፡ ጭብጥ ሳይመሰርቱ እንኳን የሰጡ ቢሆን ጭብጥ አለመያዙ በሚወሰነው ውሳኔ ላይ የተለየ ውጤት የሚያመጣ አይደለም፡፡ ጭብጡ በአግባቡ አልተመሰረተም ካለ ጭብጡ በአግባቡ ቢመሰረት ኖሮ ውሳኔው ፍ/ቤቱ ከሰጠው የተለየ ሊሆን እንደሚችል ማሳየት ነበረበት፡፡ ከቀረበዉ ማስረጃ አንጻር የስር ፍ/ቤቶች መዝነዉ ስንብቱ ህገ ወጥ ነዉ ማለታቸዉ ምንም አይነት ስህተት የተፈጸመበት አይደለም፡፡ በአጠቃላይ የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ ምንም አይነት መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስላልሆነ

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የአመልካች አቤቱታ ዉድቅ ተደርጎ ዉሳኔ እስከሰጥ ያለዉ ጊዜ ተሰልቶ የዉዝፍ ደመወዝ ማሻሻያ በማድረግ እንዲወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታዉን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸዉን የሚመስል ሲሆን እኛም አቤቱታ ከቀረበበት ዉሳኔ እና አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን መርምረናል፡፡ የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር መርምረን እንደተረዳነዉ የዚህን ችሎት ምላሽ የሚሻዉ ጭብጥ ተጠሪ ንብረት ስለማጉደሉ አመልካች ማስረጃ አቅርቦ እያለ ዉድቅ ሆኖበት ስንብቱ ህገወጥ ነዉ ተብሎ በስር ፍ/ቤቶች መወሰኑ ተገቢ ነዉ ወይስ አይደለም? የሚለዉ ነዉ፡፡

በመሠረቱ በሕብረት ስምምነት በሌላ አኳኃን ካልተወሰነ በስተቀር አሠሪ የስራ ዉልን ያለማስጠንቀቂያ ሚቋረጥ ከሚችልባቸዉ ምክንያቶች ዉስጥ አንዱ በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 27(1/መ) ስር ሠራተኛዉ የራሱን ወይም የሌላ ሰዉ ብልጽግናን በመሻት በማንኛዉም የአሠሪዉ ንብረት ወይም ገንዘብ አለአግባብ መጠቀም ይገኝበታል፡፡ ይህ ድንጋጌ ጥብቅ የሆነበት ምክንያት ሠራተኛዉ ሥራዉን በታማኝነት እንዲያከናዉንና ኃላፊነቱን በአግባቡ ባለመወጣቱ ራሱ ብቻ ሳይሆን ሌላዉ ሰዉ በአሠሪዉ ንብረት ወይም ገንዘብ ያለአግባብ እንዳይበለጽግ ነዉ፡፡ አሰሪዉ በሠራተኛዉ እጅ ያለ ንብረት መጉደሉን ማስረዳት ከቻለ ጉድለቱ በሠራተኛዉ ጥፋት ያለመከሰቱን ወይም ኃላፊነት የሌለበት መሆኑን የማስረዳት ሸክሙ የሠራተኛዉ ነዉ፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ ተጠሪ የሥራ ድርሻቸዉ በአመልካች ድርጅት ዉስጥ የሎጀስቲክ ክፍል ኃላፊ ሆነዉ ንብረትም ተረክበዉ ገቢና ወጪ ሲያደርጉ የቆዩ ሲሆኑ አመልካች ያለ ማስጠንቀቂያ ከሥራ ሊያሰናብታቸዉ የቻለዉ በዋናነት መጋቢት 30 ቀን 2014 ዓ/ም በተደረገ የዉስጥ ኦዲት ምርመራ ሪፖርት መሰረት መሆኑን፤ ሪፖርቱም ተጠሪ ከተረከቡት 5,475 ቆርቆሮዎች ዉስጥ 1,144 በእጃቸዉ ጠፍቷል ወይም አጉድለዋል የሚል መሆኑን ከመዝገቡ መረዳት ይቻላል፡፡ አመልካች ይህን ለማስረዳት የኦዲት ሪፖርቱንና ኦዲት ያደረጉት የአመልካች ሠራተኞች ቀርበዉ አስረድተዋል፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪ በስር ፍ/ቤት አመልካች በሕገ-ወጥ መንገድ ያለማስጠንቀቂያ ከሥራ አሰናብቶኛል በማለት ከሥራ መሠናበታቸዉን ከማስረዳት በቀር ባቀረቡዋቸዉ ምስክሮችም ሆኑ በሌላ ማስረጃ ጎደሉ የተባሉ ቆርቆሮዎች አለመጥፋታቸዉን ወይም አለመጉድላቸዉን ወይም ስለጉድለቱ ኃላፊነት የሌለባቸዉ መሆኑን አላስረዱም፡፡

የወረዳዉ ፍ/ቤትም ሆነ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የተጠሪ ስንበት ሕገ-ወጥ ነዉ ለማለት የሰጡት ምክንያት የኦዲት ሪፖርቱ የገቢና ወጪ ደረሰኞችን በማየት የቀረበ ነዉ፤ ቆርቆሮዎቹ በነበሩበት ክፍል ዉስጥ ሌሎች ግለሰቦች በኃላፊዎች ትዕዛዝ ይሰሩ ስለነበረ በአግባቡ ኦዲት ቢደረግ ኖሮ ሌሎች ግለሰቦች ተጠያቂ ሊሆኑ ይችሉ ነበር እንዲሁም ለተጠሪ የስንበት ደብዳቤ ሲሰጣቸዉ ጥፋቱ እንዲነገራቸዉ ሲጠይቁ እንዳማይነገራቸዉ መገለጹ ስንብቱ ከቅን ልቦና ዉጪ መሆኑን ያሳያል የሚል በማስረጃ ላይ ያልተመሰረተ ሊሆን ይችላል ከሚል መላ ምት ባልዘለለ መነሻ የኦዲት ሪፖርቱ ዉድቅ መደረጉን የሚያሳይ ነዉ፡፡

በመሠረቱ ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ ሲደረግ ገቢ መደረጋቸዉ ወይም ተጠሪ መረከባቸዉ ከተረጋገጡት 5,475 ቆርቆሮዎች ዉስጥ የወጪ ሰነድ የቀረበባቸዉ ተቀንሶ 1,144 ቆርቆሮዎች መጉደላቸዉን ለማረጋገጥ ልዩ የኦዲት ሙያ የሚጠይቅ አይደለም፡፡ ተጠሪ ዋና ሥራቸዉ የሎጀስቲክ ክፍል ኃላፊ እንደመሆናቸዉ መጠን ኃላፊነት በጎደለዉ መልኩ ወይም ሌላ ሰዉ ተጠያቂ ሊደረግ በማይችልበት መልኩ ሌላ ሰራተኛ ይሠራበት የነበረዉን ንብረት ክፍልና ንብረት ያለአንዳች ቆጠራና ርክክብ ተቀብለዉ ይሠራሉ እንዲሁም በዘፈቀደ ያለርክክብ ሌላ ሰዉ ዉክለዉ ያሰራሉ ተብሎ የሚገመት ካለመሆኑም በላይ ይህን በማስረጃ ባላስረዱበትና የማስረዳት ሸክማቸዉን ባልተወጡበት ሁኔታ የስር ፍ/ቤቶች የቀረበዉን የኦዲት ሪፖርት ዉድቅ ማድረጋቸዉ ተገቢ አይደለም፡፡

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረዉ ተጠሪ ተርክቦ ከነበራቸዉ 5,475 ቆርቆሮዎች ዉስጥ ያለዉና ሥራ ላይ የዋለዉ ተቀንሶ 1,144 ቆርቆሮ መጉደሉ የተረጋገጠ ሲሆን ለጉድለቱ ኃላፊ አለመሆኑን በመግለጽ በማስረጃ ያስተባበለዉ ነገር በሌለበት ሁኔታ አመልካች የወሰደዉ የስንብት እርምጃ ሕገ-ወጥ ነዉ ተብሎ ተጠሪ ዉዝፍ ደመወዝ ተከፍሎት ወደ ሥራ እንዲመለስ የተሰጠዉ ዉሳኔ የአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 27(1/መ) ድንጋጌ ዓለማና ይዘት ያላገናዘበ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም የሚገባዉ ነዉ፡፡ በመሆኑም ተጠሪ የአመልካችን ንብረት በማጉደሉ አመልካች ያለማስጠንቀቂያ ተጠሪን ማሰናበቱ ሕጋዊ በመሆኑ ተጠሪን ወደ ሥራ ለመመለስም ሆነ ዉዝፍ ደመወዝ ለመክፈል ሊገደድ ስለማይገባዉ የስር ፍ/ቤቶች ዉሳኔ ሊሻር የሚገባዉ ነዉ፡፡

ሲጠቃለል አመልካች የተጠሪን የሥራ ዉል ያቋረጠዉ ከሕግ ዉጭ ነዉ፣ ዉዝፍ ደመወዝ ተከፍሎት ወደ ሥራ እንዲመለስ በማለት በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለዉ ተወስኗል፡፡

**<u>ዉሳኔ</u>**

1. በዲማ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ 91/2014 ሐምሌ 11 ቀን 2014 ዓ.ም ተሰጥቶ በአኝዋ ብሄ/ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 0028/2014 ጥቅምት 14 ቀን 2015 ዓ.ም በከፊል ተሻሽሎ የተወሰነዉ እና በጋምቤላ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 01228/2015 ታሕሳስ 03 ቀን 2015 ዓ.ም በተሰጠ ዉሳኔ የጸናዉን ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ተጠሪን ከሥራ ያሰነበተዉ በሕገ-ወጥ መንገድ ነዉ ተብሎ ዉዝፍ ደመወዝ እንዲከፈላቸዉ እና ወደ ሥራ እንዲመለሱ በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠዉ ዉሳኔ ተሽሯል፡፡
3. አመልካች ተጠሪን ያለማስጠንቀቂያ ከሥራ በማሰናበት የወሰደዉ እርምጃ ሕጋዊ ነዉ ተብሎ ተወስኗል፡፡
4. የሰበር ክርክሩ ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ዉሳኔ ያገኘ ስለሆነ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ ስታወሻ፦ ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

**ማ/ተ**

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሠ/መ/ቁጥር 237667

ጥቅምት 06 ቀን 2016 ዓ/ም

ዳኞች ፡- እትመት አሰፋ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግሥቱ

አመልካች ፡- አቶ መሀመድ አወል ጠበቃ ጥሩነሽ ገረመው ቀረቡ

ተጠሪ ፡- ፀሀይ አሊ መሃመድ አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የገጠር እርሻ መሬት በኑዛዜ የሚተላለፍበትን አግባብ የሚመለከት ነዉ፡፡ አመልካች በአማራ ክልል ደቡብ ወሎ ዞን በወረባቦ ወረዳ ፍርድ ቤት በተጠሪ ላይ በመሰረቱት ክስ አክስታቸዉ ወ/ሮ አረጋሽ የሱፍ በህይወት በነበሩበት ጊዜ በወራ ባቡ ወረዳ 07 ቀበሌ አዉራጫ ከተባለዉ ቦታ አዋሳኙ በክሱ የተጠቀሰዉን የእርሻ መሬት በ2001 ዓ/ም ለተጠሪ በማስተላለፍ ያደረገችዉን ኑዛዜ በመሻር በህይወት እያለች እንድረዳት

እና አንድጦራት በሕግ በተፈቀደላት መብት መሰረት በቀን 19/03/2009 ዓ/ም በተደረገ ኑዛዜ የእርሻ መሬቷን በአዋጅ ሥልጣን በተሰጠዉ በወራባቦ ወረዳ የመሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም ጽሕፈት ቤት ፊት 3 ምስክሮች ይዛ በመቅረብ ለአመልካች በኑዛዜ አዉርሳኛለች፡፡ጽሕፈት ቤቱም በቁጥር 00-2/265/09 በቀን 19/03/2009 ዓ/ም ኑዛዜዉን በማረጋገጥ መዝግቦ ማስረጃ ሰጥቶኛል፡፡የአመልካች አክስት በቀን 07/09/2013 ዓ/ም ከዚህ አለም በሞት ተለይታለች፡፡ በመሆኑም ተጠሪ የተሻረዉን ኑዛዜ መሰረት አድርጋ በሕገ-ወጥ መንገድ የያዘችዉን መሬት ለቃ እንድታስረክብኝ ይወስንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪ በሰጡት መልስ ሟች የተናዘዘችልኝ ለእኔ ነዉ፡፡ አመልካች ያቀረበዉ ኑዛዜ ሰነድ ሀሰት ነዉ፡፡ በኑዛዜዉ ላይ ሟች አልፈረመችም፡፡ በመሆኑም ሰነዱ ይመርመርልኝ፡፡ ለእኔ የተደረገዉ ኑዛዜም ባለመሻሩ እና የሟች የቤተሰብ አባልም ስለነበርኩኝ እየጦርኳት ስለቆየሁ በኑዛዜዉ መሰረት በሟች መሬት ላይ ደብተር አሰርቻለሁኝ፡፡ ስለሆነም ክሱ ዉድቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ክርክርና ምስክሮች ሰምቶ እንዲሁም ከወረዳዉ የገጠር መሬት አጠቃቀም እና አስተዳደር ጽሕፈት ቤት ማስረጃ አስቀርቦ በመመርመር አስቀድሞ ሟች በቁጥር ወ/ወ/07/64/2001 በቀን 15/03/2001 ዓ/ም ባደረጉት ኑዛዜ አከራካሪዉን የገጠር የእርሻ መሬት ለተጠሪ ካስተላለፉ በኋላ ይህንኑ መሬት ሰነዶችን ለማረጋገጥና ለመመዝገብ ስልጣን በተሰጠዉ አካል ፊት 3 ምስክሮችን ይዘዉ ቀርበዉ ባደረጉት ኑዛዜ ለአመልካች ማስተላለፋቸዉ ተረጋግጧል፡፡ ለተጠሪ ኑዛዜ የተደረገዉ ለአመልካች ከተደረገላቸዉ ኑዛዜ ቀድሞ በመሆኑ ኑዛዜዉ ፈራሽ ነዉ፡፡ በዚሁ ምክንያት አከራካሪዉን መሬት ተጠሪ በስማቸዉ ያስመዘገቡት ሕጋዊ መብት ሳይኖራቸዉ ነዉ፡፡ እንዲሁም ተጠሪ አከራካሪዉን መሬት የሚይዙበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ በመሆኑም በተጠሪ ስም የተመዘገበዉ ተሰርዞ በአመልካች ስም እንዲመዘገብና ተጠሪ አከራካሪዉን መሬት ለቀዉ ለአመልካች ያስረክቡ በማለት ወስኗል፡፡ ተጠሪ በዉሳኔዉ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337 መሰረት ሠርዞባቸዋል፡፡

በመቀጠል ተጠሪ የሰበር አቤቱታቸዉን ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበዉ ችሎቱ ግራ ቀኙን አከራክሮ በሰጠዉ ዉሳኔ በግለጽ የሚደረግ ኑዛዜ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 881 መሰረት በመርህ ደረጃ በአራት ምስክሮች ፊት መደረግ አለበት፡፡በልዩ ሁኔታ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 882 መሰረት በሁለት ምስክሮች ፊት የሚደረገዉ ከምስክሮች መካከል አንዱ ዉል ለማዋዋል ሥልጣን የተሰጠዉ እንደሆነ ነዉ፡፡በአዋጅ ቁጥር 922/2008 አንቀጽ 2/2 መሰረት ዉል የማዋዋል ሥልጣን የተሰጠዉ ሰነድን እንዲያረጋግጥ ሥልጣን የተሰጠዉ ሲሆን ለዚህ ክርክር መነሻ የሆነዉን ኑዛዜ የመዘገበዉ የቀበሌ ወይም የወረዳ የገጠር መሬት አስተዳደር ዉል ለማዋዋል ሥልጣን የተሰጠዉ አካል አይደለም፡፡በአማራ ክልል አዋጅ ቁጥር 252/2009 አንቀጽ 17/4 መሰረት የገጠር መሬት አስተዳደር ኑዛዜ መመዝገብ ያለበት ስለመሆኑ የተመለከተ ቢሆንም ኑዛዜ ተደረገ በተባለበት ጊዜ ተፈጻሚ ሲሆን በነበረዉ አዋጅ ቁጥር 133/1998 ስር ስለኑዛዜ አመዘጋገብ በግልጽ አልተደነገገም፡፡በመሆኑም የገጠር መሬት አስተዳደር ዉል አዋዋይ ባለመሆኑ፣በኑዛዜዉ ላይ የተጠቀሱት ሦስት ምስክሮች ብቻ ስለሆኑ ለአመልካች የተደረገዉ ኑዛዜ በሕግ ፊት

የማይጸና ስለሆነ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን መሬት ተጠሪ ሊለቁ አይገባም በማለት የስር ፍርድ ቤቶችን ዉሳኔ በአብላጫ ድምጽ በመሻር ወስኗል፡፡

አመልካች በቀን 21/03/2015 ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ከላይ በተመለከተዉ መሰረት በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በተሰጠ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን የአቤቱታቸዉ ይዘት በአጭሩ፡- ተጠሪ ኑዛዉ ፎርማሊቲዉን አያሟላም በሚል በግልጽ ባልተከራከሩበት የክልሉ ሰበር ይህንን ነጥብ መሰረት በማድረግ ዉሳኔ መስጠቱ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 182/2ን እና 329/1ን የሚቃረን ነዉ፡፡የገጠር እርሻ መሬትን በተመለከተ የሚደረግ ኑዛዜ፣የስጦታ እና የኪራይ ዉል በተመለከተ ሕጋዊ መስፈርቶችን ማሟላት አለሟሟላቱን የማረጋገጥ ሥልጣን በአዋጅ ቁጥር 252/2009 አንቀጽ 17/4 ስር ለወረዳ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽሕፈት ቤት ተሰጥቶት እያለ የክልሉ ሰበር ችሎት በአዋጅ ቁጥር 922/2008 አንቀጽ 2/2 ስር የተደነገገዉን አለግባብ ተግባራዊ በማድረግ ይህ ጽሕፈት ቤት ዉል የማዋዋል ሥልጣን የለዉም፤በሦስት ምስክሮች ፊት የተደረገዉ ኑዛዜ ፎርሙን አያሟላም ሲል የሰጠዉ ዉሳኔ በሰ/መ/ቁጥር 49851 እና 36562 የተሰጠዉን የሕግ ትርጉም ጭምር የሚቃረን ነዉ፡፡ሟች ለአመልካች ያደረጉት ኑዛዜ ኋለኛዉ ኑዛዜ በመሆኑ ለተጠሪ የተደረገዉን ኑዛዜ ስለሚሽር ለአመልካች የተደረገዉ ኑዛዜ ሕጋዊ ዉጤት እንዲኖረዉ አለመደረጉ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 895/3 ስር የተደነገገዉን እና በሰ/መ/ቁጥር 96364 ስር የተሰጠዉን የሕግ ትርጉም የሚቃረን ነዉ፡፡በመሆኑም ለአመልካች የተደረገዉ ኑዛዜ የሕጉን መስፈርት ያሟላ ነዉ ተብሎ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ ተሽሮ የወረዳዉ ፍርድ ቤት ዉሳኔ ይጽናልኝ በማለት አቤቱታቸዉን አቅርበዋል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ ሟች በወረዳዉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽሕፈት ቤት ቀርበዉ 3 ምስክሮች ባሉበት የገጠር እርሻ መሬት ለአሁን አመልካች መናዘዛቸዉ ተረጋግጦ እያለ ኑዛዜዉ ለማዋዋል ሥልጣን ባልተሰጠዉ አካል የተደረገና በኑዛዜ ላይ ያሉት 3 ምስክሮች ብቻ በመሆናቸዉ ኑዛዜዉ በሕግ ፊት አይፀናም ተብሎ የተወሰነበትን አግባብነት በአማራ ክልል ተሻሽሎ በወጣዉ የገጠር መሬት አዋጅ ቁጥር 252/2009 አንቀፅ 17/4 እና ከፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 882 አንጻር ተጠሪ ባሉበት እንዲመረመር ትዕዛዝ በመስጠቱ ተጠሪ በቀን18/04/2015 ዓ/ም የተፃፈ መልሳቸዉን በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

የመልሳቸዉም ይዘት በአጭሩ፡-የወረዳው ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽሕፈት ቤት የኑዛዜ ውል የመመዝገብና ከባህር መዝገቡ ላይ የሚያያይዝ እንጂ የኑዛዜ ውልን የማዋዋልና የማረጋገጥ ስልጣን የለዉም፡፡ይህንን በተመለከተም በአዋጅ ቁጥር 922/2008 በአንቀጽ 5፣8/7፣ 17(1/ሀ-ሐ) ፣ በአማራ ክልል አዋጅ ቁጥር 263/2011 አንቀጽ 6/12 እና አዋጅ ቁጥር 252/2009 አንቀጽ 17/4 እና አንቀጽ 48/5 የተደነገገዉና በሰ/መ/ቁጥር 32899 ላይ የተሰጠዉ የሕግ ትርጉም ያሳያል፡፡ የገጠር መሬት አስተዳደር አጠቃቀም መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 252/2009 አንቀጽ 17/4 መሰረት የኑዛዜ አደራረግ በፍ/ብ/ሕግ እንደተደነገገው በግልጽ የሚደረግ ኑዛዜ መስፈርቶች ማሟላትና አግባብ ላለው የወረዳ መሬት አስተዳደርና

አጠቃቀም ጽሕፈት ቤት ቀርቦ መመዝገብ ያለበት ስለመሆኑ ተደንግጓል፡፡በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 881/2 መሰረት ኑዛዜዉ በአራት ምስክሮች ፊት ያልተደረገ በመሆኑ እና የወረዳዉ መሬት አስተዳደር ጽሕፈት ቤት ዉል የመዋዋል ሥልጣን የተሰጠዉ ባለመሆኑ ኑዛዜዉ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 882 ስር በተደነገገዉም አግባብ የተደረገ ባለመሆኑ ፈራሽ ነዉ ሲል መባሉ የሚነቀፍ አይደለም፡፡በሰ/መ/ቁጥር 49851 እና 37562 የተሰጠዉ የሕግ ትርጉም ከተያዘዉ ጉዳይ ጋር ግንኙነት ስለሌለዉ ከዚህ አኳያ የቀረበዉ ክርክር ተቀባይነት የለዉም ተብሎ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ ይጽናልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡አመልካችም የመልስ መልሳቸዉን በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

ከዚህ በላይ አጠር ባለ መልኩ የተመለከተዉን የግራ ቀኝ ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት የሚመለከት ሲሆን እኛም የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ሲል የያዘዉን ጭብጥ ከግምት በማስገባት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች ለክሳቸዉ መሰረት ያደረጉት ኑዛዜ ሕጋዊ ዉጤት የለዉም በማለት በመወሰኑ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም አመልካች በተጠሪ ላይ የመሰረቱት ክስ ሥረ-ነገር ወራሽነትን የሚመለከት ሆኖ የክሱ ምክንያት በክሱ የተጠቀሰዉ የገጠር ዕርሻ መሬት ከአክስታቸዉ በኑዛዜ የተላለፈላቸዉ ሆኖ እያለ ተጠሪ ከሕግ አግባብ ዉጭ እንደያዙባቸዉ የገለጹት ነዉ፡፡ ተጠሪ ደግሞ አመልካች ያቀረቡት ኑዛዜ በሀሰት የተዘጋጀ ነዉ፤ሟች አልፈረሙም፤ መሬቱ በኑዛዜ የተላለፈዉ ለእኔ ነዉ በማለት ክደዉ ተከራክረዋል፡፡በዚህ መልኩ ግራ ቀኙ ካቀረቡት ክርክር በመነሳት ሊያዙ የሚገባቸዉ ጭብጦች በክሱ የተጠቀሰዉ የገጠር እርሻ መሬት በሕግ አግባብ በተደረገ ኑዛዜ ለአመልካች ተላልፏል ወይስ አልተላለፈም? ተጠሪ መሬቱን የያዙት በሕግ አግባብ ነዉ ወይስ አይደለም? የሚሉ ናቸዉ፡፡

በመጀመሪያም በክሱ የተጠቀሰዉ የገጠር እርሻ መሬት በሕግ አግባብ በተደረገ ኑዛዜ ለአመልካች ተላልፏል ወይስ አልተላለፈም? የሚለዉን መርምረናል፡፡ ከላይ እንደተመለከተዉ አከራካሪዉን የገጠር እርሻ መሬት ለአመልካች ለማስተላለፍ ኑዛዜ የተደረገዉ በቀን 19/03/2009 ዓ/ም እንደሆነ አመልካች በክሳቸዉ ላይ ገልጸዋል፡፡በዚህ መልኩ አመልካች በኑዛዜ አገኘሁኝ የሚሉት የገጠር የዕርሻ መሬት በመሆኑ አመልካች መብት አገኘሁበት ያሉት ኑዛዜ በተደረገበት ጊዜ በአማራ ክልላዊ መንግሥት ተፈጻሚ ሲሆን የነበረዉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ሕግ የገጠር ዕርሻ መሬት በኑዛዜ ስለሚተላለፍበት አግባብ ምን ይላል የሚለዉን መመልከት ያስፈልጋል፡፡አስቀድሞም ለጉዳዩ ተፈጻሚ ሊሆን የሚገባዉን የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ሕግ መለየት ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ አኳያ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ኑዛዜዉ የተደረገበትን ጊዜ መሰረት በማድረግ ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ያለዉ የአማራ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 252/2009 ሳይሆን ከዚህ ቀድሞ ተግባራዊ ሲሆን የነበረዉ አዋጅ ቁጥር 133/1998 ነዉ የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡ በእኛም እምነት የአማራ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 252/2009 ተፈጻሚ መሆን የጀመረዉ ከቀን 12/11/2009ዓ/ም ጀምሮ በመሆኑ እና በክሱ

የተጠቀሰዉ ኑዛዜ የተደረገዉ ደግሞ ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት በቀን 19/03/2009ዓ/ም በመሆኑ ለተያዘዉ ጉዳይ ይህ ኋለኛዉ አዋጅ ተፈጻሚነት የለዉም በማለት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የደረሰበት ድምዳሜ ትክክል ነዉ፡፡

በክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 133/1998 አንቀጽ 7(1/ለ)፣15/1 ስር እንደተመለከተዉ ዝርዝሩ ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብ በሚወሰንበት አግባብ በክልሉ ዉስጥ ነዋሪ የሆነ በግብርና ሥራ የሚተዳደር ወይም በዚሁ ለመተዳደር የሚፈልግ ማንኛዉም ሰዉ የገጠር መሬት ይዞታ መብት (holding right) በዉርስ ወይም በስጦታ ማግኘት እንደሚችል ተደንግጓል፡፡እንዲሁም የገጠር መሬት በኑዛዜ እና ያለኑዛዜ ስለሚተላለፍበት አግባብ በአዋጁ አንቀጽ 16 ስር ተመልክቷል፡፡ሆኖም በዚህ አዋጅ ላይ መሬት በኑዛዜ ለማስተላለፍ የሚደረገዉን ኑዛዜ አጻጻፍ ስርዓት ወይም ፎርማሊቲ በተመለከተ የተደነገገ ነገር የለም፡፡በዚህ አዋጅ የተቋቋሙት የወረዳ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽሕፈት ቤትም ሆነ የቀበሌ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴ የገጠር መሬት በኑዛዜ ሲተላለፍ የሚኖራቸዉ ተግባርና ኃላፊነት ተለይቶ ተገልጾ አልተደነገገም፡፡ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም በወጣዉ ደንብ ቁጥር 51/1999 አንቀጽ 11 ላይ የገጠር መሬት በኑዛዜ ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉ ሰዎች እነማን ሊሆኑ እንደሚችሉና ከዚህ ጋር በተያያዘ ኑዛዜዉ ስለሚኖረዉ ሕጋዊ ዉጤት ከመደንገጉ በስተቀር የኑዛዜ ፎርማሊቲ አስመልክቶ የደነገገዉ ነገር የለም፡፡እንዲሁም በዚህ ደንብ አንቀጽ 25/8 ስር የወረዳዉ ተጠሪ ጽሕፈት ቤት በወረዳዉ ዉስጥ የተቋቋመ አካል በማይኖርበት ጊዜና ሁኔታ ከገጠር መሬት ጋር የተያያዙ የኪራይ፣የዋስትና የስጦታና የመሳሰሉ ስምምነቶችን እንደሚመዘግብ (Record) የተደነገገ ቢሆንም የገጠር መሬት በኑዛዜ ሲተላለፍ ስለሚኖረዉ ተግባርና ኃላፊነት በግልጽ አለመደንገጉ እንደተጠበቀ ሆኖ በድንጋጌዉ *የመሳሰሉ ስምምነቶችን* የሚለዉ አገላለጽ ኑዛዜንም ያካትታል ቢባል እንኳን የተሰጠዉ ኃላፊነት መዝግቦ መረጃ ከመያዝ ያለፈ አይደለም፡፡

ከላይ በተገለጸዉ አኳኋን ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ያለዉ ልዩ ሕግ የገጠር መሬት በኑዛዜ ሲተላለፍ ሊከተል ስለሚገባዉ ፎርማሊቲና ፎርሙን ጠብቆ ያልተደረገ ኑዛዜ ስለሚያስከትለዉ ሕጋዊ ዉጤት በግልጽ ካልደነገገ ስለኑዛዜ ፎርማሊቲ በፍትሐ ብሔር የተደነገገዉን ተፈጻሚ ማድረግ ይገባል፡፡በተያዘዉ ጉዳይ በክሱ የተጠቀሰዉ ኑዛዜ ግልጽ ኑዛዜ መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር ከቁጥር 881 እስከ 883 ስር በግልጽ የሚደረግ ኑዛዜ ማሟላት ያለበት የፎርም መስፈርቶች፡- 1)ኑዛዜዉ በጽሁፍ መደረግ ያለበት ስለመሆኑ(የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 881/1 ይመለከተዋል)፣2) በአራት ምስክሮች ፊት መደረግ ያለበት ስለመሆኑ፣ምስክሮች ችሎታ ያላቸዉ መሆን እንዳለባቸዉ እንዲሁም በኑዛዜዉ ላይ ተናዛዡና ምስክሮች መፈረም ያለባቸዉ ስለመሆኑ(የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 881(1 እና 3)፣882 እና 883 ይመለከቷል)፣ 3) ኑዛዜዉ በተናዛዡና በአራት ምስክሮች ፊት መነበብና ይኸዉ ሥርዓት የተፈጸመ ስለመሆኑ ኑዛዜዉ የሚያመላክት መሆን ያለበት ስለመሆኑ(በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 881/2 ይመለከቷል)፣ እንዲሁም 4) እነዚህን መስፈርቶች አለማሟላት ስለሚያስከትለዉ ዉጤት ተደንግጓል፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ምንም እንኳን ግልጽ ኑዛዜ በዉል አዋዋይ ፊት እንዲደረግና እንዲረጋገጥ(Authentication) እንዲሁም እንዲመዘገብ (Registration) ሕግ

ባያስገድድም በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 882 ስር እንደተመለከተዉ ግልጽ ኑዛዜ በዉል አዋዋይ ፊት የተደረገ እንደሆነ ኑዛዜዉ በሁለት ምስክሮች ፊት ከተደረገና ከተፈረመ በእነዚሁ ሁለት ምስክሮች ከተፈረመ ሕጋዊ ዉጤት ይኖረዋል፡፡ከዚህ ጋር በተያያዘ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 49851 (በቅጽ 10 እንደታተመዉ) ላይ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ ከዚህ ዉጭ ኑዛዜዉ በሕግ ዉል እንዲያዋዉል ሥልጣን በተሰጠዉ ፊት ያልተደረገ እንደሆነ ግን ኑዛዜዉ በአራት ምስክሮች ፊት ተደረጎ በአራቱም ምስክሮች የተፈረመ መሆን አለበት፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች መብት አገኘሁበት ያሉት ኑዛዜ በሦስት ምስክሮች ፊት ተደርጎ የተፈረመ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ አመልካች ኑዛዜዉ ሕጋዊ ዉጤት ሊኖረዉ ይገባል በማለት የሚከራከሩት ኑዛዜዉ በወረዳዉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽሕፈት ቤት የተደረገ ስለሆነ መስፈርቱን ያሟላል በማለት ነዉ፡፡ ከላይ እንደተመለከተዉ የወረዳዉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ተጠሪ ጽሕፈት ቤት ኑዛዜ ሲደረግ እንደዉል አዋዋይ ሆኖ ተናዛዡ ፈቃዱን በፈለገዉ መሰረት መግለጹን በማረጋገጥ ተናዛዡና ምስክሮች ሲፈርሙ ያረጋገጣል በሚል በአዋጅ ቁጥር 133/1998ም ሆነ በደንብ ቁጥር 51/1999 ላይ በግልጽ አልተደነገገም፡፡ዉል የማዋዋል እና የማረጋገጥ ጉዳይ በሕግ ሥልጣን በተሰጠዉ አካል በሚመደብ የሕግ ባለሙያ የሚፈጸም ተግባር ነዉ፡፡አከራካሪዉ ኑዛዜ በተደረገበት ጊዜ በነበረዉ ሕግ ለወረዳዉ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽሕፈት ቤት የተሰጠዉ ሥልጣን መዝግቦ መረጃ የመያዝ (Recordnig) እንጂ ኑዛዜ የማስፈጸምና የማረጋገጥ(Authentication) ተግባር እንዲፈጽም ሥልጣን አልተሰጠዉም፡፡

በመሆኑም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች ለክሳቸዉ መሰረት ያደረጉት ኑዛዜ ሕጋዊ ዉጤት የለዉም በማለት የስር ፍርድ ቤቶችን ዉሳኔ ሽሮ በመወሰኑ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2/4 እና 10(1/ሐ እና መ) መሰረት በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የሕግ ስህተት አልተፈጸመም ብለናል፡፡በዚህ መሰረት ተከታዩ ተወስኗል፡፡

## ዉሳኔ

1. የአማራ ብሔራዊ ክልል መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁጥር 0335672 ላይ በቀን 30/02/2015ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/1 መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ያወጡትን ወጭ ግራ ቀኝ የየራሰቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡

## ትዕዛዝ

1. የዉሳኔዉ ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡ሲጠይቁ ለግራ ቀኙም ግልባጩ ይሰጣቸዉ፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

**ማ/ተ**

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሠ/መ/ቁጥር 235739

ጥቅምት 07 ቀን 2016 ዓ/ም

ዳኞች ፡- እትመት አሰፋ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግሥቱ

አመልካች ፡- አቶ ዲባባ ኡርጋአ------------ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ሸዋዬ ተሾመ ------------- አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የገጠር እርሻ መሬት ባለይዞታነት መብት መፋለምን የሚመለከት ነዉ፡፡ ክርክሩ የተጀመረዉ በኦሮሚያ ክልል በምዕራብ ሸዋ ዞን በሜታ ሮቢ ወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁን ተጠሪ ከሳሽ አቶ አሰፋ ዲባባ ደግሞ ተከሳሽ በመሆን የጋብቻ ፍቺ ዉጤት ረገድ የተሰጠዉ ዉሳኔ መብቴን ነክቷል በሚል አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 358 መሰረት ባቀረቡት አቤቱታ መነሻ የስር ወረዳ ፍርድ ቤት የአሁን

አመልካችንና ተጠሪ እንዲሁም የስር ተከሳሽን ክርክር እና ማስረጃዎችን ሰምቶና መርምሮ በተጠሪ እና በስር ተከሳሽ መካከል የነበረዉን የንብረት ክርክር እስመልክቶ በጋብቻቸዉ ዉል ላይ ለባልና ሚስት የተሰጠዉ ሁለት ጥማድ መሬት ተብሎ ከተወሰነዉና በክሱ ከተጠቀሰዉ መሬት ላይ 1/4 ጥማድ መሬት የአሁን አመልካች ነዉ በማለት ወስኗል፡፡አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዉ ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ በሰጠዉ ዉሳኔ በዉሳኔዉ አዋሳኞቹ ከተጠቀሰዉ መሬት ላይ ግማሽ ጥማድ መሬት ይዞታ የአመልካች ስለሆነ ተጠሪና የስር ተከሳሽ ከሚያደርጉት የንብረት ክፍፍል ዉጭ ሊሆን ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰጠዉ ዉሳኔ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበዉ ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ በሰጠዉ ዉሳኔ ከሜታ ሮቢ ወረዳ የገጠር መሬት አስተዳደር አጠቃቀም ጽ/ቤት የቀረበዉ የጽሁፍ ማስረጃ ክርክር የተነሳበት ይዞታ በአመልካች ስም ተመዝግቦ የሚገኝ መሆኑን የሚገልጽ ቢሆንም በይዞታዉ ላይ ላይ የሚኖረዉና እየተጠቀሙበት የሚገኙት ተጠሪ እና ባለቤታቸዉ እንደሆኑ ስለተረጋገጠ በክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 130/1999 መሰረት ይዞታ የሚገኘዉ ከበተሰብ ስጦታ ጭምር በመሆኑ አመልካች አከራካሪዉን የመሬት ይዞታ ልጃቸዉ(የስር ተከሳሽ) ተጠሪን ሲያገባ በስጦታ መስጠታቸዉ ስለተረጋገጠ የይዞታ ማረጋገጫ ማስረጃ በስማቸዉ በመኖሩ ብቻ በተጠሪና በልጃቸዉ መካከል የነበረዉ ጋብቻ በመፍረሱ የእኔ ነዉ በማለት መከራከራቸዉ የሕግ ድጋፍ የለዉም በማለት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠዉን ዉሳኔ በመሻር የወረዳዉን ፍርድ ቤት ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡

በመቀጠል አመልካች ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታቸዉን አቅርበዉ ችሎቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ በሰጠዉ ዉሳኔ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት በተሰጠዉ ዉሳኔ ላይ የተፈጸመ ስህተት የለም በማለት አጽንቷል፡፡

አመልካች በቀን10/02/2015 ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ከላይ በተመለከተዉ መሰረት በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በተሰጠ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን የአቤቱታቸዉ ይዘት በአጭሩ፡- ለክሱ መነሻ ከሆነዉ መሬት ይዞታዉ በእኔ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ነዉ፡፡እንዲሁም የመንግሥት ግብር እየከፈልኩበት ይዞታዉ በቁጥጥሬ ስር ለመሆኑ የወረዳዉ የመሬት እና አካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት በላከዉ ሪፖርት አረጋግጧል፡፡ጉዳዩን ያጣሩት የአገር ሽማግሌዎችም ይዞታዉ የእኔ መሆኑን አረጋግጠዋል፡፡ በኦሮሚያ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 130/99 ስር በተደነገገዉ መሰረት አንድ የገጠር እርሻ መሬት በስጦታ ለሌላ ሰዉ ስተላለፍ የስጦታ ዉሉ በፅሁፍ መደረግ እንዳለበት እና ዉሉም በመሬት እና አከባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት መረጋገጥ እንዳለበት የተደነገገዉን በማለፍ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተጠሪ ያለ ማስረጃ በስጦታ አገኝቻለሁ በማለት ያቀረቡትን ክርክር ተቀብሎ የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ተሽሮ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠዉ ዉሳኔ ይጽናልኝ በማለት በመጠየቅ አቤቱታቸዉን አቅርበዋል፡፡

*ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

የሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ አመልካች ፍርዱን በመቃወም ባቀረቡት አቤቱታ መነሻ ጉዳዩ በማስረጃ ተጣርቶ ለተጠሪና ለስር ተከሳሽ ከተወሰነዉ የገጠር መሬት ይዞታ ላይ ½ ጥማድ መሬት ለአመልካች እንዲመለስ በተወሰነዉ መሰረት የማይመለስበትን ምክንያት ሳይገለፅ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የወሰነበት አግባብነት ከማስረጃ ምዘና መርህ አኳያ እንዲመረመር ተጠሪ መልስ እንዲሰጡ አዟል፡፡ሆኖም ተጠሪ መጥሪያ ደርሷቸዉ ባለመቅረባቸዉ መልስ የመስጠት መብታቸዉ ታልፏል፡፡

ከዚህ በላይ አጠር ባለ መልኩ የተመለከተዉ የግራ ቀኝ ክርክርና በክልሉ ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎችን እንዲሁም አመልካች ለዚህ ሰበር ችሎት ያቀረቡትን አቤቱታ ይዘት የሚመለከት ሲሆን እኛም የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ሲል የያዘዉን ጭብጥ ከግምት በማስገባት በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በይግባኝና በሰበር ታይቶ በተሰጠ ዉሳኔ ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነዉም በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግትሥት አንቀጽ 80(3/ሀ) ስር እንደተመለከተዉ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠዉ ሥልጣን ማናቸዉንም መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበትን የመጨረሻ ዉሳኔ በሕግ በዝርዝር በሚወሰነዉ አግባብ መርምሮ እንዲያርም ነዉ፡፡በዚህ የሕገ መንግሥቱ ድንጋጌ ላይ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ምንነት በግልጽ አልተደነገገም፡፡የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በተለያዩ መዛግብት ላይ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የሚያሰኙ ምክንያቶችን የሚያመላክቱ የሕግ ትርጉሞች ሲሰጥ ቆይቷል፡፡ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 80(3/ሀ) ስር በሰበር ችሎት የሚታይ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ምንነት በተመለከተ ጭምር ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል ተብሎ በተደነገገዉ አግባብ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 ላይ "መሠረታዊ የሕግ ስህተት" ለሚለዉ ሐረግ ትርጓሜ እስከተሰጠበት ጊዜ ድረስ ለሐረጉ በሕግ ትርጓሜ አልተሰጠም ነበር፡፡ስለሆነም አዋጅ ቁጥር 1234/2013 ከፀናበት ቀን 13/05/2013 ዓ/ም ጀምሮ በዚህ ችሎት ዉሳኔ ለሚሠጥባቸዉ ጉዳዮች በአዋጁ "ለመሰረታዊ የሕግ ስህተት" የተሰጠዉን ትርጓሜ ተከትሎ ዉሳኔ መስጠት የግድ ይላል፡፡
በአዋጁ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2/4 ስር "መሠረታዊ የሕግ ስህተት" የሚያሰኙ ምክንያቶች በዝርዝር እና በጥቅል አገላለጽ ትርጓሜ ተሰጥቶታል፡፡እንዲሁም ከክልል ፍርድ ቤቶች ተጀምረዉ በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች ሰበር ሰሚ ችሎቶች ታይተዉ በተሰጡ የመጨረሻ ዉሳኔዎች ላይ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል በዚህ ችሎት ታይተዉ ሊታረሙ የሚችሉ መሰረታዊ የሕግ ስህተቶች በአዋጁ አንቀጽ 10(1/ሐ እና መ) ስር የተጠቀሱት ብቻ ናቸዉ፡፡

በዚህ መሰረት መሰረታዊ የሕግ ስህተቶች ናቸዉ የሚያስብሉ ምክንያቶች - *(1)* በአዋጁ አንቀጽ 2(4/ሀ) ስር በተመለከተዉ መሰረት ሕገ መንግስታዊ ድንጋጌዎችን በሚቃረን አኳኋን በክልል ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠ የመጨረሻ ዉሳኔ ሲሆን፤ *(2)* በአዋጁ አንቀጽ 2(4/ሸ) ስር እንደተመለከተዉ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ዉሳኔ በሚቃረን አኳኋን በክልል ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠ የመጨረሻ ዉሳኔ ሲሆን፤ እንዲሁም *(3)* በአዋጁ አንቀጽ 2(4/ለ) ላይ እንደተመለከተዉ ሕግን አላግባብ በመተርጎ ወይም

ለጉዳዩ አግባብነት የሌለዉ ድንጋጌ ተጠቅሶ የተሰጠ የመጨረሻ ዉሳኔ ሆኖ ይህ ዉሳኔ የተሰጠበት ጉዳይ ለሕዝብ ጥቅም ሀገራዊ ፋይዳ ያለዉ ጉዳይ ሲሆን በሚል በሕጉ ከተጠቀሱት ሦስቱ ምክንያቶች መካከል ቢያንስ አንዱን የሚያሟላ እና ፍትህን የሚያዛባ ጉልህ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት የመጨረሻ ዉሳኔ ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነዉ፡፡

በያዝነዉ ጉዳይ አከራካሪዉ የገጠር መሬት ይዞታ ተጠሪ እና የአመልካች ልጅ የስር ተከሳሽ ጋብቻቸዉን ሲፈጽሙ አመልካች በጎጆ መዉጫነት በምስክሮች ፊት እንደሰጧቸዉ በሕግ ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን የተሰጣቸዉ የወረዳ ፍርድ ቤት እና ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተዉ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያረጋገጡት ፍሬ ነገር ነዉ፡፡የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ዉሳኔ የሰጠዉም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በማስረጃ ያረጋገጠዉን ይህንኑ ፍሬ ነገር መሰረት በማድረግ ነዉ፡፡የስጦታ ዉል በተለይም በልማድ የዳበረዉ በየአካባቢዉ ማሕብረሰብ ለጎጆ መዉጫነትትነት ተብሎ የሚሰጥ የገጠር እርሻ መሬት የተለየ ፎርም እንዲኖረዉ የሚያስገድድ ድንጋጌ በወቅቱ ተግባራዊ ሲሆን በነበረዉ በኦሮሚያ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 130/1999 ላይ አልተመለከተም፡፡በዚህ መልኩ በሕጉ ጥብቅ ፎርማሊቲ ያልተደነገገበት ምክንያት ይህ እሴት ያለዉን ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጠቀሜታ ከግምት በማስገባት ጥብቅ ስርዓት መከተል አስፈላጊ እንዳልሆነ በማሰብ ነዉ፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ለጎጆ መዉጫ ተብሎ የሚደረግ የገጠር መሬት ስጦታ የተለየ የዉል ፎርም እንዲኖረዉ ሕጉ የግድ የሚለዉ አለመሆኑን በሰ/መ/ቁጥር 107840፣ 197998፣ 206535 እና ሌሎች መሰል መዛግብት ላይ የሕግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ ከዚህም የምንገዘበዉ ከገጠር መሬት ይዞታ አጠቃቀም ጋር በተያያዘ በተለይም የባለይዞታዉ ልጅ ወይም ሌላ የባለይዞታዉ የቤተሰብ አባል ትዳር ሲይዝ ለመተዳደሪያ የሚሆን በተለምዶ ለጎጆ መዉጫ ተብሎ የሚደረግ የመሬት ስጦታ ጥብቅ የሆነ የአጻጻፍ ስርዓት ወይም የስጦታ ዉል ፎርም ባያሟላም በየማህበረሰቡ የዳበረዉን ልማድ እና ጠቃሚ እሴት ከግምት በማስገባት ሕጋዊ ዉጤት እንዲኖረዉ ማድረግ ተገቢነት ያለዉ ስለመሆኑ ነዉ፡፡በያዝነዉም ጉዳይ ጉዳዩን በይግባኝና በሰበር አይቶ ዉሳኔ የሰጠዉ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ መሬት ለተጠሪና ለስር ተከሳሽ በጎጆ መዉጫነት የተሰጠ ነዉ በማለት የደረሰበት ድምዳሜ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጁንና በተጠቃሾች መዛግብት ላይ የተሰጠዉን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መሰረት ያደረገ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

በመሆኑም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4/ሀ፣ለ እና ሸ) እና 10(1/ሐ እና መ) ስር የተደነገጉ መስፈርቶችን በሚያሟላ መልኩ በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ባለመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## <u>ዉ ሳ ኔ</u>

1. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 402561 ላይ በቀን 01/02/2015ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/1 ጸንቷል፡፡

2. ግራ ቀኝ በዚህ ችሎት ደረጃ ያወጡትን ወጭ የየራሳቸዉን እንዲችሉ ብለናል፡፡

## ትዕዛዝ

1. የዉሳኔዉ ግልባጭ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡ ለግራ ቀኙም ግልባጩ ይሰጣቸዉ፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/ተ

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ. 235430

ቀን ፡- ጥቅምት 06 ቀን 2016 ዓ/ም

ዳኞች፡- እትመት አሰፋ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

አመልካች ፡- የአቃቂ ቃሊቲ ክፍለከተማ የመሬት ልማትና ከተማ ማደስ ጽ/ቤት

ተጠሪ ፡- አቶ ደገፉ በየነ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

**ፍርድ**

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው አመልካች በስር ፍርድ ቤት ተከሳሽ፤ ተጠሪ ከሳሽ ሆነው ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን ተጠሪ በ25/08/2014 ዓ/ም ጽፈው ባቀረቡት ክስ ከግንቦት 19 ቀን 2013 ዓ/ም ጀምሮ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 12 ውስጥ 11694 ካሬ ሜትር ይዞታ አለኝ፤ አንደኛ 5356.8 ካ/ሜ ይዞታ ዳር ድንበሩ በምዕራብ የአቶ ጫኔ ጉደታ ይዞታ ከሚያዋስነን በቀር በሌሎቹ በቀሪዎቹ 3 አቅጣጫዎች በመንገድ የሚዋሰን፤ ሁለተኛ 2340 ካ/ሜ ይዞታ ዳር ድንበሩ በምዕራብ የአርቲስት አጫሉ ሁንዴሳ መታሰቢያ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከሚያዋስነው በቀር በቀሪዎቹ 3 አቅጣጫዎች በመንገድ የሚዋሰን፤ ሶስተኛ 4000 ካ/ሜ ይዞታ ዳር ድንበሩ በምዕራብ የአርቲስት አጫሉ ሁንዴሳ መታሰቢያ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከሚያዋስነው በቀር በቀሪዎቹ 3 አቅጣጫዎች በመንገድ የሚዋሰን ከ35 ዓመታት በላይ

በእጄ አድርጌ የተለያዩ ሰብሎችን ሳመርትበት የነበረውን አመልካች ምንም ዓይነት ካሳ ወይም ጥቅም ሳላገኝ ይዞታዬን ለተሽከርክሪዎች ማቆሚያ አገልግሎት ስላዋለው የፈጠረብኝ ሁከት እንዲወገድልኝ እና በዚህ ክስ ምክንያት ያወጣሁትን ወጪ በቁርጥ እንዲከፍለኝ እንዲወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

አመልካችም በ16/09/2014 ዓ/ም ጽፈው ባቀረቡት የመከላከያ መልስ ይዞታው በቂ ካሳ ተከፍሎበት የተወሰደ፤ ይህ ከተደረገ ከ2 ዓመት በላይ ጊዜ ያስቆጠረ ስለሆነ ክሱ በይርጋ ቀሪ ይሆናል የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡ በፍሬ ነገር ክርክሩም መንግስት መሬቱን ለልማት በወሰደ ጊዜ ተገቢውን ካሳ ከፍሏል፤ ጥያቄያቸው ያልተገባ ጥቅም ማግኘትን ያለመ ነው፡፡ መሬቱ ከግለሰቡ ለተወሰደበት ዓላማ ውሎ ቀሪው የተረፈው ቀሪ ይዞታ ላይ የኔ ነው ሁከት ተፈጥሮብኛል ሲሉ ያቀረቡት የሁከት ይወገድልኝ ክስ ተገቢነት የሌለው እና ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት ያለመ ስለሆነ ክሳቸው ውድቅ እንዲደረግልኝ በማለት እና ተጠሪ ያያያዙዋቸው የሰነድ ማስረጃዎች ላይም አስተያየት በመስጠት የመከላከያ መልሳቸውን አቅርበዋል፡፡

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቱም በአመልካች የቀረበውን ክሱ በይርጋ የታገደ ነው የሚለውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ መርምሮ የሁከት ተግባሩ ከቀን 19/09/2013 ዓ/ም ጀምሮ በይዞታችን ላይ የሁከት ተግባር ፈጽመውብኛል በማለት ክስ ያቀረቡ ስለሆነ መቃወሚያው ተቀባይነት የለውም በማለት የይርጋ መቃወሚያውን ውደቅ አድርጓል፡፡ በመቀጠል የፍሬ ነገር ክርክሮቹን በተመለከተ አንደኛውን ጭብጥ በተመለከተ ተጠሪ አሁን ክርክር ያቀረቡበት ይዞታ ላይ ቀድመው በእርሻ ሥራ እና ለግጦሽነት ሲገለገሉበት የነበረ ስለመሆኑ የቀረቡት ማስረጃዎች ያስረዱ በመሆኑ፤ አመልካችም ቢሆን በፕላኑ መሰረት ለሌላ አገልግሎት የሚፈለግ ይዞታ ነው ከማለት በቀር ይዞታው በተጠሪ ይዞታ ስር አልቆየም፣ በተጠሪ ይዞታ ስር አይገኝም እንዲሁም ይዞታውን ሲያርሱ አልነበረም የሚል ክርክርም ስላልቀረበ ተጠሪ ይዞታውን ለእርሻ እና ለግጦሽ ሲገለገሉበት ቆይተዋል በማለት ተወስኗል፡፡ ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ በቀድሞው ፕሮጀክት ካሳ የተከፈለባቸው መረጃዎች በተሟላ ሁኔታ በጽ/ቤታችን ተደራጅተው አይገኙም፣ የሚገኘው የቀድሞ የልማት ፕሮጀክቶች ማህደራትም ቢሆኑ በወረዳው ኮሚቴ እና በወቅቱ በነበረው ቀበሌ/ወረዳ ኃላፊ ስም እና ፊርማ እንዲሁም ባለይዞታ ተፈረመበት በልማት የተካለለውን የይዞታ መጠን ከሚገልጽ መተማመኛ በስተቀር ካሳ የተከፈለበትን ቦታ የሚያሳይ ኮኦርዲኔት የለውም፣ ካሳ የተከፈለበት ስለመሆኑ የሚያሳይ ሰነድ ወይም ደረሰኝ አልቀረበም፡፡ በመሆኑም ለግራ ቀኙ በኮኦርድኔት የተቀመጠ መረጃ ባለመኖሩ እንዲሁም ተጠሪ የካሳ ክፍያም ሆነ ምትክ ቦታ አልተሰጣቸውም ተብሎ ተወስኗል፡፡ ሶስተኛውን ጭብጥ በተመለከተ አመልካች በተጠሪ ህጋዊ ይዞታ ላይ የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን ሲያደርጉ፣ ይዞታውንም ሲይዙ የቆዩ መሆኑ ስለተረጋገጠ አመልካች በተጠሪ ላይ የፈጸሙትን የሁከት ተግባር ይዞታውን በመልቀቅ፣ ለሌላ ለ3ኛ ወገን ይዞታውን ባለማስተላለፍ መብታቸውን በመመሪያ እና ደንብ መሰረት መብታቸውን በመጠበቅ የፈጸሙትን የሁከት ተግባር ሊያስወግዱ ይገባል በማለት ተወስኗል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረቡትን የይግባኝ አቤቱታ ባለመቀበል ሰርዟል፡፡

*ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

ይሕ የሠበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው፡፡ አመልካች በቀን 03/02/2015 ዓ/ም በጻፈው የሰበር አቤቱታ አመልካች በጋራ ኮንዶሚኒየም ፕሮጀክት ምክንያት ከ1998 ዓ/ም ጀምሮ ከ16 ዓመት በላይ የተጠቀመበትን እና አሁንም ድረስ እየተጠቀመበት የሚገኘውን ይዞታ ተጠሪ የሁከት ይወገድልኝ ክስ ጥያቄያቸውን ማቅረብ የሚችሉት ይዞታው ከእጃቸው ከወጣ በ2 ዓመት ጊዜ ያላቀረቡ ስለሆነ ክሳቸው በይርጋ የሚታገድ ነው ብለን ብንከራከርም ፍርድ ቤቱ ምንም ዓይነት ማጣራት ሳያደርግ፤ የሰው ማስረጃ አስቀርቦ ሳይመረምር የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው፡፡ በፍሬ ነገር ደረጃ የሰበር አመልካች ይዞታውን ከ1998 ዓ/ም ጀምሮ ለህዝብ ጥቅም ሲባል ከይዞታቸው ለሚነሱ ግለሰቦች አስፈላጊ ካሳ ከፍለን በእጃችን አድርገናል፡፡ በከተማው ማስተር ፕላን መሰረት በዚያው ኮንዶሚኒየም ለሚኖሩ ማህበረሰብ ለተለያዩ ማህበራዊ አገልግሎት ጥቅም እየሰጠ መሆኑን አስረድተንና በእውነት ይዘን እያዘዝንበት መሆኑን እና አከራካሪውንም ቦታ በጊዜያዊነት በጥቃቅን እና አነስተኛ የተደራጁ ወጣቶች እየተጠቀሙበት ይገኛል፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ ባቀረቡት የሁከት ይወገድልኝ ዳኝነት ጥያቄ ላይ ብቻ ሁከት ተፈጥሯል አልተፈጠረም በሚለው ጭብጥ ላይ ብቻ ግራ ቀኙን አከራክሮ እና መስረጃ መርምሮ መወሰን ሲገባው ይህንን ሳያደርግ ዳኝነት ባልተጠየቀበት የሰጠው ውሳኔ አግባብነት የሌለው ነው፡፡ የሰበር አመልካች አከራካሪውን ቦታ ከ1998 ዓ/ም ጀንሮ ዛሬም ድረስ በእጁ አድርጎ በእውነት እያዘዘበት በጥቃቅንና አነስተኛ ወጣቶች ተደራጅተው ለጊዜውም ቢሆን እየተጠቀሙበት ያለ ቦታ ስለመሆኑ የሰው እና የሰነድ ማስረጃ አቅርበን ብንከራከርም ቦታው በማን እጅ እንደሚገኝ ፍርድ ቤቱ ማጣራት ሳያደርግ የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ የስር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ሙሉ በሙሉ እንዲሻርልን እና አመልካች የፈጠረው ሁከት የለም በማለት ውሳኔ እንዲሰጥለት ጠይቋል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን ተመልክቶ ተጠሪ ክስ ያቀረቡበት ይዞታ ላይ ካሳም ሆነ ምትክ ቦታ አልተሰጣቸውም በሚል ስር ፍርድ ቤት ሁከት ይወገድ በማለት የወሰነበትን አግባብነት ከመመሪያ ቁጥር 19/2006 እና ከፍ/ብ/ህ/ቁ 1149 አኳያ ለማጣራት ተጠሪ መልስ እንዲያቀርቡ አዟል፡፡ ተጠሪ በ19/03/2015 ዓ/ም በተጻፈ በሰጡት የመከላከያ መልስ ይርጋን አስመልክቶ በስር ፍርድ ቤት እንዳስረዳሁት አመልካች የሁከት ድርጊት የፈጸመው በ19/09/2013 ዓ/ም ሲሆን ተጠሪ ክስ አቅርቤ የነበረው በ25/08/2014 ዓ/ም ስለሆነ ክሱ ሁለት ዓመት ሳይሞላው የቀረበ ስለሆነ በይርጋ አይታገድም፡፡ ክስ የመሰረትኩበት ቦታ አመልካች በሰበር አቤቱታቸው ላይ የጠቀሱት መሰረተ ልማቶች እና የኮንዶምንየም ግንባታ ያሉበት ቦታ ሳይሆን የአሁኑ መልስ ሰጪ በስር ፍርድ ቤት በማስረጃ እንዳስረዳሁት በህጋዊ መንገድ በእጄ አድርጌ ከ1982 ዓ/ም እስከ 2014 ዓ/ም ድረስ ግብር እየከፈልኩበት ለእርሻ አግልግሎት ስገለገልበት የነበረ እና የአሁኑ አመልካች ከ19/09/2013 ዓ/ም ለመኪና ማቆሚያ አገልግሎት እንዲሆን በማድረግ የሁከት ድርጊት በፈጸሙበት ይዞታ ላይ ነው፡፡ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ከ1982 ዓ/ም እስከ 2013 ዓ/ም ድረስ በይዞታው ላይ ግብር በመክፈል ህጋዊ በሆነ መንድ የያዝኩት መሆኑን የሰነድ ማስረጃዎችን ወይም የግብር ደረሰኞችን በማቅረብ አረጋግጫለሁ፡፡ ተጠሪ ሁከት የተፈጸመበትን ይዞታ የአሁኑ አመልካች ሁከት እስከፈጠረበት 19/09/2013 ዓ/ም ድረስ በእጄ አድርጌ ሳዝበት እና ስገለገልበት የቆየሁ መሆኑን የሚያስረዱ የሰውም ሆነ

የሰነድ ማስጃዎችን ዘርዝሬ ያቀረብኩ ስለሆነ አመልካች ያቀረበው ቅሬታ አግባብነት የለውም በማለት የመከላከያ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ አመልካች በ12/04/2015 ዓ/ም በሰጡት የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው ተጠሪ በ25/08/2014 ዓ/ም ጽፈው ባቀረቡት ክስ ከግንቦት 19 ቀን 2013 ዓ/ም ጀምሮ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 12 ውስጥ 11694 ካሬ ሜትር ይዞታ አለኝ፤ ከ35 ዓመታት በላይ በእጄ አድርጌ የተለያዩ ሰብሎችን ሳመርትበት የነበረውን አመልካች ምንም ዓይነት ካሳ ወይም ጥቅም ሳላገኝ ይዞታዬን ለተሽከርካሪዎች ማቆሚያ አገልግሎት ስላዋለው የፈጠረብኝ ሁከት እንዲወገድልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አመልካች በበኩሉ ይዞታው በቂ ካሳ ተከፍሎበት የተወሰደ፤ ይህ ከተደረገ ከ2 ዓመት በላይ ጊዜ ያስቆጠረ ስለሆነ ክሱ በይርጋ ቀሪ ይሆናል የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርቧል፡፡ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቱም የሁከት ተግባሩ ከቀን 19/09/2013 ዓ/ም ጀምሮ በይዞታችን ላይ የሁከት ተግባር ፈጽመውብኛል በማለት ክስ ያቀረቡ ስለሆነ መቃወሚያው ተቀባይነት የለውም በማለት የይርጋ መቃወሚያውን ውደቅ በማድረግ በሥረ-ነገሩ አመልካች የፈጠረው ሁከት እንዲወገድ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

የይርጋ ክርክሩ የቀረበው ተጠሪ ክሱን ለማቅረብ የክስ የማቅረቢያ ጊዜው አልፏል በሚል ነው፡፡ ይርጋ መብትን (extinctive prescription) እና መብትን ለማስከበር የሚቀርብ ክስን በጊዜ ገደብ ቀሪ የሚያደርግ (limitation of action) ነው፡፡ እንደክሱ መሠረት ዓይነት ተፈጻሚ የሚሆነው የይርጋ ደንብና ሕግ የተለያየ ነው፡፡ ተጠሪ የሁከት ይወገድልኝ ክስ ያቀረቡ በመሆኑ ለቀረበው የክስ ምክንያት ተፈጻሚነት ያለው የይርጋ ደንብ በፍትሐ ብሔር ሕጉ አንቀጽ 1149/2/ የተመለከተው የሁለት ዓመት የይርጋ ጊዜ ነው፡፡ የይርጋ ጊዜና አቆጣጠር በተመለከተ በፍ/ሕ/ቁ. 1846 "የይርጋው መነሻ ጊዜ" በሚል ርእስ ሥር "የይርጋው ቀን መቆጠር የሚጀምረው ግዴታዉን ለመጠየቅ ተገቢ ከሆነዉ፤ ወይም ዉሉ የሚሰጠዉ መብት ከተሰራበት ቀን ጀምሮ ነዉ" በማለት ከተደነገገው ጋር ተገናዝቦ ሊመረመር ይገባል፡፡ በመርሕ ደረጃ በፍ/ሕ/ቁ. 1846 እንደተመለከተውም ይርጋ ጊዜ መቁጠር የሚጀምረው በመብቱ መሥራት ከሚችልበት ጊዜ ጀምሮ ነው፡፡ ተጠሪ በመብታቸው መሥራት የሚችሉትና የሁከት ይወገድልኝ ክስ ማቅረብ የሚችሉት በተጠሪ ይዞታ አጠቃቀም ላይ የአመልካች ኃይል ድርጊት ወይም ጣልቃ ገብነት ከተከሰተበት ጊዜ ጀምሮ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ነው፡፡

መቃወሚውን ለመወሰን የኃይል ድርጊቱ ወይም በይዞታ አጠቃቀሙ ላይ ጣልቃ ገብነት የተፈጸመው መቼ ነው የሚለውን የፍሬ ነገር ክርክር በማስረጃ ማጣራት ያስፈልጋል፡፡ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 245/1/ እንደተመለከተው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያን ለመወሰን ማስረጃ መስማት ካስፈለገ ተገቢውን ፍሬ ነገር በማስረጃ በማጣራት መወሰን ያለበት ስለመሆኑ የተደነገገ ሲሆን አመልካች ያቀረቡትን የይርጋ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ለመወሰን የኃይል ድርጊቱ ወይም በይዞታ አጠቃቀሙ ላይ ጣልቃ ገብነት የተፈጸመው

መቼ ነው፣ ይዞታው በአመልካች እጅ ከሁለት ዓመት ጊዜ በላይ የቆየ መሆን አለመሆኑን መመርመር ይገባል፤ እነዚህ ክርክሮች የፍሬ ነገር ጥያቄ በመሆናቸው ፍሬ ነገርን በሚረጋገጥበት ዘዴ ማስረጃ መስማትን ጨምሮ በማጣራት ተጠሪ በመብታቸው መስራት የሚችሉት ከመቼ ጊዜ ጀምሮ ነው፣ ይርጋው መቆጠር ያለበት ከመቼ ጊዜ ጀምሮ ነው የሚለውን በመለየት በአመልካች በቀረበው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ የሥር ፍርድ ቤቶች ሊወሰኑ ሲገባ በዚህ አግባብ ሳያጣሩ መቃወሚያውን ውድቅ በማድረግ ወደሥረ-ነገር ክርክር አልፈው መወሰናቸው መሠረታዊ የሆነ የክርክር አመራር ግድፈት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 295477 ነሀሴ 26 ቀን 2014 ዓ/ም እና የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 302819 ሰኔ 28 ቀን 2014 ዓ/ም የሠጡት ውሳኔ በሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/1/ለ/ መሰረት ተሽሯል፡፡

2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በፍርዱ በተመለከተው መሠረት አመልካች ያቀረበውን የይርጋ መቃወሚያ ለመወሰን በክሱ የተመለከተው የኃይል ድርጊቱ ወይም በይዞታ አጠቃቀሙ ላይ ጣልቃ ገብነት የተፈጸመው መቼ ነው፣ ይዞታው በአመልካች እጅ ከሁለት ዓመት ጊዜ በላይ የቆየ መሆን አለመሆኑን በግራቀኙ ማስረጃ በማጣራት መቃወሚያ ላይ በሕግ መሠረት ውሳኔ እንዲሰጥበትና ጉዳዩ በይርጋ የማይቋጭ ከሆነ በሥረ-ነገሩ ውሳኔ እንዲሰጥበት በሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/2/ መሠረት ጉዳዩን መልሠናል፡፡

3. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

- የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በውሳኔው መሠረት እንዲፈጽም አዘናል፡፡ ይጻፍ
- የሥር ፍርድ ቤት መዝገብ ይመለስ፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ማ/ተ

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

**በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**
**የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት**

የሰ.መ.ቁ 235209

ጥቅምት 07 ቀን 2016 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** እትመት አሠፋ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

ሐብታሙ እርቅ ይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

አመልካቾች፡- 1. ሰዓዳ መሀመድ ይመር
2.ሃሊማ መሀመድ ይመር
3. አልማዝ መሀመድ ይመር
4. ኑረዲን መሀመድ ይመር
----- ጠበቃ ይሄነው ደሴ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የአልብኮ ወረዳ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት---------- አልቀረቡም

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው፡፡ በዚሁ አግባብ መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካቾች መስከረም 27 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የአልብኮ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 0119502 ግንቦት 29 ቀን 2014 ዓ.ም አመልካቾች ያቀረቡት ክስ በካሳ አጣሪ ኮሚቴ ያልታየ በመሆኑ ቅድሚያ ሊቀርብ የሚገባው ለተቋሙ አስተዳደራዊ ውሳኔ እንዲያገኝ እንጂ መደበኛ ፍርድ ቤት ሊቀርብ አይገባም በማለት የሰጠው ብይን፤ ይህንኑ ብይን በማጽናት በየደረጃው ያሉ የክልሉ ፍርድ ቤቶች የሰጡት ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ጉዳዩ የገጠር መሬት ክርክር የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት አልብኮ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በስር ፍርድ ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን አመልካቾች ከሳሾች፤ የአሁን ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ አመልካቾች በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ ይዘት በአጭሩ፡- በአልብኮ ወረዳ 05 ቀበሌ ልዩ ቦታ አባዋሪሆን በተባለ ስፍራ የሚገኝ እና አዋሳኙ በክሱ የተገለጸ ስፋቱ 961.59 ካ.ሜ የሆነ መሬት ከሟች አባታችን አቶ መሐመድ ይመር በውርስ አግኝተናል፤ ተጠሪ በሕግ የተደነገጉትን ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የገጠር መሬት የሚለቀቅበትን ሥርዓት ሳይከተል እና ትክ ቦታ ሳይሰጠን ይዞታውን ለግለሰቦች ቤት መስርያ ሰጥቷል፤ ስለሆነም ይዞታውን እንዲያስረክበን እና ይዞታው ግንባታ ያልተፈጸመበት በመሆኑ በአመልካቾች እጅ እንዳለ ተቆጥሮ መብታችን እንዲከበር ይወሰንልን በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

ተጠሪ በሰጠው መልስ ለሕዝብ ጥቅም የሚለቀቅ ይዞታ አስመልክቶ በካሳ እና ተመን አከፋፈል ቅሬታ ካለ ጉዳዩን ማየት ያለበት ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንጂ የወረዳው ፍርድ ቤት አይደለም፤ አመልካቾች ያቀረቡት ክስ አስተዳደራዊ መፍትሔ ከሚሰጠው በቀር በመደበኛ ፍርድ ቤት የሚታይ አይደለም፤ ክስ የቀረበበት ይዞታ ለሕዝብ ጥቅም የተወሰደው መመሪያ ቁጥር 7/2010 ስራ ላይ ከመዋሉ በፊት ስለሆነ በወቅቱ በነበረው ሕግ የሚስተናገድ ይሆናል፤ በወቅቱ በነበረው አዋጅ ቁጥር 133/1998 እና ደንብ ቁጥር 51/1999 አንቀጽ 29/3 ላይ በግልጽ እንደተቀመጠው ተቃውሞ ያለ እንደሆነ ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ውሳኔ የሚሰጥበት ነው፤ ጉዳዩንም ወደ መደበኛ ፍርድ ቤት ማምጣት አይፈቀደም በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርቧል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድም አመልካቾች ያቀረቡትን ክስ የማየት የስረ ነገር ስልጣን ፍርድ ቤቱ አለው ወይስ የለውም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምሮ 961.59 ካ.ሜ የሆነውን የአመልካቾች ወላጆች ይዞታ ለልማት ተነሺ የሆነ ይዞታ መሆኑ ጽ/ቤቱ አሳውቆ የካሳ ስሌት ተሰርቶ ገንዘቡ ተቀማጭ ተደርጓል፤ የካሳ ስሌቱ የተሰራውም ሆነ መሬቱ ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የተወሰደው በ2010 ዓ.ም ነው፤ በቀድሞ አዋጅ እና በደንብ ቁጥር 51/1999 አንቀጽ 29 እና 33/5 እንዲሁም በመመሪያ ቁጥር 7/2010 አንቀጽ 36/9 መሠረት መሬቱ ለሕዝብ አገልግሎት የተለቀቀ እንደሆነ በቅድሚያ ተመጣጣኝ የንብረት ካሣ በወቅቱ የገበያ ዋጋ ግምት እንዲከል በማድረግ ባለይዞታው መሬቱን እንዲለቅ ሊወሰን ይችላል፤ አመልካቾች በካሣ ተመን እና አከፋፈል ላይ ቅሬታ ያላቸው እንደሆነ በካሳ ቅሬታ አጣሪ ኮሚቴ ሊቀርብ ይገባል፤ በተሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ አካል ይግባኙን ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል፤ አመልካቾች ያቀረቡት ክስ በካሳ አጣሪ ኮሚቴ ያልታየ በመሆኑ ቅድሚያ ሊቀርብ የሚገባው ለተቋሙ አስተዳደራዊ ውሳኔ እንዲያገኝ እንጂ መደበኛ ፍርድ ቤት ሊቀርብ አይገባም በማለት የአመልካቾችን ክስ በብይን ውድቅ አድርጎታል፡፡ ይህም ብይን በየደረጃው ባሉ የክልሉ ፍርድ ቤቶች ጸንቷል፡፡

አመልካቾች መስከረም 27 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈው ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይህን ውሳኔ በመቃወም የቀረበ ሲሆን ይዘቱም፡- አመልካቾች ክስ ያቀረብን በውርስ ያገኘነውን ይዞታ ቅድሚያ ትክ ቦታ ሳይሰጠን ተጠሪ ስልጣኑን ተጠቅሞ ይዞታውን እንድንለቅ የሚያደርገው ጥረት ተገቢ ስላልሆነ በሕጉ አግባብ መብታችን

እንዲከበርልን ነው፤ የስር ፍርድ ቤት የአመልካቾች ጥያቄ የካሳ መጠን ቅሬታ እንደሆነ በመቁጠር ጉዳዩ በፍርድ ቤት ሊታይ የሚገባው አስተዳደራዊ ውሳኔ ከተሰጠበት በኋላ ነው ማለቱ አግባብ አይደለም፤ አመልካቾች ቅሬታችንን ለአስተዳደር አካላት እንድናቀርብ የሚያስገድደን ሕግ ባይኖርም ለቀበሌው አስተዳደር ቅሬታችንን አቅርበን ምላሽ አላገኘንም፤ አመልካቾች በሕጋዊ መንገድ የያዝነውን ይዞታ ከሕግ ውጪ ልቀቁ ስንባል ለመደበኛ ፍርድ ቤት አቤቱታ የማቅረብ መብት አለን፤ የስር ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለማየት የሚያስችል የስረ ነገር ስልጣን የለኝም በማለት የሰጠው ብይን ሕገመንግስታዊ የሆነ ፍትህ የማግኘት መብታችንን የሚጻረር እና መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የሰበር አጣሪው ችሎት የአመልካቾችን የሰበር አቤቱታ መርምሮ አመልካቾች ከሟች ወላጅ አባታችን በውርስ ያገኘነው የገጠር መሬት ለሕዝብ ጥቅም ተብሎ ሲወሰድብን ካሳ እና ምትክ ቦታ ሳይሰጠን መቅረቱ በገጠር መሬት ላይ ያለንን የመጠቀም መብት አጥተናል ብለው ያቀረቡትን የዳኝነት ጥያቄ ለማየት የሚያስችል የሥረ ነገር ሥልጣን የለኝም በሚል በስር ፍርድ ቤት የመወሰኑን አግባብነት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 217195 ከሰጠው ውሳኔ ጋር በማገናዘብ መመርመር ያለበት ሆኖ ተገኝቷል የሚል ማስቀረቢያ ጭብጥ በመያዝ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ተደርጎ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ቀርቧል፡፡

ተጠሪ የካቲት 24 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠው መልስ ይዘት በአጭሩ፡- አመልካች ክስ አቅርበው የነበረው በመመርያ ቁጥር 7/2010 መሰረት ሲሆን ተጠሪ ግን ምሪት የሰራው በመመርያ ቁጥር 8/2005 መሰረት ነው፤ ተጠሪ በወቅቱ ምሪት ሲሰራ አመልካቾች የወራሽነት ማረጋገጫ አቅርበው ስላልነበር ተጠሪ ያሳጣቸው መብት የለም፤ ተጠሪ ለአመልካቾች እናት የካሳ ስሌት እንዲወስዱ አሳውቆ ነበር፤ ሕጉ በሚያዘው መሰረትም አመልካቾች ቅሬታቸውን ለካሳ አጣሪ ኮሚቴ ሊያቀርቡ ይገባ ነበር፤ በኮሚቴው ውሳኔ ቅር ከተሰኙ አቤቱታው ሊቀርብ የሚገባው ለወረዳ ፍርድ ቤት ሳይሆን ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፤ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤት የአመልካቾችን ክስ ውድቅ በማድረግ የሰጠው ብይን ተገቢ ስለሆነ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡

አመልካች በሰጡት የመልስ መልስ ያቀረቡትን አቤቱታ በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር እና በየደረጃው ባሉ ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ባጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪ ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራ ቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

በመሠረቱ የዳኝነት ሥልጣን የፍርድ ቤቶች ብቻ ስለመሆኑ እና ማናቸውም በፍርድ ቤት ታይተው ሊወሰኑ በሚችሉ ጉዳዮች ላይ ፍርድ ቤቶች ተፈጥሯዊ ሥልጣን ያላቸው ስለመሆኑ፤ ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም በሕግ የዳኝነት ስልጣን ለተሰጠው ሌላ አካል የማቅረብ እና የማስወሰን መብት እንዳለው ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገመንግስት አንቀጽ 79(1) እና 37 መገንዘብ ይቻላል፡፡

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ አንቀጽ 4 ላይ በግልጽ እንደተመለከተውም በቀጥታ ወይም በግልጽ ካልታገዱ በቀር የፍትሐብሔር ጉዳዮችን ተቀብሎ የማየት ስልጣን የፍርድ ቤቶች ነው፡፡

የኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ  አንቀጽ 40(1)እና(7) ድንጋጌዎችም ማንኛውም የኢትዮጵያ ዜጋ የግል ንብረት ባለቤት መሆን የተከበረለት/ላት መሆኑን፤ በጉልበቱ፣ ወይም በገንዘቡ በመሬቱ ላይ ለሚገነባው ቋሚ ንብረት ወይም ለሚያደርገው ቋሚ መሻሻል ሙሉ መብት እንዳለው፤ ይህ መብትም የመሸጥ፤ የመለወጥ፤ የማውረስ፤ የመሬት ተጠቃሚነቱ ሲቋረጥ ንብረቱን የማንሳት፤ ባለቤትነቱን የማዛወር ወይም የካሳ ክፍያ የመጠየቅ መብትን የሚያካትት እና ዝርዝር አፈጻጸሙም በሕግ የሚወሰን መሆኑን ይደነግጋሉ፡፡ የዚሁ አንቀፅ ንኡስ አንቀጽ ስምንት ደግሞ የግል ንብረት ባለቤትነት መብት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ መንግስት ለሕዝብ ጥቅም አስፋላጊ ሆኖ ሲያገኘው ተመጣጣኝ ካሳ በቅድሚያ በመክፈል የግል ንብረትን ለመውሰድ እንደሚችል ይደነግጋል፡፡

ሕጉ-መንግሥቱን ተከትለው የወጡት ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበትን እና የንብረት ካሣ የሚከፈልበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር 455/ 1997 እና የከተማን ቦታ በሊዝ ስለመያዝ የወጣው አዋጅ ቁጥር 721/2004 ድንጋጌዎችም የግል ንብረት ባለቤትነት መብት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ መንግስት ለሕዝብ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ተመጣጣኝ ካሳ በቅድሚያ በመክፈል የግል ንብረትን ለመውሰድ እንደሚችል በተመሳሳይ ሁኔታ ይደነግጋሉ፡፡

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገጠር መሬት አስተዳዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 252/2009 አንቀጽ 52/2 ድንጋጌ ይዘት በግልጽ መገንዘብ እንደሚቻለው የወረዳው ፍርድ ቤት በገጠር መሬት ይዞታ እና የመጠቀም መብት ላይ የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን እና የሚነሱ ክርክሮችን ተቀብሎ የማየት የስረ ነገር ስልጣን አለው፡፡

በያዝነው ጉዳይ አመልካቾች በስር ፍርድ ቤት ካቀረቡት የክስ አቤቱታ ይዘት መገንዘብ እንደቻልነው የአመልካቾች የዳኝነት ጥያቄ ከሟች አባታችን በውርስ ያገኘነው መሬት ለሕዝብ ጥቅም ተብሎ ሲወሰድ ሕጋዊ ሥርዓቱን ሳይከተል በመሆኑ ተጠሪ ይዞታውን ሊያስረክበን ይገባል የሚል ነው፡፡  ይህም የዳኝነት ጥያቄአቸው የንብረት መብትን ከማስከበር እና አላግባብ ተወስዷል የተባለ ይዞታን ከማስመለስ ጋር የተገናኘ ነው፡፡ ስለሆነም የወረዳው ፍርድ ቤት አመልካቾች ያቀረቡትን ክስ ተቀብሎ የመወሰን የስረ ነገር ሥልጣን አለው፡፡ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም በሰ.መ.ቁ 217195 ግንቦት 30 ቀን 2014 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ ( በቅጽ ባልታተመ ) በዚህ ረገድ አስገዳጅ የሆነ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ በመሆኑም ጉዳዩ የቀረበለት የወረዳው ፍርድ ቤት የአመልካቾችን ክስ ተቀብሎ የማየት የሥረ ነገር ስልጣን እያለው ጉዳዩ ቅድሚያ ሊቀርብ የሚገባው አስተዳደራዊ ውሳኔ እንዲያገኝ ለተቋሙ እንጂ መደበኛ ፍርድ ቤት ሊቀርብ አይገባም በማለት የአመልካቾችን ክስ በብይን ውድቅ በማድረግ ውሳኔ መስጠቱ፤ በየደረጃው ያሉ

የክልሉ ፍርድ ቤቶችም ይህንኑ ሳያርሙ መቅረታቸው መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም የወረዳው ፍርድ ቤት ግራቀኙ በፍሬነገሩ ላይ ያቀረቡትን ክርክር በሥነ ሥርዓት ሕጉ መሠረት መርቶ እና አጣርቶ ተገቢ የሆነውን ሕጋዊ ውሳኔ እንዲሰጥበት ማድረግ ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ውሳኔ

1. በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የአልብኮ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 0119502 ግንቦት 29 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠው ብይን፤ ይህንኑ ብይን በማጽናት የደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 55338 ሠኔ 06 ቀን 2014 ዓ.ም  የሰጠው ትዕዛዝ፤ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 0335660 ሐምሌ 05 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ከላይ በፍርድ ሐተታው ላይ በተገለጸው ምክንያት የአብልኮ ወረዳ ፍርድ ቤት አመልካቾች ያቀረቡትን ክስ ተቀብሎ ለማስተናገድ የሚያስችል የሥረ ነገር ሥልጣን አለው በማለት ወስነናል፡፡
3. የአብልኮ ወረዳ ፍርድ ቤት በብይን የዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ ከላይ በፍርድ ሐተታው ላይ በተገለጸው መንገድ ክርክሩን መርቶ ተገቢውን ሕጋዊ ውሳኔ እንዲወስን በማለት በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 15/2015 አንቀጽ 9(2) መሠረት ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡
   - መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/ተ

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ  ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም  ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ  አፈጻጸም  ዓላማ  አያገለግልም

**በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**
**የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት**

የሰ.መ.ቁ. 235049

ጥቅምት 6 ቀን 2016 ዓ.ም

ዳኞች፡- 1. ብርሃኑ አመነዉ

2. ረታ ቶለሳ

3. በእዉቀት በላይ

4. ቀነዓ ቂጣታ

5. ኑረዲን ከድር

አመልካች፡...... አቶ ካሳሁን ግርማ መኮንን---------------- ቀረቡ

ተጠሪ፡........... አቶ ፋሲል ሽብሩ ወ/ሚካኤል -------------- የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**<u>ፍርድ</u>**

ይህ የዉል ክርክር የተጀመረዉ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል በቤንች ሸኮ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች የሥር 2ኛ ተከሳሽ፣ የአሁን ተጠሪ የሥር ከሳሽ፣ በዚህ ችሎት የክርክሩ ተካፋይ ያልሆኑት አቶ ቁምላቸዉ ዘሪሁን 1ኛ ተከሳሽ እና አቶ ጀምበሩ ንጉሴ 3ኛ ተከሳሽ ሆኖ ሲከራከሩ ነበር፡፡ ይህ ጉዳይ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ አመልካች የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ.11109 በ04/12/2014 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልኝ በማለት በማመልከታቸዉ ነዉ፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ ከሳሽ በሥር ፍ/ቤት ባቀረቡት የክስ አቤቱታ ከሳሽ ተከሳሾች ጋር ጠቅላላ የሥራ ተቋረጭ በመስራት የሚተዳደሩ ሲሆን በሚዛን ክ/ከተማ በአዲስ ከተማ ቀበሌ ላይ ከተከሳሾች ጋር በተደረገዉ ዉል ኤክስካቫተር፣ ግሬዳር፣ ሩሎ በ1ኛ ተከሳሽ ስም በሚታወቀዉ ቁምላቸዉ ዘሪሁን ጠቅላላ ሕንጻ ተቋራጭ

በ2013 ዓ.ም በዲማ ወረዳ ጌዱ ቀበሌ ዉስጥ ለዉስጥ መንገድ ሥራ ጨረታ አሸንፎ ወደ ሥራ በመግባታቸዉ ለሥራዉ እንዲሆን የማሽኖች ኪራይ ጠቅላላ ድምር ብር 460,500 ዉስጥ ቅድሚያ ክፍያ ብር 225,000 የተከፈለ እና ቀሪ ብር 235,500 ከ9% የባንክ ወለድ ጋር እንዲከፍሉኝ በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች በዚህ ክስ ላይ ባቀረቡት መልስ የከሳሽን ክስ አምነዉ ተከራክሯል፡፡ 2ኛ ተከሳሽ (የአሁን አመልካች)) በበኩሉ ባቀረበዉ መልስ የተጠቀሱት የማሽን ዉል ስምምነቶች ሐሰት ነዉ በዉሉ ላይ አልፈረምኩም በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በኋላ ፍ/ቤቱ በተነሳዉ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በብይን ዉድቅ በማድረግ፣ ጭብጥ በመያዝ፣ የከሳሽን የሰዉ ምስክሮችን በመስማት፣ የሰነድ ማስረጃ በመመርመር ባሳለፈዉ ዉሳኔ ከሳሽ ከአዲስ አበባ ከተማ ተከራይቶ ያመጣቸዉን ኤክስካቫተር፣ ግሬዳር፣ ሩሎ ማሽኖችን ተከሳሾች ተወዳድሮ ጨረታ ያሸነፉትን የመንገድ ሥራ ለመስራት እንዲችሉ እነዚህን ማሽኖች ከከሳሽ ተከራይተዉ ሥራ መስራታቸዉን እና ክፍያ መቀበላቸዉን እና ቀሪ ያልተከፈለ ገንዘብ ብር 235,500 መኖሩን የሰዉ ምስክሮች አስረድተዋል፡፡ 2ኛ ተከሳሽ ዉሉ ተፈርሞ ወደ ሥራ ሲገባ ያዉቅ እንደነበር ነዉ፡፡ ነገር ግን 2ኛ ተከሳሽ በበኩሉ የመከላከያ ማስረጃ በማቅረብ ያስተባበለዉ ነገር የለም፡፡ 2ኛ ተከሳሽ ዕዳዉ አይመለከተኝም ይባል እንጂ ዉሉን እንደሚያዉቅ፣ ሰራተኛ ቀጥሮ ሲያሰራና ሲሰራ በነበረበት ድርጅት የተሰራ መሆኑን በማስረጃ የተረጋገጠ ስለሆነ ተከሳሾች ባልተለያየ ኃላፊነት ብር 235,500 ከመጋቢት 23/7/2014 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ 9% ወለድ ጋር ለከሳሽ እንዲከፍሉ በማለት ወስኗል፡፡

የሥር 2ኛ ተከሳሽ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን በማከራከር የሥር ፍ/ቤትን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ነዉ፡፡

አመልካች በ24/01/2015 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ፡ ተጠሪ ከአመልካች ጋር ያደረገዉ የማሽን ኪራይ ዉል የለም፤ አመልካች ዉሉን በመቃወም ማስፈረስ ይገባል የሚባልበት አግባብ የለም፡፡ ተጠሪ ከሥር 1ኛ ተከሳሽ ጋር በመመሳጠር በክፉ ልቦናና ሴራ አመልካችን ለመጉዳት ያቀረበዉ የህግና የማስረጃ ድጋፍ የሌለዉ የሐሰት ክስ ሆኖ እያለ የሥር ፍ/ቤት ከሌሎች ተከሳሾች ጋር በአንድነት የተጠቀሰዉን ገንዘብ እንዲከፍል መወሰናቸዉ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ፡፡ በተጠሪ የቀረቡት የሰዉ ምስክሮችም ቢሆን ምስክርነታቸዉ ተቀባይነት እና ተአማኒነት የሌለዉ ነዉ፡፡ የሥር ፍ/ቤት ማሽኖቹ የሰሩት ሰዓት በኪራይ ዋጋ መጠን ተባዝቶ የሚገኘዉ ጠቅላላ ተከፋይ ገንዘብ ላይ ተጠሪ ተከፍሎኛል ያለዉ ተቀንሶ ያልተከፈለዉ ቀሪ ገንዘብ ካለ አጣርቶ እንዲከፈል መወሰን ሲገባዉ፣ ቀሪ ገንዘብ መጠኑ ምን ያህል እንደሆነ ሂሳብ ተሰርቶ ባልተጣራበትና ባልተረጋገጠበት በደፈናዉ የተጠየቀዉ ገንዘብ እንዲከፈል መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ፡፡ በመሆኑም የሥር ፍ/ቤቶች ዉሳኔ ተሽሮ አመልካች ምንም ዓይነት ገንዘብ ለተጠሪ መክፈል የለበትም ተብሎ እንዲወሰንልኝ በማለት በዝርዝር አመልክቷል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን በማየት ፣በሥር ፍ/ቤት ክስ አንጻር የማሽነሪ የኪራይ ገንዘብ አመልካች ከቁምላቸዉ ዘሪሁን ጋር በጋራ ለመስራት በተዋዋሉበት ጊዜ ለተፈጸመ እና ያልተከፈለ የኪራይ ገንዘብ ስለመኖር አለመኖሩ እና በሕንጻ ተቋራጭ እና በአመልካች መካከል ያለዉ ዉል በቀጥታ 3ኛ ወገን ክስ በማቅረብ ሊጠይቃቸዉ

በሚችል ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ስለመሆን አለመሆኑ በግራ ቀኙ መካከል በ28/3/2013 ዓ.ም ከተጻፈ ዉል አኳያ በአግባቡ ተመርምሮ የመወሰኑን አግባብነት፣ ለማጣራት ሲባል የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ባዘዘዉ መሰረት በ10/5/2015 ዓ.ም የተጻፈ መልስ አቅርቧል። የመልሱም ይዘት ባጭሩ፡ የሥር ፍ/ቤቶች በግራ ቀኛችን መካከል የነበረዉን በጋራ ስራ የመስራት ዉል ስምምነት መሰረት በማድረግ የማሽን ኪራይ ዉል ጋር በማገናዘብ አጣርቶ ዉሳኔ የሰጡ በመሆኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያልተፈጸመበት በመሆኑ እንዲጸናልኝ በማለት በዝርዝር ተከራክሯል። አመልካች በ29/5/2015 ዓ.ም በተጻፈ የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታዉን በማጠናከር ተከራክሯል።

የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል። እንደመረመርነዉ አመልካች፣ አቶ ቁምላቸዉ ዘሪሁን፣ አቶ ጀምበሩ ንጉሴ እና አቶ ገዛኻኝ አርቤቶ ሁነዉ በ28/3/2013 ዓ.ም የተጻፈ በጋራ ስራ የመስራት ዉል ስምምነት ማድረጋቸዉን መዝገቡ ያሳያል። በጋራ ለመስራት ያሰቡትም ሥራ በጋምቤላ ክልል ዲማ ወረዳ ጌዱ ቀበሌ ፊደር ሮድ ኮንስትራክሽን 4.5 ኪ.ሜ የዉስጥ ለዉስጥ ፒስታ የገጠር መንገድ ለመስራት ነዉ። ይህን ሥራ ለመስራት ያቀዱት በአቶ ቁምላቸዉ ዘሪሁን በኩል በቁምላቸዉ ዘሪሁን ጠቅላላ ሥራ ተቋራጭ እና በአቶ ገዛኻኝ ኤርቤቶ የሕንጻ ሥራና የዉሃ ሥራ ተቋራጭ በተባሉት የንግድ ሥራ ፈቃዶች ነዉ። በዉሉ መሰረት ሥራዉን ለመስራት የሚያስፈልገዉን ወጪ ለመሸፈን እና በጋራ ሰርተዉ ያገኙትን ገቢ እኩል ለመካፈል መስማማታቸዉን ያሳያል። ይህ ዉል ደግሞ አመልካችን ጨምሮ በተዋዋይ ወገኖች መካከል ሕግ መሆኑን የፍ/ብ/ሕ/ቁ.1731 (1) ድንጋጌ ያስገነዝባል። በዚህ መሰረት አመልካችን ጨምሮ የሥር ተከሳሾች በ2013 ዓ.ም በዲማ ወረዳ ጌዱ ቀበሌ የዉስጥ ለዉስጥ መንገድ ሥራ ለመስራት ጨረታ አሸንፈዉ ወደ ሥራ መግባታቸዉን የሥር ፍ/ቤት የዉሳኔ ግልባጭ ያመለክታል። እንዲሁም የአሁን ተጠሪ ከአዲስ አበባ ከተማ ተከራይቶ ያመጣቸዉን ማሽኖች ኤክስካቫተር፣ ግሬደር እና ሩሎ አመልካችን ጨምሮ የሥር ተከሳሾች በጨረታ ያሸነፉትን የመንገድ ሥራ እንዲሰሩበት እና ለዚህም ደግሞ የሚከፍሉትን የኪራይ ገንዘብ መስማማታቸዉን፣ ከዚህ ዉስጥ ቅድሚያ የተከፈለ ገንዘብ እና ቀሪ ብር 235500 መኖሩን በሥር ፍ/ቤት በማስረጃ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነዉ።

የሥር ፍ/ቤቶች ፍሬ ነገር የማጣራት እና ማስረጃ መርምሮ መዝኖ ድምዳሜ ላይ ለመድረስ በሕግ በተሰጠዉ ስልጣን መሰረት በተጠሪ በኩል የቀረቡትን የሰዉ ምስክሮችን በመስማት እና የሰነድ ማስረጃን በመመርመር አመልካች እና የሥር ተከሳሾች ከፍ ሲል የተጠቀሱትን ማሽኖችን ከተጠሪ ተከራይተዉ የመንገድ ሥራዉን የሰሩበት መሆኑን የቀረበዉ ማስረጃ እንዳረጋገጠ የሥር ፍ/ቤት የዉሳኔ ግልባጭ ያሳያል። በዚህ ረገድ አመልካች ማስረጃ በማቅረብ የተጠሪን ክስና ማስረጃ ያስተባበለበት ሁኔታ እንደሌለ የሥር ፍ/ቤት የዉሳኔ ግልባጭ ያመለክታል። ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ደግሞ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበትን ማናቸዉም የመጨረሻ ዉሳኔ እንዲያርም በሕግ ከተሰጠዉ ስልጣን አንጻር አመልካችም ሆነ የሰበር አጣሪ ችሎት የያዘዉ ጭብጥ የፍሬ ነገርና የማስረጃ ጉዳይ ከሚባል በስተቀር የሥር ፍ/ቤቶች በሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆኑን የሚያመለክት ሆኖ አልተገኘም። በመሆኑም አመልካች ያቀረበዉ የሰበር አቤቱታ ከኢፌዴሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80 (3፣ ሀ) እና አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2 (4) (ለ) እና 10 (1) (መ)

መሰረት የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆኑን የሚያመለክት ስላልሆነ ቅሬታዉ ተቀባይነት የለዉም ብለናል፡፡

ሲጠቃለል የሥር ፍ/ቤቶች በዚህ ጉዳይ የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስላልሆነ ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ዉሳኔ**

1. የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ.11109 በ04/12/2014 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 (1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
3. ግራ ቀኙ የሰበር ክርክር ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

**የማይነበብ የአምስት ደኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**ማ/ተ**

*ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁጥር 234891
ጥቅምት 03 ቀን 2016

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ረታ ቶሎሳ

በእውቀት በላይ

ቀነዓ ቂጣታ

ኑረዲን ከድር

አመልካች፡- አቅሊሲያ ጠቅላላ ህንጻ ተቋራጭ ኃ/የተ/የግ/ማህበር

ተጠሪ፡-አቶ ፈቀደ ክፈተው

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን በዚሁ አግባብ መዝገቡ በዳኞች እረፍት ጊዜ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች በ20/01/2015 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው የሰበር አቤቱታ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ.ቁ. 173655 በቀን 07/11/2014 ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 294829 በ24/12/2014 ዓ.ም በዋለው ችሎት ማጽናቱ መሰረታዊ የህግ አተረጓጎም ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለቱ ሲሆን አመልከች በስር ፍ/ቤት ተከሳሽ ሆኖ ተጠሪ ደግሞ ከሳሽ ሆነው በጉዳት ካሳ ጉዳይ ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪ በስር ፍ/ቤት ነሃሴ 23 ቀን 2013 ዓ.ም ባቀረቡት ክስ በአመልካች ድርጅት ውስጥ ከህዳር 11 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ በቀን ብር 150.00 (አንድ መቶ ሃምሳ ብር) እየተከፈላቸው ተቀጥረው ይሰሩ የነበረ መሆኑን፤ ህዳር 15 ቀን 2012 ዓ.ም በአዲስ አበባ መካኒሳ አካባቢ አድማስ ዩኒቨርሲቲ ጀርባ ትቦ በመቅበር ስራ ላይ በነበሩበት ወቅት በአመልካች የተቆፈረ አፈር እና ድንጋይ ተንዶ በወገብ አቃፊ

አጥንታቸው እና በግራ ጎን የሰውነት ክፍላቸው ላይ የአጥንት ስብራትና መዛነፍ እንዲሁም በውስጥ የሰውነት ክፍል የአጥንት መገጣጠሚያ መጎዳት የነርቭ ጉዳት የደረሰባቸው መሆኑን፣ በዚህ ጉዳት ምክንያትም መራመድና መንቀሳቀስ የማይችሉና ቀድሞ የሚሰሩትን ስራ መስራት የማይችሉ መሆኑን፣ በአደጋው ወቅት እድሜያቸው 34 መሆኑንና በወንድ ልጅ በህይዎት የመኖር እድሜ ምጣኔ 70 አመት በመሆኑ ከዚህ በኋላ 36 አመት እኖራለው በማለት የወር ገቢያቸውን በዚሁ አግባብ በማስላት እንዲሁም ህክምናው ሳያልቅ አመልካች እርዳታውን ያቋረጠባቸው መሆኑን በመግለጽ ለህክምና እና ለትራንስፖርት ብር 38,480.00 (ሰላሳ ስምንት ሺህ አራት መቶ ሰማኒያ ብር) አውጥቻለው በማለት ከጉዳት ካሳ ክፍያው ጋር በድምሩ ብር 1,723,280 (አንድ ሚልየን ሰባት መቶ ሃያ ሶስት ሺህ ሁለት መቶ ሰማኒያ ብር) ተጠሪ እንዲከፍለኝ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

አመልካችም ጥቅምት 04 ቀን 2014 ዓ.ም ባቀረበው መልስ ጉዳዩ በእርቅ ያለቀ ነው የሚል መቃወሚያ ያቀረቡ ቢሆንም ማስረጃ አልቀረበበትም በማለት የስር ፍ/ቤቱ አልተቀበለውም፡፡ በፍሬ ነገር መልሱም፦ የተጠሪ ደሞዝ መቶ ሃምሳ ብር ሳይሆን በቀን ሰማኒያ ብር ነው፡፡ አመልካች ለሙከራ የተቀጠሩና የስራ መግለጫ ተሰጥቷቸው ወደ ስራ የገቡ ሲሆን አብረዋቸው የነበሩ ሰራተኞች በተሰጣቸው የስራ መግለጫ መሰረት ከአደጋው ሲያመልጡ ተጠሪ ግን ግዴታቸውን ባለመወጣታቸው አደጋው የደረሰባቸው በመሆኑ አመልካች ለአደጋው ሊጠየቅ አይገባም፡፡ ተጠሪ ለህክምና ከፈልኩት ያሉትን ብር 38,480.00 (ሰላሳ ስምንት ሺህ አራት መቶ ሰማኒያ) አመልካች ለመክፈል ከተስማማ በኋላ እምቢተኛ ሆነ በማለት ያቀረቡት ክስ ከእውነታው የራቀ ነው፡፡ ተጠሪ እድሜያቸውን እና የጉዳት መጠኑን በተመለከተ ተገቢውን ማስረጃ ያላቀረቡ በመሆኑ ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክስና ማስረጃዎች መርምሮ የጥንቃቄ መመሪያ የተባለው ሩጦ ማምለጥ በመሆኑና ከ2 ሜትር በላይ ከሆነ ጉድጓድ ውስጥ አንድ ሰው ሩጦ ያመልጣል ተብሎ የሚገመት ባለመሆኑ፣ የደህንነት መጠበቂያ የሚሆኑ ሁኔታዎች እንደሌሉ፣ ቁፋሮ በማሽን እየተደረገ ከስር ሰራተኛ እንደሚሰራ እና መሬቱም በማንኛውም ሰአት ሊደረመስና አደጋ ሊያደርስ እንደሚችል ምስክሮች ያስረዱ በመሆኑ ተጠሪ ለጉዳቱ ያበረከቱት አሰተዋጽኦ የለም፡፡ ተጠሪ በአመልካች የሥራ ቦታ ስራ ሲሰሩ ጉዳት የደረሰባቸው መሆኑ አከራካሪ ባለመሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ.2077 እና 2078 መሰረት አመልካች በተጠሪ ላይ ለደረሰው ጉዳት ሃላፊነት አለባቸው፡፡ የደሞዝ መጠንን በተመለከተ የአመልካች ምስክሮች በቀን ብር 80.00 እና 120.00 ይከፈላል በማለት መመስከራቸው እርስ በርሱ የሚጣረስ ከመሆኑ ባሻገር ምስክርነቱ ከሰራተኞች ሰማሁ የሚል በመሆኑና በአንጻሩ 1ኛ የተጠሪ ምስክር ከተጠሪ ጋር አብሮ የሚሰራና በቀን ብር 150 ይከፈለናል ሲል ምስክርነት የሰጠ በመሆኑ ፍ/ቤቱ ተጠሪ በቀን 150.00 ብር ይከፈለው ነበር የሚል ግምት ወስዷል፡፡ በፍ/ቤቱ ትዕዛዝ ከምኒልክ ሆስፒታል በተላከ ማስረጃ የተጠሪ የጉዳት መጠን 23% ሆኖ በግራ ዳሌ አጥንታቸው ላይ ቋሚና ዘላቂ ጉዳት የደረሰባቸው መሆኑን

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ያስረዳል፡፡ ከፕላንና ልማት ኮሚሽን የማእከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ የተላከው ማስረጃም በአዲስ አበባ የሚኖር የወንድ ልጅ አማካኝ የመኖሪያ እድሜ 64.9 አመት መሆኑን ያስረዳል፡፡

በተጠሪ መታወቂያ የተመለከተውን የትውልድ ቀን መሰረት በማድረግ ተጠሪ እድሜያቸው 35 የሚሆን ሲሆን አመልካች በእድሜ ረገድ ላቀረቡት ክርክር ማስረጃ ያላቀረቡ በመሆኑ ፍ/ቤቱ አልተቀበለውም በማለት በዚህ አግባብ በማስላት ብር 321,843.36 (ሶስት መቶ ሃያ አንድ ሺህ ስምንት መቶ አርባ ሶስት ብር ከሳላሳ ስድስት ሳንቲም) የጉዳት ካሳ እንዲሁም ተጠሪ ለህክምና ከፈልኩ ያሉትን ብር 38,480.00 (ሰላሳ ስምንት ሺህ አራት መቶ ሰማኒያ) አመልካች ለመክፈል ፈቃደኛ ነኝ በማለት አምነው በመቅረባቸው ይህንኑ አመልካች ለተጠሪ ሊከፍሉ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ለፌ/ከፍ/ፍ/ቤት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱ የስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ስህተት የለበትም በማለት አቤቱታውን ሰርዟል፡፡

አመልካችም የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የህግ አተረጓጎም ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት በ20/01/2015 ዓ.ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ለዚህ ችሎት ያቀረበ ሲሆን ይዘቱም፦ በስር ፍ/ቤት ከተጠሪ ጋር በሽምግልና የጨረስን በመሆኑ ተጠሪ ጉዳዩን ወደ ፍ/ቤት መውሰድ አይችልም በሚል ያቀረብነውን መቃወሚያ ፍ/ቤቱ ማለፉ አግባብነት የለውም፤ ተጠሪ ጉዳቱ የደረሰበት በአመልካች ጥፋት ስለመሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ.2037 እና ተጠሪ የአመልካች ድርጅት ሰራተኛ የነበረ በመሆኑ በአዋጅ ቁ. 1156/2011 አንቀጽ 96(3) መሰረት ሳያስረዳ የስር ፍ/ቤት ጉዳዩን ከውል ውጭ ሃላፊነት በማድረግ በፍ/ብ/ህ/ቁ.2078 መሰረት አመልካች ሃላፊነት አለበት በማለት መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፤ ተጠሪ በተሰጠው መመሪያ ባለመስራቱ ጉዳት የደረሰበትና ለአደጋው አስተዋጽኦ ያለው መሆኑን የአመልካች ምስክሮች አስረድተው እያለና የስር ፍ/ቤቱ አመልካች ምን አይነት የደህንነት መጠበቂያ ማቅረብ እንዳለበት ሳይገለጽ የደህንነት መጠበቂያ ባለመቅረቡ አመልካች ለአደጋው አስተዋጽኦ አለው በማለት መደምደሙ አግባብነት የለውም፡፡

በስር ፍ/ቤት የአመልካች 1ኛ እና 2ኛ ምስክሮች የተጠሪ ደሞዝ በቀን ብር 80.00 መሆኑን በተመሳሳይነት መስክረው እያለና 3ኛ ምስክርም እኔ ስቀጥር ብር 80.00 ይከፈለኝ ነበር በኋላ ግን በጭማሪ ብር 120.00 ደርሻለው በማለት የተሰጠውን ምስክርነት የስር ፍ/ቤቱ ይጣረሳል በማለት የተጠሪ አንድ ምስክር በሰጠው ምስክርነት ብቻ ተመስርቶ የተጠሪ ደሞዝ ብር 150.00 ነው በማለት መደምደሙ አግባብ አይደለም፤ የተጠሪ ዋና የመኖሪያ አድራሻ አዲስ አበባ ባልሆነበት የአዲስ አበባ ነዋሪ ነው ብሎ ማስላቱ እና እድሜን በተመለከተም ተቃውመን እያለ ተጠሪ የልደት፣ የጋብቻ ወይም የ8ኛ ክፍል የምስክር ወረቀት እንዲያቀርቡ ታዘው ክሱ ከተጀመረ በኋላ የተሰጠ የቀበሌ መታወቂያ ብቻ ማቅረባቸውን ተቃውመን እያለ የስር ፍ/ቤቱ ተቃውሟችንን ያለአግባብ በማለፍ ይህንኑ መታወቂያ መሰረት አድርጎ የተጠሪ እድሜ 35 አመት ነው ብሎ ደምድሞ የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ አተረጓጎም ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይሻርልን የሚል ነው፡፡

*ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

አቤቱታው የቀረበለት የሰበር አጣሪ ችሎትም የስር ፍ/ቤት የተጠሪ የቀን ክፍያ ብር 80.00 (ሰማኒያ ብር) ሳይሆን ብር 150.00( አንድ መቶ አምሳ) ነው ብሎ በመያዝ የጉዳት ካሳውን በዚሁ አግባብ አባዝቶ የወሰነበትን አግባብ ከመሰረታዊ የማስረጃ ምዘና መርሆዎች አንጻር ለማጣራት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ይቅረብ፡፡ ግራ ቀኙም የጽሁፍ ክርክር ይቀባበሉ በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ትዕዛዝ መሰረት ተጠሪ ህዳር 12 ቀን 2015 ዓ.ም የተጻፈ መልስ ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም፦ አመልካች ያቀረቡት አቤቱታም ሆነ የሰበር አጣሪ ችሎቱ ያስቀርባል ያለበት ጭብጥ የማስረጃ ምዘናን የሚመለከት በመሆኑ ለሰበር ችሎት ሊቀርብ አይገባም፡፡

የቀን ሰራተኛነት የደሞዝ እርከን የሌለውና ከአመልካች ጋር በቃል ሰምምነት ያደረግንበት ሲሆን በስር ፍ/ቤት 1ኛ የተጠሪ ምስክር ከተጠሪ ጋር በአንድ ቀን እንደ ተጠሩ በቀን ሰራተኛነት የተቀጠረና በቀን ብር 150.00 (አንድ መቶ ሃምሳ) እየተከፈለኝ ለመስራት ከአመልካች ጋር ስስማማ በቦታው የነበረ ሲሆን በአንጻሩ የአመልካች 1ኛ ምስክር ተጠሪ ሲቀጠሩ በቦታው ያልነበሩና በመሰለኝ የመሰከሩ ሲሆን የአመልካች 2ኛ ምስክር ተጠሪ ሲቀጠር በቦታው የነበሩ ቢሆንም ምስክርነት በሰጡበት እለት የአመልካች ሰራተኛ በመሆናቸው ከድርጅቱ ጋር ባላቸው የጥቅም ግንኙነት እውነቱን ለመሸሸግ በቂ ምክንያት ያላቸው ሲሆኑ 3ኛው ምስክር ደሞ ስለ ራሱ ደሞዝ እንጂ ስለ ተጠሪ ደሞዝ የማያውቅና የቅጥር ስምምነቱን ሳደርግ በቦታው ያልነበረ በመሆኑ የሱ ደሞዝ የተጠሪን ደሞዝ ለመወሰን ማነጻጸሪያ ሊሆን የማይችል ከመሆኑ ባሻገር ሶስቱም የአመልካች ምስክሮች የሰጡት ምስክርነት ተመሳሳይነት የሌለው በመሆኑ የስር ፍ/ቤት ምስክርነቱን የመዘነበት አግባብ ስህተት የሌለበት ነው፡፡

በስር ፍ/ቤት ተጠሪ ለህክምና ያወጣሁት ብር 38,480.00 (ሰላሳ ስምንት ሺህ አራት መቶ ሰማኒያ) ከጉዳት ካሳውና ከተጠሪ የእለት ደሞዝ ጋር የማይገናኝ በመሆኑና አመልካችም በስር ፍ/ቤት ባመኑት መሰረት የተወሰነ በመሆኑ ቅሬታ ካላቸው ለይተው ማቅረብ ሲገባቸው አሁን ከጠየቁት ዳኝነት ጋር ደምረው ማቅረባቸው ተገቢነት የሌለው በመሆኑ ውድቅ ተደርጎ የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ስህተት የለበትም ተብሎ እንዲወሰንልኝ እጠይቃለው የሚል ነው፡፡

አመልካችም በ04/04/2015 ዓ.ም የተጻፈ የመልስ መልስ በማቅረብ የሰበር አቤቱታውን አጠናክሮ ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በላይ አጠር ባለመልኩ የተገለጸዉ የግራ ቀኙ ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት የሚመለከት ሲሆን እኛም የሰበር አጣሪ ችሎት የያዘዉን ማስቀረቢያ ጭብጥ መሰረት በማድረግ በውሳኔው ላይ በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡አንድ ፍርድ ቤት ተከራካሪ ወገኖችን ባከራከረው ጉዳይ ላይ በመጨረሻ የሚሰጠው ፍርድ ተከራካሪዎቹ ወገኖች በዝርዝር ባላቀረቡት ወይም በግልፅ ያላመለከቱትን ጉዳይ ሊያካትት እንደማይገባ በአንቀፅ 182(2) የተመለከተ

ሲሆን የክሱ መነሻ የከሳሹ ግልፅና ዝርዝር የዳኝነት ጥያቄ በመሆኑ በተከሳሹ የሚቀርበው መልስ ፣ግራ ቀኙ በቃል የሚያደርጉት የቃል ክርክርና ፍርድ ቤቱ ይህንን መሰረት በማድረግ የሚይዘው ጭብጥ እና ማስረጃ ሰምቶ ተገቢውን ህግ መሰረት በማድረግ በመጨረሻ የሚሰጠው ፍርድ በዋነኝነት በክሱ ላይ የተጠየቀውን የዳኝነት ጥያቄ መሰረት ሊያደርግ ይገባል፡፡

በግራ ቀኙ መሀል የስራ ውልን መሰረት ያደረገ የአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነት ያለ መሆኑ ግራ ቀኙ የተማመኑበት ነጥብ በመሆኑ በተጠሪ ላይ ህዳር 15 ቀን 2012 ዓ.ም በአዲስ አበባ መካኒሳ አካባቢ አድማስ ዩኒቨርሲቲ ጀርባ ትቦ በመቅበር ስራ ላይ በነበሩበት ወቅት የደረሰባቸው አደጋ እና አደጋውን መሰረት አድርጎ የሚከፈላቸው ካሳ በመርህ ደረጃ ተሰልቶ የሚከፈላቸው በአሰሪና ሰራተኛ አዋጁ መሰረት ሲሆን ከዚህ ውጪ ካሳው ከውል ውጪ ሀላፊነትን በሚመለከቱት የፍትሐ ብሄር ህጉ ድንጋጌዎች አግባብ ሊሰላ የሚችለው በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀፅ 96(3) አግባብ ከመነሻውም ተጠሪ ክሳቸውን ሲያቀርቡ አደጋው የደረሰው በአመልካች ጥፋት መሆኑን ጠቅሰው የካሳው ስሌትም ከውል ውጪ ሀላፊነትን በሚመለከቱት የፍትሐ ብሄር ህጉ ድንጋጌዎች አግባብ እንዲሰላ መጠየቃቸው ሲረጋገጥ እና በክሳቸው አግባብ ሲያስረዱ ነው፡፡

አሁን በያዝነው ተጠሪ በስራ ላይ እያሉ በአመልካች የተቆፈረ አፈር እና ድንጋይ ተንዶ በወገብ አቃፊ አጥንታቸው እና በግራ ጎን የሰውነት ክፍላቸው ላይ የአጥንት ስብራትና መዛነፍ እንዲሁም በውስጥ የሰውነት ክፍል የአጥንት መገጣጠሚያ መጎዳት የነርቭ ጉዳት የደረሰባቸው መሆኑን ገልፀው ተገቢው ካሳ እንዲከፈላቸው ከመጠየቃቸው ውጪ አደጋው የደረሰው በአመልካች ጥፋት መሆኑን በክሳቸው ላይ በግልፅ በማመልከት ለደረሰባቸው ጉዳት ካሳ ከውል ውጪ ሀላፊነትን በሚመለከቱት የፍትሐ ብሄር ህጉ ድንጋጌዎች አግባብ እንዲከፈላቸው በመጠየቅ አመልካችም ለዚህ ክስ መልሱን እንዲሰጥ ተደርጎ ተጠሪ በክሳቸው አግባብ አደጋው የደረሰው በአመልካች ጥፋት መሆኑን ያስረዱ መሆኑን የስር ፍርድ ቤት መዝገብ አያሳይም፡፡ተጠሪ ከመነሻውም የስራ ላይ አደጋው የደረሰው በአመልካች ጥፋት መሆኑን ገልፀው ክሳቸውን ባላቀረቡበትና በዚህ አግባብም ባላስረዱበት የስር ፍርድ ቤት ለተጠሪ የሚከፈለውን የጉዳት ካሳ መጠን ከውል ውጪ ሀላፊነትን በሚመለከቱት የፍትሐ ብሄር ህጉ ድንጋጌዎች አግባብ ማስላቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላገኘነው ለተጠሪ ሊከፈላቸው የሚገባው የካሳ መጠን በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀፅ 107(1)(ለ) እና 109(4)(ለ) አግባብ ሊሆን ይገባል ብለናል፡፡

በዚህ አግባብ ስናሰላውም የተጠሪ የቀን ደመወዝ ብር 150.00 መሆኑ በወር ውስጥ ለ26 ቀናት እየሰሩ በወር ብር 3,900.00 የሚያገኙ መሆኑ ማስረጃን የመስማት፣የመመርመርና የመመዘን ስልጣን ባላቸው የስር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ ከማስረጃ ምዘና መርህ አንፃር መሰረታዊ የህግ ስህተት ያልተፈፀመበት በመሆኑ እንዳለ በመቀበል በአንቀፅ 109(4)(ለ) መሰረት የካሳው መጠን ብር 3,900.00 X 12 ወር X 5

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ዓመት X 23% = በድምሩ ብር 53,820.00 የሚመጣ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ከካሳ ስሌቱ አንፃር የፈፀመውን መሰረታዊ የህግ ስህተት በማረም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ውሳኔ

1.የፌዴራል መጀመሪያ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.173655 ሀምሌ 07 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለው ችሎት አመልካች ለተጠሪ ብር 321,843.36 (ሶስት መቶ ሃያ አንድ ሺህ ስምንት መቶ አርባ ሶስት ብር ከሳላሳ ስድስት ሳንቲም) የጉዳት ካሳ እንዲከፍል የሰጠው የውሳኔ ክፍልና ይህንን የውሳኔ ክፍል በማፅናት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በፍ/ይ/መ/ቁ.294829 ነሀሴ 24 ቀን 2014 ዓም የሰጠው ብይን በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ.348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡

2.አመልካች ለተጠሪ ሊከፍል የሚገባው የካሳ መጠን ብር 53,820.00 (ሀምሳ ሶስት ሺህ ስምንት መቶ ሀያ ብር) ሊሆን ይገባል ብለናል፡፡ቀሪው የውሳኔ ክፍል አልተነካም፡፡

3.በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በአፈጻጸም መ/ቁ.182986 በተያዘው አፈጻጸም ላይ ጥቅምት 16 ቀን 2015 ዓም የተሰጠው የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡

4.ግራ ቀኙ በሰበር ክርክሩ ምክንያት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

**<u>ጉዳዩ ውሳኔ ስላገኘ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ይመለስ፡፡</u>**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ማ/ተ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የመ.ቁ.234628

ጥቅምት 02/2016 ዓ.ም

ዳኞች፡ ተፈሪ ገብሩ(ዶ/ር)

እንዳሻው አዳነ

ተሾመ ሽፈራው

መላኩ ካሳዬ

ነፃነት ተገኝ

| | | |
|---|---|---|
| አመልካች፡ | አቶ አደፍርስ በቀለ | የቀረበ የለም |
| ተጠሪዎች፡ | 1. ወ/ሮ ቤተልሔም አለሙ | |
| | 2. ወ/ሮ ጽጌ በቀለ | |

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ በውክልና የተደረገ የስጦታ ውል ይፍረስልኝ በሚል የቀረበ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ/288648 ላይ ሰኔ 23/2015 ዓ.ም አመልካች ያቀረቡትን ይግባኝ አቤቱታ ውድቅ በማድረግ የሰጠውን ትእዛዝ በመቃወም ነው፡፡

የጉዳዩን አመጣጥ ስንመለከት በሥር የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሁን አመልካች ሐምሌ 30 ቀን 2013 ዓ.ም ፅፈው ባቀረቡት ክስ አመልካች እና 2ኛ ተጠሪን ጨምሮ አምስት እህት እና ወንድሞቻቸው የሚች እናታቸው ወ/ሮ ፀዳለ አስፋው ወራሽ መሆናቸው እንዲሁም አቶ አድማሱ በቀለ የተባሉት ወንድማቸው በቀን 27/04/2010 ዓ.ም በተደረገ ስምምነት ድርሻቸውን ለአመልካች የለቀቁላቸው መሆኑን፤ በዚህም መሰረት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/170086 ላይ ሰኔ 15/2010 ዓ.ም በተሰጠ ውሳኔ እና በመ/ቁ/184816 ህዳር 07/2011 ዓ.ም በተሰጠ የአፈፃፀም ትእዛዝ

የውርስ ሀብት የሆነው ቤት በጋራ ወራሾች ስም የተመዘገበ መሆኑን፣ ይሁን እንጂ 1ኛ ተጠሪ ከአመልካች በጀርመንኛ ቋንቋ ተፅፎ የተሰጣቸውን ውክልና ትርጉም በማዛባት 2ኛ ተጠሪ ከሆኑት እናቷ ጋር ያላቸውን የጥቅም ግንኙነት እንዲሁም አመልካች በውጪ ሀገር የሚኖሩ መሆኑን እንደመልካም አጋጣሚ በመጠቀም 1ኛ ተጠሪ የአመልካችን የውርስ ሀብት ድርሻ ነሀሴ 27 ቀን 2009 ዓ.ም በተደረገ የስጦታ ውል ለ2ኛ ተጠሪ ያስተላለፉ መሆኑን በመግለጽ የስጦታ ውሉ እንዲሰረዝላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪዎች ጥቅምት 25 ቀን 2014 ዓ.ም በተፃፈ መልስ የመጀመሪያ ደረጃ የክስ መቃወሚያ እና አማራጭ የፍሬ ነገር ክርክር አቅርበዋል፡፡ የመቃወሚያው ይዘትም አመልካች ጥር 27 ቀን 2005 ዓ.ም ባደረጉት የድርሻ መልቀቅ ስምምነት የውርስ ሀብቱ በሌሎቹ አራት ወራሾች ስም ተመዝግቦ ወደ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበርነት የተቀየረ በመሆኑ በንብረቱ ላይ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብት እና ጥቅም የላቸውም፣ የስጦታ ውሉም የተደረገው ነሀሴ 17 ቀን 2009 ዓ.ም በመሆኑ የአመልካች አቤቱታ በሁለት አመት ይርጋ ይታገዳል የሚል ነው፡፡ ከፍሬ ነገር አኳያም ተገቢ ነው ያሏቸውን መከራሪያዎችን በማንሳት ተከራክረዋል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ ግራቀኙ በችሎት ባደረጉት ክርክር አመልካች ንብረቱ በስጦታ የተላለፈ መሆኑን ያወቁት ታህሳስ 2013 ዓ.ም መሆኑን እና ለጉዳዩ አግባብነት ያለው የአስር አመት ይርጋ መሆኑን ሲገልፁ ተጠሪዎች በበኩላቸው በፅሁፍ ያቀረቡትን መቃወሚያ በማጠናከር ሞግተዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤትም በመቃወሚያው ላይ የግራ ቀኙን ምስክሮች አስቀርቦ ከሰማ በኋላ በሰጠው ብይን አመልካች ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብት እና ጥቅም አላቸው፣ ይርጋን በተመለከተ በአመልካች በኩል የቀረቡት ምስክሮች አመልካች ድርሻውን በስጦታ የተላለፈ ስለመሆኑ ታህሳስ 2013 ዓ.ም በስልክ እና በቴሌግራም የገለፁላቸው መሆኑን ቢያስረዱም የተጠሪዎች ምስክሮች አመልካች ድርሻቸውን በ2005 ዓ.ም ለቅቀው 1ኛ ተጠሪ ስጦታውን እንዲያደርጉ ውክልና የሰጧቸው መሆኑን፣ በውክልናው መሰረትም የስጦታ ውሉ እንደተደረገ በወቅቱ ያወቁ እንደነበር አስረድተዋል፣ የቀረቡትም ሰነዶች ይህን የሚያረጋግጡ በመሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/98961 በሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም መሰረት ክሱ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ መቅረብ ሲገባው ዘግይቶ የቀረበ ነው በማለት በይርጋ ውድቅ አድርጓል፡፡ አመልካች ይህንኑ በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም ፍ/ቤቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 337 መሰረት ይግባኙን ዘግቷል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታም የቀረበው እነዚህን የሥር ፍ/ቤቶችን ብይን እና ትእዛዝ በመቃወም ነው፡፡ አመልካች መስከረም 12/2015 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች አቋም ላይ ተፈፅሟል ያሉትን መሰረታዊ የህግ ስህተት ጠቅሰው በዚህ ችሎት እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡ መሰረታዊ ይዘቱም ከአከራካሪው ስጦታ ውል በኋላ በፌዴራለ መጀሚያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ/170086 ላይ ሰኔ 15/2010 ዓ.ም በተሰጠ ውሳኔ እና በመ/ቁ/184816 ህዳር 07/2011 ዓ.ም በተሰጠ የአፈፃፀም ትእዛዝ መሰረት ንብረቱ በወራሾች ስም እንዲመዘገብ የተደረገ በመሆኑ የስጦታ ውሉ ህገ ወጥ ነው፡፡ ውሉ ህገ ወጥ ከሆነ ደግሞ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/67376 እና 105652 ላይ በሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም መሰረት ለጉዳዩ አግባብነት ያለው የይርጋ ደንብ የ10 አመት ነው፡፡ ከማስረጃ አኳያ ተጠሪዎች አስቀድሞ ያልቆጠሯቸውን የጥቅም ተጋሪ እና ገለልተኛ ያልሆኑ ምስክሮች ያሰሙ ከመሆኑም በላይ አመልካች ነዋሪነታቸው ከሀገር ውጪ በመሆኑ ድርሻዬ በስጦታ የተለላፈ መሆኑን ያወኩት ታህሳስ ወር 2013 ዓ.ም በ2ኛ ተጠሪ እና አቶ ስራጅ ጀንበሬ መካከል በመ/ቁ/236881 የነበረውን ክርክር ተከትሎ ስለመሆኑ በተሻለ ሁኔታ አስረድቼ እያለሁ የስር ፍርድ ቤቶች ማስረጃውን

የመዘኑበት ሁኔታ መሰረታዊ የማስረጃ ምዘና መርህ ጥሰት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊሻር ይገበዋል የሚል ነው፡፡

የሰበር አቤቱታው በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ ቀደም ሲል በዚሁ ችሎት በመ/ቁ/105652 ላይ ከተሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም አንፃ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው የይርጋ ደንብ በዘህ ችሎት ቀርቦ እንዲመረመር በመታዘዙ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡

በዚህ መሰረት ተጠሪዎች ግንቦት 22/2015 ዓ.ም በተፃፈ መልስ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ልዩ የሆነውን ስጦታ ውል የሚመለከት የፍ/ብ/ህ/ቁ/2441 እንጂ የፍ/ብ/ህ/ቁ/1845 አይደለም፣ ሰበር ሰሚ ችሎቱ በመ/ቁ/105652 ላይ የሰጠው ትርጉም በህይወት የሌለ ስጦታ ሰጭን ጉዳይን አስመልክቶ የፍ/ብ/ህ/ቁ/2339 ድንጋጌን መሰረት አድርጎ የተሰጠው ትርጉም በመሆኑ ለቀረበው ጉዳይ አግባብነት የለውም፣ ከዚህ በተጨማሪም አመልካች በድርሻ መልቀቅ ውል ድርሻቸውን መልቀቃቸው እና ስጦታውን ከጅምሩ ያውቁ እንደነበረ በሥር ፍ/ቤት በቀረቡት ማስረጃዎች ተረጋጧል፡፡ በመ/ቁ/170086 ላይ በነበረው የውርስ ማጣራት ሂደት የአመልካች ስም የተካተተው ሂደቱን ለመጠበቅ ብቻ ነው፣ አመልካች የሰጡት ውክልናም በውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር እና በሰነዶች ማረጋገጫ ፅ/ቤት በኩል የተረጋገጠ በመሆኑ በተጭበረበረ መልኩ ተተርጉሟል ሊባል አይችልም፡፡ በምስክሮች ቃል ምዘና በኩልም የተፈጠረ ስህተት ባለመኖሩ አቤቱታው ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካችም ሰኔ 16 ቀን 2013 ዓ.ም በተፃፈ የመልስ መልስ በውርስ ማጣራት ሂደቱ የአመልካች ስም እንዲካተት የተደረገው ሂደቱን ለመጠበቅ ነው በሚል የቀረበው መከራከሪያ የማስረጃ ድጋፍ የለውም በማለት በተቀረው የሰበር አቤቱታቸውን የሚያጠናክር ምክንያት በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና መሰረታዊ የክርክሩ ይዘት ጠቅለል ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገበዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራ ቀኙ ክርክር፣ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

እንግዲ ከክርክሩ አመጣጥ መገንዘብ እንደሚቻለው አመልካች ክስ ያቀረቡት የሰጡትን የውክልና ስልጣን ትርጉም በማዛባት ተፈፅሟል ያሉትን ህገ ወጥ የስጦታ ውል ለማስፈረስ ነው፡፡ ህገ ወጥ ስጦታ ውል ይፍረስልኝ የሚል ክስ ማቅረቢያ ጊዜን አስምልክቶ በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 2441 ስር የተመለከተው የይርጋ ደንብ የሚመለከተው በስጦታ አድራጊው ላይ በተደረገ የመንፈስ መጫን ምክንያት የተደረገ ስጠታ ውልን ለማስፈረስ መሆኑን፣ ከዚህ ውጭ ባለ ምክንያት ለሚቀርብ የስጦታ ውል ይፍረስልኝ አቤቱታ ተፈፃሚነት ያለው የይርጋ ደንብ በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1845 ስር የተመለከተው የ10 ዓመት የይርጋ ደንብ ስለመሆኑ ይኸው ችሎት በሰ/መ/ቁ/105653 እና በሌሎች መዛግብት ላይ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡

ከዚህ አንፃር አመልካች የስጦታ ውሉን ለማስፈረስ ያቀረቡት ምክንያት የመንፈስ ማጫንን የሚመለከት ባለመሆኑ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው የይርጋ ደንብ በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1845 ስር የተመለከተው 10 ዓመት ይርጋ ይሆናል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የአመልካች ክስ በይርጋ ቀሪ የሚሆን አይደለም፡፡ ጉዳዩ ይህ ሆኖ እያለ የስር ፍርድ ቤቶች ለቀረበው ክስ አግባብነት የሌለውን የይርጋ ደንብ ጠቅሰው የአመልካችን ክስ ውድቅ ማድረጋቸው የቀረበውን ክስ ይዘት ያላገናዘበ እና ከዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም የተላለፈ በመሆኑ በእርግጥም ሊነቀፍ የሚገባው መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ/200091 ላይ የካቲት 15/2014 ዓ.ም በዋለው ችሎት የአመልችን አቤቱታ በይርጋ ውድቅ በማድረግ የሰጠው ብይን እና ይህንኑ ብይን በማፅናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ/288646 ላይ ሰኔ 23/2015 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. ለቀረበው ጉዳይ አግባብነት ያለው የይርጋ ደንብ በፍ/ብ/ህ/ቁጥር 2441 ስር የተመለከተው የሁለት አመት ይርጋ ጊዜ ሳይሆን በፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1845 ስር የተጠቀሰው የ10 አመት ይርጋ ጊዜ በመሆኑ የአመልካች አቤቱታ በይርጋ አይታገድም፡፡

3. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በብይን የዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ በክሱ ፍሬ ነገር ክርክር ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ ተገቢ ነው ያለውን ውሳኔ እንዲሰጥ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 341 መሰረት ጉዳዩ ይመለስለት፡፡

**<u>ትዕዛዝ</u>**

1. የዚህን ሰበር ሰሚ ችሎት ክርክር ወጪ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
2. በዚህ መዝገብ ላይ የተሰጠ የእግድ ትዕዛዝ ካለ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ማ/ተ

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ. 234613

ቀን ፡- ጥቅምት 05 ቀን 2016 ዓ/ም

ዳኞች፡- እትመት አሰፋ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

አመልካች ፡- አቶ ወርቁ አያልነህ

ተጠሪ ፡- አቶ ካሳሁን አጥናፍ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

**ፍርድ**

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠውን ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው አመልካች በስር ፍርድ ቤት 1ኛ ጣልቃ ገብ፤ ተጠሪ 1ኛ ተከሳሽ ሆነው ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩ የተጀመረው በቡሬ ወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን የገጠር መሬት ውርስ ክርክር ነው፡፡ የሥር ከሳሾች እነ ወ/ሮ ዝይን አጥናፍ ባቀረቡት የውርስ መሬት ክስ አመልካች በ13/03/2013 ዓ/ም በተጻፈ የጣልቃ ገብነት አቤቱታ የሚኞች አቶ አጥናፍ ቦጋለ እና ወ/ሮ እመቤት ገላ የልጅ ልጅ ስለሆንኩ እና እናቴ ያረፈች ስለሆነ በእናቴ እግር ተተክቼ አያቶቼን ልወርስ ይገባል በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪም በአመልካች ለቀረበው የጣልቃ ገብነት አቤቱታ የመከላከያ መልሳቸውን ሲሰጡ ተጠሪ የሚች ሻሽ አጥናፉ ተተኪ ወራሽ ለመሆናቸው ያቀረቡት የውርስ ማስረጃ ስለሌለ የመክሰስ መብት የላቸውም፤ ሚች አጥናፉ ቦጋለ ያረፉት በ1997 ዓ/ም ስለሆነ እና መሬቶቹን ከ10 ዓመት በላይ ይዤ የቆየሁ ስለሆነ ክሱ በይርጋ

ውድቅ ሊደረግ ይገባል የሚሉ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች እና በፍሬ ነገር ደረጃ ደግሞ የውርስ መሬቱን ሊካፈሉ አይገባም፤ የአመልካች እናት ስላሉ አመልካች ሊወርሱ አይገባም ተብሎ አቤቱታቸው ውድቅ እንዲደረግልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

የቡሬ ወረዳ ፍርድ ቤቱም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያውን በተመለከተ አመልካች በማረሚያ ቤት በሕግ ቁጥጥር ስር የኖረ ስለሆነ ክሱ በይርጋ የታገደ አይደለም በማለት ውድቅ በማድረግ በፍሬ ነገሩ ላይ አመልካች በማረሚያ ቤት እያሉ ያሳደጉዋቸው አያቶቻቸው ያረፉ ስለመሆኑ ተረጋግጧል፤ ሌላው የአመልካች እናት በሌላ ሀገር አርፈው በቀበሌው በምስል የተለቀሰላቸው መሆኑ በምስክሮች ተረጋግጧል፡፡ ስለሆነም አመልካች ተተኪ ሊሆኑ ይገባል በማለት ተጠሪ እና የስር ፍርድ ቤት 2ኛ ተከሳሽ የያዙትን መሬት ለአመልካች ሊያካፍሏቸው ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ የምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተጠሪን የይግባኝ አቤቱታ ባለመቀበል ሰርዟል፡፡

ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታቸውን ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በ10/03/2014 ዓ/ም በተጻፈ አቤቱታ አቅርበው ፍርድ ቤቱ መዝገቡን መርምሮ ክሱ የቀረበው ህዳር 03/2013 ዓ/ም እንደመሆኑ እና መሬቱ በአመልካች እጅ ከተያዘ ከ3 ዓመት በኋላ የቀረበ ክስ እንደመሆኑ ክሱ በይርጋ የሚታገድ ነው፡፡ ተጠሪም መሬቱን በወራሽነት እንጂ በህገ ወጥ መንገድ ያልያዙ በመሆኑ ከመሬት አዋጅ ቁጥር 252/2009 አንቀጽ 55 አንጻር የይርጋ መቃወሚያን እንዳያነሱ የሚከለከሉበት አግባብ የለም፡፡ የአመልካች ማረሚያ ቤት መቆየትም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 62 መሰረት በእስር ላይ የሚገኝ ሰው በወኪል መከራከር ከሚችል በስተቀር የይርጋ ማቋረጫ ምክንያት አይሆንም፡፡ መታሰርም በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1851 በተመለከቱት የይርጋ ማቋረጫ ምክንያቶች ውስጥ ባለመሆኑ የስር ወረዳ ፍርድ ቤት ተጠሪ በመታሰሩ ይርጋው ተቋርጧል ማለቱ የህግ መሰረት የለውም በማለት የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ በመሻር ክሱ በይርጋ ይታገዳል በማለት ወስኗል፡፡

ይሕ የሠበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው፡፡ አመልካች በ26/12/2014 ዓ/ም በጻፉት የሰበር አቤቱታ የይርጋ ጊዜው ሊቆጠር የሚገባው መብቴን ማስከበር ከቻልኩበት ከማረሚያ ቤት ከተፈታሁበት ቀን ጀምሮ አውራሾች መሞታቸውን እና መሬቱ በተጠሪ መያዙን ባወቅሁበት ጊዜ ሊሆን አይገባም ነበር ወይ? ሟች አያቴም ሆነ ወላጅ እናቴ ከሞቱ 10 ዓመት ያልሞላቸው እኔም ከማረሚያ ቤት ከተፈታሁ 2 ዓመት ያልሞላኝ መሆኑን በሰር ፍርድ ቤት ያቀረብኩት የግራ ቀኝ የሰው ምስክሮች ተረጋግጦ እያለ እና ስልጣን ያለው አካ/ጥ/ጽፈት ቤት ከሟች አያቶች ጋር በቤተሰብ አባልነት አብሬ ያደኩኝ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ የስር ፍርድ ቤቶች በህግ ቁጥጥር ስር እያለሁ ክርክሩ በ3 ዓመት ይርጋ ቀሪ ነው ተብሎ መወሰኑ መሰረታዊ የመረጃ ምዘና መርህን እና ስነ-ስርዓትን የተከተለ ነው ወይ? የሚሉትን በተገቢው መንገድ ሳያጣራ የሰጠው ውሳኔ ተገቢነት የሌለው ስለሆነ ተሽሮ የስር ፍርድ ቦቶች ውሳኔ እንዲጸናልኝ፡፡ አውራሾች የሞቱበት ጊዜ በተጠሪው እንኳን የታመነውን ብንይዝ 2002 ዓ/ም እና 2008 ዓ/ም ሆኖ ሳለ፤ አመልካች በህግ ቁጥጥር ስር የዋልኩት 2000 ዓ/ም ሆኖ 2011 ዓ/ም የተፈታሁ መሆኔ ባልተካደበት፤ ሟች መሞታቸውን እና መሬቱ

በሌላ ሰው መያዙን ያወኩት ከማረሚያ ቤት ስፈታ መሆኑን እያስረዳው እና ወዲያውኑ ወራሽነቴን አረጋግጬ መብቴን ስጠይቅ የስር ፍርድ ቤቱ ሟች የሞቱበትን ጊዜ ብቻ በመያዝ ክሱ በይርጋ ይታገዳል በማለት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስሆነ ሙሉ በሙሉ እንዲሰረዘልኝ እና የወረዳው እና የከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ውሳኔ እንዲጸናልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል።

የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን ተመልክቶ አመልካች በማረሚያ ቤት የነበረ ስለመሆኑ ግራ ቀኙን ባላከራከረበት ሁኔታ በወቅቱ መብቱን መጠየቅ ይችል ነበር በማለት በስር ክልሉ ሰበር ችሎት የይርጋ መቃወሚያውን በሚመለከት የደረሰበትን መደምደሚያ አግባብነት ለማጣራት ተጠሪ መልስ እንዲያቀርቡ አዟል። ተጠሪ መጥሪያ ደርሷቸው ያላቀረቡና መልስ ያላቀረቡ በመሆኑ የመከላከያ መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፏል።

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን እንደሚከተለው መርምረናል።

እንደመረመርነው የሥር ከሳሾች እነ ወ/ሮ ዝይን አጥናፍ ባቀረቡት የውርስ መሬት ክስ አመልካች በ13/03/2013 ዓ/ም በተጻፈ የጣልቃ ገብነት አቤቱታ የሟቾች አቶ አጥናፍ ቦጋለ እና ወ/ሮ እመቤት ገላ የልጅ ልጅ ስለሆንኩ እና እናቴ ያረፈች ስለሆነ በእናቴ እግር ተተክቼ አያቶቼን ልወርስ ይገባል በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል። ተጠሪ በበኩላቸው ሟች አጥናፉ ቦጋለ ያረፉት በ1997 ዓ/ም ስለሆነ እና መሬቶቹን ከ10 ዓመት በላይ ይዤ የቆየሁ ስለሆነ ክሱ በይርጋ ውድቅ ሊደረግ ይገባል የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርበዋል። የስር ወረዳ ፍርድ ቤቱም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያውን በተመለከተ አመልካች በማረሚያ ቤት በሕግ ቁጥጥር ስር የኖረ ስለሆነ ክሱ በይርጋ የታገደ አይደለም በማለት ውድቅ ያደረገ ሲሆን የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በበኩሉ የአመልካች ማረሚያ ቤት መቆየትም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 62 መሰረት በእስር ላይ የሚገኝ ሰው በወኪል መከራከር ከሚችል በስተቀር የይርጋ ማቋረጫ ምክንያት አይሆንም። መታሰርም በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1851 በተመለከቱት የይርጋ ማቋረጫ ምክንያቶች ውስጥ ባለመሆኑ የስር ወረዳ ፍርድ ቤት ተጠሪ በመታሰሩ ይርጋው ተቋርጧል ማለቱ የህግ መሰረት የለውም በማለት የሥር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሽሯል።

የይርጋ ክርክሩ የቀረበው አመልካች ክሱን ለማቅረብ የክስ የማቅረቢያ ጊዜው አልፏል በሚል ነው። ይርጋ መብትን (extinctive prescription) እና መብትን ለማስከበር የሚቀርብ ክስን በጊዜ ገደብ ቀሪ የሚያደርግ (limitation of action) ነው። እንደክሱ መሠረት ዓይነት ተፈጻሚ የሚሆነው የይርጋ ደንብና ሕግ የተለያየ ነው። የቀረበዉ ክስ በይርጋ ቀሪ ሊሆን የሚገባ መሆን አለመሆኑን በመወሰን ረገድ ፍርድ ቤቶች መሰረት እንዲያደርጉ የሚጠበቅባቸዉ በከሳሽ ክስ ላይ የተመለከተዉን የክስ ምክንያት እንጂ ተከሳሽ ለይርጋዉ መሰረት ይሆናል በማለት በበኩሉ ያቀረበዉን ሌላ የክርክር ምክንያት አለመሆኑንም መገንዘብ ያስፈልጋል። ሁሉም የገጠር የእርሻ መሬት ጋር የተያያዘ የክስ ዓይነት ላይ ተመሳሳይ የይርጋ ደንብ ተፈጻሚ ሊሆን አይችልም። ክሱ ይዞታ እንዲለቀቅ የሚቀርብ የይዞታ መብትን ለማስከበር የሚቀርብ ክስ ወይም የገጠር መሬት ውርስ ይገባናል በሚል የቀረበ ክስ ወይም ከገጠር መሬት ጋር የተያያዘ ውልን መሠረት ያደረገ ክስ

መሆኑ እየታየ እንደክሱ የዳኝነት መሠረት ክሱ በይርጋ ቀሪ የሚሆንበት ጊዜና ለጉዳዩ ተፈጻሚ የሚሆነው የይርጋ ደንብ ወይም ድንጋጌ የተለያየ ነው፡፡ ስለሆነም የክሱን መሠረት መለየት የይርጋ ክርክሩንም ሆነ ቀጣይ ያሉ ሂደቶችን ለመመራት አስፈላጊ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

የአመልካች የክስ መሠረት የሆነው የገጠር መሬት ውርስን መሠረት ያደረገ በመሆኑና በመሬት አዋጅ ቁጥር 252/2009 ስለውርስ መሬት የሚመለከት የይርጋ ድንጋጌ የሌለው በመሆኑ ተፈፃሚነት ያለዉ እንደአግባብነቱ በፍትሐ ብሔር ሕጉ አንቀጽ 1000 ሆነ 1845 የተመለከተው የይርጋ ደንብ ነዉ፡፡ የይርጋ ጊዜና አቆጣጠር በተመለከተ በፍ/ሕ/ቁ. 1846 “የይርጋው መነሻ ጊዜ” በሚል ርእስ ሥር “የይርጋው ቀን መቆጠር የሚጀምረው ግዴታዉን ለመጠየቅ ተገቢ ከሆነዉ፤ ወይም ዉሉ የሚሰጠዉ መብት ከተሰራበት ቀን ጀምሮ ነዉ” በማለት ከተደነገገው ጋር ተገናዝቦ ሊመረመር ይገባል፡፡ በመርሕ ደረጃ በፍ/ሕ/ቁ. 1846 እንደተመለከተውም ይርጋ ጊዜ መቁጠር የሚጀምረው በመብቱ መሥራት ከሚችልበት ጊዜ ጀምሮ ነው፡፡ አመልካች በመብታቸው መሥራት የሚችሉትና የውርስ መሬት መጠየቅ የሚችሉት አውራሾቻችው መሞታቸውንና መሬቱ በተጠሪ መያዙን ካወቁበት ጊዜ ጀምሮ ነው፡፡ አመልካች በማረሚያ ቤት በሕግ ቁጥጥር ስር ቆይተው የተፈቱ ስለመሆኑ በሥር ወረዳ ፍርድ ቤት የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነው፡፡ አመልካች ታስረው መቆየታቸው እና አውራሾቻቸው መሞታቸውን መቼ አወቁ ወይም መሬቱ በተጠሪ መያዙን መቼ አወቁ የሚለው ይርጋው መቆጠር ያለበት ከመቼ ጊዜ ጀምሮ ነው የሚለው የይርጋ አቆጣጠር የሚመለከት እንጂ በፍ/ሕ/ቁ. 1851 መሠረት የይርጋ ማቋረጫ ምክንያትን የሚመለከት አይደለም፡፡

በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 245/1/ እንደተመለከተው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያን ለመወሰን ማስረጃ መስማት ካስፈለገ ተገቢውን ፍሬ ነገር በማስረጃ በማጣራት መወሰን ያለበት ስለመሆኑ የተደነገገ ሲሆን ተጠሪ ያቀረቡትን የይርጋ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ለመወሰን እና አመልካች ለረጅም ጊዜ ታስረው የቆዩ መሆኑን መሰረት አድርገው የተከራከሩ ስለሆነ በመብታቸው ለመስራት አውራሾቻው መሞታቸውን መቼ አወቁ እንዲሁም መሬቱ በተጠሪ መያዙን መቼ አወቁ የሚለውን ፍሬ ነገር በማስረጃ በማጣራት በመብታቸው መስራት የሚችሉት ከመቼ ጊዜ ጀምሮ ነው፣ ይርጋው መቆጠር ያለበት ከመቼ ጊዜ ጀምሮ ነው የሚለውን በመለየት በተጠሪ በቀረበው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ የሥር ፍርድ ቤቶች ሊወስኑ ሲገባ በዚህ አግባብ ሳያጣሩ የሰጡት ውሳኔ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥሮች 187728፣ 224539 እና በሌሎች መዛግብት ከሰጠው አስገዳጅ ትርጉም አንጻር መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 03-110813 ሰኔ 30 ቀን 2014 ዓ/ም፣ የምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 80106 መስከረም 28 ቀን 2014 ዓ/ም እና

የቡሬ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 30657 ሰኔ 17 ቀን 2013 ዓ/ም የሠጡት ውሳኔ በሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/1/ለ/ መሰረት ተሽሯል።

2. የቡሬ ወረዳ ፍርድ ቤት በፍርዱ በተመለከተው መሠረት አመልካች በመብታቸው መስራት የሚችሉት ከመቼ ጊዜ ጀምሮ ስለመሆኑ በግራቀኙ ማስረጃ በማጣራት ተጠሪ ባቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ በሕግ መሠረት ውሳኔ እንዲሰጥበትና ጉዳዩ በይርጋ የማይቋጭ ከሆነ በሥረ-ነገሩ ውሳኔ እንዲሰጥበት በሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/2/ መሠረት ጉዳዩን መልሠናል።

3. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ አመልካች የራሳቸውን ይቻሉ ብለናል።

<u>ትዕዛዝ</u>

- ❖ የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ። የቡሬ ወረዳ ፍርድ ቤት በውሳኔው መሠረት እንዲፈጽም አዘናል። ይጻፍ
- ❖ መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ማ/ተ

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሠ/መ/ቁጥር 234309

ጥቅምት 06 ቀን 2016 ዓ/ም

ዳኞች ፡- እትመት አሰፋ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግሥቱ

አመልካች ፡- አቶ ካሳሁን አህመድ

ተጠሪ፡- የቁንዝላ ከተማ መሪ ማዘጋጃ ቤት } አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል።

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ለሕዝብ ጥቅም ተብሎ ተወሰደ ለተባለዉ የመሬት ይዞታ ምትክ መሬት ለማሰጠትና በይዞታዉ ላይ ይገኝ ነበር የተባለዉን አትክልት ግምት ለማስከፈል የቀረበ ክስ አስመልክቶ የተሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ በሚል ለማሳረም የቀረበ የሰበር አቤቱታ የሚመለከት ነዉ። አመልካች በአማራ ክልል የሰሜን አቸፈር ወረዳ ፍርድ ቤት በተጠሪ ላይ በመሰረቱት ክስ በምስራቅ ቀጭን የእግር መንገድ፣ በምዕራብ መንገድ፣ በሰሜን ሃጅ አብዱ እና በደቡብ በመንገድ ተዋስኖ ከሚገኝ ይዞታዬ ላይ 1300

ካሬ ሜትር ለመንገድ ሥራ ተብሎ የተወሰደ በመሆኑ ትክ መሬት እንዲሰጠኝ፣ የአትክልት ግምትም ብር 70,000.00(ሰባ ሺህ ብር) እንዲከፈለኝና ለቀሪዉ መሬቴ ካርታም እንዲሰራልኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪም ባቀረበዉ መከላከያ መልስ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለዉም፡፡ በሰነድ አልባ መመሪያ መሰረት ታይቶ የሚስተናገድ እንጂ በፍርድ ቤት የሚታይ አይደለም፡፡በ2005 ዓ/ም የአመልካች አባት ይዞታ በሰነድ አልባ ተመዝግቧል፡፡ ሌላዉ ይዞታ የጣና አካል ነዉ፡፡ በቁንዝላ ከተማ ምሪት የተጀመረዉ በ1979 ዓ/ም ነዉ፡፡ ነባሩን መንገድ ማስፋፋት እንጂ አዲስ መንገድ ስላልተሰራ ነባሩ መንገድም የመንግስት ይዞታ ስለነበረ ካሳ ሊጠይቁ አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡

ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ አስቀድሞ በሰጠዉ ዉሳኔ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ መሰረት በማድረግ ክሱን ዉድቅ በማድረግ በፍሬ ነገር ረገድ ደግሞ መሬቱ ለመንገድ የተወሰደዉ ምን ያክል እንደሆነ ብሎም በመሬቱ ላይ የለማ አትክልት የነበራቸዉ ስለመሆኑ አመልካች በማስረጃ አላስረዱም በሚል ክሱን ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት አመልካች ይግባኝ ለባህር ዳርና አካባቢዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዉ ፍርድ ቤቱም በመ/ቁጥር 0328234 ላይ በቀን 04/04/2014ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ በክሱ በተጠቀሰዉ አዋሳኝ ዉስጥ አመልካች ምን ያህል ሕጋዊ ይዞታ አላቸዉ? መጠኑ ምን ያህል እንደሆነ ከዚህ ቦታዉ ለመንገድ ምን ያህል እንደተወሰደባቸዉ በገለልተኛ አካል በማጣራት ለመንገድ ልማት ተብሎ የተወሰደባቸዉ ቦታ ላይ ያለሙት አትክልት ምን እንደሆነና የአትክልቶች ግምት በባለሙያ አስገምቶ የሚቀርብለትን ማስረጃ መሰረት አድርጎ እንዲወስን ዉሳኔዉን ሽሮ መልሶለታል፡፡ይህንን ተከትሎ የወረዳዉ ፍርድ ቤት መዝገቡን አንቀሳቅሶ ለሚመለከተዉ አካል ትዕዛዝ ሰጥቶ እንዲጣራ አድርጎ በሰጠዉ ዉሳኔ አመልካች ክስ የቀረበበት ቦታ ላይ ሕጋዊ የሆነ የይዞታ መብት ያላቸዉ ስለመሆኑ የማስረዳት ሸክም እያለባቸዉ የማስረዳት ግዴታቸዉን አልተወጡም፡፡ፍርድ ቤቱም በገለልተኛ ባለሙያ ክስ በቀረበበት ቦታ ላይ አመልካች ሕጋዊ ይዞታ መብት ያላቸዉ መሆን አለመሆኑ ሲያጣራ ክስ የቀረበበት ቦታ የግለሰብ ይዞታ እንዳልሆነ እና በማንም ስም ያልተመዘገበ ይዞታ ስለመሆኑ ማረጋገጡን በመግለጽ አመልካች ከተጠሪ የተሻለ ማስረጃ በማቅረብ አላስረዱም በማለት ክሱን ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡

አመልካች በዉሳኔዉ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለባህር ዳር እና አካባቢዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337 መሰረት መዝገቡን ዘግቷል፡፡በመቀጠል አመልካች የሰበር አቤቱታቸዉን ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ችሎቱ ተጠሪን ሳያስቀርብ አቤቱታቸዉን ሰርዞባቸዋል፡፡

አመልካች በቀን 05/01/2015 ዓ/ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ከላይ በተገለጸዉ መሰረት በተሰጠ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን የአቤቱታቸዉ ይዘት በአጭሩ፡- ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ይዞታ የአባቴ የሃጅ አህመድ ከማል ይዞታ መሬት ሲሆን አትክልት አልምቶ ሲጠቀምበት የኖረ እና በሞት ከተለየ በኂላ ይዤ ስጠቀምበት መኖሬን አስመስክሬ አስረድቻለሁ፡፡እንዲሁም መንገዱ የወጣዉ በወል

መሬት ላይ ሳይሆን በአመልካች ቦታ ላይ መሆኑን በማጣሪያ ምስክር ጭምር አስረድቻለሁ። በዚህ መልኩ ለሕዝብ ጥቅም በዋለ መሬቴ ላይ የተለያዩ አትክልቶች ማስረዳቴን አስቀድሞ ቀርቦ የነበረዉን ይግባኝ የተመለከተዉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አረጋግጦ ጭብጥ ይዞ ለወረዳዉ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ሲመልስ የመሰረታቸዉ ጭብጦች የቦታዉ መጠን ምን ያህል እንደሆነ፣ከዚህ የአመልካች ይዞታ ላይ ለመንገድ ሥራ ተብሎ የተወሰደዉ መሬት ምን ያህል እንደሆነ፣በቦታዉ ላይ አመልካች ያለማሁት አትክልት ምን አይነት እንደነበረና ግምቱ በገለልተኛ ባለሙያ ተጣርቶ እንዲወሰን ነዉ። በዚህ መልኩ ፍርድ ቤቱ ጭብጥ ይዞ ሲመልስ ይዞታዉ የአመልካች መሆኑን አረጋግጦ እያለ የወረዳዉ ፍርድ ቤት ከተያዘለት ጭብጥ ዉጭ በሆነ አኳኋን አመልካች በመሬቱ ላይ መብት እንዳለዉ አላስረዳም በማለት ዉሳኔ መስጠቱ ስህተት ነዉ።የስር ፍርድ ቤት በገለልተኛ አካል አላጣራም።በባለሙያ የቀረበለትን ማስረጃ ከቀረቡለት የምስክሮች ቃል እና ከሌሎች የሰነድ ማስረጃዎች ጋር አገናዝቦ መርምሮ አለመወሰኑም በሰ/መ/ቁጥር 168522 እና 36848 ላይ የተሰጠዉን የሕግ ትርጉም የጣሰ በመሆኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ተብሎ ይታረምልኝ በማለት ተከራክረዋል።

የሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ የባህር ዳር እና አካባቢዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ለክሱ ምክንያት በሆነዉ ይዞታ ለአመልካች ያለዉ ሕጋዊ ይዞታ መጠን ምን ያህል እንደሆነ ተጣርቶ እንዲወሰን ወደ ስር ፍርድ ቤት በነጥብ በተመለሰበት ሁኔታ የስር የወረዳ ፍርድ ቤት የዞኑ ከተማ ልማት ኮንስትራክሽን መምሪያ አከራካሪዉ ይዞታ በማንም ስም እንዳልተመዘገበ ፣ ምንም አይነት ሰነድ እና ግንባታ እንደሌለ መነሻ ሰነድ በሌለበት ለመንገድ የተወሰደዉ ምን ያህል እንደሆነ ለማጣራት መቸገሩን በመግለፅ የሰጠዉን ምላሽ መሰረት በማድረግ የአመልካችን ክስ ዉድቅ በማድረግ የወሰነበትን አግባብነት ቀደም ሲል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲጣራ ከመለሰዉ ነጥብ ጋር በማገናዘብ ተጠሪ ባለበት እንዲመረመር ትእዛዝ በመስጠቱ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ አዟል።በዚህ መሰረት አመልካች ለተጠሪ መጥሪያ ማድረሱን የሚያሳይ ማረጋገጫ ያቀረበ ቢሆንም ተጠሪ በተሰጠዉ ቀነ ቀጠሮ ባለማቅረቡ መልስ የመስጠት መብቱ ታልፏል።

ከላይ አጠር ባለ መልኩ የተገለጸዉ ግራ ቀኙ በስር ፍርድ ቤቶች ያቀረቡትን ክርክርና በየደረጃዉ ባሉ ፍርድ ቤቶች የተሰጠ ዉሳኔ ይዘት እና የአመልካችን የሰበር አቤቱታ ይዘት የሚመለከት ሲሆን እኛም በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩ እንደሚከተለዉ አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ መርምረናል።

እንደተመረመረዉም በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 80(3/ሀ እና ለ) ስር እንደተመለከተዉ ለፌዴራል እና ለክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች ሰበር ሰሚ ችሎቶች የተሰጠዉ ሥልጣን ማናቸዉንም መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበትን የመጨረሻ ዉሳኔ በሕግ በዝርዝር በሚወሰነዉ አግባብ መርምረዉ እንዲያርሙ ነዉ። በዚህ የሕገ መንግሥቱ ድንጋጌ ላይ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ምንነት በግልጽ አልተደነገገም። የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በተለያዩ መዛግብት ላይ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የሚያሰኙ ምክንያቶችን የሚያመላክቱ የሕግ ትርጉሞች ሲሰጥ ቆይቷል።ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በሕገ መንግሥቱ

አንቀጽ 80(3/ሀ) ስር በሰበር ችሎት የሚታይ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ምንነት በተመለከተ ጭምር ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል ተብሎ በተደነገገዉ አግባብ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 ላይ “መሠረታዊ የሕግ ስህተት” ለሚለዉ ሐረግ ትርጉም እስከተሰጠበት ጊዜ ድረስ ለሐረጉ በሕግ ትርጓሜ አልተሰጠም ነበር፡፡ስለሆነም አዋጅ ቁጥር 1234/2013 ከፀና በኋላ በዚህ ችሎት ዉሳኔ ለሚሠጥባቸዉ ጉዳዮች ከጥር 13 ቀን 2013 ዓ/ም ጀምሮ በጸናዉ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 “ለመሰረታዊ የሕግ ስህተት” የተሰጠዉን ትርጓሜ መመልከት የግድ ይላል፡፡

በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2/4 ስር “መሠረታዊ የሕግ ስህተት” የሚያሰኙ ምክንያቶች በዝርዝር እና በጥቅል አገላለጽ ተተርጉሟል፡፡ በዚህ ትርጓሜ ላይ በመንተራስ ከክልል ፍርድ ቤቶች ተጀምረዉ በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች ሰበር ሰሚ ችሎቶች ታይተዉ በተሰጡ የመጨረሻ ዉሳኔዎች ላይ ተፈጽመዋል ሊባሉ የሚችሉ እና በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ታይተዉ ሊታረሙ የሚችሉ መሰረታዊ የሕግ ስህተቶች በአዋጁ አንቀጽ 10(1/ሐ እና መ) ስር ተደንግገዋል፡፡

በዚህ መሰረት መሰረታዊ የሕግ ስህተቶች ናቸዉ የሚያስብሉ ምክንያቶች *(1)* በአዋጁ አንቀጽ 2(4/ሀ) ስር በተመለከተዉ መሰረት ሕገ መንግስታዊ ድንጋጌዎችን በሚቃረን አኳኋን በክልል ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠ የመጨረሻ ዉሳኔ ሲሆን ፤*(2)* በአዋጁ አንቀጽ 2(4/ሸ) ስር እንደተመለከተዉ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ዉሳኔ በሚቃረን አኳኋን በክልል ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠ የመጨረሻ ዉሳኔ ሲሆን፤*(3)* በአንቀጽ 2(4/ለ) ላይ እንደተመለከተዉ ሕግን አላግባብ የሚተረጉም ወይም ለጉዳዩ አግባብነት የሌለዉ ድንጋጌ ተጠቅሶ የተሰጠ የመጨረሻ ዉሳኔ ሆኖ ይህ ዉሳኔ የተሰጠበት ጉዳይ ለሕዝብ ጥቅም ሀገራዊ ፋይዳ ያለዉ ጉዳይ በሚል በሕጉ ከተጠቀሱት ሦስቱ ምክንያቶች መካከል ቢያንስ አንዱን የሚያሟላ እና ፍትህን የሚያዛባ ጉልህ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት የመጨረሻ ዉሳኔ ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነዉ፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በተለያዩ መዛግብት ከሰጣቸዉ የሕግ ትርጉሞች አንዱ በመጀመሪያ ደረጃ ዳኝነት ሥልጣን እና በይግባኝ ሰሚነት የሚዳኙ ፍርድ ቤቶች የማስረጃ አቀራረብን፣ አግባብነትን፣ ተቀባይነትን እና ማስረጃ አቅርቦ አንድን ፍሬ ነገር የማስረዳት ሸክም የሚመለከቱ መርሆዎች (Principles of Production, relevancy, admissibility and burden of proof of evidence) አተገባበር በሚቃረን አኳኋን እንዲሁም የማስረጃ ምዘናን ወይም የማስረዳት ደረጃን (standards of proof or weight of evidence) የሚመለከቱ መሰረታዊ መርሆዎች በመጣስ የመጨረሻ ዉሳኔ መስጠታቸዉ በግልጽ ሲያረጋገጥ እንደመሰረታዊ የሕግ ስህተት ተቆጥሮ በፌዴራልም ሆነ በክልል ሰበር ሰሚ ችሎቶች ታይቶ ሊታረም እንደሚችል ነዉ፡፡ እንዲሁም ለአንድ ማስረጃ ተገቢዉን ዋጋ ሳይሰጡ እና በአንድ ማስረጃ ይዘት ላይ በግልጽ የተመለከተዉን በአግባቡ ያላገናዘበ ዉሳኔ መስጠት ወይም በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠዉን ነጥብ ከተገቢዉ ሕግ ጋር ሳያገናዝቡ መወሰን እንደመሰረታዊ የሕግ ስህተት የሚቆጠርና በሰበር ሰሚ ችሎት ሥልጣን ማእቀፍ ዉስጥ ታይቶ ሊታረም የሚገባ ስለመሆኑ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 44804(ቅጽ 11 ላይ እንደታተመዉ)፣226113 እና በሌሎች መዛግብት ላይ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡

*ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 169522(ቅጽ 24 ላይ እንደታተመዉ) በሰጠዉ የሕግ ትርጉም ከተለያዩ አስተዳደር ክፍል የሚቀርብ ማስረጃ እንደአግባብነቱ ለፍርድ ቤቱ ከቀረቡት ሌሎች የሰዉ እና የሰነድ ማስረጃዎች ይዘት ጋር ተገናዝቦ ተገቢዉ ዋጋ ሰጥቶ አለመመዘንና እና ከአስተዳደር ክፍል የቀረበ ማስረጃ ብቻ ሙሉ በሙሉ በመቀበል ዉሳኔ መስጠት ሕግን አለመከተልና ፍትሕን በእጅጉ የሚጎዳ በመሆኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ በማለት የሕግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡

በያዝነዉ ጉዳይ ከላይ እንደተመለከተዉ የባህር ዳርና አካባቢዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር በይግባኝ ተመልክቶ በመ/ቁጥር 0328234 ላይ በቀን 04/04/2014ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ የስር ፍርድ ቤትን ዉሳኔ ሽሮ ጉዳዩን ለስር ፍርድ ቤት ሲመልስ የያዛቸዉ ጭብጦች “በክሱ በተጠቀሰዉ አዋሳኝ ዉስጥ አመልካች ምን ያህል ሕጋዊ ይዞታ አላቸዉ? መጠኑ ምን ያህል እንደሆነ? ከዚህ ቦታ ላይ ለመንገድ ምን ያህል እንደተወሰደባቸዉ? በገለልተኛ አካል እንዲጣራ አድርጎና ለመንገድ ልማት ተብሎ የተወሰደባቸዉ ቦታ ላይ ያለሙት አትክልት ምን እንደሆነና የአትክልቶች ግምት መጠን በባለሙያ አስገምቶ የሚቀርብለትን ማስረጃ መሰረት አድርጎ ዉሳኔ እንዲሰጥ፡፡” የሚል ነዉ፡፡ ይህም የሚያሳያን ከፍተኛዉ ፍርድ ቤት በሰጠዉ ዉሳኔ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ መሬት የአመልካች እንደሆነና ከዚህ መሬታቸዉ ላይ ለመንገድ ልማት ተብሎ ተቀንሶ እንደተወሰደባቸዉ ተረጋግጧል በማለት ደምድሞ የሰጠዉ ዉሳኔ አለመኖሩን ነዉ፡፡ በመሆኑም አመልካች ጉዳዩ ለወረዳ ፍርድ ቤት የተመለሰዉ ለመንገድ ሥራ የተወሰደዉ መሬት ስፋት እና የአትክልቱ አይነት እንዲሁም ግምቱ ብቻ እንዲጣራ ብቻ እንጂ መሬቱ የአመልካች መሆን አለመሆኑ ጭምር እንዲጣራ አይደለም በማለት ያቀረቡት ክርክር የይግባኝ ሰሚዉን ፍርድ ቤት ዉሳኔ ይዘት ያላገናዘበ ከመሆኑም በተጨማሪ በዚህ ረገድ የወረዳዉ ፍርድ ቤት ስህተት ፈጽሟል የሚያስብል ምክንያት የለም፡፡

እንዲሁም የወረዳዉ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት የሰጠዉን ዉሳኔ መሰረት በማድረግ መዝገቡን በማንቀሳቀስ ለሚመለከተዉ አካል ትእዛዝ ሰጥቶ የቀረበለትን ማስረጃ እና አስቀድሞ ግራ ቀኙ ያቀረቡትን ማስረጃዎች መርምሮና መዝኖ ለመንገድ ሥራ የዋለዉ መሬት የወል መሬት እንጂ የአመልካች የግል ይዞታ አለመሆኑን ምዛን በሚደፋ አኳኋን ከቀረቡት ማስረጃዎች ማረጋገጡን በመግለጽ ክሱን ዉድቅ በማድረግ መወሰኑን የዉሳኔዉ ይዘት ያሳያል፡፡በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት አመልካች ያቀረቡትን ይግባኝና የሰበር አቤቱታ በየደረጃዉ ባሉ ፍርድ ቤቶች ተቀባይነት አላገኘም፡፡ለመንገድ ልማት ሥራ ተብሎ ይዞታቸዉ እንደተወሰደባቸዉ፣ የተወሰደባቸዉ ይዞታ ስፋትና በይዞታዉ ላይ ያፈሩትን ንብረት አይነት እንዲሁም ግምቱን ተገቢዉንና አሳማኝ ማስረጃ አቅርበዉ ክሳቸዉን የማስረዳት ሸክም የአመልካች ነዉ፡፡ በመሆኑም አመልካች በዚህ መሰረት ተገቢዉንና አሳማኝ ማስረጃ በማቅረብ አለማስረዳታቸዉን ማስረጃ እንዲመረምርና እንዲመዝን ሥልጣን ተሰጠዉ የስር ፍርድ ቤት አረጋግጧል፡፡ ይህንን መሰረት በማድረግ የስር ወረዳ ፍርድ ቤት ወስኖ በየደረጃዉ ባሉ ፍርድ ቤቶች በትእዛዝ የጸናዉ ዉሳኔ በሰ/መ/ቁጥር 169522(ቅጽ 24 ላይ እንደታተመዉ) 44804(ቅጽ 11 ላይ እንደታተመዉ)፣226113 እና በሌሎች መዛግብት ላይ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በተሰጡ ዉሳኔዎች ላይ ከማስረጃ አቀባበል እና የማስረጃ ምዘና

መርሆዎች አተገባበር ጋር በተያያዘ የተሰጠዉን የሕግ ትርጉም የሚቃረን ነዉ የሚያስብል ምክንያት አላገኘንም፡፡

ሲጠቃለል በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ከላይ በተመለከተዉ መሰረት በትእዛዝ የጸናዉ ዉሳኔ ሕገ መንግሥቱን የማይቃረን፣አስቀድሞ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት የሠጠዉን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የማይቃረን፣ አከራካሪዉ ጉዳይ ለሕዝብ ጥቅም አገራዊ ፋይዳ አለዉ ሊባል የማይችል ከመሆኑም በተጨማሪ በግልጽ ሕግን አለአግባብ በመተርጎም ወይም ለጉዳዩ አግባብነት የሌለዉ ድንጋጌ ተጠቅሶ የተወሰነ እና ፍትሕን የሚያዛባ ጉልህ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል የሚያስብል ሁኖ አልተገኘም፡፡በመሆኑም በዉሳኔዉ ላይ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10(1/ሐ እና መ) ስር የተደነገጉ መስፈርቶችን በሚያሟላ መልኩ በዚህ ችሎት ደረጃ ተመርምሮ ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስላልተፈጸመ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## <u>ዉ ሳ ኔ</u>

1. የሰሜን አቸፈር ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 0160245 ላይ በቀን 12/07/2014ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ፣ የባህር ዳርና አካባቢዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 03-30691 ላይ በቀን 29/07/2014ዓ/ም የሰጠዉ ትእዛዝ እና የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 113289 ላይ በቀን 24/10/2014ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/1 መሰረት ጸንቷል፡፡
2. ግራ ቀኝ በዚህ ችሎት ደረጃ ያወጡትን ወጭ የየራሳቸዉን እንዲችሉ ብለናል፡፡

## <u>ትዕዛዝ</u>

1. የዉሳኔዉ ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡ ለግራ ቀኙም ግልባጩ ይሰጣቸዉ፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/ተ

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ.መ.ቁ 234162

ቀን ጥቅምት 6 2016 ዓ.ም

ዳኞች፡ እትመት አሰፋ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

አመልካች፡ የሸክላ ሱቆች አካባቢ አ.ማ ጠበቃ ሳሙኤል ደመቀ ቀረቡ

ተጠሪ፡ አንድነት ቅቤና ቅመማ ቅመም ነጋዴዎች አ.ማ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል

**ፍርድ**

ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ የቀረበው አመልካች የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አዲስ ከተማ ምድብ በመ.ቁ 97605 በ27/4/14ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ፤ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 288067 በ16/10/14ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ እንዲሁም በ21/11/14ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ ቅር በመሰኘት በ3/13/14ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ ስላቀረበ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ተጠሪ በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በአመልካች ላይ ባቀረበው ክስ አመልካች እና ተጠሪ በአዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወረዳ 8 ውስጥ የሚገኝ 2315ሜ.ካ ቦታ በጋራ ለማልማት በሊዝ ወስደን በላዩ ላይም ግንባታ ገንብተን ይዞታው በእጃችን ይገኛል፡፡ አመልካች እና ተጠሪ በጋራ ለማልማት ለወሰድነው ለዚህ ቦታ በሊዝ መክፈል ያለበትን ክፍያ ተጠሪ ብር 2,214,340.16 ለአዲስ ከተማ ክ/ከተማ መሬት

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ባለስልጣን ማስ/ጽ/ቤት የከፈልን ሲሆን ይዞታው የጋራችን እንደመሆኑ አመልካች ግን እስካሁን መክፈል ያለበትን የድርሻውን የዚህን ክፍያ ግማሹን ብር 1,107,170.08 አልከፈለም፡፡ እንዲከፍል ቢጠየቅም ፈቃደኛ አልሆነም፡፡ ስለሆነም አመልካች የሊዝ ክፍያውን ግማሽ ብር 1,107,170.08(አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ሰባት ሺህ አንድ መቶ ሰባ ብር ከ08/100) ከነህጋዊ ወለዱ እንዲከፍል እንዲወሰንልን በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡ ማስረጃዎችንም አቅርቧል፡፡

አመልካች የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችን አቅርቦ በፍሬጉዳዩ ላይ ባቀረበው መልስ አመልካች እና ተጠሪ በክሱ የተጠቀሰውን የሊዝ ይዞታ በ1990ዓ.ም ሲወስዱ ድርሻቸው እኩል የሆነ የጋራ ባለመብቶች የነበሩ ቢሆንም ቋሚ የሊዝ ውል በ14/6/05ዓ.ም ሲፈረም ግን በአስተዳደራዊ ውሳኔ አመልካች እና ተጠሪ የሚኖራቸው ድርሻ በአባላት ቁጥር እንዲወሰን በመደረጉ ድምር የአባላት ቁጥር 355 ሲሆን ከዚህ ውስጥ አመልካች ያለው ድርሻ የ70 አባላት ብቻ ነው፡፡ ስለዚህ በመቶኛ ሲቀመጥ በይዞታው እና በተሰራው ህንጻ ላይ አመልካች 19.72%፤ ተጠሪ ደግሞ 80.28% የባለቤትነትና የተጠቃሚነት መብት አላቸው፡፡ ከዚህ አስተዳደራዊ ውሳኔ ጋር በተያያዘ የፍ/ቤት ክርክር ነበረ ሲሆን የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 199333 በ14/9/11ዓ.ም፤ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ደግሞ ጉዳዩን በይግባኝ አይቶ በመ.ቁ 180804 በተሰጡ ውሳኔዎች አመልካች በህንጻው ላይ ያለው የባለቤትነትና የተጠቃሚነት ድርሻ 19.72% ብቻ ሆኖ ሳለ ለሊዝ የተከፈለውን ክፍያ ግን 50% የሚሸፍንበት ህጋዊ ምክንያት ባለመኖሩ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ በማለት ተከራክሯል፡፡ ማስረጃዎችንም አቅርቧል፡፡

ፍርድ ቤቱ በአመልካች የቀረቡትን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች በብይን ውድቅ አድርጎ በፍሬጉዳዩ ላይ ክሱን በመስማት ጭብጥ ይዞ ከቀረቡት ማስረጃዎች አንጻር ጉዳዩን በመመርመር ይዞታው በጋራ ለአመልካች እና ለተጠሪ የተሰጠ ስለመሆኑ እና ተጠሪ የሊዝ ክፍያ የከፈለ ስለመሆኑ በግራቀኙ የታመነ ሲሆን ይዞታው ከተሰጣቸው በኋላ በይዞታው እና በተሰራው ህንጻ ላይ አመልካች 19.72% ተጠሪ ደግሞ 80.28% የባለቤትነትና የተጠቃሚነት መብት ያላቸው ስለመሆኑ አስተዳደራዊ ውሳኔ ተሰጥቶ አስተዳደራዊ ውሳኔው የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ 199333 በ14/9/11ዓ.ም፤ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ደግሞ ጉዳዩን በይግባኝ አይቶ በመ.ቁ 180804 ውሳኔውን በማጽናት ውሳኔ የሰጠ ስለመሆኑ አመልካች ያቀረባቸው የውሳኔ ግልባጮች የሚያረጋግጡ ሲሆን በግራቀኙም የታመነ ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ አመልካች የሊዝ ክፍያውን ሊከፍል የሚገባው በተለየው 19.72% ድርሻ ልክ እንጂ ግማሽ ሊከፍል የሚገባበት የህግ ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ለሊዝ ከከፈለው ሙሉ ክፍያ ላይ አመልካች ሊከፍል የሚገባው 19.72% ብር 436,667.88(አራት መቶ ሰላሳ ስድስት ሺህ ስድስት መቶ ስልሳ ሰባት ብር ከ88/100) ብቻ ነው፡፡ ወለድን በተመለከተ ተጠሪ አመልካች ክፍያ እንዲከፍለው የጠየቀ ስለመሆኑ በክሱ ላይ የገለጸ ይሁን እንጂ ማስጠንቀቂያ የሰጠ ስለመሆኑ በማስረጃ ያላረጋገጠ ቢሆንም አመልካች የሀብቱ ተጠቃሚ በመሆኑ በድርሻው ልክ መክፈል የሚገባውን ቢከፍል ኖሮ ተጠሪ ለአመልካች ድርሻ የከፈለውን የገንዘብ መጠን ሊከፍል የማይችል በመሆኑ አመልካች ገንዘቡ ከተከፈለበት ግዜ ጀምሮ ያለውን ህጋዊ ወለድ ለተጠሪ የመክፈል ሀላፊነት አለበት በማለት አመልካች ብር 436,667.88(አራት መቶ ሰላሳ ስድስት ሺህ ስድስት መቶ ስልሳ ሰባት ብር ከ88/100)

ማ ስታወሻ፦ ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

አመልካች መብቱን ካገኘበት ከ20/3/05ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ 9% ህጋዊ ወለድ ጋር ለተጠሪ ሊከፍል ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ ወጪና ኪሳራንም በተመለከተ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች ከላይ በተገለጸው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱም የተጠሪን መልስ ተቀበሎ ጉዳዩን በመመርመር የስር ፍ/ቤት በደረሰኝ ቁጥር 923571 ተጠሪ በ13/1/12ዓ.ም የከፈለው ብር 1,068,390.16 (አንድ ሚሊዮን ስልሳ ስምንት ሺህ ሶስት መቶ ዘጠና ከ16/100) አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍለው መወሰኑ በአግባቡ ነው በማለት በዚህ ረገድ የስር ፍ/ቤቱን ውሳኔ በማጽናት፤ አመልካች የዚህ ገንዘብ ህጋዊ ወለድ 9% የሚከፍልበት የህግ አግባብ ስለሌለ ወለድን በተመለከተ የስር ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር እንዲሁም የስር ፍ/ቤት ወጪና ኪሳራን በተመለከተ የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡

የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ከላይ የተገለጸውን ውሳኔ በ16/10/14ዓ.ም ሰጥቶ መዝገቡን ከዘጋ በኋላ አመልካች ለፍ/ቤቱ ባቀረበው አቤቱታ ፍ/ቤቱ አመልካች የብር 1,068,390.19 (አንድ ሚሊዮን ስልሳ ስምንት ሺህ ሶስት መቶ ዘጠና ከ19/100) ድርሻ ብር 436,667.86(አራት መቶ ሰላሳ ስድስት ሺህ ስድስት መቶ ስልሳ ሶስት ብር ከ86/100) ያለወለድ ለተጠሪ እንዲከፍል ውሳኔ መስጠት ሲገባው በስህተት አመልካች ብር 1,068,390.19 (አንድ ሚሊዮን ስልሳ ስምንት ሺህ ሶስት መቶ ዘጠና ከ19/100) ለተጠሪ እንዲከፍል ተብሎ ስለተጻፈ ስህተቱ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 208 መሰረት እንዲታረምልኝ በማለት በመጠየቁ ፍ/ቤቱ የተጠሪን አስተያየት ተቀብሎ አቤቱታውን መርምሮ ፍ/ቤቱ በ16/10/14ዓ.ም በዋለው ችሎት በደረሰኝ ቁጥር 923571 የተመለከተው ገንዘብ ወለድ የማይመለከተው መሆኑን በፍርድ ሀተታው ከጻፈ በኋላ አመልካች የዚሁ ገንዘብ ድርሻው 19.7% ወይም ብር 436,667.86(አራት መቶ ሰላሳ ስድስት ሺህ ስድስት መቶ ስልሳ ሶስት ብር ከ86/100) መብቱን ካገኘበት ህዳር 20 ቀን 2005ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ ህጋዊ ወለድ 9% ጋር ለተጠሪ ይከፈል መባል ሲገባው በፍርድ ሀተታው እና በውሳኔው የተመለከተውን ብር 1,068,390.19 (አንድ ሚሊዮን ስልሳ ስምንት ሺህ ሶስት መቶ ዘጠና ከ19/100) አመልካች ለተጠሪ ይክፈል ተብሎ መጻፉ ስህተት ስለሆነ አመልካች ብር 436,667.86 (አራት መቶ ሰላሳ ስድስት ሺህ ስድስት መቶ ስልሳ ሰባት ብር ከ86/100) መብቱን ካገኘበት ከህዳር 20 ቀን 2005ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ ህጋዊ ወለድ 9% ጋር ጨምሮ ለተጠሪ እንዲከፍል በማለት በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 208 መሰረት ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

አመልካች ከላይ በተገለጹት ውሳኔዎች ቅር በመሰኘት ለዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት ባቀረበው የሰበር አቤቱታ ተጠሪ ከ22 አመት በፊት የከፈለውን ክፍያ አመልካች በድርሻው እንዲተካለት ያቀረበው ክስ በከፊል በይርጋ አይታገድም ተብሎ መቃወሚያው ታልፎ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው፤ ተጠሪ ባልጠየቀው እና ምክንያቱ ባልተገለጸ አመልካች ከህዳር 20 ቀን 2005ዓ.ም ጀምሮ ህጋዊ ወለድ ይክፈል መባሉ እንዲሁም የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በይግባኝ ጉዳዩን አይቶ ውሳኔ ከሰጠ በኋላ የአመልካች ድርሻ እንዲለይና ስህተቱ እንዲታረም አቤቱታ ሲቀርብለት የራሱን ውሳኔ በመሻር ከህዳር 20 ቀን 2005ዓ.ም

ጀምሮ አመልካች ወለድ ጭምር ይክፈል በማለት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው በማለት ውሳኔው እንዲሻር፤ ወጪና ኪሳራም እንዲከፈለው እንዲወሰንለት ጠይቋል፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ በሰበር አጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ በቀረበው ጉዳይ በስር ፍ/ቤት ለተጠሪ ተወስኖ የነበረውን ታሳቢ ወለድ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ከሻረው በኂላ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 208 ስህተት እንዲታረም በቀረበ አቤቱታ በዋናው ፍርድ ላይ በመሻር የወሰነውን ከህዳር 20/2005ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ ጋር ዋናውን ገንዘብ ይክፈል ሲል ራሱ የሰጠውን ውሳኔ በሚሽር ሁኔታ የወሰነበትን አግባብ ለማጣራት ለሰበር ችሎቱ ይቅረብ ተብሎ በ7/3/15ዓ.ም በመታዘዙ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎ ተጠሪ 3/4/15ዓ.ም በተጻፈ ያስቀርባል ተብሎ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር ባቀረበው መልስ የስር ፍ/ቤትም ሆነ የከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካች የተጠቀሰውን ገንዘብ ከህዳር 20 ቀን 2015ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ ህጋዊ ወለድ ጋር ለተጠሪ ሊከፍል ይገባል ተብሎ መወሰኑ የሚነቀፍ አይደለም ተብሎ ውሳኔው እንዲጸና በማለት ጠይቋል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አላቀረበም፡፡

ይህ የሰበር ሰሚ ችሎትም የአመልካችን የሰበር አቤቱታ አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ትእዛዝ እንዲሁም ከተገቢዎቹ የህግ ድንጋጌዎች አንጻር የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ እና ትእዛዝ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 208 ፍርድቤቱ በሰጠው መጥሪያ፤ በወሰነው ፍርድ፤ በሰጠው ውሳኔና ትእዛዝ ላይ የአጻጻፍ ስህተት፤ የቁጥር አጻጻፍ ጉድለት ወይም ያልታሰበና ባለማስተዋል የተዘለለ ድንገተኛ የቃል ስህተት መኖሩን ራሱ ያረጋገጠ እንደሆነ ወይም ከባለጉዳዮቹ አንዱ ሲያመለክት በቁጥር 207 የተነገረውን የስነስርአት ጉድለት የሚመለከት ጉዳይ ካልሆነ በቀር ፍ/ቤቱ ሊያርመው ይችላል በማለት ደንግጓል፡፡

የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 37303 (ቅጽ 8) የክርክር ዋነኛ ጭብጥ በሆነ ጉዳይ ላይ አከራክሮ የሰጠውን ውሳኔ ፍ/ቤት በድጋሚ "ስህተት ለማረም" በሚል ምክንያት ሊለውጥ ወይም ሊያሻሽል የማይችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 208ን መሰረት በማድረግ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡

አመልካች በሰበር አቤቱታው በስር ፍ/ቤት ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረበው ክስ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት ያቀረብነው መቃወሚያ ታልፎ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ሲል ያቀረበውን ክርክር በተመለከተ ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ እንዲረዳ ይህ የሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች እና ተጠሪ ክርክር ያደረጉበትን የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አዲስ ከተማ ምድብ 3ኛ ፍትሃብሄር ችሎት የመ.ቁ 97605 የሆነውን መዝገብ በትእዛዝ አስቀርቦ እንደመረመረው አመልካች በተጠሪ በ16/2/14ዓ.ም በተጻፈ የቀረበው ክስ በይርጋ ቀሪ ነው ሲል ያቀረበውን መቃወሚያ ፍ/ቤቱ መርምሮ አመልካች ለገንዘቡ መከፈል ምክንያት የሆነው ይዞታ ላይ መብት የተሰጠው በካቢኔ ውሳኔ በ2005ዓ.ም ስለመሆኑ እና በዚሁ ጉዳይ እስከሰበር ሰሚ ችሎት ክርክር ተደርጎ ውሳኔ የተሰጠው በ2009ዓ.ም ስለመሆኑ ተጠሪ በክርክሩ ማስረዳቱን እና ይህም በአመልካች አለመካዱን በፍሬነገር ደረጃ በማረጋገጥ ይህ ከሆነ ደግሞ ይርጋው

መታሰብ ሊጀምር የሚገባው አመልካች በይዞታው ላይ መብት ካገኘበት ግዜ ጀምሮ እንጂ ክፍያው ከተከፈለበት ግዜ ሊሆን ስለማይገባ እና በይዞታው ላይም ክርክር የነበራቸው መሆኑ የይርጋ ግዜውን የሚያቋርጠው በመሆኑ ክሱ በይርጋ አይታገድም በማለት መቃወሚያውን ውድቅ በማድረግ የሰጠውን ብይን ይህ የሰበር ሰሚ ችሎት የሚነቀፍ ሆኖ አላገኘውም፡፡

ፍሬጉዳዩን በተመለከተ የስር የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ በይግባኝ ያየው የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የስር ፍ/ቤት በደረሰኝ ቁጥር 923571 ተጠሪ በ13/1/12ዓ.ም የከፈለው ብር 1,068,390.16 (አንድ ሚሊዮን ስልሳ ስምንት ሺህ ሶስት መቶ ዘጠና ከ16/100) አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍለው መወሰኑ በአግባቡ ነው በማለት በዚህ ረገድ የስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ጸንቷል በማለት፤ አመልካች የዚህ ገንዘብ ህጋዊ ወለድ 9% የሚከፍልበት የህግ አግባብ የለም በማለት ወለድን በተመለከተ የስር ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር ውሳኔ ሰጥቶ መዝገቡን ከዘጋ በኂላ ብር 1,068,390.19 (አንድ ሚሊዮን ስልሳ ስምንት ሺህ ሶስት መቶ ዘጠና ከ19/100) ድርሻ ብር 436,667.86(አራት መቶ ሰላሳ ስድስት ሺህ ስድስት መቶ ስልሳ ሶስት ብር ከ86/100) ያለወለድ አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል ውሳኔ መስጠት ሲገባው በስህተት አመልካች ብር 1,068,390.19 (አንድ ሚሊዮን ስልሳ ስምንት ሺህ ሶስት መቶ ዘጠና ከ19/100) ለተጠሪ እንዲከፍል ተብሎ ስለተጻፈ ስህተቱ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 208 መሰረት እንዲታረምልኝ በማለት በአመልካች አቤቱታ ሲቀርብለት በፍርድ ሀተታው እና በውሳኔው የተመለከተውን ብር 1,068,390.19 (አንድ ሚሊዮን ስልሳ ስምንት ሺህ ሶስት መቶ ዘጠና ከ19/100) አመልካች ለተጠሪ ይክፈል ተብሎ መጻፉ ስህተት ስለሆነ አመልካች ብር 436,667.86(አራት መቶ ሰላሳ ስድስት ሺህ ስድስት መቶ ስልሳ ሶስት ብር ከ86/100) ለተጠሪ እንዲከፍል በማለት በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 208 መሰረት ትእዛዝ መስጠቱ ይህ የሰበር ሰሚ ችሎት ተገቢ ሆኖ አግኝቶታል፡፡ ሆኖም የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በውሳኔው ላይ አመልካች ለተጠሪ የዋናውን ገንዘብ ህጋዊ ወለድ 9% የሚከፍልበት የህግ አግባብ የለም በማለት በዚህ ረገድ የስር ፍ/ቤት አመልካች ለተጠሪ ከህዳር 20 ቀን 2005ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ 9% ህጋዊ ወለድ ጭምር እንዲከፍል የሰጠውን ውሳኔ በመሻር ውሳኔ ከሰጠ በኂላ በአመልካች በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 208 መሰረት የቀረበለትን የስህተት ይታረምልኝ አቤቱታ መነሻ በማድረግ የስር ፍ/ቤት አመልካች ለተጠሪ ከህዳር 20 ቀን 2005ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ 9% ህጋዊ ወለድ ጭምር እንዲከፍል በማለት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር የሰጠውን ውሳኔ በመሻር አመልካች ለተጠሪ ከህዳር 20 ቀን 2005ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ 9%ህጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፍል በማለት የሰጠውን የውሳኔ ክፍል ይህ የሰበር ሰሚ ችሎት በፌደራል ፍርድቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4)(ለ) እና(ሸ) እንዲሁም አንቀጽ 10(1)(ሀ) ከደነገጉት አንጻር መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝቶታል፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 288067 በ21/11/14ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

2. የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 288067 በ21/11/14ዓ.ም አመልካች ለተጠሪ ከህዳር 20 ቀን 2005ዓ.ም ጀምሮ የሚታሰብ ህጋዊ ወለድ 9% እንዲከፍል በማለት የሰጠው የትእዛዝ ክፍል በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
3. ከላይ በውሳኔው ክፍል በተራ ቁጥር 2 ከተጠቀሰው ነጥብ ውጪ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 288067 በ21/11/14ዓ.ም አመልካች ለተጠሪ ብር 436,667.86(አራት መቶ ሰላሳ ስድስት ሺህ ስድስት መቶ ስልሳ ሶስት ብር ከ86/100) እንዲከፍል በማለት የሰጠው የትእዛዝ ክፍል በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
4. በዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሳራ አመልካች እና ተጠሪ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
5. የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይድረስ፡፡
6. በዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት ትእዛዝ የቀረበው የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አዲስ ከተማ ምድብ 3ኛ ፍትሃብሄር ችሎት የመ.ቁ 97605 የሆነውን መዝገብ በመጣበት አኳኋን ለፍርድቤቱ ይመለስ፡፡
7. መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/ተ

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ.መ.ቁ 234012

ቀን ጥቅምት 5 2016ዓ.ም

ዳኞች፡ እትመት አሰፋ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

አመልካች፡ የንፋስ ስልክ ላ/ክ/ከተማ ወረዳ 6 ቤቶች አስተዳደር

ተጠሪ፡ ወ/ሮ ጎፉ ታምሬ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ የቀረበው አመልካች የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ንፋስስልክ ላፍቶ ምድብ በኮ.መ.ቁ 162704 በ21/6/14ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 291544 በ14/10/14ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት በ2/13/14ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ ስላቀረበ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ተጠሪ በስር የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በአመልካች(ስር 1ኛ ተከሳሽ) እና አሁን የሰበር ክርክሩ ላይ በሌሉት ወ/ሮ አያልነሽ ተካ(ስር 2ኛ ተከሳሽ) ላይ ባቀረቡት ክስ የአባቴ አቶ ታምሬ ቅጣው ህጋዊ ወራሽ

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ስሆን አባቴ በን/ስ/ላ/ክ/ከተማ ወረዳ 6 አስተዳደር ስር የሚገኝ የቤ.ቁ 411 እና 418 በሆነው ቤት እንዲኖርበት ተፈቅዶለት የነበረ ሲሆን የቤ.ቁ 418 በህገወጥ መንገድ ለ3ኛ ወገን ወረዳ አስተዳደሩ በማከራየቱ እንዲመለስለት ጥረት ቢያደርግም ቤቱ ሳይመለስ አባቴ ሞቷል፡፡ ሟች አባቴ አዋጅ ቁጥር 47/67 ከመውጣቱ በፊት የቦታው ስፋት 1000ካ.ሜ በሚሆንበት ቦታ ላይ 17 ክፍል ቤቶችን ሰርቶ ይኖር ነበር፡፡ በወቅቱ የነበረው መንግስት በአዋጅ ቁጥር 47/67 የከተማ ትርፍቤትና መሬትን ሲወርስ ለመኖሪያ የሚሆነውን ቤት እንዲመርጥ ተደርጎ የቤ.ቁ 411 እና 418ን መርጧል፡፡ በወቅቱ የነበረው አስተዳደር የአባቴን የቤተሰብ ብዛት ታሳቢ በማድረግ የቤ.ቁ 411 እና 418 የግሉ ቤት እንዲሆን በመተው ሌሎች ቤቶችን ወርሷል፡፡ በዚሁ መሰረት አባቴ ከነበሩት 17 ክፍል ቤቶች ሁለቱ ክፍል ይኸውም የቤ.ቁ 411 እና 418 ያልተወረሱ ቤቶች እንዲመለሱ በተለያየ ግዜ አስተዳደሩን ሲጠይቅ ቆይቷል፡፡ አመልካች (ስር 1ኛ ተከሳሽ) ህገወጥ በሆነ ሁኔታ ያልተወረሰውን የማያስተዳድረውን ቤት ለስር 2ኛ ተከሳሽ ልጅ ለወ/ሮ ዝናሽ አዳነ በማከራየት በህገወጥ መንገድ የኪራይ ገንዘብ ይሰበስባል፡፡ የቤ.ቁ 418 የሆነው ቤት በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሰረት ያልተወረሰ ቤት ስለሆነ ይህን ቤት አመልካች እና የስር 2ኛ ተከሳሽ እንዲያስረክቡኝ እንዲወሰንልኝ እንዲሁም ቤቱን አላግባብ በማከራየት የሰበሰቡትን ገንዘብ ለተጠሪ እንዲሰጡ እንዲወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ማስረጃዎችንም አቅርበዋል፡፡

አመልካች እና የስር 2ኛ ተከሳሽ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለውም በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርበው ፍ/ቤቱም ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለኝም በማለት በብይን መዝገቡን በመዝጋቱ ጉዳዩ በይግባኝ ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ቀርቦ ፍ/ቤቱም የስር ፍ/ቤትን ብይን በመሻር የስር ፍ/ቤቱ ጉዳዩን የማየት ስልጣን አለው በማለት ጉዳዩን ወደስር ፍ/ቤት መልሷል፡፡ በዚሁ መሰረት አመልካች (ስር 1ኛ ተከሳሽ) በፍሬጉዳዩ ላይ ባቀረበው መልስ የተጠሪ አባት በህይወት እያሉ አለአግባብ የተወሰደ ቤት ነው በማለት ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡ ተጠሪ ከቤቱ የተሰበሰበው ገንዘብ እንዲመለስላቸው የጠየቁትን በተመለከተ የሚመለስ ገንዘብ የለም በማለት ተከራክሯል፡፡ ስር 2ኛ ተከሳሽም በፍሬጉዳዩ ላይ ባቀረቡት መልስ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን የቤ.ቁ 418 የሆነውን ቤት ከአመልካች(ስር 1ኛ ተከሳሽ) ተከራይተው የሚገለገሉበት ቤት መሆኑን በመግለጽ ተከራክረዋል፡፡

ፍርድቤቱም በን/ስ/ላ/ክ/ከተማ ወረዳ 5 የቤ.ቁ 418 የሆነው ቤት ላይ ህጋዊ መብት ያለው ማነው የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምሮ የቤ.ቁ 411 እና 418 የተጠሪ አውራሽ የሆኑት ሟች አቶ ታምሬ ቅጣው የምርጫ ቤት መሆኑ በቅጽ 004 ላይ የተገለጸ ስለመሆኑ ተጠሪ ካቀረቡት ማስረጃ የተረጋገጠ ከመሆኑም በላይ አመልካችም ሆነ የስር 2ኛ ተከሳሽ ይህን በማስተባበል የተከራከሩበት ሁኔታ ባለመኖሩ ለክርክሩ መነሻ የሆነው የቤ.ቁ 418 የሆነው ቤት የሟች አቶ ታምሬ ቅጣው የምርጫ ቤት ስለሆነ ቤቱ ላይ ህጋዊ መብት ያላቸው ተጠሪ ናቸው፡፡ ተጠሪ ከቤቱ ላይ አመልካች ለስር 2ኛ ተከሳሽ በማከራየት የቤት ኪራይ ስለሰበሰበ ይህን የቤት ኪራይ ለተጠሪ እንዲከፍል እንዲወሰንልኝ ሲሉ የጠየቁትን ዳኝነት በተመለከተ አመልካች ለስር 2ኛ ተከሳሽ በምን ያህል ገንዘብ በማከራየት ገንዘብ እንደሰበሰበ ተጠሪ ያላስረዱ በመሆኑ በማለት በዚህ ረገድ ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ ውድቅ በማድረግ በንፋስልክ ላፍቶ ክ/ከተማ የሚገኘውን ስር 2ኛ ተከሳሽ

ከአመልካች(ስር 1ኛ ተከሳሽ) ተከራይተው የያዙት ቤት የተጠሪ ወላጅ አባት ቤታቸው በመንግስት በአዋጅ ቁጥር 47/67 ሲወረስ ለተጠሪ አባት የምርጫ ቤታቸው ተደርጎ የተሰጠ ቤት ስለሆነ አመልካች እና የስር 2ኛ ተከሳሽ ቤቱን ለተጠሪ እንዲያስረክቡ በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች ከላይ በተገለጸው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቦ ፍ/ቤቱም የአመልካችን መልስ ተቀብሎ ጉዳዩን በመመርመር ተጠሪ በስር ፍ/ቤት በመሰረቱት ክስ የቤ.ቁ 418 በአዋጅ ቁጥር 47/67 ያልተወረሰ መሆኑን፤ ይልቁንም ቤቱን አቶ ታምሬ ቅጣው የምርጫ ቤታቸው አድርገው ያስቀሩ መሆኑን ለዚህም እንደማስረጃ ቤቱን በምርጫ ቤትነት ያስቀሩ ስለመሆኑ ያስረዳልኛል ያሉትን ቅጽ 004 ያቀረቡ ሲሆን አመልካች በበኩሉ ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 47/67 ተወርሷል ቢልም ስለመወረሱ የሚያስረዳውን ቅጽ 000 አላቀረበም፡፡ የስር ፍ/ቤትም ለን/ስ/ላ/ክ/ከተማ ወረዳ 06 ቤቶች አስተዳደር በሰጠው ትእዛዝ ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 47/67 የተወረሰ ስለመሆኑ አጣርቶ እንዲገልጽ በጠየቀው መሰረት ወረዳው በ10/2/14ዓ.ም እና በ23/2/14ዓ.ም በተጻፈ በላከው ምላሽ በአዋጅ ቁጥር 47/67 ቤቶች የሚወረሱበትን ቅጽ 000 ማግኘት አለመቻሉን ገልጿል፡፡

የስር ፍ/ቤትም አመልካች ቤቱ በመንግስት የተወረሰ ስለመሆኑ በማስረጃ አለማረጋገጡን፤ ተጠሪ ግን ቤቱ ለአባታቸው በምርጫ ቤትነት የቀረ ስለመሆኑ ቅጽ 004 የሆነውን በማቅረብ በተሻለ ሁኔታ ቤቱ በመንግስት ያልተወረሰ መሆኑን በማስረዳታቸው የስር ፍ/ቤቱ የቤ.ቁ 418 የሆነውን ቤት አመልካች ለተጠሪ እንዲያስረክብ መወሰኑ አግባብ ነው በማለት የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ከላይ የተገለጹትን ውሳኔዎች በመቃወም ሲሆን ይዘቱም የስር ፍ/ቤት ከአስተዳደር አካል ስለመምጣቱ ያልተረጋገጠ፤ አጠራጣሪ እና በተጠሪ እጅ ብቻ የሚገኝ የተባለ ቅጽ 004 የተባለ የሰነድ ማስረጃን እንደበቂ በመቁጠር ይህን ቅጽ በተመለከተ በቂ ማጣራት ሳያደርግ እና በአዋጅ የተወረሰን እና ከአርባ አመት በላይ መንግስት ሲያስተዳደረው የነበረውን ቤት ለተጠሪ በምርጫ የተተወላቸው ቤት ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የማስረጃ ምዘና ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ እንዲሻር፡፡ ተጠሪ ክስ ያቀረቡበት ለክርክሩ መነሻ የሆነው ይዞታ ላይ በግዜው በነበረው መንግስት የተሰጠ የይዞታ ማረጋገጫ የሌለው፤ በአዋጅ ቁጥር 47/67 ያልተወረሰ ስለመሆኑ ደጋፊ ማስረጃዎች ያልቀረበበት፤ በዚህ ሁሉ አመታት ተጠሪ አላግባብ ከአዋጁ ውጪ ተወስዶብኛል ሲል ለሚመለከተው የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ አቅርበው ውሳኔ አግኝተው ባለመብት መሆናቸውን ባላረጋገጡበት የስር ፍ/ቤቱ አስተዳደሩ ቤቱን ለተጠሪ እንዲያስረክብ የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባዋል፡፡

የስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ለረጅም ግዜ በመንግስት በኪራይ ሲተዳደሩ የነበሩ ቤቶችን በሚመለከት በተለያዩ መዝገቦች ከሰጠው የህግ ትርጉም ጋር የሚጻረር ውሳኔ በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ነው፡፡ ተጠሪ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሰረት

ለሳቸው እንዲሆን የተፈቀደላቸው መሆኑን ወይም ከአዋጅ ውጪ ተወስዶብናል የሚሉ ከሆነም እንዲመለስላቸው የአዋጅ ቁጥር 110/87 እና አዋጅ ቁጥር 572/2000 በሚደነግገው አግባብ ሳያስወስኑ ለረጅም አመታት በመንግስት ይዞታ ስር የነበረን ቤት እንዲመለስላቸው ቀጥታ ለመደበኛ ፍ/ቤት ማቅረብ እንደማይችሉ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 31682፣ 209196፣ 211464 አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 9 መሰረት ለፍርድ ቤቶች የስልጣን ጉዳይ በማናቸውም ግዜ ሊነሳ የሚችል ስለመሆኑ የደነገገ ሲሆን ይህን ድንጋጌ በተመለከተም የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በተደጋጋሚ ግዜ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ ስለሆነም የስር ፍ/ቤቶች የስረነገር ስልጣን ሳይኖራቸው ቤትና ይዞታው ለተጠሪ ይመለስ በማለት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ነው፡፡ ስለሆነም የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ እንዲሻር የሚል ነው፡፡

ይህ አቤቱታው በሰበር አጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ ለክርክር ምክንያት የሆነው ቤት ለረጅም ጊዜ በከተማ አስተዳደር በኪራይ ሲተዳደር ያለ መሆኑ ተረጋግጦ ባለበት ሁኔታ የተጠሪ ቤት ነው፣ አመልካች ይልቀቅ ተብሎ የተወሰነበትን አግባብ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 455161፣48699፣ 31682 እና ተያያዥ ጉዳዮች በሰጠው የህግ ትርጉሞች ጋር በማገናዘብ ለማጣራት ለሰበር ችሎቱ ይቅረብ ተብሎ በ21/3/15ዓ.ም በመታዘዙ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎ ተጠሪ በ24/4/15ዓ.ም በተጻፈ ባቀረቡት መልስ የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት አልተፈጸመበትም የሚሉበትን ምክንያት በመዘርዘር እንዲጸና፣ ወጪና ኪሳራ እንዲከፈላቸው እንዲወሰንላቸው ጠይቀዋል፡፡ አመልካች በ13/7/15ዓ.ም በተጻፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ይህ የሰበር ሰሚ ችሎትም የአመልካችን የሰበር አቤቱታ አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከተገቢዎቹ የህግ ድጋጌዎች አንጻር የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

የፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በኢፌዲሪ ሕገመንግስት አንቀጽ 80(3) ሆነ በፌደራል ፍርድቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10 ላይ በመጨረሻ ውሳኔ ላይ በተፈጸመ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት እንጂ ማስረጃው ተመዝኖ የተደረሰበትን የፍሬነገር ድምዳሜ ላይ እንዲመለከት ስልጣን አልተሰጠውም፡፡ ነገር ግን ማስረጃን ለመመዘን ስልጣን የተሰጠው ፍርድቤት ማስረጃ ሲቀበል የተከራካሪዎችን እኩል የመደመጥ መብት ካላከበረ፣ የማስረዳት ሸክም (burden of production) የማን ነው የሚለውን ካልለየ፣ የማስረጃ ተቀባይነትና ተገቢነት ላይ መከተል የሚገባውን ስርአት ካልተከተለ፣ በምዘና ግዜ የሁሉንም ተከራካሪዎች ማስረጃ አብሮ ካልመዘነ፣ የተለየ የማስረዳት ደረጃ(standard of proof) የሚጠይቁ ጉዳዮችን በሚጠይቀው ደረጃ ልክ መረጋገጡን ካላሳየ እና በመሰረታዊ ህግ ሆነ በስነስርአት ህግ ያሉትን የማስረጃ ህጎችና መርሆዎች ካላከበረ ጉዳዩ የማስረጃ ምዘና ሳይሆን የህግ አተረጓጎም ስህተትና ፍርድቤት ያለበትን ሀላፊነት አለመወጣት ስለሚሆን ሰበር ሰሚ ችሎቱ የሚመለከተው ጉዳይ ስለመሆኑ በሰ.መ.ቁ 172206 እና በርካታ መዝገቦች ላይ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡

በያዝነው ጉዳይ ተጠሪዋ በስር የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በአመልካች እና ስር 2ኛ ተከሳሽ ላይ ባቀረቡት ክስ ወላጅ አባቴ ሟች አቶ ታምሬ ቅጣው ቤታቸው በመንግስት በአዋጅ ቁጥር 47/67 ሲወረስ የምርጫ ቤት ተደርጎ የተሰጣቸው እና በአዋጅ ቁጥር 47/67 ያልተወረሰው በን/ስ/ላ/ክ/ከተማ ወረዳ 6 አስተዳደር ስር የሚገኘው የቤ.ቁ 418 የሆነውን ቤት አመልካች እና ስር 2ኛ ተከሳሽ እንዲያስረክቡኝ እንዲሁም ከቤቱ የተሰበሰበው የኪራይ ገንዘብ ለተጠሪ እንዲከፈለኝ እንዲወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ፍሬነገርን በማስረጃ የማጣራት በህግ ስልጣን የተሰጠው የስር ፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ለክርክሩ መነሻ የሆነው የቤ.ቁ 418 የሆነው ቤት የተጠሪ ወላጅ አባት ሟች አቶ ታምሬ ቅጣው የምርጫ ቤት ስለመሆኑ ተጠሪ በሰነድ ማስረጃነት ያቀረቡት ቅጽ 004 ላይ የተገለጸ መሆኑን እና ይህን አመልካችም ሆነ የስር 2ኛ ተከሳሽ አለማስተባበላቸውን በፍሬነገር ደረጃ በማረጋገጥ አመልካች እና የስር 2ኛ ተከሳሽ የቤ.ቁ 418 የሆነውን ቤት ለተጠሪ እንዲያስረክቡ በማለት የሰጠው ውሳኔ እና ይህንኑ ውሳኔ ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በማጽናት የሰጠውን ውሳኔ ይህ የሰበር ሰሚ ችሎት የፌደራል ፍርድቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4)(ሀ-ሸ) እና አንቀጽ 10(1)(ሀ) ከደነገጉት አንጻር መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አላገኘውም፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ንፋስስልክ ላፍቶ ምድብ በኮ.መ.ቁ 162704 በ21/6/14ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 291544 በ14/10/14ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ጸንተዋል፡፡
2. በዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሳራ አመልካች እና ተጠሪ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
3. በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 184000 የተጀመረው አፈጻጸም ታግዶ እንዲቆይ በዚህ የሰበር ችሎት መዝገብ በ17/4/15ዓ.ም የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ ለፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ይጻፍ፡፡
4. መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ማ/ተ

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ.መ.ቁ 234010

ቀን ጥቅምት 7 2016ዓ.ም

ዳኞች፡ እትመት አሰፋ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

አመልካች፡ ወ/ሮ አዲሴ ድልቦ -ጠበቃ ከበደ ወ/ጊወርጊስ ቀረበ

ተጠሪ፡ ወ/ሮ አዛለች ወጁ ወኪል ሁንዴ ኦሞሽ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ የቀረበው አመልካች የደቡብ ብሔር ብሔሮችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት የአሠራ ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ 21557 በ28/5/12ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ፤ የደቡብ ብሔር ብሔሮችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት የዳውሮ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 13925 በ14/4/13ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ፤ የደቡብ ብሔር ብሔሮችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ወላይታ ምድብ ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 34910 በ25/9/13ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የደቡብ ብሔር ብሔሮችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 36395 በ8/2/14ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት በ30/12/14ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ ስላቀረቡ ነው፡፡

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የጉዳዩ አመጣጥ ተጠሪ በስር የአሰራ ወረዳ ፍ/ቤት በአመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ አመልካች በአሰራ ወረዳ አጋራ ቀበሌ ያለውን እና በላዩ ላይ ካለው አትክልት ጋር መሬት በአደራ ለተጠሪ የሰጠኒትን ትመልስልኝ በማለት ክስ አቅርባብኝ ተጠሪም አመልካች መሬቱን ሸጣልኛለች በማለት ተከራክሬ በጉዳዩ ላይ እስከ ክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ድረስ ተከራክረን መሬቱ ለአመልካች እንዲመለስ ሆኖም በመሬቱ ላይ ያለውን የአትክልት ግምቱን አመልካች ለተጠሪ እንድትከፍል በማለት ለተጠሪ መብት በመጠበቅ በሰጠው ውሳኔ መሰረት አይነታቸው፤ የዋጋ ግምታቸው እና የተወሰኑት ደግሞ ብዛታቸው በክሱ ውስጥ የተዘረዘሩትን በድምሩ የዋጋ ግምታቸው ብር 246,500.00 (ሁለት መቶ አርባ ስድስት ሺህ አምስት መቶ ብር) እንድትከፍለኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ማስረጃዎችንም አቅርበዋል፡፡

አመልካች ለክሱ መልስ ካቀረቡ በኂላ ፍ/ቤቱ ክሱን በመስማት ክርክር ባስነሳው ይዞታ ላይ ያለው ቋሚ እና ተንቀሳቃሽ ንብረቶች በባለሙያና ከፍ/ቤት ተወካይ ባለበት ከነግምታቸው ጭምር ተጣርቶ እንዲቀርብ በሰጠው ትእዛዝ መሰረት ከወረዳው የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ልማት ጽ/ቤት እና ከፍ/ቤት ተወካይ ምላሽ ከቀረበለት በኂላ ጉዳዩን መርምሮ ቋሚ ንብረት ከቆርቆሮ ክዳን ቤት እና ከሌሎች ተነሽ ካልሆኑ ንብረቶች ጭምር ግምቱ ብር 56,035.3፤ ክርክር ያስነሳው ይዞታ ወደነበረበት የተመለሰ በመሆኑ በይዞታው ጉዳይ አመልካች ከተጠሪ የወሰደችውን ብር 10,000.00(አስር ሺህ) ፤ የዳኝነት ብር 5346(አምስት ሺህ ሶስት መቶ አርባ ስድስት)፤ ተጠሪ በክሱ ምክንያት ያወጣችውን ወጪ እና ኪሳራ ብር 3,000.00(ሶስት ሺህ) በድምሩ ብር 76,381.3(ሰባ ስድስት ሺህ ሶስት መቶ ሰማንያ አንድ ብር ከሶስት ሳንቲም) አመልካች ለተጠሪ እንድትከፍል በማለት ወስኗል፡፡

ተጠሪ ከላይ በተገለጸው የክፍያ መጠን ውሳኔ ላይ ቅር በመሰኘት እንዲሁም አመልካችም ከላይ በተገለጸው ውሳኔ ቅር በመሰኘት በየራሳቸው በተለያዩ መዝገቦች የይግባኝ ቅሬታ ለዳውሮ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱም መዝገቦቹን በማጣመር መልስ ከተቀበለ በኂላ ቤቱን በተመለከተ የዳውሮ ዞን ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን መምሪያ ገምቶ እንዲያቀርብ እንዲሁም አትክልትን በተመለከተ የዳውሮ ዞን እርሻና ተፈጥሮ ሀብት ልማት መምሪያ ገምቶ እንዲያቀርብ ትእዛዝ ሰጥቶ የዳውሮ ዞን ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን መምሪያ ቁጥሩ እና ቀኑ በተገለጸ ለፍ/ቤቱ ባቀረበው ሪፖርት የቤቱ አጠቃላይ ግምት ብር 94,578.56 (ዘጠና አራት ሺህ አምስት መቶ ሰባ ስምንት ብር ከሀምሳ ስድስት ሳንቲም) መሆኑን የገለጸ ሲሆን የዳውሮ ዞን እርሻና ተፈጥሮ ሀብት ልማት መምሪያ ቁጥሩ እና ቀኑ በተገለጸ የአትክልት ግምት ብር 86,605.00 (ሰማንያ ስድስት ሺህ ስድስት መቶ አምስት ብር) መሆኑን ከገለጸ በኂላ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ የስር ፍ/ቤቱን ውሳኔ በማሻሻል አመልካች ለተጠሪ የቤቱ ግምት ብር 94,578.00 (ዘጠና አራት ሺህ አምስት መቶ ሰባ ስምንት ብር) እና የአትክልት ግምት ብር 86,605.00(ሰማንያ ስድስት ሺህ ስድስት መቶ አምስት ብር) በድምሩ ብር 181,183.56 (አንድ መቶ ሰማንያ አንድ ሺህ አንድ መቶ ሰማንያ ሶስት ብር ከሀምሳ ስድስት ሳንቲም) እንድትከፍል በማለት፤ የስር ፍ/ቤት በይዞታው ምክንያት የተወሰደውን ገንዘብ አመልካች ለተጠሪ እንድትመልስ በማለት የሰጠው ውሳኔ ከክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ውጪ ነው በማለት በመሻር፤ የስር ፍ/ቤት የግራቀኙን ውል በመጥቀስ ውሉን ያፈረሰችው አመልካች ለተጠሪ እንደትከፍል

የሰጠው ውሳኔ ከክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ውጪ በመሆኑ ነው በማለት በመሻር፤ የጠበቃ አበል 10% ብር 18,118.35(አስራ ስምንት ሺህ አንድ መቶ አስራ ስምንት ብር ከሰላሳ አምስት ሳንቲም) አመልካች ለተጠሪ እንድትከፍል በድምሩ አመልካች ለተጠሪ ብር 205,725.91(ሁለት መቶ አምስት ሺህ ሰባት መቶ ሀያ አምስት ብር ከዘጠና አንድ ሳንቲም) እንድትከፍል በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች ከላይ በተገለጸው የቤት እና የአትክልት ግምት እንዲሁም የጠበቃ አበል ክፍያን በተመለከተ በተሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለደቡብ ብሔር ብሔሮችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ወላይታ ምድብ ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው ፍ/ቤቱም የተጠሪን መልስ ተቀብሎ ጉዳዩን በመመርመር የፍ/ቤቱን ውሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ በዚሁ ላይ አመልካች የሰበር አቤቱታ ለደቡብ ብሔር ብሔሮችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ፍ/ቤቱም የተጠሪን መልስ ተቀብሎ ጉዳዩን መርምሮ የፍ/ቤቱን ውሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ከላይ የተገለጹትን ውሳኔዎች በመቃወም ሲሆን ይዘቱም የስር የወረዳው ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ በይግባኝ ያየው የዳውሮ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የንብረት እና የአትክልትን ግምት ተገምቶ እንዲቀርብ በሰጠው ትእዛዝ መሰረት ባለሙያዎች ሲሄዱ አመልካችም ሆንኩ ጠበቃዬ በሌለንበት ጉዳዩ ሳይነገር በድብቅ የተፈጸመ በመሆኑ እንዲሁም በስር ፍ/ቤት ትእዛዝ ተገምቶ በቀረበው መሰረት ግምቱ ከብር 70,000.00(ሰባ ሺህ) ወደ ብር 205,000.00(ሁለት መቶ አምስት ሺህ ብር) አድጎ እንድከፍል መወሰኑ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ እንዲሻርልኝ እንዲወሰንልኝ፡፡ በስር የወረዳው ፍ/ቤት በአመልካች የቤት እና የንብረት ግምትን በተመለከተ ለቀረበብኝ ክስ መልስ ስሰጥ ቤቱ የተሰራውና የተለያዩ አትክልቶች የተተከሉት ይዞታው ለአመልካች ከተመለሰልኝ በኋላ ነው በማለት ተከራክሬ ለዚሁ ክርክሬ ደግሞ ያቀረብኩትን ምስክሮቼን ሳይሰማ ውሳኔ መስጠቱ እና ይህንኑ በተመለከተም የይግባኝ ቅሬታዩን ለዳውሮ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀርብም ምስክሮቼ በወረዳው ፍ/ቤት እንዲሰሙ ውሳኔ ሊሰጥ ሲገባው ይህን ሳይፈጽም ውሳኔ መስጠቱ እና በዚሁ ላይ ያቀረብኩትን ቅሬታ ጉዳዩን በይግባኝ እና በሰበር ደረጃ ያዩት የክልሉ የበላይ ፍ/ቤቶች ውድቅ በማድረግ የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ እንዲሻር፤ ወጪና ኪሳራ እንዲከፈለኝ እንዲወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

ይህ አቤቱታቸው በሰበር አጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ ለክሱ ምክንያት የሆኑት አትክልቶች የተተከሉት የሽያጭ ውሉ በፍ/ቤት ፈርሶ ግራቀኙ ወደነበሩበት እንዲመለሱ ከተወሰነ በኋላ ነው በሚል በአመልካች ቀርቦ የነበረው መከራከሪያ በምስክሮች ሳይጣራ የታለፈበትን አግባብነት ለማጣራት ለሰበር ችሎቱ ይቅረብ ተብሎ በ28/4/15ዓ.ም በመታዘዙ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎ ተጠሪ በ6/6/15ዓ.ም በተጻፈ ባቀረቡት መልስ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ውድቅ ሊደረግ ይገባል የሚሉበትን ምክንያት በመዘርዘር ውድቅ እንዲደረግ እና ወጪና ኪሳራ እንዲከፈላቸው እንዲወሰንላቸው ጠይቀዋል፡፡ አመልካች በ5/7/15ዓ.ም በተጻፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

*ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

ይህ የሰበር ሰሚ ችሎትም የአመልካችን የሰበር አቤቱታ አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከተገቢዎቹ የህግ ድንጋጌዎች አንጻር የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 205075 የገጠር መሬት ሽያጭ ውል ህገወጥ በመሆኑ ውሉ ሲፈርስ የውሉን መፍረስ ተከትሎ ገዥው በመሬቱ ላይ ያለማቸውን ተክሎች ለማልማት ያወጣቸውን ወጪዎች (book value) እንዲተኩለት ማድረጉ ተገቢ እንደሆነ በ24/5/14ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡

በያዝነው ጉዳይ አመልካች እና ተጠሪ ቀድሞ በነበራቸው የመሬት ሽያጭ ውል ክርክር ጉዳዩ እስከ ክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ ደርሶ ፍ/ቤቱም መሬቱ ለአመልካች እንዲመለስ ሆኖም ለክርክሩ መነሻ የሆነውን የመሬት ይዞታ ላይ ያሉትን ንብረቶች ግምት አመልካች ለተጠሪ እንድትከፍል በማለት ለተጠሪ መብት በመጠበቅ በሰጠው ውሳኔ መሰረት ጉዳዩ በመጀመሪያ ደረጃ የቀረበለት የስር የወረዳው ፍ/ቤት የቤት እና የአትክልትን ዋጋ ግምት በተመለከተ የሰጠውን ውሳኔ በይግባኝ ያየው የዳውሮ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ለተጠሪ በጠበቀው መብት መሰረት አመልካች የቤት እና የአትክልት ግምት ትክፈል በማለት የሰጠውን ውሳኔ ይህ የሰበር ሰሚ ችሎት የሚነቀፍ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ሆኖም የስር የወረዳውን ፍ/ቤት ውሳኔ በይግባኝ ያየው የዳውሮ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት እና አትክልት ግምት በሚመለከታቸው አካላት ተገምቶ እንዲቀርብ በሰጠው ትእዛዝ መሰረት ተገምቶ የቀረበው የቤት እና የአትክልት ዋጋ የገበያ ዋጋ ግምት (market value) ስለመሆኑ ከቀረበው የዋጋ አገማመት ይህ የሰበር ሰሚ ችሎት ግንዛቤ ወስዷል፡፡ በመሆኑም የቤቱ እና የአትክልት ግምት ሊገመት የሚገባው ቤቱን ለመስራት እና አትክልቱን ለማልማት የወጣውን ወጪ (book value) መሰረት በማድረግ በመሆኑ የዳውሮ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የቤቱን እና የአትክልት የገበያ ዋጋ ግምት በሚመለከታቸው አካላት በማስገመት በቀረበለት ውጤት መሰረት የቤቱን አጠቃላይ ግምት ብር 94,578.56 (ዘጠና አራት ሺህ አምስት መቶ ሰባ ስምንት ብር ከሀምሳ ስድስት ሳንቲም) እና የአትክልት ግምት ብር 86,605.00(ሰማንያ ስድስት ሺህ ስድስት መቶ አምስት ብር) እንዲሁም የጠበቃ አበል ክፍያን በመደመር አመልካች ለተጠሪ ብር 205,725.91(ሁለት መቶ አምስት ሺህ ሰባት መቶ ሀያ አምስት ብር ከዘጠና አንድ ሳንቲም) እንድትከፍል በማለት የሰጠው ውሳኔ እና ይህንኑ ውሳኔ ጉዳዩን በይግባኝ እና በሰበር ደረጃ ያዩት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ሰሚ ችሎቶች በማጽናት የሰጡትን ውሳኔ ይህ የሰበር ሰሚ ችሎት የፌደራል ፍርድቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4)(ሽ) እንዲሁም አንቀጽ 10(1)(ሐ) ከደነገጉት አንጻር ሊታረም የሚገባው መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝቶታል፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

## ውሳኔ

ማ ስታወሻ፦ ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

1. የደቡብ ብሔር ብሔሮችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት የዳውሮ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 13925 በ14/4/13ዓ.ም አመልካች የቤት እና የአትክልት እንዲሁም የጠበቃ አበል በድምሩ ብር ብር 205,725.91(ሁለት መቶ አምስት ሺህ ሰባት መቶ ሀያ አምስት ብር ከዘጠና አንድ ሳንቲም) እንድትከፍል በማለት የሰጠው ውሳኔ እና ይህንኑ ውሳኔ የደቡብ ብሔር ብሔሮችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ወላይታ ምድብ ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 34910 በ25/9/13ዓ.ም እንዲሁም የደቡብ ብሔር ብሔሮችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 36395 በ8/2/14ዓ.ም በማጽናት የሰጡት ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተሻሽለዋል፡፡
2. የደቡብ ብሔር ብሔሮችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት የዳውሮ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የመ.ቁ 13925 የሆነውን መዝገብ አንቀሳቅሶ የዳውሮ ዞን ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን መምሪያ ቤቱን ለመስራት የወጣውን ወጪ (book value) ገምቶ እንዲያቀርብ እንዲሁም የዳውሮ ዞን እርሻና ተፈጥሮ ሀብት ልማት መምሪያ አትክልቱን ለማልማት የወጣውን ወጪ (book value) ገምቶ እንዲያቀርብ ትእዛዝ በመስጠት ከሁለቱ አካላት የሚቀርብለትን ምላሽ መርምሮ ተጠሪ ባቀረቡት የቤት እና አትክልት ዋጋ ግምት ይከፈለኝ የዳኝነት ጥያቄ ላይ እንዲሁም ከዚሁ ጋር ተያይዞ የጠበቃ አበልንም በተመለከተ ውሳኔ ሊሰጥ ይገባል በማለት ጉዳዩን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 343(1) መሰረት መልሰንለታል፡፡
3. አመልካች እና ተጠሪ በዚህ የሰበር ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
5. መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ማ/ተ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰበር መ/ቁ 233857

ጥቅምት 09 ቀን 2016 ዓ.ም

ዳኞች፡ ብርሃኑ አመነው

ረታ ቶሎሳ

በእውቀት በላይ

ቀነዓ ቂጣታ

ኑረዲን ከድር

አመልካች፡- አቶ ረዘነ አለም ወ/ጊዮርጊስ

ተጠሪዎች፡1ኛ/ ወ/ሮ ዋጋዬ ጉታ ገቢሳ

2ኛ/ አቶ አብዮት ሙለታ

3ኛ/ ወ/ሮ መቅደስ ግርማ

4ኛ/ ብርሃን ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

መዝገቡ ለዚህ ችሎት የቀረበው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 166366 በቀን 01/02/2014 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 277878 በቀን 14/10/2014 ዓ.ም ይግባኙን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 337 መሰረት በመሰረዙ ዉሳኔዉ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል በሰበር እንዲታረም አመልካች ባቀረቡት አቤቱታ መነሻ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ሲታይ በስር ፍ/ቤት ከሳሽ አመልካች ሲሆኑ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ተከሳሽ በመሆን እንዲሁም 3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች ጣልቃ ገብ በመሆን ተከራክረዋል፡፡አመልካች በቀን 06/12/2012 ዓ.ም ባቀረቡት ክስ በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 12 የቤት ቁጥር B41/40 የሆነውን ቤት በተመለከተ ለ1ኛ ተጠሪ በሰጠሁት ውክልና ያለፈቃዴ ቤቱን ለ2ኛ ተጠሪ በቀን 03/02/2010 ዓ.ም በተደረገ የሽያጭ ውል አስተላልፈዋል፤የሽያጭ ውል መደረጉንም በ06/11/2012 ዓ.ም የ1ኛ ተጠሪን ውክልና ለመሻር እና ቤቱ 5 ዓመት መሙላቱን ወይም አለመሙላቱን ለማጣራት ስሄድ ላውቅ ችያለሁ፤በመሆኑም የሽያጭ ውሉ የተደረገው 5 ዓመት ሳይሞላው በመሆኑና ከሽያጩም የተሰጠኝ ገንዘብ ስለሌለ የሽያጭ ውሉ ፈርሶ ቤቱን እንዲያስረክቡ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

1ኛ ተጠሪ ባቀረቡት መልስ አመልካች ቤቱን እንዳስተዳድርና መሸጥ መለወጥ እንድችል ውክልና ሰጥተውኛል፤ቤቱ የተሸጠው ግን አመልካች ከ2ኛ ተጠሪ ጋር የውል ድርድር ጨርሶ ፈርሚልኝ ብለኝ ነው፤አምስት ዓመት ሳይሞላው ለምን በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት ውሉ እንደተፈፀመ አላውቅም፤የሽያጩንም ገንዘብ ወስደዋል፤አሁን ውሉ ይፍረስ የሚለው የቤቱ ዋጋ ስለጨመረ የተሻለ ጥቅም ፍለጋ ነው፤አመልካች ቤቱን ለ2ኛ ተጠሪ ከሸጡላቸው በኋላ 2ኛ ተጠሪ ለ3ኛ ተጠሪ የሸጡላቸው ሲሆን 3ኛ ተጠሪ መልሰው ለ1ኛ ተጠሪ ቤቱን ሸጠውልኛል፡፡ይህ ሁሉ ሲደረግ አመልካች ያውቁ ነበር፤ የሽያጭ ውሉ ሲደረግ ቤቱ ከተላለፈላቸዉ አምስት ዓመት ባይሞላውም ክሱ የቀረበው አምስት ዓመት ከሞላ በኋላ ነው፤ ሌሎች ውሎች ፀንተው ባሉበትና 1ኛ ተጠሪ 3ኛ ተጠሪ ላይ እንደውሉ እንዲፈጽሙ በመ/ቁ166658 ክስ መስርቼ በሂደት ላይ ባለንበት ሁኔታ ውሉ ፈርሶ ወደነበርንበት መመለስ አንችልም በማለት ተከራክረዋል፡፡2ኛ ተጠሪ ባቀረቡት መልስ ቤቱን የገዛሁት ከአመልካች ጋር በቀን 02/02/2004 ዓ.ም በተደረገ ውል መሬት አስተዳደር ቀርቤ ያላገቡ እና እዳና እገዳ የሌለበት መሆኑን በማረጋገጥ የአመልካች ተወካይ ከሆኑት 1ኛ ተጠሪ የገዛሁ ሲሆን በቅን ልቦና የተደረገ ውል ነው፤ውል መደረጉንም አመልካች ያውቁ ነበር ቤቱን ከገዛሁ በኋላ በሽያጭ ወደ 3ኛ ወገን አስተላልፈዋለሁ፤ክፍያውንም ለአመልካች ተወካይ የከፈልኩ በመሆኑ ያልተቀበሉት ገንዘብ ካለ ተወካያቸውን ይጠይቁ፤ ገንዘብ አለመቀበላቸው ለውል መፍረስ ምክንያት ሊሆን አይችልም፤ቤቱን ለ3ኛ ተጠሪ በሽያጭ አስተላልፈዉ 3ኛ ተጠሪም ለ4ኛ ተጠሪ (ባንክ) በዋስትና ይዞ ገንዘብ አበድሯል በመሆኑም ክሱ ውድቅ እንድደረግ በማለት ተከራክረዋል፡፡

3ኛ ተጠሪ በስር ፍ/ቤት 1ኛ ጣልቃ ገብ በመሆን ባቀረቡት መልስ በአመልካች ስም ተመዝግቦ ይገኝ የነበረውን ቤት በፍ/ብ/ህ/ቁ 1723 መሰረት በቅን ልቦና ከአመልካች ተወካይ በብር 1,180,000 (አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ሰማኒያ ሺህ) ገዝቻለሁ ገንዘቡንም ከፍያለሁ አመልካች ገንዘቡን አለመቀበላቸው ውሉን አያፈርሰውም ቤቱ በስሜ የሚገኝ በመሆኑ የቤቱ ባለቤት እኔ እንጂ አመልካች አይደሉም በማለት ተከራክረዋል፡፡4ኛ ተጠሪ በስር ፍ/ቤት 2ኛ ጣልቃ ገብ በመሆን ባቀረበው መልስ ቤቱ አምስት ዓመት ሞልቶት እዳውም ተከፍሎ ማለቁን በማረጋገጥ 3ኛ ተጠሪ ገዝተውታል፤ውሉ የተደረገው በአመልካች ወኪል አማካይነት በመሆኑ የአመልካች አለማወቅ ውሉን ቀሪ አያደርገውም ቤቱ በ3ኛ ተጠሪ ስም የተመዘገበ መሆኑን አረጋግጬ በዋስትና በመያዝ ገንዘብ አበድሬአለሁ በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች ውድቅ በማድረግ በፍሬ ነገር ላይ ማስረጃ ሰምቶና አመዛዝኖ 2ኛ ቤቱን ተጠሪ ከአመልካች የገዙት ቤቱ አምስት ዓመት ሳይሞላው ስለሆነ ውሉ ህገ-ወጥ ውል በመሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1808(2) መሰረት ፈርሷል፡፡ነገር ግን 2ኛ ተጠሪ ቤቱን ለ3ኛ ተጠሪ የሸጡ በመሆኑና 3ኛ ተጠሪም ስመ ሀብት በስማቸው አዙረው ቤቱን አስይዘው ከ4ኛ ተጠሪ የተበደሩ በመሆኑ በአመልካች እና በ2ኛ ተጠሪ መካከል የተደረገው ውል ቢፈርስም በፍ/ብ/ህ/ቁ 1817 መሰረት ተዋዋዮች ወደ ነበሩበት ሊመለሱ ስለማይገባ እንዲሁም አመልካች በውሉ ምክንያት የደረሰበትን ጉዳት ባለመጠየቁ ተለዋጭ ማቻቻያ መስጠት አልተቻለም ሆኖም ወደ ነበሩበት መመለስ አይቻለም በማለት ወስኗል፡፡አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡ ቢሆንም ግራ ቀኙን በማከራከር የስር ፍ/ቤት ውሳኔን አጽንቶቷል፡፡አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘት በአጭሩ፡-የስር ፍ/ቤት ቤት ቤቱ የተሸጠዉ አምስት ዓመት ያልሞላው በመሆኑ ፈራሽ ነው እያለ ፍ/ብ/ህ/ቁ 1815 መሰረት በማድረግ ለተዋዋይ ወገኖች በቅን ልቦና መብት ተፈጥሮላቸዋል ሲል የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው፤በውሉ መሰረት 1ኛ ተጠሪ ለ2ኛ ተጠሪ 2ኛ ተጠሪ ለ3ኛ ተጠሪ የገዙበትን ገንዘብ በመመለስ ውሉን አፍርሶ ወደ ነበሩበት መመለስ ምንም ዓይነት አስቸጋሪ እና መሰናክል የማይፈጥር ሆኖ እያለ ሁለቱም ፍ/ቤቶች የፍ/ህ/ቁ 1817 ጠቅሰው አግባብነት የሌለው ውሳኔ መስጠታቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

ማ ሳታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የአመልካች አቤቱታ በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ በቀረበው ጉዳይ ሽያጭ የተፈፀመው አመስት ዓመት ያልሞላው ኮንደሚኒየም ቤት መሆኑ ተረጋግጦ የመጀመሪያው ውል ይፍረስ ተብሎ ተወሰነ ከመሆኑ አንፃር ተዋዋዮቹን ወደ ነበሩበት ለመመለስ የሚያሰናክል ነገር ስለመኖሩ የቀረበ ክርክር በሌለበት ወደነበሩበት ሊመለሱ አይቻልም ተብሎ በስር ፍ/ቤት የተወሰነበት አግባብ ከፍ/ብ/ህ/ቁ 1816 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች አንፃር ለመመርመር ሲባል መዝገቡ ለሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ታዟል፡፡1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች መልስ እንዲያቀርቡ ችሎቱ ቢያዝም ሊገኙ ባለመቻላቸው በጋዜጣ ጥሪ ተደርጎላቸው ባለመቅረባቸው መልስ የማቅረብ መብታቸው ታልፏል፡፡3ኛ ተጠሪ ባቀረቡት መልስ አመልካች የማስተዳር ዉክልና ሰጠሁ ይበሉ እንጂ በወቅቱ አመልካችና 1ኛ ተጠሪ ባደረጉት የገንዘብ ብድር ስምምነት ውል ቤቱን በመያዣ ሰጥተው ገንዘቡን በወቅቱ ባለመመለሳቸው 1ኛ ተጠሪ ቤቱን ወስደዋል፤ይህንንም በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ166658 በሆነው መዝገብ 1ኛ ተጠሪ ቤቱን መግዛታቸውን የመሰከሩበት ቃል ተመዝግቦ ይገኛል፤አመልካች ቤቱ ሲሸጥ ያውቁ ነበር፤ 3ኛ ተጠሪ ቤቱን ከ2ኛ ተጠሪ ስገዛ ተገቢውን ጥንቃቄ አድርጌ 5 ዓመት የሞላው መሆኑን አረጋግጬ በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ኤጀንሲ ቀርቤ ሰነዶች ተመርምረው የቤቱ ጠቅላላ ክፍያ ተከፍሎ መጠናቀቁን አጣርቼ የትዳር ሁኔታቸው ያላገቡ መሆናቸውን አረጋግጠው በቅን ልቦና የተፈፀመ ግዢ ነው ሰበር በመ/ቁ 142851 (በቅጽ 23) ትርጉም ሰጥቶበታል፤ አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ ቤቱ ሲሸጥ 5 ዓመት ሞልቶታል የሚል የሀሰት ሰነድ በማቅረባቸው ፖሊስ አጣርቶ ተጠያቂ ሆነዋል፤የቤቱ እጣ የወጣው በ1999 ዓ.ም ሲሆን ቤቱ በተሸጠ ጊዜ 11 ዓመት አልፎት ነበር፤ በስር ፍ/ቤት በአመልካች እና በ1ኛ ተጠሪ መካከል የተደረገው ውል ቢፈርስም በቅን ልቦና ከውል በመነጨ መብት ያገኘሁትን 3ኛ ተጠሪ አስመልክቶ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1816 እና 1817 በሚያዘው መሰረት ውሉ እንደረጋ እንዲቀር የተሰጠው ውሳኔ ህግን መሰረት ያደረገ በመሆኑ እንዲፀና በማለት ተከራክረዋል፡፡

4ኛ ተጠሪ ባቀረቡት መልስ የስር ፍ/ቤቶች የደረሱበት ድምዳሜ ውል በመሰረታዊነት ተፈፃሚ ሊደረግ የሚገባ መሆኑን እና የ3ኛ ወገኖችን መብት ለማስጠበቅ ፍርድ ቤቶች ህግን የመተርጎም ሚና በመሆኑ ውሳኔው የሚነቀፍ አይደለም፤ንብረቱ ለ3ኛ ተጠሪ በስማቸው የተዛወረ እንደመሆኑ መጠን 4ኛ ተጠሪ ባንክ በቅን ልቦና ንብረቱን በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሰረት ለሚመለከተው አካል በመያዣነት ያስመዘገበ እና ብድር የሰጠ በመሆኑ ተዋዋይ ወገኖች ወደነበሩበት ቢመለሱ 4ኛ ተጠሪ ባንክ ለብድር ክፍያ ማስፈፀሚያ የሚሆን መያዣ

የሚያጣ በመሆኑ የብድሩን አከፋፈል አዳጋች የሚያደርገው በመሆኑ ተዋዋይ ወገኖች ወደነበሩበት መመለሳቸው ከፍ ያለ መሰናክል ይፈጥራል በማለት የስር ፍ/ቤት መወሰኑ አግባብነት ያለው ውሳኔ በመሆኑ እንዲፀናልን በማለት ተከራክረዋል፡፡አመልካች ለ3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች ላቀረቡት መልስ የመልስ መልስ በማቅረብ የሰበር አቤቱታቸውን አጠናክረዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በአጭሩ ከላይ የተገለጸዉን የሚመስል ሲሆን እኛም አቤቱታ ከቀረበበት ዉሳኔ እና አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን መርምረናል፡፡እንደመረመርነዉ አቤቱታዉ ለሰበር ችሎት የቀረበዉ ሽያጭ የተፈፀመው አምስት ዓመት ያልሞላው ኮንደሚኒየም ቤት መሆኑ ተረጋግጦ የመጀመሪያው ውል ይፍረስ ተብሎ ተወሰነ ከመሆኑ አንፃር ተዋዋዮቹን ወደ ነበሩበት ለመመለስ የሚያሰናክል ነገር ስለመኖሩ የቀረበ ክርክር በሌለበት ወደነበሩበት ሊመለሱ አይቻልም ተብሎ በስር ፍ/ቤት የተወሰነበት አግባብ ከፍ/ብ/ህ/ቁ 1816 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች አንፃር ለመመርመር ተብሎ ነዉ፡፡

በመሰረቱ ዉል በተዋዋይ ወገኖች መካከል መብትና ግዴታ የሚፈጥረዉ እና በህግ አስገዳጅነት የሚኖረዉ ስለዉል አመሰራረት በህግ የተደነገጉትን ሁኔታዎች አሟልቶ የተደረገ ሲሆን ነዉ፡፡ይኸዉም ተዋዋዮቹ ለመዋዋል ችሎታ ያላቸዉ ሰዎች መሆኑን፣በነጻ ፈቃዳቸዉ ያደረጉት መሆኑን፣የዉለታዉ ጉዳይ የሚቻልና ህጋዊ የሆነ መሆኑን እና በህግ የተደነገገዉን የዉል አጻጻፍ ስርዓት(ፎርም) ያሟላ መሆን ይኖርበታል፡፡(የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1678 ይመለከቷል)፡፡በህጉ የተደነገገዉን የዉል አመሰራረት መስፈረትና ስርዓት አሟልቶ የተደረገ ዉል ህግ ሆኖ ተዋዋይ ወገኖችን የሚያስገድድ ስለመሆኑም የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1731(1) ድንጋጌ ይዘት ያሥገነዝባል፡፡ሆኖም ዉሉ ከጅምሩ የአመሰራረት ጉድለት አለበት ወይም በአፈጻጸም ሂደት በተከሰተ ሁኔታ ዉል እንዳይፈጸም ያደረገ እንደሆነ ከተዋዋዮቹ ወይም ጥቅም ያለዉ ሶስተኛ ወገን ዉሉ እንዲፈርስ ወይም እንዲሰረዝ ጥያቄ ሊነሳበት ይችላል፡፡ዉል የማፍረስ /invalidation/ መነሻ ምክንያቶች በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1808 ስር ተዘርዝረዋል፡፡እነዚህም ውል አመሠራረት ላይ የፈቃድ ጉድለት መኖር፣ ከተዋዋይ ወገኖች ችሎታ ማጣት፣ የውለታው ጉዳይ ህገወጥነት ወይም ኢሞራላዊነት ወይም የውሉ አቀራረጽ /ፎርም/ በህግ የተደነገገውን ሥርዓት አለመጠበቅ የሚሉ ናቸው፡፡ከእነዚህ ምክንያቶች በአንዱ ወይም በሌላው መነሻ ውሉ እንዲፈርስ ጥያቄ በማንና መቼ መቅረብ እንዳለበትም በህጉ ተመልክቷል፡፡የዳኝነት ጥያቄዉ ተቀባይነት አግኝቶ ዉሉ እንዲፈርስ ወይም እንዲሰረዝ ከተደረገ ዉጤቱ ዉለታዉን ለመፈጸም የተሰራዉ ስራ ሁሉ ቀሪ ሆኖ ተዋዋይ ወገኖች ዉለታ

ከመደረጉ በፊት እንደነበሩበት ሁኔታ እንዲመለሱ መደረግ እንደሚገባ ፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1815 ስር ተደንግጓል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ ለክርክር ምክንያት የሆነዉ የኮንደሚኒየም ቤት ሽያጭ ዉል ሲሆን የአመልካቹ ተወካይ የሆኑት 1ኛ ተጠሪ እና በ2ኛ ተጠሪ መካከል በቀን 03/02/2010ዓ.ም የተደረገዉ ዉል በህግ የተቀመጠዉ አምስት ዓመት ሳይሞላዉ ነዉ በሚል የስር ፍርድ ቤቶች ዉሉ እንዲፈርስ የሚል ድምዳሜ ላይ መድረሳቸዉን ተገንዝበናል፡፡የኮንደሚኒየም ቤት ማስተላፍ አስመልከቶ የወጣዉ አዋጅ ቁጥር 19/97 ላይ ባለመብቱ ቤቱን በሽያጭ ወይም በስጦታ የማስተላፍ መብት ላይ የጊዜ ገደብ ተደርጎበታል፡፡አዋጁ አንቀጽ 14(2) ላይ እንደተደነገገዉ ገዥ(ባለመብት) ዋጋዉን ከፍሎ ቢያጠናቅቅም ቤቱን ለሶስተኛ ወገን በሽያጭ ወይም በስጦታ ማስተላለፍ የሚችለዉ ቤቱን ከገዛ አምስት ዓመት ሲሞላዉ ብቻ ነዉ፡፡ጊዜዉም የሚቆጠር እጣዉ ከደረሰዉ ቀን ሳይሆን ቤት የደረሰዉ ሰዉ ከአስተዳደሩ ጋር ዉል ካደረገበት ቀን ጀምሮ ስለመሆኑ ሰበር ችሎቱ ገዥ ዉሳኔ የሰጠበት ጉዳይ ነዉ፡፡ (ሰበር መ/ቁ 65140 ቅጽ13፣መ/ቁ 158899 ቅጽ23 እና ሌሎች መዝገቦችን ይመለከቷል)፡፡ በመሆኑም ኮንደሚኒየም ቤት የደረሰዉ ገዥ (ባለመብት) በህግ የተቀመጠዉን ጊዜ ገደብ ሳይጠበቅ ቤቱን ለማስተላለፍ የሚያደርገዉ ዉል በህግ የተከለከለ እና ዉል ተደርጎም ቢሆን በህግ የተመለከተዉን ክልከላ በመተላለፉ ሊፈርስ የሚገባ መሆኑን ነዉ፡፡አመልካቹ ቤቱን ከአዲስ አበባ ቤቶች ልማትና ማስተላለፍ ኤጀንሲ በቀን 03/07/2007ዓ.ም በተደረገ ዉል ያገኙ ሆኖ እያለ በተወካያቸዉ (1ኛ ተጠሪ) አማካይነት ለ2ኛ ተጠሪ የሸጡት በቀን 03/02/2010ዓ.ም የሽያጭ ዉል ማስተላለፋቸዉ በህጉ የተቀመጠዉን አምስት ዓመት ጊዜ ገደብ የጣሰ በመሆኑ ዉሉ ሊፈርስ ይገባል መባሉ የሚነቀፍ አይደለም፡፡

ቀጥሎ የሚነሳዉ ጥያቄ ግራቀችን ከዉሉ በፊት ወደ ነበሩበት ቦታ መመለስ ይቻላል ወይስ አይቻልም የሚለዉ ነዉ፡፡በመሰረቱ ዉል እንዲፈርስ ወይም እንዲሰረዝ ሲደርግ በዉሉ ምክንያት የተሰሩት ስራዎች ቀሪ ሁነዉ ተዋዋይ ወገኖች ከዉሉ በፊት ወደ ነበሩበት ቦታ እንዲመለሱ ይደረጋል፡፡የፍ/ብ/ህግ/ቁጥር 1815 ይህንኑ ያስገነዝባል፡፡ይህም ማለት ጉዳዩ የሽያጭ ዉል ሲሆን ገዥ የገዛዉን ነገር ለሻጭ ይመልሳል፤ሻጭም የተቀበለዉን ገንዘብ ለገዥ ይመልሳል ማለት ነዉ፡፡ይሁን እንጂ በሁለት መሰረታዊ ምክንያቾች ሲኖሩ በዉሉ ምክንያት የተሰራዉ ስራ ጸንቶ የሚቀርበት ሁኔታ ሊኖር እንደሚችል በህግ ተደንግጓል፡፡አንደኛዉ ምክንያት የሶስተኛ ወገን መብት ለመጠበቅ ሲባል(የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1816 የሚመለከት) ሲሆን በቅን ልቦና ለሆነ ሶስተኛ ወገን የተሰራዉ ስራ ዉጤት ጠቃሚ ከሆነ እንደረጋ እንዲቀር ሁለተኛዉ ምክንያት በፍ/ብ/ህግ

ቁጥር1817 ላይ እንደተመለከተዉ ዉለታዉን ለመፈጸም የተሰራዉን ስራ ለማፍረስ የማይቻል ሲሆን ወይም አስቸጋሪ ሆኖ ሲገኝ ወይም ከፍ ያለ መሰናክል የሚያመጣ ሲሆን እነዚህ የተሰሩ ስራዎች እንደረጉ እንዲቀሩ ይደረጋል፡፡ከሕጉ ድንጋጌ መገንዘብ የሚቻለው ውለታው (contract) እና ውሉን ለመፈፀም የተሰሩ ስራዎች (acts) የሚለያዩ መሆናቸው ነው፡፡ስለሆነም ውሉን በራሱ በአንድ በኩል፣ውሉን ለመፈፀም የተከናወኑ ተግባራትን በሌላ በኩል ለይቶ ማየት አስፈላጊ ነው፡፡ሰበር ችሎቱ በመ/ቁ/39336 ቅጽ 8 ላይ እንደታተመዉ የሰጠዉ ዉሳኔ ይህንኑ ያስገነዝባል፡፡ፍርድ ቤቶችም ዉል እንዲፈርስ ወይም እንዲሰረዝ ሲወስኑ ዉጤቱን በመወሰን ረገድ በህጉ የተደነገጉት ልዩ ሁኔታዎች ባገናዘበ እና የተሰሩ ስራዎችን በጥንቃቄ በመመርመር ሊሆን ይገባል፡፡

ከዚህ አኳያ ሲታይ የስር ፍርድ ቤት ዉሉ ተከትሎ የተሰሩ ስራዎችን በተለይም ሶተኛ ወገን የሆኑት የአሁኑ 3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች ያቋቋሙትን መብት መነሻ በማድረግ የተሰሩትን ስራዎች አፍርሶ ወደ ነበሩበት ሁኔታ ለመመለስ አስቸጋሪ መሆኑን በማረጋገጥ የተሰሩ ስራዎች እንደረጉ እንደቀሩ መወሰኑን መገንዘብ ተችሏል፡፡በተለይም 4ኛ ተጠሪ የቤቱ ስመ ሀብት በ3ኛ ተጠሪ የተመዘገበ እና ከእዳና እገዳ ነጻ መሆኑን ጉዳዩ ከሚመልከተዉ አስተዳደር አካል በማረጋገጥ ቤቱን (ዋስትና) መያዣ አድርጎ ለ3ኛ ተጠሪ ገንዘብ ብድር መስጠቱም የተረጋገጠ ፍሬነገር ከመሆኑ አኳያ ሶስተኛ ወገን ጥቅም ላይ የሚደርሰዉን ከፍ ያለ ጉዳት ለማስቀረት የሚያስችል ዉሳኔ በመሆኑን ያሣያል፡፡በዚህ ረገድ ሰበር ችሎቱ በተመሳሳይ ሁኔታ በመ/ቁ/ 41388 ቅጽ 8 ላይ እንደታተመዉ ባንኩ ያቋቋመዉ የመያዣ ዉል በቅን ልቦና አለመሆኑ ካልተገለጸ በቀር መያዣ ውል የሚፀና ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3051/1/ እና /2/ ድንጋጌዎች ምርኩዝ አድርጎ የሰጠዉ ዉሳኔ ይህንኑ የሚያጠናክር ነዉ፡፡ሰበር አጣሪ ችሎት በዚህ ረገድ ክርክር እንዳልቀረበ አድርጎ ጭብጥ መያዙ በስር ፍርድ ቤት ጣልቃ ገብ የሆኑት 3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች ያቀረቡትን ክርክር ያገናዘበ አይደለም፡፡

ሲጠቃለል በአመልካች ወኪል እና በ2ኛ ተጠሪ መካከል የተደረገዉ የኮንደሚንየም ቤት ሽያጭ ዉል በህግ የተመለከተዉን የጊዜ ገደብ ሳይጠብቅ የተደረገ ሽያጭ መሆኑን ተከትሎ ዉሉ እንዲፈርስ መወሰኑ ተገቢ ቢሆንም ዉሉ መፍረሱን ተከትሎ ወደ ነበሩበት መመልስ ይቻላል ወይስ አይቻልም የሚለዉን ነጥብ በተመለከተ በቅን ልቦና መብት ያቋቋሙትን 3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች ጥቅም ለማስጠበቅ ሲባል ስራዎቹ እንደረጉ እንዲቀር መወሰኑ ህጉን እና በክርክሩ ተረጋገጠ ፍሬነገር እንዲሁም ሰበር ችሎቱ በተለያዩ መዝገቦች የሰጠዉን ዉሳኔ ያገናዘበ ነዉ ከሚባል በስተቀር በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80/3/ሀ እና በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4) እና 10 ስር ለሰበር ችሎቱ ከተሰጠ ስልጣን ጋር

ተገናዝቦ ሲታይ በዉሳኔዉ ላይ በህግ አተገባበርም ሆነ አተረጓጎም ረገድ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚያስችል ምክንያት የለም ብለናል፡፡ በመሆኑም የሚከተለዉ ተወስኗል፡፡

**ዉሳኔ**

1ኛ/ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/166366 ላይ በቀን 01/02/2014ዓ.ም የሰጠዉን ፍርድ በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/277878 ላይ በቀን14/10/2014ዓ.ም የሰጠዉ ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሠረት ጸንቷል፡ ይጻፍ፡፡

2ኛ/ክርክሩ ያስከተለዉን ዉጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ በዳኞች እረፍት ጊዜ ተሰርቶ ዛሬ ጥቅምት 9 ቀን 2016 ዓ.ም ተነበበ

መዝገቡ ዉሳኔ ያገኘ ስለሆነ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/ተ

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰበር መዝገብ ቁጥር 233286

ጥቅምት 8 ቀን 2016 ዓ.ም

ዳኞች፡...

1. እትመት አሠፋ
2. ደጀኔ አያንሳ
3. ብርቅነሽ እሱባለው
4. ሀብታሙ እርቅይሁን
5. ብርሃኑ መንግስቱ

አመልካች፡- አቶ ንጉሴ አመሃ------------------------ አልቀረቡም

ተጠሪዎች፡-1ኛ. ወ/ሮ ትዕግስት አመሃ
2ኛ. አቶ አትናትዮስ አመሃ
3ኛ. ወ/ሮ ትዝታ አመሃ
4ኛ. ወ/ሮ መሰረት አመሃ
5ኛ. አቶ ኪዳኔ አመሃ
} አልቀረቡም

ለምርመራ የተቀጠረውን መዝገብ መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚው ችሎች በሰበር መዝገብ 394335 ግንቦት 23 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ለአመልካች የተደረገ ስጦታ ስለሌለ አከራካሪውን የውርስ ሃብት የሆነውን ይዞታ ግራ ቀኙ እኩል እንዲካፈሉ የሰጠው ውሳኔ ፣ ይህን ውሳኔ በመቃወም የቀረበውን የይግባኝ አቤቱታ በይግባኝ ሰሚው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመሰረዙ የተፈፀመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም በማለት ማጽናቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ በሰበር ሰሚ ችሎቱ ሊታረም ይገባል በማለት አመልካች ነሀሴ 19 ቀን 2014 ዓ.ም የሰበር አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ጉዳዩ የገጠር የእርሻ መሬት ክርክር የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሰሜን ሸዋ ዞን ደራ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በስር ፍርድ ቤት በተደረገው ክርክር ተጠሪዎች ከሳሾች ፣ አመልከች ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪዎች በደራ ወረዳ ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ ይዘት በአጭሩ፡- አመልካች ወንድማቸው መሆኑን ገልፀው ፣ ሟች እናታችን ወ/ሮ መብራት ንጉሴ እናትዋ ወ/ሮ ዘርፏ ክብረት ከዚህ አለም በሞት ሲለዩ የሟች እናቷን ይዞታ የውርስ ድሻዋን እንዲያካፍላት ወንድሟ አቶ ታደሰ ንጉሴን በዚሁ ፍርድ ቤት ከሳ ፍርድ ቤቱ ሟች እናታችን እና ወንድሟ አቶ ታደሰ ንጉሴ እኩል እንዲካፈሉ ወስኖ በአፈጻጸም እጇ ካስገባች በኋላ ሞታለች፡፡ አመልካች የእናታችን ተወካይ ስለነበረ ሊያካፍለን ፈቃደኛ በለመሆን ይዞ የሚገኘውን፡- 1ኛ) በወረ ሁላ ቀበሌ ደረባ በሚባል ቦታ የሚገኝ ስፋቱ 0.5694 የሆነ በምስራቅ አቶ ዘገዬ ልጃለም ፣ በምዕራብ ፣ በደቡብ እና በሰሜን በአቶ ታደሰ ንጉሴ የሚዋሰነውን የእርሻ ቦታ፤ 2ኛ) በዚሁ ቀበሌ በምስራቅ አቶ ዘገዬ ልጃለም ፣ በምዕራብ መብራት ንጉሴ ፣ በደቡብ መብራት ንጉሴ ፣ በሰሜን ታደሰ ንጉሴ የሚያዋስኑትን ስፋቱ 402.6 ሜትር የሖነውን ይዞታ ወራሽነታችን ተረጋግጦ የውርስ ድርሻንን እንዲያካፍለን ይወሰንልን በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን መዝገቡ ያመለክታል፡፡

አመልካችም ለክሱ በሰጡት መልስ ክርክር የቀረበበት መሬት ሁለት ቦታ ሳይሆን አንድ መሬት ነው፡፡ ተጠሪዎች የውርስ መሬት ይበሉ እንጂ ይህ መሬት በስጦታ ያገኘሁት ነው፡፡ ሌላ ገቢ የሌለኝ መሆኑ በቀበሌው አፈ - ጉባኤ ተረጋግጧል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ክሱ በተሰማ ጊዜ ተጠሪዎች ክርክር ያስነሳው መሬት ለአመልካች በስጦታ አለመተላለፉን ፣ የተደረገለት ስጦታም ትክክል አለመሆኑን ፣ መሬቱ አንዱ የመኖሪያ ቤት ግቢ ሲሆን ሌላኛው ደግሞ የእርሻ መሬት ሆኖ ተያይዞ ይገኛል፡፡ አመልካች ነጋዴ በመሆኑ የራሱ ገቢ ያለው ከመሆኑም በላይ ከአባቱ በውርስ ያገኘው አምስት ቦታዎችን እየተጠቀመ ነው፡፡ መሬቱ የእናታች በመሆኑ ለሁላችንም እኩል ልካፈ ይገባል በማለት የተከራከሩ ሲሆን ፤ አመልካች በበኩላቸው መሬቱ እናታችን በሕይወት እያለች ሰጥታኝ ስጦታውም ሥልጣን ባለው አካል የተመዘገበ ነው፡፡ ተጠሪዎች የራሳቸው ገቢ ስላላቸው በቅድሚያ የመውረስ መብት ይከበርልኝ የሚል ክርክር አቅርበዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ተገቢነው ያለውን ማጣራት አድርጎ መዝገቡን እንደመረመረው፡- በተደረገው ማጣራት ክርክር የቀረበበት ይዞታ አንድ ቦታ የሚገኝ መሆኑንና በአመልካች ስም ተመዝግቦ ያለ መሆኑን ፣ ይዞታውንም ከእናቱ በስጦታ ያገኘው እንደሆነ እና ሌላ ገቢ የሌለው መሆኑ ከደራ ወረዳ ገጠር መሬት አስተዳደር አጠቃቀም ጽ/ቤት እና ከቀበሌው አስተዳደር ጽ/ቤት ማስረጃ ስለቀረበ ህጉ ያስቀመጠውን መስፈርት ሁሉ አሟልቶ ለአመልካች የተሰጠውን ይዞታ ተጠሪዎች የውርስ ይዞታ ብለው መጠየቅ አይችሉም፡፡ ምንም እንኳን ግራ ቀኙ የእናታቸው ወ/ሮ መብራት ንጉሴ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ ቢሆኑም ተጠሪዎች አመልካች እንዲያካፍላቸው የጠየቁትን ይዞታ አመልካች በህጋዊ መንገድ በስጦታ ያገኘው በመሆኑ ተጠሪዎች ያቀረቡት ክስ ውድቅ ነው በማለት ወስኗል፡፡

ተጠሪዎች ይህንን ውሳኔ በመቃወም ባቀረቡት የይግባኝ አቤቱታ ጉዳዩን የተመለከተው የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የቀረበውን ቅሬታ እንደመረመረው፡- አመልካች ስጦታ ተሰጥቶኛል የሚለው ሐምሌ 18 ቀን 2010 ዓ.ም በተፃፈ የስጦታ ውል ነው፡፡ ለአመልካች በስጦታ ተላልፏል የተባለው ይዞታ ሟች የግራ ቀኙ እናት የእናቷን ውርስ ከወንድሟ ጋር ተከራክራ በአፈፃፀም መዝገብ ቁጥር 22485 ሚያዝያ 14 ቀን 2011 ዓ.ም እጇ የገባ መሆኑ ግራ ቀኙን ያከራካረ ጉዳይ አይደለም፡፡ አመልካች የተከራካሪዎቹ እናት ከእናቷ በውርስ ያገኘችውን ይዞታ ሐምሌ 18 ቀን 2010 ዓ.ም በተፃፈ የስጦታ ውል አስተላልፋልኛለች በማለት የሚያቀርበው ክርክር በመዝገቡ ውስጥ ካለው የሰነድ ማስረጃ ጋር ስለምጣረስ እውነትነት የለውም፡፡ በሌላ በኩል አመልካች ተሰጥቶኛ የሚለው ይዞታ አንድ ቦታ ብቻ ነው ያለው ቢልም ፤ የአፈፃፀም መዝገቡ ሁለት ቦታዎች በውርስ ለሟች ወ/ሮ መብራቴ ንጉሴ የደረሱ መሆኑን ያመለክታል፡፡ በአጠቃላይ አመልካች አከራካሪውን ይዞታ በስጦታ አገኘሁ የሚለው እናቱ የውርስ ድርሻዋን ተካፍላ በእጇ ሳታስገባ በመሆኑና ስጦታው ተሰጥቷል ቢባል እንኳን በሁለቱም ቦታ የሚገኙ ይዞታዎች ለአመልካች እንዳልተሰጡ በመዝገቡ ወስጥ ያሉ ማስረጃዎች ስለሚያመለክቱ ለአመልካች ሕጋዊ የስጦታ ውል አልተደረገም በማለት የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔን በመሻር በክሱ ላይ አዋሳኞቹ እና መጠኑ የተመከቱት ይዞታዎች የውርስ ሃብት በመሆኑ ግራ ቀኙ እኩል ሊካፈሉ ይገበል በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች በውሳኔው ባለመስማማት ያቀረቡት ይግባኝ በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት መሰረዙን ተከትሎ ጉዳዩ የተመለከተው የሰበር ሰሚው ችሎት አመልካች የተከራካሪዎቹ እናት ከእናቷ በውርስ ያገኘችውን ይዞታ በስጦታ ተላልፎልኛል የሚለው ሐምሌ 18 ቀን 2010 ዓ.ም መሆኑና ሟች የግራ ቀኙ እናት የእናቷን ውርስ ከወንድሟ ጋር ተከራክራ በአፈፃፀም እጇ የገባው ሚያዝያ 14 ቀን 2011 መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ ተረጋግጧል፡፡ ሟች የተከራካሪዎቹ እናት ከእናቷ በውርስ የምደርሳትን ይዞታ ከወንድሟ ጋር የነበረው ክርክር ውሳኔ አግኝቶ ድርሻዋ ተለይቶ በአፈፃፀም እጇ ከገባ በኋላ በክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ስጦታ ለሚገባው ሰው በስጦታ ውል ከምታስተላለፍ በቀር፤ በውሳኔ ሊደርሳት የምችለውን የይዞታ መጠንና አዋሳኞቹን ሳትለይ አስቀድማ ስጦታ ታደርጋለች ተብሎ አይገምትም፡፡ አድርጋ ከሆነም ሕጋዊ ውጤት የለውም፡፡ የውሉ

ይዘትም ሲታይ በስምምነቱ ላይ የተመለከተው ይዞታ መጠንና አዋሳኞቹ በአፈፃፀም ሂች እጅ ከገባው ለክርክሩ ምክንያት ከሆነው ይዞታ ጋር አንድ አለመሆኑ የስጦታ ውሉን እውነተኛነት ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ ነው፡፡ በሌላ በኩል ስምምነቱ ውል መዝጋቢው አካል ዘንድ መመዝገቡ ብቻውን ውሉን ሕጋዊ አያደርገውም፡፡ በአጠቃላይ ሕጋዊ የሖነ ውል የለም ተብሎ ለክርክሩ ምክንያት የሖነውን ይዞታ አመልካች እና ተጠሪዎች እኩል እንዲካፈሉ የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አልተፈፀመበትም በማለት የሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔን አጽንቷል፡፡

አመልካች ነሀሴ 19 ቀን 2014 ዓ.ም ጽፈው ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይህን ውሳኔ በመቃወም የቀረበ ሲሆን ይዘቱም፡- ተጠሪዎች በስር ወረዳ ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ አመልካች የእናታችንን የውርስ ሀብት ያከፍለን እንጅ እናታችን ንብረቱን የራሷ ሳታደርግ በስጦታ ማስተላለፏ አግባብ አይደለም የሚል ክርክር አላቀረቡም፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሥር ፍርድ ቤት ያልተነሳ ክርክርን መሠረት አድርጎ የደራ ወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔን መሻሩ የፍ.ሥ.ሥ.ቁ 329(1) ድንጋጌን ይቃረናል፡፡ እናቴ በስጦታ ያስተላለፈችልኝ ይዞታ አስቀድሞ በመዝገብ ቁጥር 16972 መጋቢት 7 ቀን 2010 ዓ.ም መብቷን በውሳኔ ያስከበረች ይዞታ በመሆኑ ፤ ለአፈፃፀም የበቃ መብት ውሳኔው መፈፀሙን ሳትጠብቅ በስጦታ እንዳታስተላልፍ የሚከለክላት ሕግ በሌለበት ውሳኔው አልተፈፀም በማለት ያልተነሳን ክርክር መሠረት አድርጎ የወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔ መሻሩ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነው፡፡ የተፈረደበት ሰው ፍርዱ በይግባኝ እስካልተቀየረ ድረስ የፍርድ ባለመብትነቱን የሚቀይር ነገር የለም፤ ክርክር የተነሳበት ይዞታ በተገቢው መንገድ ከእናቴ በስጦታ የተላለፈልኝ መሆኑ እና በስሜ ተመዝግቦ እንደሚገኝ ከሚመለከተው የመንግስት አካል ማረጋገጫ የቀረበ ሲሆን ተጠሪዎች ይህ ሕጋዊ ውል እንዲፈርስላቸው ያቀረቡት ዳኝነት ሳይኖር እና የስጦታ ውሉ ሊፈርስ የሚችልበት በሕጋዊ ምክንያት ሳይኖር የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው እና የሰበር ሰሚ ችሎቶች ሕጋዊነቱ ተረጋግጦ የተመዘገበውን ውል ዋጋ ማሳጣታቸው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነው በማለት ስህተቱ እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡

የሰበር አጣሪው ችሎት የአመልካችን የሰበር አቤቱታ መርምሮ ለክርርክሩ መነሻ የሆነው መሬት ላይ ስጦታ አድራጊ በፍርድ መብቷን አረጋግጣ በስረ ነገር ክርክሩ ላይ ውሳኔ ተሰጥቶ እያለ መሬቱ በአፈጻጸም እጇ አልገባም በሚል ምክንያት ስጦታው ውድቅ መደረጉ እና ሌሎች ተያያዥ ነገሮች መጣራት ያለበት በመሆኑ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ትዕዛዝ ተሰጥቶ ተጠሪዎች ተከታዩን መልስ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪዎች ታህሳስ 11 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጡት መልስ ይዘትም ባጭሩ፡- የዳራ ወረዳ ፍርድ ቤት ስጦታ ውሉን አስመልክቶ የተነሳውን ክርክር ማለፉን በመቃወም የቀረበውን ይግባኝ የተመለከተው የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የዳራ ወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔን ያሻሻለው ስጦታው ውሸት መሆኑን አጣርቶ እና የወረዳ ፍርድ ቤት የስጦታ ውሉን አስመልክቶ የቀረበውን ክርክር አልፎ የሰጠው

ውሳኔ ሕገ - ወጥ መሆኑን አረጋግጦ አመልካች መሬቱን እንዲያካፍለን ውሳኔ መስጠቱ ባልተነሳ ክርክር ላይ ተመስርቶ ነው የሚያሰኝ አይደለም፡፡ አመልካች ሟች እናታችን የስጦታ ውል ሰጥታኛለች የሚለው ሐምሌ 18 ቀን 2010 ዓ.ም ሲሆን ውሉ በወረዳው መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት የተመዘገበው ሐምሌ 15 ቀን 2010 ዓ.ም ስጦታው ከመደረጉ በፊት ነው፡፡ አመልካች እንደሚለው ውሉ ተደርጎ ብሆን ኖሮ መመዝገብ የነበረበት ከተደረገ በኋላ እንጅ ከመደረጉ በፊት አይደለም፡፡ አመልካች ሆን ብሎ ከወረዳው መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት ጋር በመመሳጠር እናታችን ያላደረገችውን የውሸት ውል በማድረግ እና በማስመዝገብ መሬት ተሰጥቶኛል በማለት እየተከራከረ ሲሆን ፣ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እናታችን ድርሻዋ መሆኑን ያላወቀችውን መሬት አዋሳኝ ጠቅሳ ስጦታ ማድረግ ስለማትችል የቀረበው የስጦታ ውል የውሸት መሆኑን ገልፆ ውሳኔ ሰጠ እንጅ ፣ በሰበር አቤቱታ ላይ እንደተመለከተው ያልተፈፀመ ፍርድ መብት አያጎናጽም በሚል አልወሰነም፡፡ እናታችን ውሳኔን በራሷ ስላስፈፀመች አመልካች በፍርድ ያገኘችውን መብት ሰጥታኛለች በማለት የሚያቀርበው ክርክር በሥር ፍርድ ቤት ያልተነሳ አዲስ ክርክር በመሆኑ ተቀባይነት የለውም፡፡ እናታች ፍርዱን ካስፈፀመች በኋላ ለአመልካች ያደረገች የስጦታ ውል የሌለ ሲሆን አመልካች በውሸት አዘጋጅቶ ያቀረበው ውል ተቀባይነት የለውም፡፡ እናታችን የስጦታ ውልን አድርጋለች ቢባል እንኳን ውሉ ላይ ተጽፎ ያለው አንድ ቦታ የሚገኝ መሬት ብቻ ሲሆን እናታችን ግን የፍርድ ባለመብት ሆና በአፈፃፀም እጇ የገቡ መሬቶች ሁለት ቦታ የሚገኙ ናቸው፡፡ አመልካች በውሸት ባዘጋጀው የስጦታ ውል ምንም መሬት ማግኘት የለበትም እንጅ ያግኝ ቢባል እንኳን ሊያገኝ የሚገባው በውሉ ላይ የተመለከተውን አንድ መሬት ብቻ ነው፡፡ ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች ለሰበር ቅሬታው ምክንያት የሆነው ውሳኔ ፀንቶ ወጪ እና ኪሳራ እንድወሰንላቸው ጠይቀዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከፊ ሲል የተመለከተው ሲሆን ችሎቱም ለሰበር አቤቱታው መሠረት የሆነው ውሳኔ መሠረታዊ ሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ አግባብነት ካለው የሕግ ድንጋጌ አንፃር እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 40 (2)ድንጋጌ መሠረት የግል ንብረት ማለት ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ ወይንም ንብረት የማፍራት መብት የተሰጣቸው ማህበራት በጉልበታቸው ፣ በመፍጠር ችሎታቸው ወይንም በካፒታላቸው ያፈሩት ንብረት መሆኑ ተደግጓል። በዚህ መልክ የተገኘ ባለሃብትነት በህግ ከተመለከቱት ሥርዓቶች ውጭ ልገደብ የማይችል የሕግ ጥበቃ የተደረገለት ሰፊ መብት እንደሆነ የፍትሐብሔ ሕግ ቁጥር 1204 ያስገነዝበናል። ባለሀብትነት በሕግ ወይንም ባለጉዳዮች በሚያደርጓቸው ሕጋዊያን ተግባሮች የሚተላለፍ ሲሆን የማይንቀሳቀሱ ንብረቶች ባለሀብትነት ሲተላለፍ በማይንቀሳቀስ ንብረት መዝገብ ማስመዝገብ አስፈላጊ መሆኑን የፍትሐብሔር ሕጉ ቁጥር 1184 እና 1185 ያስገነዝበናል። በዚህ መልክ ሀብትነቱ ለሌላ ሰው ስተላለፍ ሀብትነት ቀሪ እንደሚሆን ከፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 1189 ድንጋጌ መረዳት ይቻላል። የባለሀብትነት ምስክር ወረቀት የሚሰጠው በፍ/ሕ/ ሕግ ቁጥር 1553- 1636 ድንጋጌዎች መሠረት ነው። የማይንቀሳቀሱ ንብረቶች በኢኮኖሚ እንቅስቃሴ

ውስጥ ያላቸው ሚና ከፍተኛ በመሆኑ የባለሀብትነት መብቱ እና ሌሎች በነዚህ ንብረቶች ላይ መብትን የሚያቃቁሙ ሕጋዊያን ተግባሮች በጽሁፍ ሆኖ በማይንቀሳቀስ ንብረት መዝገብ ላይ ሰፍሮ የነዚህ መብቶች መኖር በተለየ ማስረጃ እንድረጋገጥ መደረጉ ሕጉ ለነዚህ ንብረቶች የተለየ ጥበቃ እደሚያደርግ ማሳያ ነው። የባለሀብትነት ምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው የንብረቱ ባለሃብት እንደሆነ እንደምቆጠር ከፍ/ሕ/ሕግ ቁጥር 1195 ድንጋጌ መረዳት ይቻላል። የፍ/ሕ/ ሕግ ቁጥር 1195 የሕግ ግምት ሊስተባበል የሚችል ስሆን በፍ/ሕ/ ሕግ ቁጥር 1196 ሥር የተመለከቱት ሁኔታዎች መኖራቸዉን በማንኛውም ማስረጃ በማረጋገጥ ሊስተባበል ይችላል።

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አዋጅ ቁጥር 1/1987 አንቀጽ 40(4) አርሶ አደሮች መሬት በነፃ የማግኘት እና ከመሬታቸው ያለመፈናቀል መብት እንዳላቸው ይደነግጋል። የገጠር መሬት የመጠቀም መብት በምርት ፣ በውርስ ወይንም በስጦታ ሊገኝ እንደሚችል የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጣቃቀም አዋጅ ቁጥር 130/1999 ቁጥር 5 እና 9 እንዲሁም አዋጁን ለማስፈፀም የወጣው ደንብ ቁጥር 130/1999 ቁጥር 3 ይደነግጋል፡፡ የገጠር መሬት በስጦታ የሚተላለፈው ለቤተሰብ አባል መሆኑን አዋጁ ቁጥር 5(5) እና 9(5) ፣ እንዲሁም መሬት የሌላቸው መሆኑ በቀበሌው ምክር ቤት ለተረጋገጠ የልጅ ልጅ መሆኑን ደንብ ቁጥር 151/2005 ቁጥር 10(2) (ሐ) ድንጋጌ ያመለክታል፡፡ "ሕጋዊ የመሬት ይዞታ" ማለት ሕጋዊ በሆነ ሁኔታ አግባብ ባለው አካል ለተጠቃሚዎች የተሰጠ መሬት ፣ ወይንም በውርስ ወይንም በስጦታ የተገኘ እንደሆነ በአዋጁ ቁጥር 2(3) ሥር ትርጉም ተሰጥቶበታል፡፡ ማንኛውም ሰው በሕግ ያልተሰጠውን መሬት ሲጠቀም ከተገኘ ያለምንም ቅደመ ሁኔታ የያዘውን መሬት እንዲለቅ እንደምገደድ እና ለፈፀመው ድርጊትም ተጠያቂ እንደምሆን ቁጥር 15(14) ያመለክታል፡፡ በሕጉ አግባብ የገጠር መሬት የመጠቀም መብት ያገኘው ሰውም በአዋጁ ቁጥር 16 የተዘረጋውን ሥርዓት ተከትሎ በሕግ አግባብ የይዞታ መብቱ ሊያስከብር ይችላል፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪዎች የጠየቁት ዳኝነት መገኛው ፣ አዋሳኞቹ እና ስፋቱ በክሱ ላይ የተመለከተውን መሬት ሟች እናታቸው የሟች እናቷን የውርስ ይዞታ ድርሻዋን እንዲያካፍላት ወንድሟ አቶ ታደሰ ንጉሴን ከሳ በፍርድ ካገኘችው የውርስ ይዞታ ድርሻቸውን እንዲያካፍላቸው ያቀረቡትን ክስ አመልካች ተጠሪዎች የውርስ ነው የሚሉት መሬት በስጦታ የተላለፈላቸው የግል ይዞታቸው እንጅ የውርስ ሀብት አይደለም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ክሱ በተሰማ ጊዜ ተጠሪዎች ክርክር ያስነሳው መሬት ለአመልካች በስጦታ አለመተላለፉን ፣ የተደረገለት ስጦታም ትክክል አለመሆኑን ስከራከሩ ፣ አመልካች በበኩላቸው መሬቱ እናታችን በሕይወት እያለች ሰጥታኝ ስጦታውም ሥልጣን ባለው አካል የተመዘገበ ነው የሚል ክርክር አቅርበዋል፡፡ ተጠሪዎች አከራካሪው ይዞታ የውርስ ስለሆነ አመልካች የውርስ ድርሻችንን ያከፍለን የሚል እንጅ ለአመልካች የተደረገው ሥጦታ እንዲፈርስ ያቀረቡት ክስ መኖሩን መዝገቡ አያመለክትም፡፡

የፍትሐ ብሔር ክርክር የሚመራው በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ መሆኑን የህጉ ቁጥር 1 ድንጋጌ ያስረዳል፡፡ የሥነ ሥርዓት ሕጉ ክስ ፣ የመከላከያ መልስ እና የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ የሚቀርብበትን ሥርዓት የዘረጋ ሲሆን ፍርድ ቤቶችም የቀረበላቸውን የፍትሐ ብሔር ክርክር የሥነ ሥርዓት ሕጉ በተዘረጋው አግባብ የመምራት ኃላፊነት አለባቸው፡፡

ውል የሚቋቋው በሕግ አግባብ ሆኖ በሕጉ የተመለከቱ መለኪያዎች አለመሟላት ውሉን አንድም ፈራሽ (voidable) አልያም ከነአካቴው ዋጋ አልባ (void) ሊያደርገው ይችላል፡፡ በፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 1808(1) ሥር የተመለከቱት ግድፈቶች ውሉን ፈራሽ (voidable) የሚያደርጉ ሲሆን ፣ በቁጥር 1808(2) ከተመለከቱት ግድፈቶች ውስጥ ውሉ የተደረገበት ጉዳይ ወይንም ምክንያት ከህግ ውጭ ከሆነ ፣ ወይንም ሕልናን የሚቃረን ሲሆን ውሉን ዋጋ አልባ (void) ሊያደርገው እንደምችል ከድንጋጌው ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡

የደራ ወረዳ ፍርድ ቤት አከራካሪው ይዞታ አመልከች ከእናቱ በስጦታ ያገኘው መሆኑን የሚያመለክት ማስረጃ ከደራ ወረዳ ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት እና ከቀበሌው አስተዳደር ጽ/ቤት ስለቀረበ ህጉ ያስቀመጠውን መስፈርት ሁሉ አሟልቶ ለአመልካች የተሰጠውንና በስሙ የተመዘገበውን መሬት ተጠሪዎች የውርስ ነው በማለት ሊጠይቁ አይችሉም በማለት ተጠሪዎች ያቀረቡትን ክስ ውድቅ በማድረግ የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ተጠሪዎች ባቀረቡት የይግባኝ አቤቱታ ጉዳዩን የተመለከተው የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ለአመልካች ሕጋዊ የስጦታ ውል አልተደረገም በማለት የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔን ሽሯል፡፡ በፍትሐ ብሔር ሕጉ 826(2) እና በሌሎች የውርስ ህጉ ድንጋጌዎች መሰረት ለወራሾች በውርስ ሊተላለፍ የሚችለው በሕግ ጥበቃ የተደረገለት የአውራሹ የሐነ የንብረት መብት መኖሩ ሲረጋገጥ ነው፡፡ አከራካሪው ይዞታ የውርስ ሳይሆን በስጦታ ለአመልካች የተላለፈ ለመሆኑ ከሚመለከተው አካል ማስረጃ ስለቀረበ ሟች በአከራካሪው ይዞታ ላይ የነበራቸው መብት ቀሪ ስለሆነ በውርስ ለተጠሪዎች ሊተላለፍ የሚችል አይደለም፡፡ ተጠሪዎች ያቀረቡት ክስ የውርስ ድርሻን የሚመከለት በመሆኑ የደራ ወረዳ ፍርድ ቤት አከራካሪው ይዞታ በስጦታ ለአመልካች የተላለፈ በመሆኑ እና የስጦታ ውሉ እንድፈርስ ዳኝነት ባልተጠየቀበት የስጦታ ውሉን ሕጋዊነት መርምሮ ውሳኔ መስጠት ሥነ ሥርዓታዊ ባለመሆኑ በተጠሪዎች የቀረቡትን ክስ ውድቅ ማድረጉ አግባብ ሆኖእያለ የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ሥልጣን ባየው ፍርድ ቤት ያልተነሳን አዲስ ክርክር መሠረት አድርጎ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን መሻሩ የፍ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ 329(1) ድንጋጌን ፣ እንዲሁም በሰበር መዝገብ ቁጥር 37762 (በቅጽ 8 እንደታተመው) የተሰጠውን አስገዳጅ ውሳኔ የሚቃረን ነው፡፡ ጉዳዩን ለሁለተኛ ጊዜ በቀረበ ይግባኝ እንደሁም በሰበር የተመለከቱት የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው እና ሰበር ሰሚ ችሎቶችም ውሳኔውን ማጽናታቸው ተገቢነት የለውም፡፡

ሲጠቃለል ለክራክሩ ምክንያት የሆነው መሬት ከግራ ቀኙ እናት ወ/ሮ መብራት ንጉሴ በተደረገ የስጦታ ውል ለአመልካች ተላልፎ በስሙ ተመዝግቦ የሚገኘውን ይዞታ የፀና የስጦታ ውል እያለ እና የውል

ማ ስታወሻ፦ ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ይፍረስልኝ ዳኝነት ባልቀረበበት አመልካች በሥጦታ ያገኙት መሬት የውርስ ሀብት ነው ተብሎ ለተጠሪዎች ድርሻቸውን እንዲካፍሉ መወሰኑ ፤ ጉዳዩን በይግባኝ እና በሰበር የተመለከቱት ፍርድ ቤቶችም ይህንኑ ውሳኔ ማጽናታቸው መሠረታዊ የሕግ ስህተት በመሆኑ ቀጣዩ ተወስኗል፡፡

**ውሳኔ**

1. የኦሮሚያ የጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሰሚው ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 394335 ግንቦት 23 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ እና ትዕዛዝ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ - ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 ቁጥር 9(1/ለ) መሠረት **ተሽሯል፡፡**
2. የደራ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 27022 ሰኔ 22 ቀን 2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ እና ትዕዛዝ በፍ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ. 348 (1) መሠረት **ፀንቷል፡፡**
3. የውል ይፍረስልኝ ጥያቄ ባልቀረበበት እና የፀና ውል እያለ በውል ለአመልካች ከተላለፈው ይዞታ ላይ ተጠሪዎች የውርስ ድርሻ የላቸውም በማለት ተወስኗል፡፡
4. ይህ ውሳኔ ለአመልካች በተደረገው የስጦታ ውል መብቴ ተነክቷል በሚል የሚቀርበውን ክስ የሚከለክል አይደለም፡፡
5. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የግላቸውን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ውሳኔ አግኝቶ ስለተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ማ/ተ

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ.መ.ቁ 233250

ጥቅምት 05 ቀን 2016 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** እትመት አሠፋ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

ሐብታሙ እርቅ ይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

አመልካቾች፡- 1. ወ/ሮ እኩልነት ተስፋዬ ከጠበቃ ራሄል ከፍያሌው ጋር ቀረቡ

2. አቶ ሐብታሙ አበበ--- ቀረቡ

ተጠሪ፡- የአዲስአበባ ከተማ አስተዳደር የፐብሊክ ሰርቪስ ስ/ስ/ል/ቢሮ አልቀረቡም

ይህ መዝገብ የመ.ቁ 208801 የከሆነው መዝገብ ጋር ተጣምሮ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው 1ኛ አመልካች ነሐሴ 17 ቀን 2014 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 275119 ጥቅምት 09 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለው ችሎት የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 280685 መጋቢት 15 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ በመሻር 1ኛ አመልካች ክስ ለማቅረብ የሚያስቸላቸው መብት ሳይኖር፤ ኮንዶሚንየም ቤቱ ላይ ምንም መብት ሳይኖራቸው እና ተወዳድረው ያሸነፉት ባለ ሁለት መኝታ ኮንዶሚንየም ቤት ሳይኖር ባቀረቡት ክስ መነሻነት በስር ፍርድ ቤቱ የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ አይደለም በማለት የሰጠው ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 217807 ግንቦት 19 ቀን 2014

ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ጉዳዩ በሽልማት ተሰጥቷል የተባለን የኮንዶሚንየም ቤት ለማስመለስ የቀረበን ክስ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በስር ፍርድ ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን 1ኛ አመልካች ከሳሽ፤ በዚህ የሰበር ክርክር የሌለ የልደታ ክፍለከተማ መሬት ልማት ማኔጅመንት 1ኛ ተከሳሽ፤ የአሁን ተጠሪ 2ኛ ተከሳሽ፤ የአሁን 2ኛ አመልካች ደግሞ 3ኛ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የአሁን 1ኛ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ ይዘት በአጭሩ፡- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በስሩ ባሉት ሴክተር መስሪያ ቤቶች ካሉ ሠራተኞች መካከል በስራ አፈጻጸማቸው ከፍተኛ ጥረት ያደረጉትን እና የላቀ አፈጻጸም ያላቸውን ሰራተኞች ለማበረታታት የኮንዶሚንየም ቤትን ሸልሟል፤ በዚሁ መሠረት 1ኛ አመልካች በልደታ ክፍለከተማ መሬት ማኔጅመንት በሰነድ አልባ ይዞታዎች መስተንግዶ ስር የመስክ ልኬት እና ሽንሻኖ ባለሙያ ነኝ፤ በ2011 ዓ.ም ባሳየሁት ከፍተኛ የስራ አፈጻጸም የስር 1ኛ ተከሳሽ በአንደኛ ደረጃ በማስቀመጥ የገንዘብ እና የሰርተፍኬት ሽልማት ሰጥቶኛል፤ የልደታ ክፍለከተማ ፐብሊክ ሰርቪስ እና የሰው ሀብትና ልማት ጽ/ቤት በላከው መሠረትም እንደገና ከመሬት ልማት ማኔጅመንት ጽ/ቤት እና ደጋፊ የስራ ሂደቶች ከ1ኛ እስከ 3ኛ ከየጽ/ቤት ከወጡ ባለሙያዎች ውስጥ አንድ ሰው በነፍስ ወከፍ በፐሮሰስ ካውንስል ጸድቆ እንዲላክ በተባለው መሠረት ከሁሉም ጽ/ቤቶች በአንደኝነት ተመርጬ ስለተላክሁ ምርጥ ፈጻሚ ተብዬ ሽልማት አግኝቻለሁ፤ የአዲስአበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ጽ/ቤት 1ኛ ለወጣ ባለሁለት መኝታ የኮንዶሚንየም ቤት፤ 2ኛ ለወጣ ባለአንድ መኝታ ኮንዶሚንየም ቤት ፤ 3ኛ ለወጣ ደግሞ ስቱዲዮ ኮንዶሚንየም ቤት ሽልማት ሰጥቷል፤ 2ኛ አመልካች የልደታ ክፍለከተማ መሬት ልማት ማኔጅመንት የሰው ሐብት አስተዳደር ቡድን መሪ ነው፤ 2ኛ አመልካች በየትኛውም የስራ ሂደት አልተወዳደሩም፤ በተግባርም በስራ አፈጻጸም አላሸነፉም፤ ሆኖም ስልጣናቸውን ተጠቅመው 1ኛ አመልካችን ከ1ኛ ወደ 3ኛ ደረጃ ዝቅ በማድረግ ራሳቸውን 1ኛ በማድረግ ባለሁለት መኝታ የኮንዶሚንየም ቤት እንዲሰጣቸው አድርገዋል፤ ውድድሩ ባለሙያ ለባለሙያ ነው፤ 2ኛ አመልካች የሰው ሐብት ቡድን መሪ እንጂ ባለሙያ ባለመሆናቸው ስልጣናቸውን አላግባብ እንደተጠቀሙ ያሳያል፤ ስለሆነም አላግባብ የተወሰደውን ባለሁለት መኝታ ኮንዶሚንየም ቤት ማግኘት እንድችል የስር 1ኛ ተከሳሽ እና የአሁን ተጠሪ ጉዳዩን በገለልተኛ ወገን አጣርተው ለፍርድ ቤቱ እንዲያሳውቁ ተደርጎ ቤቱ ይገባታል ተብሎ እንዲወሰንልኝ በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የስር 1ኛ ተከሳሽ እና የአሁን 2ኛ አመልካች የፍርድ ቤቱ መጥሪያ ደርሶአቸው ስላልቀረቡ መልስ የመስጠት መብታቸው የታለፈ መሆኑን ከመዝገቡ ጋር ተያይዞ የቀረበልን የውሳኔ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

የአሁን ተጠሪ በሰጠው መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርቦ በብይን የታለፈ ሲሆን በፍሬነገሩ ላይ በሰጠው መልስ ደግሞ የተሸላሚ ፈጻሚዎች አመራረጥ በሶስቱ ፐል ከ1ኛ እስከ 3ኛ ድረስ ከየጽ/ቤቱ ተደራጅቶ ተልኳል፤ በዚሁ መሠረት ከፐሉ 1ኛ የሆኑት 2ኛ አመልካች ናቸው፤ የስራ ሂደት መሪ ከባለሙያ

ጋር መወዳደር የለበትም የሚለው ሀሳብ በመስፈርቱ ያልተካተተ እና በመስፈርቱ ላይ ማንኛውም የአዲስአበባ ከተማ አስተዳደር ምርጥ ፈጻሚ ሰራተኛ የሆነ እንደሚወዳደር የተካተተ በመሆኑ በከተማ ደረጃ በዚህ መልክ የተወዳደሩ መሆናቸው ጨምሮ 1ኛ ተከሳሽ ተሸላሚዎችን ዝርዝር ያላከበት ደብዳቤ ተያይዟል፤ ስለሆነም ተጠሪን ሊጠይቁ የሚችሉበት ምክንያት ስለሌለ ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም የልደታ ክፍለከተማ አስተዳደር ፐብሊክ ሰርቪስ እና የሰው ሀይል ልማት ጽ/ቤት የተለዩትን ፈጻሚዎች ለአዲስአበባ ከተማ ፐብሊክ ሰርቪስ እና የሰው ሀይል ልማት ቢሮ የላከው በድጋሚ አወዳድሮ እና ለይቶ ነው ወይስ ቀድሞ በተለዩት ደረጃዎች መሰረት ነው? ውድድሩ ሲካሄድ የነበረው እና በመስፈርቱ መሰረት ፈጻሚዎች የተለዩት በየጽ/ቤታቸው ነው ወይስ እንደ ፑል በጥቅሉ ነው የተመረጡት? ውድድሩ የተካሄደው እና በመስፈርቱ መሰረት የመለየት ተግባር የተደረገው በገለልተኛ አካል ነው ወይስ አይደለም? 2ኛ አመልካች በውድድሩ ውስጥ ተካተው ነበር ወይስ አልነበረም? 1ኛ አመልካች 3ኛ ደረጃ መደረጋቸው በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? ተከሳሾች ክርክር የቀረበበትን ባለሁለት መኝታ ኮንዶሚንየም ቤት ለ1ኛ አመልካች ለቀው ሊያስረክቡ ይገባል ወይስ አይገባም? የሚሉትን ጭብጦች በመያዝ ከሚመለከተው የአስተዳደር አካለ ስለጉዳዩ ተጣርቶ እንዲቀርብለት ካደረገ በኋላ መርምሮ የልደታ ክፍለከተማ አስተዳደር ፐብሊክ ሰርቪስ እና የሰው ሀይል ልማት ጽ/ቤት በላከው ምላሽ ላይ በጥቅሉ በመስፈርቶቹ አግባብ ለይቶ እንደላከ የገለጸ ቢሆንም ፈጻሚዎቹ የተገመገሙበት እና ከእያንዳንዱ መስፈርት አንጻር የተለኩበት ማስረጃ አልቀረበም፤ ውድድሩ የተካሄደው በፑል ደረጃ ሲሆን የመሬት ልማት ማኔጅመነት አንዱ ፑል በመሆኑ ከጽ/ቤቱ ከ1ኛ እስከ 3ኛ የተመረጡት ፈጻሚዎች ሽልማቱ ይመለከታቸዋል፤ 1ኛ አመልካች በ2011 ዓ.ም በተቀመጠው መለያ መስፈርት መሰረት 1ኛ የወጡ ስለመሆኑ በተገለጸበት ሁኔታ በዚያው ተመሳሳይ መስፈርት በድጋሚ ሲለይ 3ኛ መሆናቸው ተገልጿል፤ ሆኖም በድጋሚ በተደረገው መረጣ ላይ ውድድሩ የተካሄደው እና ውጤቱ የተለከው በ2ኛ አመልካች አማካኝነት መሰረት ሲሆን የተሰራባቸውን መስፈርት የሚያሳይ ሰንጠረዥ ቀርቧል፤ ሆኖም የአዲስአበባ ከተማ ፐብሊክ ሰርቪስ እና የሰው ሀብት አስተዳደር በላከው ትዕዛዝ መሠረት በካቢኔ የጸደቀ አይደለም፤ 1ኛ አመልካች በተደጋጋሚ የሚቀሩ እና መስፈርቱን የማያሟሉ ስለመሆኑ የመሬት ልማት ማኔጅመንት ጽ/ቤት ገልጾ አቴንዳንስ ተልኳል ያለ ቢሆንም የአቴንዳንስ አባሪ አልተላከም፤ ደረጃው የጸደቀው 2ኛ አመልካች በጻፉት ደብዳቤ ላይ ብቻ በመመርኮዝ ነው፤ ቡድን መሪው ተወዳዳሪም ነጥብ ሰጪም አወዳዳሪም በሆኑበት ሁኔታ፤ ሌላ ገለልተኛ ወገን በመስፈርቱ መሰረት ውጤት ባልሰጠበት ሁኔታ 1ኛ አመልካች ከ1ኛ ደረጃ ወደ 3ኛ ደረጃ መደረጋቸው በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገመንግስት አንቀጽ 25 ላይ የተደነገገውን መሠረታዊ የሆነ የእኩልነት መብት የሚጥስ ነው፤ 1ኛ አመልካች በ2011 ዓ.ም በተደረገው ምዘና 1ኛ ደረጃ የወጡ በመሆኑ እና ለ1ኛ ደረጃ ለወጣ ፈጻሚ ሊሰጥ የሚገባ ሽልማት ሊሰጣቸው ስለሚገባ ተከሳሾች አከራካሪውን ባለ ሁለት መኝታ ኮንዶሚንይም ቤት ለቀው ሊያስረክቧቸው ይገባል ሲል ወስኗል፡፡

የአሁን ተጠሪ ይህን ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 275119 የይግባኝ አቤቱታ አቅርቧል፡፡ ይግባኙ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ 1ኛ አመልካች

ማ ስታወሻ፦ ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ባለሁለት መኝት ኮንዶሚንየም ቤት ሊያስገኝላቸው የሚችል 1ኛ ደረጃ አፈጻጸም አግኝተው እንደነበር በስር 1ኛ ተከሳሽ መስሪያ ቤት የተሰጣቸው ስለመሆኑ ያቀረቡት የሰነድ ማስረጃ ያሳያል፤ ሆኖም 1ኛ አመልካች ከ2ኛ አመልካች ጋር ተወዳድረው በስራ አፈጻጸም በልጠው 1ኛ ወጥተው የተሰጣቸው ስለመሆኑ ያቀረቡት ማስረጃ የለም፤ 1ኛ አመልካች የስር 1ኛ ተከሳሽ ባዘጋጀው መስፈርት 1ኛ ደረጃ ውጤት እንዳላቸው ማስረጃ ያቀረቡ ቢሆንም ተጠሪ ባዘጋጀው መስፈርት መሠረት ተወዳድረው 1ኛ ደረጃ ላይ ያስቀመጣቸው ውጤት አለመኖራቸው መዝገቡ ውስጥ ያሉት የሰነድ ማስረጃዎች ያስረዳሉ፤ 2ኛ አመልካች እንደማንኛውም ሰራተኛ ሊወዳደር የሚችል ሲሆን እንዳይወዳደር የሚያደርግ መስፈርት የለም፤ ለኮንዶሚንየም ቤቱ ተብሎ በመወጣው መስፈርት መሠረት ከ2ኛ አመልካች እና ከሌላ ግለሰብ ጋር ተወዳድረው 1ኛ እንደሆነ ምንም የሚያሳይ ውጤት በሌለበት 1ኛ አመልካች ቤቱን እንዲሸለሙ የሚያደርጋቸው ውጤት ሳይኖራቸው እና 1ኛ ደረጃ መውጣታቸውን የሚያሳይ ምንም ዓይነት ማስረጃ ሳይኖራቸው የስር 1ኛ ተከሳሽ በራሱ መስፈርት አወዳድሮ 1ኛ ስላደረጋቸው ብቻ ባለሁለት መኝታ ኮንዶሚንይም ቤት ማግኘት አለብኝ ብለው ክስ ማቅረባቸው የሕግ መሠረት የለውም፤ 1ኛ አመልካች ከሳሽ ሊያደርግ የሚያስችላቸው ምንም ዓይነት አመላካች ማስረጃ በሌለበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 33(2)(3) መሠረት ክስ ማቅረባቸው ተገቢ አይደለም በማለት በስር የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር 1ኛ አመልካች ለባለ ሁለት መኝታ ኮንዶሚንየም ቤት ተወዳድረው 1ኛ ደረጃ ስለመሆናቸው እና ቤቱ የሚገባቸው ስለመሆኑ ምንም ማስረጃ ሳይኖር ይገባኛል ብለው ክስ ማቅረባቸው የሕግ እና የማስረጃ ድጋፍ የለውም በማለት ወስኗል።

1ኛ አመልካች በተራቸው ይህን ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 217807 የይግባኝ አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 መሠረት ይግባኛቸው ተሰርዟል።

በሌላ በኩል የአሁን 2ኛ አመልካች በፊናቸው የስር የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 270258 የይግባኝ አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 መሠረት ይግባኛቸው ተሰርዟል።

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ከላይ የተመለከቱትን ውሳኔዎች በመቃወም ነው። 1ኛ አመልካች የሰ.መ.ቁ 233250 በሆነው መዝገብ ነሐሴ 17 ቀን 2014 ዓ.ም ጽፈው ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይዘት በአጭሩ፦ ተጠሪ የ1ኛ አመልካች 1ኛ መውጣትን እና 2ኛ አመልካች አላግባብ ስልጣኑን በመጠቀም ድርጊቱን እንደፈጸመ አልተቃወመም፤ ተጠሪ ሽልማቱ ለእገሌ ይገባል የሚል ክርክር አላቀረበም፤ 2ኛ ተጠሪም የክርክሩ አካል ባልሆነበት ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ባልተጠየቀ ዳኝነት ላይ የተሰጠ ውሳኔ ነው፤ 2ኛ አመልካች ለብቻው ያቀረበው ይግባኝ ውድቅ በተደረገበት ሁኔታ ተጠሪ ባቀረበው ይግባኝ መነሻነት የተሰጠው ውሳኔ በአቋራጭ መብት እንዲያገኝ የሚያደርግ ነው፤ 2ኛ አመልካች ተጠሪ ባቀረበው ይግባኝ ላይ የክርክሩ አካል አይደሉም፤ ይግባኙ አያስቀርብም ተብሎ እያለ የተሰጠው ውሳኔ ከስነ ስርዓት ውጪ ነው፤ አመልካች ክሱን ለማቅረብ የሚያስችል መብት እንዳለኝ የሚያሳዩ አግባብነት ያላቸውን ማስረጃዎች እና

ክርክሮች ለስር ፍርድ ቤቱ አቅርቤአለሁ፤ ስለሆነም ይህ ታልፎ አመልካች መብት የላትም በሚል በስር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የ1ኛ አመልካች የሰበር አቤቱታ በሰበር አጣሪው ችሎት ተመርምሮ የይግባኝ ቅሬታ ያቀረበው የአሁን ተጠሪ ሲሆን ቅሬታውም ሀላፊ ሳልሆን ሀላፊ ተብያለሁ የሚል ሆኖ ባለበት ፍርድ ቤቱ የስር 3ኛ ተከሳሽ ያቀረበውን የይግባኝ ቅሬታ ሰርዞ ባለበት እና ከይግባኝ ባይ መብት አንጻር ብቻ ቅሬታውን መርምሮ ውሳኔ ሊሰጥ ሲገባው ባልተጠየቀ ዳኝነት በ3ኛ የስር ተከሳሽ ላይ የተሰጠውን ውሳኔ ጭምር በመሻር የወሰነበት አግባብነት ከይግባኝ አቀራረብ እና አወሳሰን ሥነ ሥርዓታዊነት አንጻር ለመመርመር የሚል ጭብጥ ተይዞ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ተደርጎ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ቀርቧል፡፡

ተጠሪ ጥር 12 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠው መልስ ይዘት በአጭሩ፡- የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሰጠው ውሳኔ ላይ የተጠሪን ጥፋት ሳያመላክት በደፈናው ባለሁለት መኝታ ኮንዶሚንየም ቤት እንድናስረክብ መወሰኑ ከስራ ድርሻችን ጋር ስለማይገናኝ ይግባኝ መጠየቃችን እና 1ኛ አመልካች በጉዳዩ ላይ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጎ መወሰኑ ተገቢ ነው፤ 1ኛ አመልካች በሌሉበት ይግባኙ አልታየም፤ 2ኛ አመልካች ለብቻቸው ይግባኝ መጠየቃቸው በእኛ በኩል አይታወቅም መጥሪያም አልደረሰንም፤ ውሳኔዎቹ የተወሰኑነት በተለያየ ችሎት በመሆኑ ከፍተኛው ፍርድ ቤት ይህን ያውቅ ነበር ማለትም አይቻልም፤ የግራቀኞችን ክርክርም ፍጹም የተለያየ ነው፤ 1ኛ አመልካች 2ኛው አመልካች ይግባኝ ማለታቸውን ያውቁ ከነበር መዝገቦቹ ይጣመሩልኝ ማለት ይችሉ ነበር፤ አመልካች አሉኝ የሚሏቸው ማስረጃዎች ከክፍለከተማው እንጂ ከተጠሪ አይደሉም፤ አመልካች ክስ ከማቅረባቸው አስቀድሞ ለተጠሪ ያቀረቡት አቤቱታ የለም፤ ስለሆነም በስር ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ ስለሆነ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡

1ኛ አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልሰ መልስ ሰጥተዋነል፡፡

በሌላ በኩል የአሁን 2ኛ አመልካች ተጣምሮ በታየው የሰ.መ.ቁ 208801 በሆነው መዝገብ ሠኔ 04 ቀን 2013 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የመንግስት ሠራተኞች የደረጃ እድገት የቅሬታ አፈታት እና አጠቃላይ አስተዳደራዊ ጉዳይ በአዋጅ ቁጥር 1064/2010 አንቀጽ 81 እና በአዋጅ ቁጥር 56/2010 መሠረት በአስተዳደር ፍርድ ቤት የሚታይ እንጂ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለውም፤ ተጠሪ እና የስር 1ኛ ተከሳሽ ጉዳዩን የህዝብ እምባ ጠባቂ ተቋም እንዲያየው ተደርጎ በሕግ አግባብ የተሰራ መሆኑ ተረጋግጧል፤ 2ኛ አመልካች ሀላፊ ሳልሆን ሰራተኛ ነኝ፤ ሠራተኞችን የማወዳድርበት እና በግል የምሽልምበት ሥልጣን የለኝም፤ በ 2011 ዓ.ም አዲስ በተላከው ሰርኩላር መሠረት ሠራተኞችን በማወዳደር ያሸነፉትን መስሪያ ቤቱ ለይቶ በአግባቡ የተሰራ ነው፤ አቤቱታ ቀርቦበትም በገለለልተኛ አካል ተረጋግጧል፤ አመልካች ለሚመለከተው የአስተዳደር ፍርድ ቤት ክስ አቅርበው በሕግ አግባብ የተሰራ መሆኑ አረጋግጦ ክሱን ውድቅ አድርጎታል፤ ስለሆነም በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የ2ኛ አመልካች የሰበር አቤቱታ በሰበር አጣሪው ችሎት ተመርምሮ የስራ አፈጻጸምን መሠረት በማድረግ የአዲስአበባ አስተዳደር ሰራተኛውን በማወዳደር የሰጠውን ሽልማት መሠረት በማድረግ በግራቀኙ መካከል የነበረውን ክርክር ስር ፍርድ ቤት በማየት የወሰነበት አግባብነት ከፍርድ ቤቱ የዳኝነት ሥልጣን ጋር በማገናዘብ ለመመርመር የሚል ማስቀረቢያ ጭብጥ ተይዞ 1ኛ አመልካች መልስ እንዲሰጡት ተደርጎ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ቀርቧል፡፡

1ኛ አመልካች ሐምሌ 02 ቀን 2013 ዓ.ም በሰጡት መልስ 1ኛ አመልካች ለፍርድ ቤት ክስ ከማቅረቤ በፊት ለተለያዩ የአስተዳደር አካላት አቤቱታ አቅርቤ ተገቢውን ምላሽ አላገኘሁም፤ ለአዲስአበባ ከተማ ፍርድ ቤት ጉዳዩን አቅርቤም ሥልጣን የሌለው መሆኑ እና በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ክስ እንዳቀርብ ተገልጾልኛ፤ ጉዳዩ በኮሚቴ ታይቷል ለአስተዳደር ፍርድ ቤት ቀርቧል የተባለው ሐሰት ነው፤ የእምባ ጠባቂ ተቋም ግራቀኛችንን አላነጋገረም ሌላም ገለልተኛ አካል በዳኝነት አላየውም፤ ስለሆነም በስር የመጀመሪያው ደረጃ ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡

የግራቀኙ ክርክር እና በየደረጃው ባሉት ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ከላይ የተመለከተውን ይመስላል፡፡ ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት የተያዘውን ማስቀረቢያ ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ  እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሒደት መገንዘብ እንደቻልነው ጉዳዩ የቀረበለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሰጠው ውሳኔ የአሁን ተጠሪ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመ.ቁ 275119 በሆነው መዝገብ ይግባኝ ጠይቆ ይግባኙ የቀረበለት ፍርድ ቤት በስር የፌዴራል መጀመሪያ ፍርድ ቤት የተሰጠውን ውሳኔ የሻረው መሆኑን እና ይህም ውሳኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በትዕዛዝ የጸና መሆኑን፤ በሌላ በኩል የአሁን 2ኛ አመልካች በፊናቸው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 270258 ይግባኝ ጠይቀው ይግባኙ የቀረበለት ፍርድ ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 መሠረት ይግባኛቸውን የሰረዘ መሆኑን እና አመልካቾች በየፊናቸው ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተጣምረው በታዩት መዝገቦች የሰበር አቤቱታ ያቀረቡ መሆኑን ነው፡፡ ይህም የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በስር ፍርድ ቤት በተሰጠ አንድ ውሳኔ ላይ ሁለት ተከራከሪ ወገኖች / 2ኛ አመልካች እና ተጠሪ / በተለያየ መዝገብ በየፊናቸው ያቀረቡለትን ይግባኝ ለየብቻ አይቶ የተለያየ ውሳኔ የሰጠ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

በመሠረቱ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ መሠረታዊ ዓላማ  ክርክሮችን ሥርዓት ባለው መንገድ በመምራት በአፋጣኝ እንዲታዩ በማድረግ ጊዜን፣ ጉልበትን እና ገንዘብን በመቆጠብ ፍትሐዊ ውሳኔ መስጠት ነው፡፡ ተመሳሳይ በሆነ ጉዳይ ተመሳሳይ የሆኑ ተከራካሪ ወገኖች በአንድ ፍ/ቤት በተለያዩ መዝገቦች መከራከራቸው ሲታወቅ ጉዳዩን በመጀመሪያም ሆነ በይግባኝ ደረጃ የተመለከቱት ፍ/ቤቶች እነዚህ ሁለት ጉዳዮች ተጣምረው እንዲታዩ ካላደረጉ በቀር በአንድ ጉዳይ ላይ በተለያዩ አኳኋን ፍርድ ሊሰጥ ይችላል፡፡ በተመሳሳይ ተከራከሪ ወገኖች በሚከራከሩበት ተመሳሳይ ጉዳይ አንድ ፍ/ቤት በተለያዩ ክስ ተቀብሎ

በማስተናገዱ ምክንያት የተለያየ ፍርድ መስጠቱ በየትኛውም መለኪያ ቢሆን ፍትሐዊ እና ሕጋዊ ካለመሆኑም በላይ በዚህ አኳኋን የተሰጡትንም ፍርዶች ማስፈፀም አዳጋች ነው፡፡

ይህንንም በመገንዘብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ እንደዚህ ያለ ሁኔታ እንዳያጋጥም ሥርዓት ዘርግቷል፡፡ ይኸውም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 8(1) ላይ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ነገር አንድ አይነት ወይም ተመሳሳይነት ያለው ሆኖ ምላሽ የሚያስፈልገውም የሥረ - ነገር ጭብጥና ተከራከሪ ወገኖችም ተመሳሳይ ሆነው ጉዳዩ በቅድሚያ ሥልጣን ላለው ፍ/ቤት ቀርቦ በመሰማት ላይ እያለ ሌላው ፍ/ቤት ይህንኑ አንድ የሆነውን ጉዳይ ተቀብሎ ለመከራከር አይችልም በማለት ተመሳሳይ የሆነው ጉዳይ በአንድ ፍ/ቤትም ሆነ በሌላ ፍ/ቤት በቀረበ ጊዜ ክርክሩ ሊቀጥል እንደማይገባ አስገዳጅነት ባለው ሁኔታ ደንግጓል፡፡ ምናልባትም ይኸው ሥርዓት ሳይፈፀም ተመሳሳይ የሆነውና በተመሳሳይ ተከራካሪ ወገኖች የተነሳው ጉዳይ በተለያየ ክስ አማካኝነት በተለያየ ፍ/ቤት ቀርቦ በመሰማት ላይ የሚገኝ መሆኑ ከታወቀም የክርክሩ ተነጣጥሎ መታየት ለዳኝነት ሥራ አመራር ወይም ለትክክለኛ ውሳኔ አሰጣጥ የማይመች ወይም የማይገባ ሆኖ ስለሚገኝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 11 መሰረት ተጣምሮ መታየት ይኖርበታል፡፡

በያዝነው ጉዳይ የአሁን አመልካች እና ተጠሪ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በየፊናቸው የይግባኝ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ይግባኙ የቀረበለት ፍርድ ቤት በአንድ መዝገብ ተከራከሪ የነበሩ የተለያዩ ወገኖች በየፊናቸው ይግባኝ ሊያቀርቡ የሚችሉበት ሥርዓት እንዳለ በመገመት በተቻለው ሁሉ ጥንቃቄ በማድረግ ጉዳዮቹን አጣምሮ ማየት ሲገባው 2ኛ አመልካች እና ተጠሪ በየፊናቸው ያቀረቡትን ይግባኝ በተለያየ መዝገብ ተመልክቶ የተለያየ ውጤት ያለው ውሳኔ መስጠቱ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ የተቀመጠውን የክርክር አመራር ሥርዓት ያላገናዘበ እና ሕጉ ሊያሳካ ካሰበው ዓላማ ውጪ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በሌላ በኩል ዋናውን ጉዳይ በሚመለከት በስር ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ መሆን አለመሆኑን እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተጠሪ ባቀረበው የይግባኝ አቤቱታ መነሻነት በስር የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተሰጠውን ውሳኔ የሻረው 1ኛ አመልካች ከሳሽ ሊያደርግ የሚያስችላቸው ምንም ዓይነት አመላካች ማስረጃ በሌለበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 33(2)(3) መሠረት ክስ ማቅረባቸው ተገቢ አይደለም በማለት በስር የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር 1ኛ አመልካች ለባለ ሁለት መኝታ ኮንዶሚንየም ቤት ተወዳድረው 1ኛ ደረጃ ስለመሆናቸው እና ቤቱ የሚገባቸው ስለመሆኑ ምንም ማስረጃ ሳይኖር ይገባኛል ብለው ክስ ማቅረባቸው የሕግ እና የማስረጃ ድጋፍ የለውም በማለት ነው፡፡

በመሠረቱ የአንድ መብትና ግዴታ ምንጭ ሕግ ወይም ውል ሲሆን አንድ ከሳሽ ሌላውን ወገን በተከሳሽነት ፍርድ ቤት መክሰስ የሚያስችለው ምክንያት (cause of action) እንዲኖረው የግድ የሚል መሆኑንና ለመክሰስ የሚያስችል ጥቅም ወይም መብት በማረጋገጥ አቤቱታ ካላቀረበ በቀር በማናቸውም ሰው ላይ ክስ ሊያቀርብ የማይችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 33(2)እና(3) ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡ ሆኖም በአንድ ወገን ላይ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብት ወይም ጥቅም መኖሩ ብቻውን ውጤት የሚያመጣ ሳይሆን

ከሳሹ ተጣሰብኝ ወይም ተደፈረብኝ ወይም አልተፈፀመልኝም የሚለውን ግዴታ በሌላው ወገን በሕግ ወይም በውል የተገኘ መብቱ / ጥቅሙ / የተጣሰበት መሆኑን፣ ተከሳሹ መብቱ የተደፈረበት ወይም ግዴታ ያልተፈፀመበት መሆኑን፣ መብቱ በመደፈሩ ወይም ሊፈፀምለት ይገባው የነበረው ግዴታ ባለመፈፀሙ ጥቅም የቀረበት ወይም ጉዳት የደረሰበት መሆኑን፣ እንዲሰጥለት የሚጠይቀው ዳኝነት (relief) በሕግ የተፈቀደ መሆኑን ካለሳዩ በቀር ያቀረበው ክስ ተቀባይነት ሊኖረው የማይገባ ስለመሆኑም ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 33(2)እና(3) ፤ 231 ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ መዘንዘብ ይቻላል፡፡ በመሆኑም አንድን ክስ የሚያቀርብ ተከራካሪ ወገን ይህንን ሊያስረዳ የሚችል ጠቋሚ ማስረጃ (Prima facie evidence) ሊያቀርብ ይገባል፡፡ ከሳሽ የሆነው ወገን ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 33(2)እና(3) ድንጋጌ አኳያ የሚጠበቅበት ክስ በመሰረተበት ነገር / ሐብት / ላይ ከሕግ ወይም ከውል የመነጨ መብት ወይም ጥቅም እንዳለው እና ይሄው ጥቅሙ ወይም መብቱ በተከሳሹ የተነካበት ወይም የተጣሰበት መሆኑን እንጂ ገና ተከሳሹ ሳይጠራ በክሱ የተጠቀሰውን ፍሬነገር በማስረጃ እንዲያረጋግጥ አይደለም፡፡ ይህም ከሳሽ የሆነው ተከራካሪ ወገን ከጅምሩ እንዲያረጋግጥ የሚጠበቅበት አለኝ የሚለውን መብት በክስ አቤቱታው ላይ እንዲያሳይ እና ይህንንም የሚያረጋግጥለት ጠቋሚ ማስረጃ ማቅረብ እንደሆነ፤ ክስ የማቅረብ መብት ወይም ጥቅም ማስረዳት መቻል እና እንደክሱ አቀራረብ ወይም እንደተጠየቀዉ ዳኝነት ዉሳኔ ለመስጠት የሚያስችል የማስረጃ ምዘና ደረጃ ልዩነት ያላቸው መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ተከራካሪ የሆኑ ወገኖች የሚያቀርቧቸውን ክርክሮች ለመወሰን በሕግ አግባብ የተቋቋሙ ፍ/ቤቶች ደግሞ ተከሳሽ ወገን ክሱን ለማስተባበል የሚያቀርበውን መከራከሪያ እና ማስረጃ መሠረት በማድረግ ፍሬነገርን አጣርተው እና ማስረጃ መዝነው ዉሳኔ መስጠት የሚጠበቅባቸው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 33/2 እና 231፤ 182 እና 273 ድንጋጌዎች ይዘት ያስገነዝቡናል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም በዚህ ረገድ በተለይም የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 33 እና 231 አተገባበርን አስመልክቶ በሰ.መ.ቁ 82234፤ 135639፤ 144052 እና በሌሎችም መዝገቦች ላይ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡

በያዝነው ጉዳይ አመልካች ዳኝነት የጠየቁበትን ጉዳይ ለመጠየቅ የሚያስችል የአዲስአበባ ከተማ አስተዳደር የላቀ የስራ አፈጻጸም ያላቸውን ሠራተኞች የኮንዶሚንየም ቤት ለመሸለም ባወጣው መመሪያ መሠረት ተወዳድረው የባለሁለት መኝታ የኮንዶሚንየም ቤት አሸናፊ መሆናቸውን እና ይህንኑ መብታቸውንም ለማስከበር የሚያስችል የክስ ምክንያት ያላቸው መሆኑን በክሳቸው ላይ ገልጸዋል፡፡ ይህንኑ ክሳቸውን ለማስረዳትም የተለያዩ ማስረጃዎችን አቅርበዋል፡፡ እነኚህም ማስረጃዎች አመልካች ይገባኛል በሚሉት ባለሁለት ኮንዶሚንየም ቤት ላይ መብት ያላቸዉ ስለመሆኑ አስረጂ ወይም ጠቋሚ ማስረጃ እንደሆኑ ግንዛቤ የሚወሰድበት ነው፡፡ አመልካች አስተዳደሩ ባወጣው መስፈርት መሰረት በስራ አጻጸም የተሻለ ውጤት እንዳላቸው እና ባለሁለት መኝታ ኮንዶሚንየም ቤቱ የሚገባቸውን መሆኑን በመግለጽ ያቀረቡትን ክስ ለማስረዳት የሚያስችላቸውን የተለያዩ ማስረጃዎችን እስካቀረቡ ድረስ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ሊሰጥ የሚገባው በተቃራኒው የሚከራከሩት አካላት በጉዳዩ ላይ የሰጡትን መልስ መሠረት በማድረግ አከራካሪ የሆነው የፍሬነገር ጭብጥ ከተለየ በኋላ አመልካች ያቀረቧቸው ማስረጃዎች ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸው ማስረጃዎች መሆን አለመሆናቸው በአግባቡ ተለይተው፤ ተመዝነው እና ተከራካሪዎቻቸው ካቀረቡት

ክርክር እና ማስረጃ እንዲሁም ከተገቢው ሕግ ጋር ተገናዝበው አመልካች በጠየቁት ዳኝነት መሠረት ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችሉ መሆን አለመሆናቸው በመግለጽ ዉሳኔ የሚሰጥበት እንጂ አመልካች ክሱን ለማቅረብ የሚያስችል አመላካች ማስረጃ አላቀረቡም ተብሎ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 33/3 መሠረት የአመልካችን ክስ ውድቅ ለማድረግ የሚያስችል አይደለም፡፡

በመሆኑም ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከግራ ቀኙ ክርክር እና ክርክራቸውን ለማስረዳት ካቀረቡት ማስረጃ አንፃር አመልካች ያቀረቧቸው ማስረጃዎች እንደክስ አቀራረባቸው ለማስረዳት የሚያስችሉ አግባብነት ያላቸው ማስረጃዎች መሆን አለመሆናቸው በአግባቡ ከተለዩ በኋላ በእያንዳንዱ ማስረጃ ላይ ተገቢ የሆነ ሕጋዊ ትንታኔ በመስጠት ተከራካሪዎቻቸው ካቀረቡት ማስረጃ ጋር አገናዝበው በቀረበለት ይግባኝ ላይ ውሳኔ መስጠት ሲገባው ይህንኑ ሳያደርግ የአመልካችን ክስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 33/3 መሠረት ውድቅ በማድረግ የሰጠው ውሳኔ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 33/2፣ 33/3 እና 231/1(ሀ) ድንጋጌዎችን ያላገናዘበ እና ኢ-ሥነ-ሥርዓታዊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም ተጠሪ ባቀረበው ይግባኝ መነሻነት በስር የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ የነበረው ውሳኔ የተሻረ እና የጸና ውሳኔ የሌለ በመሆኑ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በግራቀኙ የቀረበለትን ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ ተገቢውን ሕጋዊ ውሳኔ እንዲሰጥ ማድረግ ስነ ስርዓታዊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ውሳኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 270258 ግንቦት 18 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ብይን፣ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 275119 ጥቅምት 09 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፣ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የፌዴራል ጠቅላይ ፍረድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 217807 ግንቦት 19 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ስ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በውሳኔ የዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ ከላይ በፍርድ ሐተታው ላይ በተገለጸው መንገድ ክርክሩን መርቶ ተገቢውን ሕጋዊ ውሳኔ እንዲሰጥበት በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343/1 እና በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(2) መሠረት ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

## ትዕዛዝ

- በዚህ መዝገብ የተሰጠው ውሳኔ ትክክለኛ ግልባጭ የመዝገብ ቁጥሩ 208801 ከሆነው መዝገብ ጋር እንዲያያዝ ታዟል፡፡
- መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት**

**ማ/ተ**

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
## የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ 233060

ጥቅምት 5 ቀን 2016 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

እንዳሻው አዳነ

ተሾመ ሽፈራው

መላኩ ካሳዬ

ነጻነት ተገኝ

አመልካች፡- ወ/ሮ ከድጃ ሞሳ } አልቀረቡም

ተጠሪ ፡- ወ/ሮ ደረጃ ዑመር

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ የተያዘው ክርክር በባህርዳር ከተማ ወረዳ ሼሪያ ፍ/ቤት ሲጀምር የአሁን ተጠሪ ከሳሽ፤ አቶ ሞሳ አህመድ ተከሳሽ፤ እንዲሁም የአሁን አመልካች ጣልቃ ገብ ነበሩ፡፡ ተጠሪ መጋቢት 16 ቀን 2013 ዓ/ም ጽፈው ባቀረቡት ክስ ከተከሳሽ አቶ ሞሳ አህመድ ጋር በሸሪያ ህግ መሰረት ተጋብተን ለ55 ዓመታት በጋብቻ ስንኖር ልጆች እና የጋራ ንብረት አፍርተናል፤ በተለይ ለክርክር ምክንያት የሆነው በባህርዳር ከተማ በዳግማዊ ሚኒሊክ ክፍለ ከተማ በ 105 ካ.ሜ ይዞታ ላይ የሚገኝ መኖሪያ ቤት በጋብቻ ውስጥ የተፈራ የጋራ ንብረታችን ነው፡፡ ስለሆነም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በመካከላችን አለመግባባት በመፈጠሩ ጋብቻው ፈርሶ በጋብቻ ውስጥ ያፈራናቸው የጋራ ንብረቶች ክፍፍል እንዲደረግልን በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ተከሳሽ በሰጡት መልስ በአሁን ተጠሪ እና በተከሳሽ መካከል ያለው ጋብቻ ባይፈርስና አለመግባባቱ በስምምነት ለመፍታት ጥረት ቢደረግ ፤ ጋብቻው የሚፈርስ ከሆነ ግን ከሳሽ የጋራ ንብረት ነው በማለት ያቀረቡት በባህርዳር ከተማ በዳግማዊ ሚኒሊክ ክፍለ ከተማ በ 105 ካ.ሜ ይዞታ ላይ የሚገኝ መኖሪያ ቤት የጋራ ልጃችን የሆነችው የአሁን አመልካች አረብ አገር ሰርታ ባመጣችው ገንዘብ የተገዛ ንብረቷ እንጂ የባልና ሚስት የጋራ ንብረት ባለመሆኑ ከሳሽ የጋራ ንብረት ነው ልካፈል ይገባል በማለት ያቀረቡት አቤቱታ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል።

ይህ በእንዲህ እዳለ የአሁን አመልካች ወደክርክሩ ጣልቃ ገብተው ለክርክር ምክንያት የሆነውን በባህርዳር ከተማ በዳግማዊ ሚኒሊክ ክፍለ ከተማ በ 105 ካ.ሜ ይዞታ ላይ የሚገኝ መኖሪያ ቤት አረብ ሀገር ሰርቼ በላኩት ገንዘብ ተከሳሽ የገዛልኝ የግል ንብረቴ በመሆኑ በጋብቻ ውስጥ እንደተፈራ ንብረት ተቆጥሮ በግራ ቀኙ መካከል ክፍፍል ሊደረግ አይገባም በማለት ተከራክረዋል። ከሳሽ ለጣልቃ ገብ በሰጡት መልስ መኖሪያ ቤቱ ጣልቃገብ በክርክራቸው እንደገለጹት የግል ንብረታቸው ሳይሆን በጋብቻ ውስጥ የተፈራ የጋራ ንብረት ነው፤ ጣልቃ ገብ እና ተከሳሽ በመመሳጠር ያቀረቡት ክርክር በመሆኑ ውድቅ እንዲያደርግልኝ ብለዋል። በሌላ በኩል የሥር ፍ/ቤት ተከሳሽ ክርክር የተነሳበት መኖሪያ ቤት የጣልቃ ገብ ነው በማለት ደግፈው ተከራክረዋል።

የግራ ቀኙን ክርክር በዚህ መልኩ የሰማው የስር ፍ/ቤት ጋብቻው መፍረሱን አረጋግጦ የኢዳ ቀለብ ብር 1500.00 ተከሳሽ ለከሳሽ እንዲከፍል እና ንብረትን በተመለከተ የታመኑና በማስረጃ የተረጋገጡ ንብረቶችን ከሳሽና ተከሳሽ እንዲካፈሉ ወስኗል። አከራካሪውን በባህርዳር ከተማ በዳግማዊ ሚኒሊክ ክፍለ ከተማ በ 105 ካ.ሜ ይዞታ ላይ የሚገኝ መኖሪያ ቤት በተመለከተ ተከሳሽ ከእሙሀይ መልሺው በ2004 ዓ.ም በብር 160000.00 (አንድ መቶ ስድሳ ሺህ) የገዙት ቢሆንም ልጃቸው ብር ልካ የተገዛ ነው በሚል ቤቱ የጣልቃ ገብ ነው፤ ስመሀብቱም ከአቶ ሞሳ አህመድ ወደ ጣ/ገብ ኸድጃ ሞሳ ይዛወር በማለት ወስኗል።

የአሁን ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ቅሬታቸውን ለባህርዳርና አካባቢዋ የዞን ሼርያ ፍ/ቤት አቅርበዋል። ነገር ግን ዳኛው የግራቀኙ ዘመድ በመሆናቸው ባላቸው ዝምድና ምክንያት ጉዳዩን ለማየት አልችልም በማለታቸው ጉዳዩ ለክልሉ ጠቅላይ የሸርያ ፍ/ቤት በማዛወር እንዲታይ ተደርጓል።

የክልሉ ጠቅላይ ሸሪአ ፍርድ ቤት ከዞኑ የተላከውን መዝገብ ተቀብሎ ፋይል በመክፈት ክርክራቸውን ካቀባበለ በኋላ በዞኑ ሸሪአ ፍርድ ቤት ሌላ ተጨማሪ ዳኛ የሌለ በመሆኑ፤ በሌላ ዞን ዳኛ እንዲታይ ቢባልም ግራቀኙ ጉዳዩ ተመልሶ ከሚሄድ እና ጊዜ ከሚወስድ በክልሉ ጠቅላይ ሸሪአ ፍርድ ቤት ታይቶ ይወሰንልን በማለት ተስማምተው በመጠየቃቸው፤ እንዲሁም ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን ማየቱ ጊዜና ወጪ ቆጣቢ መሆኑንና

አከራክሮ መወሰኑ ተገቢ መሆኑን አምኖበታል በማለት ጉዳዩን በራሱ አይቶ ውሳኔ ሰጥቷል። በሰጠው ውሳኔ የስር ጣልቃ ገብ ብር 160000.00 ከላከች ወላጆቿ ይመልሱላት፤ ቤትና ቦታው ግን በእርሷ ስም ስለመገዛቱ ያላስረዳች በመሆኑና በግዥ ውል ሰነዱም የእርሷ ስም የሌለ በመሆኑ ልትጠይቅ አይገባም፤ ቤትና ቦታው የባልና ሚስት ነው ይካፈሉት በማለት በማሻሻል ወስኗል።

የአሁን አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ቅሬታቸውን ለአማራ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበዋል። ችሎቱ ጉዳዩን አስቀርቦ መርምሮ አንድ ክስ ከአንድ ፍርድ ቤት ወደሌላ ተመሳሳይ ደረጃ ወዳለው ፍርድ ቤትም ሆነ እራሱ ከፍ ያለው ፍርድ ቤት በምን ሁኔታ ሊስተናገድ እንደሚችል በሥነ ሥርዓት ህጉ የመለከተ በመሆኑ ፤ በከፍተኛው ሸሪአ ፍርድ ቤት ሌላ ዳኛ ባለመኖሩ፤ ተከራካሪዎቹን ከሚኖሩበት ከተማ ውጪ ለሚገኝ ሌላ የዞን ሸሪአ ፍርድ ቤት መላክ የባለጉዳዮችን ጊዜና ጉልበት አላግባብ ማባከን በመሆኑና የሥነ ሥርዓት ህጉም አላማ በአነስተኛ ወጪ በተፋጠነ ሁኔታ ለክርክሮች ዕልባት መስጠት በመሆኑ፤ እንዲሁም አመልካችም በክልሉ ሸሪአ ፍርድ ቤት ሊታይ አይገባም የሚል ተቃውሞ ያላቀረቡ በመሆኑ በአጠቃላይ የተሻለ ደረጃ ባለው ጠቅላይ ሸሪአ ፍርድ ቤት ክርክሩ መመራቱ የሚነቀፍ ባለመሆኑ አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረቡት ቅሬታ ተቀባይነት የለውም። ፍሬ ጉዳዩን በተመለከተም ቤትና ቦታው የባልና ሚስት መሆኑና አመልካች ብር 160000.00 የላከች ስለመሆኑ በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነው። በሌላ በኩል ቤትና ቦታው የአመልካች እንደሆነ የስር ተከሳሽ አምነው መልስ ሰጥተዋል። አመልካች የጠየቁት ዳኝነት በተከሳሽ ከታመነ ደግሞ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 242(1) መሰረት ውሳኔ መስጠት ሲገባ ግማሽ ባለሙብት የሆኑት አምነው እያለ ቤቱ የባልና ሚስት ስለሆነ ገንዘቡን ይመልሱ በሚል መወሰኑ ከተከራካሪ ወገኖች ሀሳብ እና ክርክር የወጣ ነው። ስለሆነም ውሳኔው ተሻሽሎ ቤቱን አመልካችና ተጠሪ በአይነት ወይም አንዳቸው ለሌላዋ ግምት በማስገባት ወይም ሸጠው ይካፈሉ። የስር ተከሳሽ አቶ ሞሳ አህመድ በቤቱ ላይ መብትና ጥቅም የላቸውም ተልኳል የተባለውን ገንዘብ ቤት ገዝቼበታለሁ ስላሉ ሊጠየቁ አይገባም። የአሁን አመልካች ከላከችው ብር 160000.00 ውስጥ ግማሹን ብር 80000.00 (ሰማንያ ሺህ) የአሁን ተጠሪ ልትከፍል ይገባል በማለት ወስኗል።

የሰበር አቤቱታው ለዚህ ፍርድ ቤት የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው። አመልካች ነሐሴ 6 ቀን 2014 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር ማመልከቻ ተፈፀመ የሚሉትን ስህተት ዘርዝረው ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት አመልካች አረብ አገር በመስራት በላኩት ብር 160,000.00 ለእኔ ተብሎ ስለመገዛቱ በተረጋገጠበት፤ እናትና አባቴ ይህን ቤት ለመግዛት የሚያስችል አቅም እንደሌላቸው ፤ ቤቱ የተገዛውም በወላጅና ልጅነት ባለ

መተማመን መሆኑ በተረጋገጠበት ሁኔታ፤ ይህንንም እናትና አባቴ በተለያየ ጊዜ ያምኑ ሲሆን የክልሉ ሰበር ችሎት ሙሉ በሙሉ ቤቱን ለእኔ ሊወስን ሲገባ ግማሹ የአባትሽ ድርሻ ስላሙኑ ብቻ ይገባሻል የእናትሽ ድርሻ ግን ስለካዱ የተገዛበትን በድርሻቸው ብር 80000.00 (ሰማንያ ሺ) ትክፈል በማለት የሰጠው ፍርድና ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ተሻሽሎ ቤቱ ሙሉ በሙሉ ይገባሻል ተብሎ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

ጉዳዩ በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ የባህርዳር ሸሪያ ፍ/ቤት በሰጠው ውሳኔ ለዞኑ የሸርያ ፍ/ቤት ቀርቦ ሳይታይ ለክልሉ ጠቅላይ ሸርያ ፍ/ቤት የቀረበበት አግባብነት ከፍ/ቤት ስልጣን አንጻር ሊጣራ ይገባል ተብሎ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብና ተጠሪ መልስ እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡

በሰጡት መልስ አጣሪ ችሎቱ ያስቀርባል ያለበትን ነጥብ በተመለከተ የአሁን ተጠሪ በስር ፍ/ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለዞኑ የሸሪያ ፍ/ቤት የይግባኝ አቤቱታየን ባቀርብም የዞኑ ፍ/ቤት ዳኛ ከአመልካች አባት ጋር ዝምድና ስላለኝ ጉዳዩን ማየት አልችልም፤ ሌላ ዳኛም ስለሌለ ጉዳዩ ለጠቅላይ ሸሪአ ፍርድ ቤት ይቅረብ በማለት ትዕዛዝ ሰጥተዋል፡፡ ስለሆነም የዞኑ ሸሪያ ፍርድ ቤትን በመዝለል የቀረበ ይግባኝ የለም፡፡ አመልካችም በጠቅላይ ሸሪአ ፍርድ ቤት መታየቱን በመቃወም አልተከራከሩም፡፡ በሌላም በኩል የከፍተኛው ሸሪያ ዳኛ አንድ ሰው ብቻ በመሆናቸው ወደሌላ ችሎት መምራት አልተቻለም፡፡ በአጠቃላይ በህጉ አግባብ ታይቶ የተወሰነ በመሆኑ የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም ሊፀና ይገባል ብለዋል፡፡ አመልካችም የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ነው፡፡ በበኩላችን የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መሰረት ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ እንደተቻለው አከራካሪ ሆኖ እስከዚህ ፍርድ ቤት የዘለቀውን በባህርዳር ከተማ በዳግማዊ ሚኒሊክ ክፍለ ከተማ በ 105 ካ.ሜ ይዞታ ላይ የሚገኝ መኖሪያ ቤት በተመለከተ በስር ከሳሽና ተከሳሾች የጋብቻ ዘመን ከእሙሀይ መልሺው በ2004 ዓ.ም በብር 160,000.00 (አንድ መቶ ስድሳ ሺህ) ተገዝቶ ስመሀብቱ በተከሳሻ ተመዝግቦ እንደሚገኝ በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ የስር ፍርድ ቤት ባልና ሚስት ቤቱን የገዙት ቢሆንም ልጃቸው የሆነችው የአሁን አመልካች ብር ልካ የተገዛ ነው በሚል ቤቱ የአመልካች ነው፤ ስመሀብቱም ከአባቷ ወደ ጣ/ገብ ይዛወር በማለት ወስኗል፡፡ ይግባኙ የቀረበለት የዞን ሼርያ ፍ/ቤት ብቸኛ ዳኛ የተከራካሪ ዘመድ በመሆናቸው ባላቸው ዝምድና ምክንያት ጉዳዩን ለማየት አልችልም በማለታቸው ጉዳዩ ለክልሉ ጠቅላይ የሸርያ ፍ/ቤት ተዛውሮ እንዲታይ ተደርጓል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ሸሪአ ፍርድ ቤት በበኩሉ በዞኑ

ሸሪአ ፍርድ ቤት ሌላ ዳኛ አለመኖሩን ፤ በሌላ ዞን ይታይ ቢባልም ግራቀኙ ጉዳዩ ተመልሶ ከሚሄድ በክልሉ ጠቅላይ ሸሪአ ፍርድ ቤት ታይቶ ይወሰን በማለት መስማማታቸውን በማረጋገጥ ፤ ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን ማየቱ ተገቢ መሆኑን አምኖበት አይቶ ቤትና በታው በአመልካች ስም ስለመገዛቱ አለመረጋገጡን መሰረት በማድረግ ቤትና በታው የባልና ሚስት ነው፤ የተላከው ገንዘብ ይመለስላት  በማለት በማሻሻል ወስኗል። የክልሉ ሰበር ችሎትም ውሳኔውን ይበልጥ አሻሽሎ ቤቱን አመልካችና ተጠሪ ይካፈሉ፤ የስር ተከሳሽ አቶ ሞሳ አህመድ ካቀረቡት ክርክር አንጻር በቤቱ ላይ መብት የላቸውም፤ ይልቁንም አመልካች ከላከችው ብር 160000.00 ውስጥ የቤቱ ግማሽ ባለድርሻ የሆኑት ተጠሪ ብር 80000.00 (ሰማንያ ሺህ) ሊከፍሉ ይገባል በማለት ወስኗል።

እንደተመለከትነው የአመልካች ቅሬታ የክልሉ ሰበር ችሎት ሙሉ በሙሉ ቤቱን ለእኔ ሊወስን ሲገባ ግማሹ የአባትሽ ድርሻ ስላሙኑ ይገባሻል የእናትሽ ድርሻ ግን ስለካዱ የተገዛበትን በድርሻቸው ብር 80000.00 (ሰማንያ ሺ) ትክፈል ማለቱ ስህተት በመሆኑ ይታረምልኝ በማለት የቀረበ ነው። ይህም ሆኖ አጣሪ ችሎቱ የወረዳው ሸሪያ ፍ/ቤት በሰጠው ውሳኔ ለዞኑ የሸርያ ፍ/ቤት ቀርቦ ሳይታይ ለክልሉ ጠቅላይ ሸርያ ፍ/ቤት የቀረበበት አግባብነት ከፍ/ቤት ስልጣን አንጻር ሊጣራ ይገባል በሚል ጭብጥ በመያዙ ይህንኑ በቅድሚያ መርምረናል።

ከፍሲል እንደተገለፀው ይግባኝ ለዞኑ ሸሪአ ፍርድ ቤት ቀርቦ የነበረ ሲሆን የዞኑ ሸሪኣ ፍ/ቤት ዳኛ የተከራካሪ ዘመድ በመሆናቸውና ለማየት አልችልም በማለታቸው በፍርድ ቤቱም ሌላ ዳኛ ባለመኖሩ ምክንያት ጉዳዩ ለክልሉ ጠቅላይ የሸርያ ፍ/ቤት ተዘውሮ እንዲታይ ተደርጓል።

እንደሚታወቀው የሸሪዓ ፍ/ቤቶችን አቋም ለማጠናከር የፌዴራሉ አዋጅ ቁጥር 188/1992 የወጣ ሲሆን በአማራ ክልል በተመሳሳይ አዋጅ ቁጥር 132/98 ወጥቷል። በጋብቻና ፍቺ ጉዳይ ላይ እነዚህ ፍርድ ቤቶች ያላቸው የስረ ነገር የዳኝነት ስልጣንም ተመልክቷል። ፍርድ ቤቶቹ የያዙዋቸውን ጉዳዮች ሥርዓት ባለው ሁኔታ ለመምራት እንዲያስችላቸው በሥራ ላይ ያሉትን የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጎች ተከትለው እንደሚሰሩ፤ እንዲሁም በሸሪዓ ፍርድ ቤቶች የተነሱ ጉዳዮች በሰበር ሰሚ ችሎት ሊታዩ የሚችለው የሸሪዓ ፍ/ቤቶች ጉዳዩን ሲመሩ የፈፀሙት የስነ ሥርዓት ሕግ ግድፈት ካለ ብቻ ስለመሆኑ በአዋጆቹ ተመልክቷል።

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 31(1)(ሐ)(ለ) ስር ከተመለከተው ድንጋጌ ይዘት መረዳት እንደሚቻለው  የበላይ የሆነው ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ ትዕዛዝ ቢሰጥ ለሁለቱም ተከራካሪ ወገኖችና ለማስረጃው ምቹ መሆኑን የተረዳው እንደሆነ ወይም ይህን ትዕዛዝ መስጠቱ ባጭር ጊዜ ውስጥ ትክክለኛን ፍርድ ለማስገኘት የሚያስችል መሆኑን የገመተ እንደሆነ ጉዳዩ ወደራሱ እንዲተላለፍለት አዘ ዳኝነቱን ለማየት ይችላል።

በተያዘው ጉዳይም የክልሉ ጠቅላይ ሸሪአ ፍርድ ቤት ጉዳዩን መርምሮ በከፍተኛው ሸሪአ ፍርድ ቤት ሌላ ዳኛ አለመኖሩን፤ ተከራካሪዎቹን ከሚኖሩበት አካባቢ ውጪ በሚገኝ ሌላ የዞን ሸሪአ ፍርድ ቤት ዳኛ ይግባኙ እንዲታይ መላክ ጊዜና ጉልበት ማባከን መሆኑን፤ ይህም የሥነ ሥርዓት ህጉን አላማ የሚያሳካ አለመሆኑን፤ እንዲሁም የአሁን አመልካችም ቢሆን ይግባኙ በክልሉ ሸሪአ ፍርድ ቤት እንዳይታይ አለመከራከራቸውን ይልቁንም መፍቀዳቸውን መሰረት በማድረግ ጉዳዩን ወደራሱ እንዲተላለፍለት አዞ ዳኝነት መስጠቱ የሚነቀፍ ሆኖ አላገኘነውም። ስለሆነም ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ሲመራ የፈፀመው የስነ ሥርዓት ሕግ ግድፈት አለ የሚሰኝ ሆኖ አላገኘነውም።

በፍሬ ጉዳዩ ላይ አመልካች ያቀረቡትን ቅሬታ በተመለከተም አከራካሪውን ቤትና ቦታ ባልና ሚስት በትዳራቸው ዘመን በግዥ የተገኘ መሆኑና አመልካች ብር 160000.00 ከአረብ ሀገር የላከች መሆኑ ስልጣን ባላቸው የስር ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል። ከዚህም ሌላ ቤትና ቦታው ለአመልካች መግዛቱንና የሷ መሆኑን የስር ተከሳሽ አምነዋል። የተጠሪ (የስር ከሳሽ) ክርክር ደግሞ ቤቱ የጋብቻ ንብረት መሆኑንና በትዳር ወቅት ተፈርቶ በባል ስም ተመዝግቦ መኖሩን መሰረት ያደረገ ነው። በፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1195 ድንጋጌ መሰረት የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሃብትነትን በማወቅ በአስተዳደር ክፍል የምስክር ወረቀት ሲሠጥ የምስክር ወረቀቱን ያገኘው ሰው የማይንቀሳቀሰውን ንብረት ባለሃብት ሆኖ ሊቆጠር እንደሚገባ ተመልክቷል። ይህን ማስረጃ የያዘ ሰው የንብረቱ ባለሃብት ተደርጎ የሚወሰድ በመሆኑ ቤቱ በስማቸው የሚገኘው የስር ተከሳሽ መሆኑ በህጉ ይገመታል። አመልካች አረብ አገር በመስራት በላኩት ብር 160,000.00 ለእኔ ተብሎ የተገዛ ነው፤ ወላጆቼ ቤቱን ለመግዛት የሚያስችል አቅም የላቸውም፤ የተገዛውም በቤተሰብ መተማመን ስለሆነ ሙሉ በሙሉ ቤቱ ለእኔ ሊወስን ይገባል በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ህጉንና የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር መሰረት ያደረገ ባለመሆኑ የምንቀበለው አይሆንም።

ይልቁንም የአመልካች አባት የአመልካችን የዳኝነት ጥያቄ አምነው በመከራከራቸውና ለታመነውና ውሳኔ እንዲሰጥበት ለተጠየቀው ነገር ለይቶ ውሳኔ ሊሰጥ እንደሚገባ በሥነ ሥርዓት ህጉ የተደነገገ በመሆኑ የክልሉ ሰበር ችሎት አመልካች የጠየቁት ዳኝነት በስር ተከሳሽ በመታመኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 242(1) መሰረት ውሳኔ ሊሰጥ ይገባል በማለት ውሳኔውን አቃንቶ ቤቱን የአሁን አመልካችና ተጠሪ እንዲካፈሉ፤ እንዲሁም የአሁን አመልካች ከላከችው ብር 160000.00 ውስጥ ግማሹን በድርሻቸው ብር 80000.00 (ሰማንያ ሺህ) የአሁን ተጠሪ ሊከፍሉ ይገባል በማለት መወሰኑ ህጉን የተከተለ ነው ከሚባል በቀር የሚነቀፍ ሆኖ አላገኘነውም።

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በአጠቃላይ ቅሬታ የቀረበበት ውሳኔ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ባለመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 03-111778 በቀን 27/10/2014 ዓ.ም የስር ፍርድ ቤት ያሳለፈውን ውሳኔ በማሻሻል የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡
3. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/ተ

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

**በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**
**የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት**

የሰበር መዝገብ ቁጥር 232529

ጥቅምት 6 ቀን 2016 ዓ.ም

ዳኞች፡…

1. እትመት አሠፋ
2. ደጀኔ አያንሳ
3. ብርቅነሽ እሱባለው
4. ሀብታሙ እርቅይሁን
5. ብርሃኑ መንግስቱ

| | |
|---|---|
| አመልካች፡- አቶ መርሻ አግማሴ | የቀረበ የለም |
| ተጠሪ፡- አቶ ደሴ ይግዛው | |

ለምርመራ የተቀጠረውን መዝገብ መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሰሚው ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 112399 ሰኔ 14 2014 ዓ.ም በዋለው የሥር ፍርድ ቤቶች በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው የመሬት ለመሬት ለውጥ ፈርሶ ወደ ነበሩበት እንዲመለሱ የሰጡትን ውሳኔ በመሻር አመልካች በለውጥ ያገኘውን መሬት ለሌላ ሶስተኛ አካል አሳልፎ በለውጥ ከሰጠ በኋላ የለውጥ ውሉ ፈርሶ በለውጥ የሰጠው መሬት እንዲመለስለት የሚያቀርበው ክስ የክስ ምክንያት የለውም በማለት የሥር ቤቶችን ውሳኔ መሻሩ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ሰሚው ችሎት ሊታረም ይገባል በማለት አመልካች ነሓሴ 4 ቀን 2014 ዓ.ም የሰበር አቤቱታ ስላቀረቡ ነው፡፡

*ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

ጉዳዩ የገጠር እርሻ መሬት ለውጥ ውል መፍረስን የሚመለከት ክርክር ሆኖ ክርክሩ የተጀመረው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በደራ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በዚህ ፍርድ ቤት አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ አመልካች ያቀረቡት ክስ ይዘት፡- በደራ ወረዳ ሽሜ ቀበሌ ጀፈጀፉ ጎጥ በምራቅ ሙጨ አላምረው ፣ በምዕራብ ክሉ ፣ በሰሜን ይስማው ዘጌ እና በደቡብ ቦሉ የሚዋሰን ስፋቱ አንድ ቃዳ የሆነ መሬት በ1989 ዓ.ም በስሜ ተቆጥረበት በ1996 ዓ.ም በችግር ምክንያት ለተጠሪ ብሸጥለትም በ2007 ዓ.ም እንዲመልስልኝ ጠይቄው ሽምግልና ተቀምጠን መሬት በመሬት ስንለዋወጥ በለውጥ የሰጠኝን ፎግዳ ጎጥ በምሥራቅ እህትነሽ ካሴ ፣ በምዕራብ ማንዴ አላምኔ ፣ በሰሜን እህትነሽ ካሴ እና በደቡብ ይርጋ እንየው የሚዋሰን አንድ ቃዳ መሬት የተጠሪ ወንድም አቶ ፍቃዴ ይግዛው በ1989 ዓ.ም የተመራው(የተቆጠረበት) እና ካርታ አሰርቶ የያዘው በመሆኑ የለውጥ ውሉ ፈርሶ(ተሰርዞ) ተጠሪ መሬቴን እንዲለቅልኝ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

ተጠሪም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያን በማስቀደም በፍሬ ነገሩ ላይ በተሰጡት መልስ፡- የለውጥ መሬቱን ወንድሜ አልወሰደበትም ፤ ፎግዳ ጎጥ ያለውን መሬት አመልካች ለ3ኛ ወገን ለግራ ጌታ አራጋው ይባቤ አሳልፎ ሰጥቶታል ፤ በለውጥ መሬቱ ላይ ቤት ሰርቼ የተለያዩ አታክልቶችን አልምቸበታለሁኝ ፤ የቀረበው ክስ የተንኮል ነው ፤ የለወጥኩት መሬት የኔ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ሰምቶ ፤ እንዲሁም የደራ ወረዳ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት እንዲጣራ አድርጎ መዝገቡን እንመረመረው፡- አመልካች እና ተጠሪ መሬት ለመሬት የተለዋወጡት በ2007 ዓ.ም በመሆኑ 10 ዓመት ሳይሞላ በ2013 ዓ.ም የቀረበው ክሱ በይርጋ አይታገድም፡፡ ፎግዳ ጎጥ ያለው መሬት የተጠሪ ሳይሆን የወንድሙ የአቶ ፍቃዴ ይግዛው መሆኑ ምስክሮች ያስረዳ ሲሆን ከደራ ወረዳ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት የቀረበው ሪፖርት መሬቱን በ1989 ዓ.ም የተቆጠረው አቶ አበባው እርቄ ሆኖ በ1996 ዓ.ም ደግሞ የተቆጠረው አቶ ፍቃዴ ይግዛው ሲሆን መሬቱን ግራ ጌታ አራጋው ይባቤ በለውጥ የያዘውን መሆኑን ያመለክታል፡፡ ይህም ተጠሪ በመሬቱ እንዳልተቆጠረበትና መሬቱ የ3ኛ ወገን መሆኑን የሚያመለክት ሲሆን ፎግዳ ያለው መሬት የተጠሪ ሳይሆን የወንድሙ አቶ ፍቃዴ ይግዛው መሆኑንና በ2012 ዓ.ም በስሙ ካርታ እንዳሰራበት የአመልካች ምስክሮችም አስረድተዋል፡፡ አንድ ሰው ለ3ኛ ወገን ሊያስተላለፈው የሚችለው በህግ ጥበቃ የሚደርግለትን ያለውን መብት ነው፡፡ ተጠሪ ለአመልካች በለውጥ የሰጠው መሬት የራሱ ያልሆነና የ3ኛ ወገን በመሆኑ የአመልካችን የባለቤትነት መብት የሚጎዳ እና ሁለም ስጋት ውስጥ እንድኖር የሚያደርግ ነው፡፡ መሬቱ የተጠሪ ነው ፣ ወንድሙ እንዲለውጠው ፈቅዶለታል ቢባል እንኳን የለውጥ ውሉ ስላልተመዘገበ ፈራሽ ነው፡፡ በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው የመሬት ለመሬት ለውጥ ውል ሊፀና የማይችል ፈረሽ በመሆኑ ውሉ ፈርሶ ወደነበሩበት ሊመለሱ ይገባል በማለት ተጠሪ በደራ ወረዳ ሽሜ ቀበሌ ፎግዳ ጎጥ በምሥራቅ እህትነሽ ካሴ ፣ በምዕራብ ማንዴ አላምኔ ፣ በሰሜን እህትነሽ ካሴ እና በደቡብ ይርጋ እንየው የሚዋሰን አንድ ቃዳ መሬት ለአመልካች እንዲያስረብበው ፤ እንዲሁም አመልካች በደራ ወረዳ ሽሜ ቀበሌ ጀፈጀፉ ጎጥ በምራቅ ሙጨ አላምረው ፣

በምዕራብ ክሉ ፣ በሰሜን ይስማው ዘጌ እና በደቡብ ቦሉ የሚዋሰን ስፋቱ አንድ ቃዳ የሆነውን መሬት አመልካች ከ3ኛ ወገን በማስለቀቅ ለተከሳሽ እንዲመልስ ወስኗል፡፡

ተጠሪ ውሳኔውን በመቃወም ያቀረቡት የይግባኝ አቤቱታ በደቡብ ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት መሰረዙን ተከትሎ ያቀረበውን የይግባኝ አቤቱታ የመረመረው የሰበር ሰሚው ችሎት አመልካች የለውጡን መሬት ተጠሪ ይዞብኛል በማለት ክስ አላቀረበም፡፡ ይህንኑ መሬት 1ኛው የአመልካች ምስክር ከአመልካች ለውጨ እነ ነኝ የያዝኩት በማለት መስክሯል፡፡ አመልካች ከተጠሪ የለወጠውን መሬት ለ3ኛ ወገን አሳልፎ በለውጥ በሰጠበት ሁኔታ የለውጥ ውሉ ይፍረስልኝ ፤ በለውጥ የሰጠሁት መሬት ይመለስልኝ በማለት የሚያቀርበው ክስ የክስ ምክንት የለውም በማለት የሥር ፍርድ ቤቶች በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ ቁጥር 33(2) መሠረት የቀረበውን ክስ መዝጋት ሲገባቸው የመሬት ለውጥ ውሉ ፈረሽ ነው በማለት የሰጡት ውሳኔ ተገቢ አይደለም በማለት የሥር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ ሽሯል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይሕንን ውሳኔ በመቃወም ሆኖ አቤቱታው ይዘት በአጭሩ፡- አመልካች በሕግ አግባብ ያገኘሁትን መሬት ስለውጠው ተጠሪ ግን የማያዝበትንና የራሱ ያልሆነውን መሬት የራሴ ነው በማለት ለለውጥ አቅርቦ ተለዋውጠናል፡፡ በለውጥ ያስተላለፈልኝ ይዞታ የተጠሪ ሳይሆን ወንድሙ አቶ ፍቃዴ ይግዛው የተቆጠረበት በመሆኑ ለእኔ ሰይመዘገብልኝ ስለታለፈብኝ የለውጥ ውሉ ሕጉ-ወጥ በመሆኑ ያለመሬት አየር ላይ አስቀርቶኛል፡፡ ግራ ጌታ አራጋው ይባቤ በለውጥ መሬቱን ከእኔ ጋር የተለዋወጠ ቢሆንም አመልካች በለወጠኝ መሬት ካርታ አላሰራሁበትም ፤ ካርታ ያሰራሁት በቀድመሞ መሬቴ መሆኑን ፤ ፎግዳ ያለው መሬት የፍቃዴ ይግዛው እንጂ የተጠሪ አለመሆኑን ፤ ከስጋቱ አኳያ ለውጡን አፍርሶ በራሱ መሬት ላይ ካርታ ማሰራቱን መስክረዋል፡፡ የውል ይፍረስልኝ አቤቱታ የክስ ምክንያት ያለው መሆኑን የፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 1784 እና 1808(2) ተደንግጎ እያለ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት የክስ ምክንያት የለውም ማለቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት በመሆኑ ውሳኔው ተሽሮ የወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲፀና ጠይቀዋል፡፡

የሰበር አቤቱታው በሰበር አጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ ለአመልካች በለውጥ የተሰጠው ይዞታ የራሱ ሳይሆን የወንድሙ ይዞታ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት አመልካች ያቀረበው ክስ የክስም ምክንያት የለውም በማለት የወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔን የመሻሩ አግባብነት ለማጣራት ለሰበር ሰሚ ችሎቱ እንዲቀርብ ትዕዛዝ በመስጠቱ ተጠሪ መጥሪያ ደርሷቸው በጽሑፍ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ተጠሪ ያቀረቡት መልስ ይዘት፡- መሬቱ የግሌ እንጅ ፍቃዴ ይግዛው አይደለም ፤ መሬቱ የእሱ ቢሆን ኖሮ መሬቱን ስንለዋወጥ የመሬቱ ባለቤት ነው የተባለው ግለሰብ በእማኝነት አይፈርምም ነበር፡፡ በዚህ ወቅት የኔ መሬት ነው ብሎ ተቃውሞ አላቀረበም ፤ አመልካችም እንዲለቅለት አልጠየቀም ፤ መሬቱ የኔ ነው የሚል ግለሰብ በለሌበት እና እንዲለቅ ያስገደደው ሰው ሳይኖር አመልካች የለውጥ ውሉ ይፍረስልኝ ለማለት የሚያበቃው የሕግ ምክንያት ባለመኖሩ ያቀረበው ክስ የክስ ምክንት የለውም መባሉ በአግባቡ ነው፡፡ አመልካች ከተጠሪ በለውጥ ያገኘውን መሬት በይዞታው ሥር አድርጎ ፣ በስሙ አስመዝግቦ እየተጠቀመበት

ይገኛል፡፡ አመልካችን ክስ ለማቅረብ ያበቃው ምክንያት ከአመልካች የለወጥኩት መሬት ለገጠር ከተማ ቅርብ በመሆኑ በከተማ ቢካለል ተጠቃሚ እሆናለሁ ከሚል እሳቤ ተነስቶ ነው፡፡ አመልካች ከተጠሪ በለውጥ የያዘውን መሬት ለሌላ 3ኛ ወገን አስተላልፎት እያለ ፣ ተጠሪ የያዝኩትን መሬት ቤት ሰርቼበት እና የተለያዩ አትክልቶችን መያዜን ስያይና ለገጠር ከተማ ቅርብ በመሆኑ ወደ ከተማ ሊካለል ይችላል ብሎ ያቀረበው ክስ ነው በማለት የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲፀናላቸው ጠይቀዋል፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከፌ ሲል የተመለከተው ሲሆን ችሎቱም ለሰበር አቤቱታው መሠረት የሆነው ውሳኔ መሠረታዊ ሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ አግባብነት ካለው የሕግ ድንጋጌ አንፃር እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3/ሀ) ላይ በግልጽ እንደተመለከተዉ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ስልጣን መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉን ዉሳኔዎች በማረም ላይ የተገደበ ነዉ፡፡ መሠረታዊ የህግ ስህተት ማለት ምን ማለት ነዉ? ወይም አንድ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚቻለዉ መቼ ነዉ? የሚለዉን ጽንሰ ሃሳብ አስመልክቶ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በበርካታ መዛግብት ላይ በሰጠዉ ዉሳኔ አመላካች መስፈርቶችን ለማስቀመጥ የሞከረ ቢሆንም፣ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በህግ ደረጃ ወጥ የሆነ ትርጓሜ አልተሰጠዉም ነበር፡፡ ይሁንና ከጥር 13 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ ስራ ላይ የዋለዉ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 መሠረታዊ የህግ ስህተት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ትርጓሜ ይሰጣል፡፡ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ተግባራቸዉን ተጠያቂነት ባለበት ሁኔታ ዉጤታማ፣ ቀልጣፋ፣ ተደራሽ እና ተገማች በሆነ ሁኔታ እንዲያከናዉኑ ማድረግን አንዱ ዓላማዉ ያደረገዉ ይህ አዋጅ ካካተታቸዉ አዳዲስ ድንጋጌዎች ዉስጥ አንዱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ለሚለዉ ጽንሰ ሃሳብ ትርጓሜ መስጠቱ እና በክልሎች ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠ ዉሳኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሊታይ የሚችልበትን ሁኔታ አስመልክቶ የተለየ ድንጋጌ ማካተቱ ነዉ፡፡ በአዋጁ በትርጉም ክፍል አንቀጽ 2(4) ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ እንደሚቻለዉ አንድ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚቻለዉ የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች የሚቃረን፣ ህግ ያላግባብ የሚተረጉም ወይም ለጉዳዩ አግባብነት የሌለዉን ህግ የሚጠቅስ፣ ለክርክሩ አግባብነት ያለዉ ጭብጥ ሳይያዝ ወይም ከክርክሩ ጋር የማይዛመድ አግባብነት የሌለዉ ጭብጥ ተይዞ የተወሰነ፣ በዳኝነት ታይቶ ሊወሰን የሚገባዉን ጉዳይ ዉድቅ በማድረግ የተወሰነ፣ በፍርድ አፈፃፀም ሂደት ከዋናዉ ፍርድ ጋር የማይገናኝ ትዕዛዝ የተሰጠበት፣ ጉዳዩን አይቶ የመወሰን የዳኝነት ስልጣን ሳይኖር የተወሰነ፣ የአስተዳደር አካል ወይም ተቋም ከህግ ዉጭ የሰጠዉ ዉሳኔ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ዉሳኔ በመቃረን የተወሰነ ሲሆን ነዉ፡፡

በመሆኑም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ በሚል የሰበር አቤቱታ ሲቀርብለት ለአቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉ ጉዳይ መሠረታዊ የህግ ስህተት

የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚቻለዉ ዉሳኔዉ/ትዕዛዙ/ብይኑ ከላይ በዝርዝር ከተመለከቱት ሁኔታዎች ዉስጥ ቢያንስ አንዱን ያሟላ ሆኖ ሲገኝ ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 10 ላይ ከተመለከቱት ድጋጌዎች የምንገነዘበዉ ነዉ። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ለሰበር አቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉ በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠ ዉሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን ሲሆን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታዉን ተቀብሎ በሰበር የማየት ስልጣን የሚኖረዉ ዉሳኔዉ/ትዕዛዙ/ብይኑ የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ዉሳኔ የሚቃረን ሲሆን እንዲሁም አግባብነት የሌለዉን ህግ በመጥቀስ ወይም ህግን ያላግባብ በመተርጎም የተሰጠ ዉሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን ሆኖ ጉዳዩም አገራዊ ፋይዳን የሚመለከት ሲሆን ብቻ ስለመሆኑ የአዋጁ አንቀጽ 10 (1/ሐ/ እና /መ) ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ። ከዚህም የምንረዳዉ የሰበር አቤቱታ የቀረበበት የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ዉሳኔ ከእነዚህ ሦስቱ ሁኔታዎች ዉጪ ባሉት ሁኔታዎች፣ መሠረታዊ የህግ ስህተትን መስፈርት አስመልክቶ በአዋጁ አንቀጽ 2(4) ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ዉስጥ አንዱን የሚያሟላ ሆኖ ቢገኝ እንኳን፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን በሰበር የማረም ስልጣን የሌለዉ መሆኑን ነዉ። ስለሆነም ይህ የፌዴራል ጠቅላይ ሰበር ሰሚ ችሎት የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን ዉሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን በመቃወም የቀረበለት አቤቱታ አዋጅ ቁጥር 1234/2013 ስራ ላይ ከዋለ በኋላ ከሆነ ዉሳኔዉ/ትዕዛዙ/ብይኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን ያለመሆኑን በመወሰን ረገድ እነዚህኑ ልዩ ሁኔታዎች ማለትም በአዋጁ አንቀጽ 10(1/ሐ) ላይ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ከግምት ዉስጥ የማስገባት ኃላፊነት ይኖርበታል።

በተያዘው ጉዳይ ለሰበር አቤቱታው ምክንያት የሆነው ውሳኔ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሰሚው ችሎት ሰኔ 14 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለው ችሎት አመልካች በለውጥ ያገኙትን መሬት ለግራ ጌታ አራጋው ይባቤ በመሬት ለመሬት ለውጥ አሳልፎ በመስጠት በለውጥ የያዙትን መሬት እየተጠቀሙ እያለ የመሬት ለመሬት ለውጥ ውሉ ፈርሶ በለውጥ ውሉ ተጠሪ እጅ ገብቶ የነበረው መሬት እንዲመለስላቸው ያቀረቡትን ክስ የመሬት ለመሬት የለውጥ ውሉ ሊፈርስ የሚችልበት ሕጋዊ ምክንያት የለም በማለት የሰጠው ውሳኔ ከፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10 (1/ሐ/ እና /መ) ስር ከተመለከቱት ድንጋጌዎች አንፃር ሲታይ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም። ስለሆነም ተከታዩ ተወስኗል።

**ውሳኔ**

1. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሰሚው ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 112399 ሰኔ 14 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ ፣ ውሳኔና ትዕዛዝ በፍ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ. 348 (1) መሠረት **ፀንቷል፡፡**

2. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የግላቸውን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ውሳኔ አግኝቶ ስለተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

**ማ/ተ**

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰበር መ/ቁ 231497

ጥቅምት 07 ቀን 2016 ዓ.ም

ዳኞች፡ ብርሃኑ አመነው

ረታ ቶሎሳ

በእውቀት በላይ

ቀነዓ ቂጣታ

ኑረዲን ከድር

አመልካች፡- ፍስሃ ገብሩ ተገኝ አሸማዊ ሰያፍ

ተጠሪዎች፡- 1ኛ/ወ/ሮ ውዳሴ ማርያም ገ/ሚካኤል ጠበቃ ገ/እግዚአር ሄር ተስፋዬ

2ኛ/ የቀድሞ የቂርቆስ ክ/ከ/ ይዞታ አስተዳደር የሽግግር ጊዜ አገ/ኀ/ጽ/ቤት (አሁን የቂርቆስ ክ/ከ መሬት ልማትና አስ/ጽ/ቤት )

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

መዝገቡ ለዚህ ችሎት የቀረበው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 44510 በቀን 10/12/2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት በወሰነዉ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 281946 በቀን 14/10/2014 ዓ.ም በዋለው ችሎት ይግባኙን በመሰረዙ ዉሳኔዉ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል በሰበር ችሎት እንዲታረም አመልካች ባቀረቡት አቤቱታ መነሻ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ሲታይ በስር ፍ/ቤት ከሳሽ የአመልካች አውራሽ የሆኑት እማሆይ ማርጋሬት ሳህሌ ሲሆኑ ተጠሪዎች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡የአመልካች አውራሽ ባቀረቡት ክስ አሮጊት በመሆኔ 1ኛ ተጠሪ እንድትጠረኝ እና እንድትንከባከበኝ በሚል በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 4 የቤት ቁጥር 257 የካርታ ቁጥሩ 32196 ስፋቱ 335 ካ.ሜ የሆነውን ቤት ኑዛዜ ስጦታ የፈፀምኩላት ሲሆን ተጠሪዋም ቤቱን በስሟ ካዞረች በኋላ ጠይቃኝ የማታውቅ በመሆኑ በጋራ ለሚያውቁን ሰዎች ብነግርም ምላሽ አላገኘሁም፤ኑዛዜውን አፍርሼ ሰነዱን ለ2ኛ ተጠሪ በማቅረብ ይዞታው በእጄ ያለና እየኖርኩበት በመሆኑ ስመ ሀብቱን ወደ ስሜ እንዲያዞር ብጠይቀውም ፈቃደኛ አልሆነም፡፡በመሆኑም ለ1ኛ ተጠሪ ያዞርኩት ስመ ሀብት ወደ አመልካች እንዲዞር ለ2ኛ ተጠሪ ትዕዛዝ እንዲሰጥልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

1ኛ ተጠሪ ባቀረቡት መጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ክስ የቀረበበት ቤት ግምቱ 510,000 ሳይሆን ከ10,000,000 (አስር ሚሊዮን) ብር በላይ በመሆኑ ተገቢ ዳኝነት ሳይከፈልበት የቀረበ ክስ መሆኑን፤የአመልካች አውራሽ በአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤት ተመሳሳይ ክስ አቅርበዉ ፍ/ቤቱ ከመጀመሪያ ደረጃ እስከ ሰበር በቅደም ተከተል በመ/ቁ 01946፣ 9359 እና 11431 ክሱ ውድቅ ተደርጎባቸዋል፤በድጋሚ ለፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 09798 የስጦታ ውል ይፍረስልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀው በቀን 10/11/2006 ዓ.ም ፍርድ ቤቱ ክሱን ውድቅ በማድረግ የወሰነ በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 5 መሰረት ክሱ ውድቅ እንዲደረግ፤በፍሬ ነገር ላይ በሰጡት የመከላከያ መልስ የካቲት 7 ቀን 1986 ዓ.ም የተደረገው የቁም ኑዛዜ ቤቱ አብዛኛው ወጪ የተሸፈነው በ1ኛ ተጠሪ ገንዘብ ስለሆነ ሰጥተውኛል፤ኑዛዜው ፈራሽ ሊሆን ይችላል በሚል ሰኔ 19 ቀን 1990 ዓ.ም በውል አዋዋይ አካል ዘንድ ቀርበው ስጦታ በመስጠታቸው በ1ኛ ተጠሪ ስም ነሐሴ 08 ቀን 1990 ዓ.ም ከተዛወረ 27 ዓመት ሞልቶታል፤ስለሆነም ስጦታን በተመለከተ 2 ዓመት ይርጋ ወይም ደግሞ ኑዛዜውን በሚመለከት በፍ/ብ/ህ/ቁ 1845 መሰረት በ10 ዓመት ይርጋ የሚታገድ ስለሆነ ክሱ ውድቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችን በመመርመር የአመልካች አውራሽ ክሰ የቀረበበት ቤት ግምት ዝቅ አድርገው በማቅረባቸው ተጨማሪ የዳኝነት እንዲከፍሉ፤ስጦታ እንዲቀነስ ወይም እንዲሻር የሚቀርብ ጥያቄ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ መቅረብ እንዳለበት የፍ/ብ/ህ/ቁ 2441(1) ላይ የተደነገገ በመሆኑ ስጦታው የካቲት 7 ቀን 1986 ዓ.ም ወይም ሰኔ 19 ቀን 1990 ዓ.ም የተደረገ በመሆኑ በይርጋ ታግደዋል፤እንዲሁም በድጋሚ የቀረበ ክስ በመሆኑ ክሱ ተቀባይነት የለውም በማለት

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ወስኗል፡፡አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ቢያቀርቡም ፍርድ ቤቱ ይግባኙን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 መሰረት ሰርዞታል፡፡አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአመልካች አቤቱታ ይዘት በአጭሩ፤-በስር ፍ/ቤት በነበረው ክርክር ተጠሪ መጥሪያ እንዲደርሳቸው ተፈልገው ባለመገኘታቸው መጥሪያው በመኖሪያ አድራሻቸው ተለጥፎ ስላልቀረቡ እንዲሁም በጋዜጣ ጥሪ ተደርጎላቸው ባለመቅረባቸው የታለፈ መሆኑን ተጠሪ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 78 ድንጋጌ መሰረት ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት የለውም በማለት ፍርድ ቤቱ መጀመሪያ የሰጠውን ብይን መሻሩ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው፡፡ተጠሪ ከሀገር ውጭ መሆናቸውን ምስክር ቆጥረው በጭብጡ መሰረት ሳያስመሰክሩ እኔ የቆጠርካቸው ምስክሮች ሳይሰሙና ምክንያት ሳይገለጽ በዝምታ በማለፍ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ የሚቃረን ወይም ወደ ጎን ትቶ እና ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር በመ/ቁ 53113 እና 50376 የሰጠውን አስገዳጅ ትርጉም ጥሶ መወሰኑ እንዲሁም በህገ መንግስቱ አንቀጽ 25 መሰረት በህግ ፊት እኩል የመታየት መብቴን መጣሱ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው፤በመ/ቁ 09798 ላይ በነበረዉ ክርክር የተጠሪ እናት ጉዳይ እንድታስፈጽምልኝ በሰጠኋት ውክልና ተጠቅማ ከልጇ ጋር በመመሳጠር ቤቴን ቀምታኛለች፡የተደረገው የስጦታ ውል የአመልካች አይደለም፡ ክሱም ስመ ሀብቱ ወደ ስሜ ይዙር የሚል ነበር፡ፍ/ቤቱም አከራክሮ ስጦታው በአግባቡ የተፈረመ ነው በማለት ውሳኔ ሰጠ እንጂ ስጦታዉ ሊሰረዝ የሚገባ መሆን አለመሆኑን እንዲሁም ስመ ሀብቱ የዞረበትን ምክንያትና አግባብነት ላይ የሰጠው ውሳኔ የለም፤በመ/ቁ 09798 እና በመ/ቁ 44510 የቀረበው ክርክር የተለያየ ስረ-ነገርና ጭብጥ ላይ ሆኖ ሳለ አስቀድሞ በፍርድ ያለቀ ነው ብሎ ፍ/ቤቱ ውሳኔ መስጠቱ ሰበር በመ/ቁ 28522 የሰጠውን ትርጉም የሚቃረን ነው፤የስር ፍ/ቤት በፍ/ብ/ህ/ቁ 2441(1) መሰረት በይርጋ ይታገዳል ሲል የሰጠው ውሳኔ ሰበር በመ/ቁ 42346 የሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም ተቃርኖ የተወሰነ በመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታቸውን አቅርበዋል፡፡

የአመልካች አቤቱታ በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ የአመልካች አውራሽ እማሆይ ማርጋሬት ሳህሌ ወ/ማሪያም ደካማ አሮጊት በመሆኔ 1ኛ ተጠሪ ትጠረኛለች ትንከባከበኛለች በሚል በስሜ ተመዝግቦ የሚገኘውን ቤቴን ሰጥቻት በስሟ ካዞረች በኋላ አንድም ቀን ጠይቃኝ የማታውቅ በመሆኑ የስጦታ ውሉ ፈርሶ የቤቱ ስመ ሀብት ወደ ስሜ እንዲዞር በሚል በስር ፍ/ቤት ያቀረቡት አቤቱታ ከ2 ዓመት በኋላ የቀረበ በመሆኑ በይርጋ ቀሪ ነው እንዲሁም ቀደም ብሎ ውሳኔ ተሰጥቶበታል በሚል የተወሰነበትን አግባብነት ቀደም ሲል ተወስኖዋል ከተባለው የመ/ቁ

09798 ይዘት ከፍ/ብ/ህ/ቁ 810(2)፣ 2464(1) እና ሰበር በመ/ቁ 47487 እና በተመሳሳይ ሌሎች መዝገቦች ከተሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም ጋር ለመመርመር ሲባል መዝገቡ ለሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ታዟል፡፡1ኛ ተጠሪ ባቀረቡት መልስ አመልካች ከስጦታ አድራጊ ጋር ምንም ዝምድና ሳይኖራቸው በተንኮል ውክልና በመውሰድ ተጠሪ በሀገር ውስጥ አለመኖራቸውን ሲያውቅ መ/ቁ 44510 በማስከፈት ውሳኔ ያስወሰኑ ቢሆንም እንዳወኩኝ ውሳኔው ተሽሮ ባለሁበት በድጋሚ ክርክር እንዲደረግ በማስረጃ አረጋግጩ ባለሁበት የተሰጠ ውሳኔ በመሆኑ ስህተት የለበትም፤አመልካች ምስክሮቼ አልተሰሙልኝም በማለት የሚያቀርቡት መከራከሪያ በስር ፍ/ቤት ያልቀረበ አዲስ አቤቱታ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም፤ አመልካች እና ወ/ሮ ቀለመወርቅ በቀለ በስር ፍ/ቤት ከተጠሪ ጋር ተከራክረው ሁለቱም ለከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ይግባኛቸው የተሰረዘ ሲሆን ወ/ሮ ቀለመወርቅ በቀለ የሰበር አቤቱታ ለጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 218119 አቅርበው አያስቀርብም ተብሎ ተዘግቶባቸው እያለ የአሁን አመልካች አቤቱታ ያስቀርባል የተባለበት ሁኔታ ተገቢነት የሌለው በመሆኑ ውድቅ ሊደረግ ይገባል፤ሟች ቀደም ሲል ቤቱን በ1988 በኑዛዜ እንዲሁም በ1990 ዓ.ም በህግ ፊት በስጦታ ውል አማካይነት አስተላልፈው እያለ የስጦታ ውሉን ደብቀው ኑዛዜውን ስለሻርኩ የቤቱ ባለቤትነት ይዛወርልኝ የሚል ክስ አቅርበው ውድቅ ሲደረግባቸው የስጦታ ውል አድርገሻል ቢባልም ፊርማው የእኔ አይደለም በማለት ተጠሪን፣ የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንሲ እና ቂርቆስ ክፍለ ከተማ መሬት አስተዳደር ላይ በመ/ቁ 09798 ክስ አቅርበው ውሳኔ ተሰጥቶበት እያለ በድጋሚ በመ/ቁ 44510 ለሁለተኛ ጊዜ ክስ ማቅረባቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 5/3 መሰረት ተገቢነት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡2ኛ ተጠሪ ባቀረበው መልስ አመልካች እኛን የሚመለከት አቤቱታ አላቀረቡም፡በስር ፍ/ቤት እኛ ላይ ቀርቦ የነበረው ክስ ያለአግባብ ቤቱን ወደ 1ኛ ተጠሪ አዙራችኋል የሚል ሲሆን እኛም የአመልካችን ይዞታ ወደ 1ኛ ተጠሪ ያዞርነው አመልካች ለወ/ሮ ጊዮርጊስ ወ/ገብርዔል በሰጡት ውክልና እና በስጦታ ውል መሰረት ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡አመልካች አቤቱታቸዉን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኙ ክርክር ከላይ የተገለፀውን የሚመስል ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ፣ጉዳዩ ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች አንፃር መርምረነዋል፡፡እንደመረመርነውም ለክሱ ምክንያት የሆነዉ ለ1ኛ ተጠሪ የተደረገዉ ኑዛዜ ስለፈረሰ የቤቱ ስመ ሀበት ወደ አመልካቹ አዉራሽ እንደመለስ የሚል ነበር፡፡ይሁንና የስር ፍርድ ቤት ክሱ በሁለት ዓመት ይርጋ ጊዜ ታግዷል እንዲሁም ዳግም

የቀረበ ክስ ነዉ በሚል በብይን ዉድቅ ማድረጉን ዉሳኔዉ ያሣያል፡፡በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትም ጸንቷል፡፡በዚህ ዉሳኔ ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ ህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን ለሰበር ችሎቱ ከተሰጠዉ ስልጣንና ሃላፊነት በማገናዘብ መርምረናል፡እንደሚታወቀዉ የሰበር ችሎቱ ስልጣን የመጨረሻ ዉሳኔ በተሰጠባቸዉ ጉዳዮች ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞ ሲገኝ ይህንኑ በማረም ላይ የተገደበ መሆኑን ከሰበር ስርዓት መሰረታዊ ዓላማ የምንገነዘበዉ ጉዳይ ነዉ፡፡የኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80/3/ሀ ይዘትና መንፈስ ይህንኑ የሚያመለከት ሲሆን ጥር 13 ቀን 2013ዓ.ም የጸደቀዉ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 በሰበር ሊታረም የሚገባ የመጨረሻ ዉሳኔ ላይ መሰረታዊ ህግ ስህተት ተፈጽሟል የሚያሰኙት ሁኔታዎች ምንድናቸዉ ለሚለዉ ትርጉም ሰጥቷል(አንቀጽ 2/4/ይመለከታል)፡፡

በአዋጁ አንቀጽ 4 ስር ከሀ-ሸ እንደተዘረዘረዉ በሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚችል የመጨረሻ ዉሳኔ፣ ፍርድ፣ ብይን ወይም ትእዛዝ ላይ የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች የሚቃረን፣ ህግን አለ አግባብ የሚተረጉም ወይም ለጉዳዩ አግባብነት የሌለዉን ህግ የሚጠቅስ፤ለክርክሩ አግባብነት ያለዉ ጭብጥ ሳይያዝ ወይም ከክርክሩ ጋር የማይዛመድ አግባብነት የሌለዉ ጭብጥ ተይዞ የተወሰነ፣ በዳኝነት ታይቶ ሊወሰን የሚገባዉን ጉዳይ ዉድቅ በማድረግ የተወሰነ፣ በፍርድ አፈጻጸም ሂደት ከዋና ፍርድ ጋር የማይገናኝ ትእዛዝ የተሰጠበት፣ጉዳዩን አይቶ የመወሰን የዳኝነት ስልጣን ሳይኖር የተወሰነ፣የአስተዳደር አካል ወይም ተቋም ከህግ ዉጭ የሰጠዉ ዉሳኔ ወይም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ዉሳኔ በመቃረን የተወሰነ ዉሳኔ ጉዳይ ስለመሆኑ ተደንግጓል፡፡

በዚህ ጉዳይ በአጣሪ ችሎት የተያዘዉ ጭብጥ 1ኛ ተጠሪ ትጠረኛለች ትንከባከበኛለች በሚል በስሜ ተመዝግቦ የሚገኘውን ቤቱን ሰጥቻት በስሟ ካዞረች በኋላ አንድም ቀን ጠይቃኝ የማታውቅ በመሆኑ የስጦታ ውሉ ፈርሶ የቤቱ ስመ ሀብት ወደ ስሜ እንዲዞር በሚል የአመልካች ኡወራሽ በስር ፍ/ቤት ያቀረቡት አቤቱታ ከ2 ዓመት በኋላ የቀረበ በመሆኑ በይርጋ ቀሪ ነው እንዲሁም ቀደም ብሎ ውሳኔ ተሰጥቶበታል በሚል የተወሰነበትን አግባብነት ቀደም ሲል ተወስኖዋል ከተባለው የመ/ቁ 09798 ይዘት ከፍ/ብ/ህ/ቁ 810(2)፣ 2464(1) እና ሰበር በመ/ቁ 47487 እና በተመሳሳይ ሌሎች መዝገቦች ከተሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም ጋር ለመመርመር ሲባል ነዉ፡፡

ስጦታ ገደብ ያለበት ወይም ግዴታ የተጣለበት ሊሆን እንደሚችል በፍ/ብ/ህ/ቁ.2452/1/ ስር ተመልክቷል፡፡ስጦታ ሰጪውም ተቀባዩ ግዴታውን ባለመፈጸሙ ምክንያት ስጦታው እንዲፈርስለት ለመጠየቅ እንደሚችል የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2464/1/ ያስገነዝባል፡፡ዉሉ እንዲፈርስ

የዳኝነት ጥያቄ ሊቀርብ የሚችለዉም ገደብ ሲጣስ ወይም ሲሟላ ወይም ግዴታዉ እንዲፈጸም መጠየቅ ከሚቻልበት ጊዜ ጀምሮ ነዉ፡፡በዚህ ጉዳይ በክሱ የተጠቀሰዉ ፍሬነገር ኑዛዜውን አፍርሼ ሰነዱን ለ2ኛ ተጠሪ በማቅረብ ይዞታው በእጄ ያለና እየኖርኩበት በመሆኑ ስመ ሀብቱን ወደ ስሜ እንዲያዞር ብጠይቀውም ፈቃደኛ አልሆነም፤ በመሆኑም ለ1ኛ ተጠሪ ያዞርኩት ስመ ሀብት ወደ አመልካች እንዲዞር ለ2ኛ ተጠሪ ትዕዛዝ እንዲሰጥልኝ የሚል ሲሆን ፍሬነገር የማጣራትና የማረጋገጥ ስልጣንና ሃላፊነት በህግ የተሰጠዉ የስር ፍርድ ቤት እንዳረጋገጠዉ በ1986 ዓ.ም የተደረገዉ ኑዛዜ በ1990 ዓ.ም በተደረገ ስጦታ ዉል መተካቱንና የስጦታ ዉል እንዲፈርስ የአመልካቹ አዉራሽ በመ/ቁ/09798 ላይ ክስ አቅርበዉ ዉድቅ ተደረገባቸዉ መሆኑን ነዉ፡፡ከዚህ መገንዘብ የሚቻለዉ ተናዛዧ ያደረኩትን ኑዛዜ አፍርሻለሁ ቢሉም ኑዛዜዉ ቀሪ ሆኖ በስጦታ ዉል የተተካ መሆኑንና የስጦታ ዉል ሊፈርስ አይገባም ተብሎ ፍርድ የተሰጠበት እና ይህም በይግባኝ ያልተለወጠ መሆኑን ያሣያል፡፡ይህም ሆኖ የስር ፍርድ ቤት ክሱን ዉድቅ ያደረገዉ በሁለት ምክንያት ነዉ፡፡አንደኛዉ በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 2441(1) መሰረት ክሱ በሁለት ዓመት ይርጋ ታግዷል የሚል ሲሆን ሁለተኛዉ ደግሞ ክሱ የቀረበዉ ለሁለተኛ ጊዜ ነዉ የሚል ነዉ፡፡

ይርጋ በተመለከተ የተጠቀሰዉ ድንጋጌ ለክርክሩ አግባብነት አለዉ ወይ የሚለዉ ሲታይ ክሱ ተጠሪ ስጦታ ሰጪን አላጠረችም፤ አልጠየቀችም የሚል ሲሆን ፍ/ብ/ህግ ቁጥር 2441(1) ስር) የተደነገገዉ ሁለት ዓመት ይርጋ  ጊዜ ተፈጻሚ የሚሆነዉ የስጦታ ዉሉ በመንፈሽ መጫን የተደረገ ነዉ በሚል የሚቀርብ ክስ በሚመለከት ስለመሆኑ ሰበር ችሎት በመ/ቁ 42346 ላይ ሰጠዉ ገዥ ዉሳኔ ያሣያል፡፡ስለዚህም ከክሱ ምክንያት አኳያ ሲታይ ይህ የይርጋ ድንጋጌ ለዚህ ክስ አግባብነት የለውም፡፡

ክሱ ዉድቅ የተደረገበት ሁለተኛዉ ምክንያት ስጦታ እንዲፈርስ ከዚህ ቀደም ክስ ቀርቦ ዉድቅ ተደርጓል በሚል ፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር5(3) ምርኩዝ ተደርጎ ነዉ፡፡በመሠረቱ የክርክር አመራር ሥርዓት የተዘረጋበት ዓይነተኛ ዓላማ ክርክሮች በአነስተኛ ወጪ፣ጊዜ እና ጉልበት እልባት እንዲያገኙ ማስቻል መሆኑ እሙን ነዉ፡፡ከዚህ ዓላማ አንጻር በፍትሓብሔር ሥነሥርዓት ህግ ከተካተቱት ጽንሰ ሃሳቦች አንዱ የመጨረሻ ፍርድ ያገኘ ጉዳይ ላይ ዳግም ክስ ሊቀረብ አይገባም /Res judicata/ የሚለው መርህ ሲሆን ይህ ጽንሰ ሀሣብ በ1958ቱ የፍትሓ ብሔር ሥነ ስርዓት ሕጋችን ውስጥ በቁጥር 5 ድንጋጌ ስር በግልጽ ተቀምጦ እናገኘዋለን፡፡በዚህ ድንጋጌ መሠረት የመጨረሻ ፍርድ ያገኙ ጉዳዮች ማለት በማናቸውም መልክ በሕግ በተቋቋመ ፍ/ቤት ወይም የዳኝነት ስልጣን በተሰጠዉ አካል ቀርበው የመጨረሻ ውሳኔ ያገኙ ጉዳዮችን የሚሸፍን መሆኑንና በፍርድ፣ በብይን፣ በውሣኔ፣ በትአዛዝ፣ ወይም ጊዜያዊ አገልግሎት ባልሆነ

*ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ  ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም  ለግንዛቤ እንጂ*
*ለፍርድ  አፈጻጸም  ዓላማ  አያገለግልም*

ትእዛዝ የመጨረሻ ውጤት አግኝተው በሌላ መልክ መንቀሣቀስ የማይችል የክርክር ነጥቦችን ሁሉ የሚያጠቃልል ጉዳይ መሆኑን እንገነዘባለን፡፡

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ 5/1/1 ሥር በተመለከተው አኳኋን አንድ ጉዳይ አስቀድሞ በፍርድ ያለቀ ነው ለማለት መረጋገጥ ያለባቸዉ አራት መሰረታዊ ነጥቦች ናቸዉ፡፡እነሱም ጉዳዩ በህግ ስልጣን የተሰጠዉ አካል የመጨረሻ ዉሳኔ ያገኘ መሆን ፣ቀድሞ የቀረበዉ ክስ ስረ ነገር እና ለዉሳኔ መሰረት የተደረገዉ ጭብጥ አሁን ከቀረበዉ ክስ ጋር አንድ ወይም ተመሳሳይ መሆን ፣እንዲሁም ተከራካሪዎቹ አንድ መሆን ወይም ከቀድሞ ተከራካሪዎች መብት ያገኙ ሶስተኛ ወገኖች ከሆኑ በዚያዉ ነገር ሁለተኛ ክስ ማቅረብ እንደማይችሉ ነዉ፡፡በመሆኑም በቀረበው ክስ በቀድሞው ክርክር ተሣታፊ የነበሩ ወገኖች ወይም ከእነሱ መብት በተላለፈላቸው ወገኖች መካከል የሚካሄድ መሆን አለመሆኑ፣በሁለተኛው ክስ የቀረበዉ የፍሬ ነገር ጉዳይና ጭብጥ ከመጀመሪያው ጋር ተመሣሣይ መሆን አለመሆኑና የመጨረሻ ፍርድ ያረፈበት መሆን አለመሆኑ ተጣርቶ ጉዳዩ የመጨረሻ ፍርድ ያገኘ ከሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 5/1/ እና 244(2)ለ ድንጋጌ መሰረት በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ መዘጋት አለበት፡፡

ከዚህ አኳያ የስር ፍርድ ቤት ክሱን በብይን ሲዘጋ የጠቀሰዉ መ/ቁ/09798 ዉሳኔ ይዘት ሲታይ ሰኔ 19 ቀን 1990ዓ.ም ተደረገ የተባለዉ የስጦታ ዉል ሀሰተኛ ነዉ በሚል እንዲፈርስ የተጠየቀበት መሆኑን፤ ፍርድ ቤቱ ለዉሳኔ መሰረት ያደረገዉ ጭብጥ የስጦታ ዉል አለ ወይስ የለም፤የስጦታ ዉሉን በመመዝገብና ስም በማዛወሩ ሂደት የተፈጸመ ስህተት አለ ወይስ የለም የሚሉና ተያያዥ ጭብጦች ስለመሆኑ የፍርዱ ይዘት ያሣያል፡፡በአሁኑ ክስ የኑዛዜ ስጦታ እንዲፈርስ የተጠየቀበት ምክንያት 1ኛ ተጠሪ ስጦታ ሰጪን እንዲትጦር እና እንደትንከባከብ የተጣለባትን ግዴታ አልተወጣችም በሚል ምክንያት መሆኑን መዝገቡ ያሣያል፡፡ይህ ከሆነ ደግሞ ዉሳኔ የሚፈልገዉ ጭብጥ በስጦታ ዉሉ የተቀመጠ ግዴታ አለ ወይስ የለም፤ አለ ከተባ ተጠሪ ግዴታዋን ተወጥታለች ወይስ አልተወጣችም የሚል እና ህጋዊ ዉጤቱን የሚመለከት ነዉ፡፡የክርክሩ ጭብጥ ይህ ከሆነ ደግሞ በዚህ ረገድ ቀደም ሲል መ/ቁ/09798 የክርክር ጭብጥ ሆኖ ዉሳኔ ስለመሰጠቱ መዝገቡ ስለማሳይ በተመሳሳይ ጭብጥ ዉሳኔ ተሰጥቷል ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡ በመሆኑም ምንም አንኳን ተከራከሪ ወገኖች እና ለክርክሩ ምክንያት የሆነዉ ስረነገር ተመሳሳይ ቢሆንም በሁለቱ መዝገቦች ላይ ዉሳኔ የሚፈለግዉ ጭብጥ የተለያየ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ የስር ፍርድ ቤት ለዉሳኔዉ ምርኩዝ ያደረገዉ የፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 5(3) ስለመሆኑ በመ/ቁ/44510 ላይ በቀን 10/12/2013ዓ.ም የሰጠዉ ብይን ይዘት ያሣያል፡፡ድንጋጌዉ የሚለዉ በቀድሞ ክርክርና ሙግት ላይ በግልጽ ዳኝነት ተጠይቆበት ጥያቄዉ ተቀባይነት ሳያገኝ የታለፈ እንደሆን በዚህ ቁጥር አግባብ ዳኝነት

እንደተከለከለ ይቆጠራል፡፡ይህም ማለት ከሳሹ በግልጽ ዳኝነት የጠቀበትን ጉዳይ ፍርድ ቤቱ በዝምታ ካለፈዉ እንደተነፈገ የሚታይ እና ምናልባትም ዉሳኔዉ በይግባኝ ካልታረም በዚያዉ ጉዳይ ዳግም ዳኝነት ሊጠየቅበት ማይችል እንደሆነ ነዉ፡፡ስለዚህም ክሱ ለሁለተኛ ጊዜ የቀረበዉ ነዉ ወይስ አይደለም የሚለዉ ከስረ ነገሩ አኳያ ሲታይ አንድም በዚያዉ ስረነገር ጭብጥ ተይዞ ዉሳኔ የተሰጠበት መሆኑን ወይም በግልጽ ዳኝነት ተጠይቆ ፍርድ ቤቱ በዝምታ ያለፈዉ ከሆነ ነዉ፡፡በዚህ ረገድ የክርክሩ መሰረት የኑዛዜ ስጦታ አሁን በቀረበዉ ክስ ላይ የተገለጸዉ ስረነገር በቀድሞ ክስ ላይ ዳኝነት ተጠይቆበት ተቀባይነት እንዳላገኘ የስር ፍርድ ቤት ያረጋገጠዉ ጉዳይ መሆኑን ከብይኑ ይዘት ተገንዝበናል፡፡ይህ ከሆነ ደግሞ የፍ/ብ/ስ/ስህግ ቁጥር 5(3) ምርኩዝ በማድረግ ለሁለተኛ ጊዜ የቀረበ ክስ ነዉ ማለቱ የሚነቀፍበት ምክንያት የለም፡፡

ሲጠቃለል ስጦታ ተቀባይ ግዴታዋን አልተወጣችም በሚል የኑዛዜ ስጦታ ዉል እንዲፈርስ የቀረበን ክስ የሥር ፍርድ ቤት በሰጠዉ ብይን በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 2441(1) ስር የተደነገገዉን ሁለት ዓመት ይርጋ ጊዜ ገደብ ያለቦታዉ መጠቀሙ ስህተት ነዉ ብለናል፡፡ይሁንና ሁለተኛዉ ምክንያት ማለትም በዚሁ ጉዳይ ቀደም ሲል ዳኝነት ተጠይቆበት ተቀባይነት አላገኘም በሚል የፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 5(3) በመጠቀስ የሰጠዉ ብይን ክፍል ህጉን ያገናዘበ ነዉ ከሚባል በስተቀር ስህተት ነዉ ለማለት የሚያስችል ምክንያት አላገኘንም፡፡በሌላም በኩል ሌላኛዋ ወራሽ ለሰበር ያቀረቡት አቤቱታ በመ/ቁ/ 218119 ለሰበር አያስቀርብም ተብሎ መዘጋቱን መዝገቡ ያሣያል፡፡በመሆኑም ክሱ ለሁለተኛ መቅረቡ እስከተረጋገጠ ድረስ ይህ ምክንያት ብቻዉን ክሱን ዉድቅ ለማድረግ የሚያስችል በመሆኑ ከፍ/ብ/ስ/ስህግ ቁጥር (3)፤244(2/ለ) እና ፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4) እና 10 ስር ለሰበር ችሎቱ ከተሰጠ ስልጣን ጋር ተገናዝቦ ሲታይ በዉሳኔዉ ላይ በህግ አተገባበርም ሆነ አተረጓጎም ረገድ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚያስችል ምክንያት የለም ብለናል፡፡ በመሆኑም የሚከተለዉ ተወስኗል፡፡

<u>ዉሳኔ</u>

1ኛ/ በዚህ ጉዳይ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠዉን ብይን በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/281946 ላይ በቀን 14/10/2014ዓ.ም የሰጠዉ ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሠረት ጸንቷል፡ ይጻፍ፡፡

2ኛ/ክርክሩ ያስከተለዉን ዉጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ በዳኞች እረፍት ጊዜ ተሰርቶ ዛሬ ጥቅምት 9 ቀን 2016 ዓ.ም ተነበበ

**መዝገቡ ዉሳኔ ያገኘ ስለሆነ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/ተ

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ.መ.ቁ. 229641

ጥቅምት 5 ቀን 2016 ዓ.ም

ዳኞች፡- 1. ብርሃኑ አመነዉ

2. በእዉቀት በላይ

3. ቀነዓ ቂጣታ

4. ተሾመ ሽፈራዉ

5. ኑረዲን ከድር

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ባህር ትራንስፖርትና ሎጂስቲክ አገልግሎት ድርጅት ---ነገረ ፈጅ አሸናፊ ነጋ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ዋለ ኤሌክትሮ መካኒካል ሥራዎች ----- ጠበቃ ቃኛው ጥሩነህ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

ይህ የውል ግዴታ ባለመወጣት ለደረሰ ጉዳት ካሳ እና ኪሣራ ይከፈለኝ ክርክር የተጀመረዉ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች የሥር ከሳሽ፣ የአሁን ተጠሪ የሥር ተከሳሽ ሆኖ ሲከራከሩ ነበር፡፡ ይህ ጉዳይ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ አመልካች የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ.213668 ሚያዚያ 30 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልን በማለት በማመልከቱ ነዉ፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ አመልካች በሥር ፍ/ቤት ባቀረበዉ የክስ አቤቱታ ከሳሽ በሞጆ ወደብ ተርሚናል በመጀመሪያ ዙር ግንባታ ወቅት በቀድሞ የውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት የተሠሩ የኤሌክትሪክ ሥራዎች አገልግሎት መስጠት ባለመቻላቸው ለማሰራት ጥናት በማስጠናት እና በግኝቱ መሠረት ለማሰራት በማሰብ ተጫራቾች ባወዳደረው መሠረት ተከሳሽ በማሸነፍ የብልሽት ምርመራ የመለየት ጥናት ለመሥራት ብር 3,403,640 (ሦስት ሚሊዮን አራት መቶ ሦስት ሺህ) እና በጥናቱ መሠረት የማስተካከያ ሥራውን በአግባቡ ያልተገጠሙ ሥራዎች ካሉ በአግባቡ መግጠም፤ የተጎዱ ዕቃዎች ካሉ ዕቃዎቹን በመግዛት የመግጠም

የማስተካከያ ሥራ መሥራትና አጠናቆ ኤሌክትሪክ ሥራ በአግባቡ የተከናወነ መሆኑን ማረጋገጥና ተያያዥ ተግባራትን ለማከናወን ሥራ ብር 3,503,400 (ሦስት ሚሊዮን አምስት መቶ ሦስት ሺህ አራት መቶ) የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 1,036,056 (አንድ ሚሊዮን ሰላሳ ስድስት ሺህ አምሳ ስድስት) አካቶ በአጠቃላይ በብር 7,943,096 (ሰባት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ አርባ ሦስት ሺህ ዘጠና ስድስት) እ.ኤ.አ ከተከሳሽ ጋር ሴፕቴምበር 15/2015 (በ04/1/2008 ዓ.ም) ውል ተፈራርመናል። የመጀመሪያ ዙር ጥናት ሠርቶ በማጠናቀቁ በውሉ የተገለጸው ገንዘብ ተከፍሎታል። ተከሳሽ የማስተካከያ ሥራ እንዲቀጥል የሥራ ትህዛዝ ቢሰጠውም ፈቃደኛ ባለመሆኑ ውይይት ቢደረግም ባለመፈጸሙ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ግንቦት 22 ቀን 2009 ዓ.ም ውሉ እንዲቋረጥ ተደርጓል።

ተከሳሽ ጨረታን ሲሳተፍና አሸንፎም ሲዋዋል የጨረታ ሰነዱን በገዛበት ወቅት ስለ ግንባታ ሳይቱ ምንነት ስለሚገዙ ዕቃዎች  ግንዛቤ የወሰደ ሆኖ እያለ ሥራውን ሰርቶ ማስረከብ ሲገባው ቀጣዩን ማስተካከያ ሥራ ለመሥራት የዋጋ ማስተካከያ ካልተደረገ አልሰራም የዉሉን ድንጋጌዎች እና አስገዳጅ የሰበር ዉሳኔን የሚቃረን በመሆኑ፣ ተከሳሽ የዉል ግዴታዉን ባለመወጣቱ ከሳሽ ሌላ ጨረታ በማዉጣት በብር 14,91,0000 (አሥራ አራት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ አሥር ሺህ) በማሰራት ተጨማሪ ወጪ እንዲናወጣ ስላደረገን፤ በዉሉ መሰረት ቅጣት እና ተጨማሪ ሥራ ለማስጨረስ ያወጠናዉን ወጪ በአጠቃላይ ብር 3,177,238.40 (ሦስት ሚሊዮን አንድ መቶ ሰባ ሰባት ሺህ ሁለት መቶ ሰላሳ ስምንት 40/100) ካሳ ማስጠንቀቂያ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ ጋር እንዲከፍል በማለት ዳኝነት ጠይቋል።

ተጠሪ በዚህ ክስ ላይ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያነሳ ሲሆን፣ በፍሬ ነገር ያቀረበዉ መልስ፡ ምህራፍ አንድ ጥናት ማድረግና ጉድለት የመለየት ሥራ የመሥራትና የጥናቱ ግኝቱን ለአሠሪው ማቅረብ በመጨረሻም አነኚህ ጉድለቶች የሚታረሙበት የእርምት ስራ መጠቆም በመሆኑ ይህ ተሰርቶ ገንዘብ ተከፍሎኛል። ሁለተኛውን ምዕራፍ የቀረበው ዘገባ የአሰሪው መ/ቤት ሲያጸድቀውና ሥራው እንዲቀጥል ትህዛዝ ሲሰጥ የእርምት የማስተካከያ ትግበራ ሥራ መሥራት ቢሆንም ከሳሽ በዚህ አግባብ አጽድቀው ወደ ሥራ እንድገባ አላደረገም። ለሥራዉ አለመሰራት ጥፋቱ የከሳሽ ስለሆነ የተጠቀሰዉን ገንዘብ መክፈል የለብንም። የከሳሽ ክስ ተቀባይነት አለዉ የሚባልበት አግባብ አለ የሚባል ሆነ ቅጣቱ መታሰብ ያለበት በምዕራፍ አንድ ክፍያ ላይ ሳይሆን በምዕራፍ ሁለት ክፍያ ላይ ነዉ። የዉሉ ጊዜ የተጠናቀቀዉ ከሳሽ በቀረበዉ ጥናት ላይ በጊዜ ምላሽ ባለመስጠቱ ነዉ። በመሆኑም ከሳሽ በተሰጠዉ ስልጣን መሰረት ጥናቱን አጽድቆ ሥራዉ እንዲቀጥል ትዕዛዝ መስጠት ሲገባዉ ይህን ባለማድረጉ ችግሩ የተፈጠረ ስለሆነ ክሱ ዉድቅ እንዲሆንልን እንዲወሰንልን በማለት ተከራክሯል።

ከዚህ በኋላ የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት ግራ ቀኙን በመስማት፣ በተከሳሽ የተነሳዉን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በብይን ዉድቅ በማድረግ፣ የሰዉ ምስክሮችን በመስማት እና የሰነድ ማስረጃ በመመርመር ባሳለፈዉ ዉሳኔ ተከሳሽ በገባዉ ምዕራፍ አንድ የጥናት ሥራ ታህሳስ 4 ቀን 2008 ዓ.ም አጠናቆ በዉሉ አንቀጽ 1 መሰረት ሪፖርት ያቀረበ ሲሆን፣ ከሳሽ በተለያየ ጊዜ ሪፖርቱን መነሻ በማድረግ ስብሰባ ሲያደርግ እንደነበር መስከረም 4 ቀን 2009 ዓ.ም የተጻፈዉ ቃለ ጉባኤ ያሳያል። ከዚህ ቃለ ጉባኤ መረዳት እንደሚቻለዉ ሪፖርቱን አይተዉ ተገቢ አስተያየት እንዲያቀርብ የተቋቋመዉ ባለሙያዎችን ያቀፈ ኮሚቴ ባቀረበዉ አስተያየት በመጀመሪያው ውል ላይ ተጨማሪ 28.12 በመቶ በተጨማሪ ሥራው ተፈቅዶ ሥራው ተሰርቶ ፕሮጀክቱ ለተፈለገው ዓላማ

እንዲውል አስተያየት ያቀረበ ቢሆንም በውሉ አንቀጽ መሠረት ሪፖርቱ ስለመጽደቁ በጽሁፍ ለተከሳሽ የደረሰ መሆኑን የሚያሳይ ነገር የለም። ተከሳሽ ለሁለቱም ምዕራፎች አስቀድሞ ዋጋ ያስቀመጠ ሲሆን፣ ዉል በተዋዋይ ወገኖች መካከል ሕግ መሆኑን የፍ/ብ/ሕ/ቁ.1731 ድንጋጌ ያስገነዝባል። ነገር ግን ከሳሽ በአንድ በኩል ጥናቱን ተቀብያለሁ እያለ በሌላ በኩል በጥናቱና በዉላቸዉ አንቀጽ 15.8 መሰረት የሥራ ለውጦች ሲኖር የውሉን እስከ 30 በመቶ ድረስ ማስተካከያ ሊደረግ እንደሚችል ተመልክቷል። ይህ የሥራ ለዉጥ ሊከሰት የቻለዉ በተከሳሽ ጥፋት አለመሆኑን ከተያዘዉ ቃለ ጉባኤ መደረት ይቻላል። ሁለተኛዉ ምዕራፍ ሥራ ሳይሰራ ለመቅረቱ ምክንያት የከሳሽ የበላይ ኃላፊዎች ሪፖርቱን ሳያጸድቅ በመቅረቱ መሆኑን እና በጥናቱ መሰረት ሥራ ባይሰራ በአገር ላይ ችግር የሚያመጣ መሆኑንና ከሳሽ ቸልተኛ መሆኑን ከቃለ ጉባኤዉና ከምስክሮች ቃል መረዳት ይቻላል። ይሁን እንጂ ከሳሽ በቃለ ጉባኤ የቀረበዉን የዉሳኔ ሃሳብ ተከሳሽ የተስማመበትን 28.12 ጭማሪ በማድረግ ስራዉን ማሰራት ሲገባዉ ሌላ ጨረታ በማዉጣት ላልተፈለገና ለተጋነነ ወጪ ራሱን የዳረገ መሆኑ ተረጋግጧል። ከሳሽ የቀረበውን ሪፖርት ተቀብሎ ግን በሪፖርቱ መሠረት አይሰራም ማለቱ በተቋቋመው ኮሚቴ መሠረት ጭማሪ ክፍያ ተደርጎ ይሠራ የሚለውን አስተያየት ባለመቀበሉ ተከሳሽ በጥናቱ መሠረት ካልተሠራ በሀገር ላይ ችግር እንደሚያመጣ መገለጹ በባለሙያዎች የተረጋገጠ በመሆኑ፤ በእነዚህ ምክንያቶች ተከሳሽ ጥፋተኛ አይደለም በማለት ወስኗል።

ከሳሽ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱም ይግባኙን በትዕዛዝ ዉድቅ በማድረግ የሥር ፍ/ቤትን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል። የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ነዉ።

አመልካች በ21/10/2014 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ፡ በግራ ቀኞችን መካከል በተደረገዉ ውል አንቀጽ 1.1 /ለ/ ላይ በግልጽ እንደተመለከተው ተጠሪ የምህራፍ 2ን ሥራ መሥራት ያለበት ቀድሞ በውሉ ልዩ ሁኔታ /scc/ ላይ በተመለከተው Specifications and Drawings ወይም ሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች በጽሁፍ በሚያደርጉት ስምምነት ብቻ ስለመሆኑ በግልጽ በማያሻማ አግባብ ተመላክቷል። በመሆኑም ሁለቱ ወገኖች አንደኛው ወገን የውሉ ዋጋ ማሻሻያ ረቂቅ ምክረ አሳብ ባይቀበል ቸልተኛ ሊባል የሚችልበት ሕጋዊ ሆነ የውል መሠረት የለውም። አመልካች ተጠሪ በገባው ውል መሠረት መስራት የሚችለው ሥራ 28.12 በመቶ የዋጋ ማስተካከያ ማሻሻያ አላደርገም ማለቱ የውል መብቱን ቢያሳይ እንጂ ቸልተኝነት መደረጉ ከውል መሠረታዊ ባህሪና ዓላማ እና ውል በተዋዋይ ወገኖች መካከል ሕግ ነው የሚለውን መርህ የሚቃረን ነው። የሥር ፍ/ቤት በፍርዱ ላይ በውሉ አንቀጽ 15.8 መሠረት የስራ ለውጥ ሲኖር የውል ዋጋውን እስከ 30 በመቶ ማስተካከል ይፈቅዳል እና የሥራ ለውጡ የተከሰተው በተጠሪ ጥፋት አይደለም ማለቱ ከምን ተነስቶ እንደሆነ እና የዋጋው ማስተካከያ ለማድረግ አስገዳጅ ምክንያት እንደሆነ በቂ ትንታኔ አልሰጠም። የሥር ፍ/ቤት ተጠሪ ለጥናቱም ሆነ ለጥፈናዉ ዋጋ በማስቀመጥ ዉል የገባ መሆኑንና ይህም ዉል ሕግ መሆኑን ተቀብሎ ሳለ አመልካች ጥናቱን ተቀብያለሁ እያለ በጥናቱ መሰረት ሊሰራ አይገባም ማለቱ ከዉል መሰረታዊ ሃሳብ ጋር የሚጋጭ ነዉ በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ በተዋዋይ ወገኖች መካከል ያለዉን የዉል ዓይነት ያላገናዘበ ነዉ። አመልካች የመጀመሪያ ምዕራፍ ሥራ (ጥናት) ተቀብሎ ክፍያ መፈጸሙ ተጠሪ በገባዉ ዉል መሰረት ምዕራፍ ሁለት ሥራዎችን እንዲሰራ ለማድረግ ነዉ። ተጠሪ በዉላችን ከተመለከተዉ ዉጭ በጥናቱ ላይ የተመለከቱትን ነገሮች የስራ ዋጋ ሊሻሻልኝ ይገባል በማለት የመጠየቅ መብት የለዉም። የሥር ፍ/ቤት ከዉል መሰረታዊ ባህሪና ዓላማ በሚቃረን ሁኔታ ዉላችን

ወደ ጎን በመተዉ፣ በጥናቱ መሰረት ካልተሰራ የሚያስከትለዉን አገራዊ ችግር ምን እንደሆነ ተጠሪ ባላስረዳበት፣ የዉሉን ዓይነትና የተለየ ባህሪ ሳይገነዘብ የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ የሥር ፍ/ቤቶች ዉሳኔ ተሽሮ በክሳችን የተጠቀሰዉን ገንዘብ እንዲከፍለን እንዲወሰንልን በማለት አመልክቷል።

የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን በማየት ፣ተጠሪ በተገባው ውል መሠረት የመጀመሪያውን ዙር ሰርተው በማጠናቀቅ ክፍያውም ተፈጽሞላቸው እያለ የውሉ ሁለተኛ ምህራፍ የሆነውን ማስተካከያ ስራውን በሚመለከት ከውሉ ውጪ 28.12 የዋጋ ማስተካከያ እንዲደረግ የቀረበውን አስተያየት አመልካች ሳይቀበል በመቅረቱ ቸልተኝነቱን የሚያሳይ ነው፤ በቀረበው ጥናት መሠረት ባሠራ ሀገራዊ ችግር ስለሚያመጣ ተጠሪ ጥፋተኛ ባለመሆኑ የተጠየቀውን ካሳ ሊከፈል አይገባም በሚል የተወሰነበትን አግባብነት ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1731፤1790፤2090 ለማጣራት ሲባል የሰበር አቤቱታው ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ባዘዘዉ መሰረት ተጠሪ ጥቅምት 3 ቀን 2015 ዓ.ም የተሻሻለ መልስ አቅርቧል። የመልሱም ይዘት ባጭሩ፡ የሥር ፍ/ቤቶች በዚህ ጉዳይ በግራ ቀኛችን መካከል የተደረገዉን ዉል እና በሕግ አግባብ አጣርቶ የሰጡት ዉሳኔ ምንም ዓይነት መሰረታዊ የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት ስለሆነ የሰበር አቤቱታዉ ዉድቅ ሆኖ የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ እንዲጸናልን በማለት በዝርዝር ተከራክሯል። አመልካች በ13/8/2013 ዓ.ም በተጻፈ የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታዉን በማጠናከር ተከራክሯል።

የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል። በአመልካች እና በተጠሪ መካከል መስከረም 4 ቀን 2008 ዓ.ም በተደረገዉ ዉል መሰረት አመልካች ለማሰራት የፈለገዉን የኤሌክትሪክ ሥራዎችን ተጠሪ በዉሉ በተጠቀሰዉ ዋጋ በምዕራፍ አንድ ጥናት ለማድረግ እና በምዕራፍ ሁለት ጥገና ለማከናወን ለመስራት ግዴታ የገባ መሆኑን የሥር ፍ/ቤት የዉሳኔ ግልባጭ ያሳያል። ይህ ዉል በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1731 (1) መሰረት በግራ ቀኛቸዉ መካከል ሕግ መሆኑ ግልጽ ነዉ። ተጠሪ በዉሉ መሰረት የምዕራፍ አንድ የጥናት ሥራዉን በማጠናቀቅ ሪፖርቱን ለአመልካች በማቅረብ ክፍያ የተፈጸመለት መሆኑን ግራ ቀኙን ያላከራከረ ጉዳይ ነዉ። ነገር ግን ግራ ቀኛቸዉን ያከራከረዉ የምዕራፍ ሁለት የጥገና ሥራ ጉዳይ ነዉ። ይህን ሥራ በተመለከተ ተጠሪ በጥናቱ መሰረት መሰራት ስላለበት የዋጋ ማስተካከየ ሊደረግ ይገባል በማለት ይህን ጥያቄዉን በሪፖርቱ ላይ ጠቅሶ ለአመልካች ያቀረበ ሲሆን፤ አመልካች በበኩሉ በጥናቱ መሰረት ሳይሆን በዉላችን ላይ በተጠቀሰዉ ዋጋ መሰረት ሊሰራ ይገባም የዋጋ ማስተካከየ መደረግ የለበትም በማለት ተከራክሯል።

ከዚህ አንጻር የሥር ፍ/ቤት በተቋቋመዉ ኮሚቴ የቀረበዉን የዉሳኔ ሃሳብ እና ባለሙያዎች ቀርበዉ የሰጡትን የምስክርነት ቃል መሰረት በማድረግ በፍሬ ነገር ደረጃ ያረጋገጠዉ ሁለተኛዉ ምዕራፍ የጥገና ሥራ በጥናቱ በተመለከተዉ አግባብ መሆን እንደሚገባዉ፣ በጥናቱ ላይ በተለየዉ አግባብ ካልተሰራ መብራቱ ሊበራ እንደማይችል፣ እንዲሁም በጥናቱ መሰረት ካልተሰራ ሀገራዊ ችግር የሚያስከትል መሆኑን አመልክቷል።

በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የተደረገዉ ዉል ሕግ ቢሆንም አመልካች የኤሌክትሪክ ሥራዎች ያለበት ችግር በጥናት እንዲለይ ያደረገበት ምክንያት ጥናቱ የለያቸዉን ችግሮች ጠግኖና ገጥሞ አስተካክሎ ጥገና በማድረግ

መብራት እንዲበራ ለማድረግ እንደሆነ ይገመታል፡፡ ነገር ግን ከጥናቱ በፊት የጥናቱን ዉጤት ታሳቢ ሳያደርግ የጥገና ዋጋ ላይ ተስማምተዉ ዉል ማሰራቸዉ ግልጽ ነዉ፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ ጉዳይ አስተያየቱን ያቀረበዉ ኮሚቴ እንደገለጸዉና በኮሚቴዉ የተሳተፉት ባለሙያዎች በፍ/ቤት ቀርበዉ የምስክርነት ቃላቸዉን እንደሰጡት በጥናቱ መሰረት ካልተሰራ ሀገራዊ ችግር እንደሚያከትል፣ መብራትም እንደማይበራ የሙያ ምስክርነት ቃላቸዉን መስጠታቸዉን የሥር ፍ/ቤት የዉሳኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡ ይህ ደግሞ የሙያ ጉዳይ በመሆኑ፣ የዘርፉን ሙያ በሚቃረን አግባብ ሥራዉ እንዲሰራ ማድረግ ተቀባይነት የለዉም፡፡ ለዚህ መፍትሔ ይሆን ዘንድ ኮሚቴዉ ባቀረበዉ የዉሳኔ ሃሳብ በዉሉ አንቀጽ 15.8 መሠረት የስራ ለውጦች ሲኖሩ የውሉን ዋጋ እስከ 30 በመቶ ድረስ ጭማሪ ማስተካከያ በማድረግ ሥራዉን ማሰራት እንደሚቻል ስለሚያመለክት፤ ሥራዉ በጥናቱ መሰረት መሰራት ስለሚገባዉ ጥናቱ የሥራ ለዉጥ መኖሩን ስለሚያመለክት የዉሉን ዋጋ 28.12 ጭማሪ ማስተካከያ በማድረግ ሥራ እንዲሰራ እንዲደረግ ነዉ፡፡ አመልካች ግን ይህን የኮሚቴዉን የዉሳኔ ሃሳብ ባለመቀበል ጨረታ በመዉጣት በከፍተኛ ወጪ ሥራዉን ያሰራ መሆኑን መዝገቡ ያሳያል፡፡

በመሆኑም አመልካች ከተጠሪ ጋር ያደረገዉን ዉል ይዘትና ዓላማ እንዲሁም የቀረበዉን የጥናት ዉጤትና የተቋቋመዉ ኮሚቴ ያቀረበዉን የዉሳኔ ሃሳብ ታሳቢ በማድረግ፣ በጥናቱ መሰረት በዉሉ ከተመለከተዉ በላይ የሥራ ለዉጦች መኖራቸዉ እስከተረጋገጠ ድረስ፤ በዉሉ አንቀጽ 15.8 መሰረት የዉሉን ዋጋ 28.12 ጭማሪ ማስተካከያ በማድረግ ሥራዉ እንዲሰራ ማድረግ ሲገባዉ፣ ይህን ሳያደርግ አዲስ ጨረታ በማዉጣት ሥራዉ በከፍተኛ ወጪ እንዲሰራ ማድረጉ፣ በአመልካች ምክንያት የተፈጠረ ችግር እንጂ በተጠሪ በኩል የዉል ግዴታዉን ባለመወጣቱ የመጣ ችግር አለመሆኑን ያስገነዝባል፡፡ ስለሆነም በግራ ቀኛቸዉ መካከል በተደረገዉ ዉል መሰረት ሁለተኛዉ ምዕራፍ የጥገና ሥራ ሳይከናወን የቀረዉ አመልካች በዉሉ በተመለከተዉ አግባብ ባለመፈጸሙ እንጂ ተጠሪ የዉል ግዴታዉን ሳይወጣ በመቅረቱ መሆኑን የሚያመለክት ነገር የለም፡፡ አመልካች ራሱ በዉሉ በተመለከተዉ አግባብ ሳይፈጽም የቀረ በመሆኑና ተጠሪ የዉሉን ግዴታ ባለመወጣቱ ስላልሆነ፣ ለደረሰዉ ጉዳት ተጠሪ የጉዳት ኪሳራ እንዲፍለዉ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1771 መሰረት የሚጠይቅበት አግባብ የለም፡፡ ስለዚህ የሥር ፍ/ቤቶች በዚህ ጉዳይ የሰጡት ዉሳኔ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ.1731፣ 1771 1790 እና 2090 አንጻር ሲታይ የሚነቀፍበት የህግ አግባብ የለም፡፡ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በኢፌዴሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80 (3) (ሀ) እና አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2 (4) (ለ) እና 10 (1) (ለ) መሰረት ከተሰጠዉ ስልጣን አንጻር አመልካች ያቀረበዉ ቅሬታ የሥር ፍ/ቤት በሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆኑን የሚያመለክት ስላልሆነ ቅሬታዉ ተቀባይነት የለዉም ብለናል፡፡

ሲጠቃለል የሥር ፍ/ቤቶች በዚህ ጉዳይ የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት ስለሆነ ተከታዩን ወስነናል፡፡

**<u>ዉሳኔ</u>**

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ.213668 ሚያዚያ 30 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 (1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
3. ግራ ቀኙ የሰበር ክርክር ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

*ማ ሳታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/ተ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰበር መ/ቁ 226211

ጥቅምት 2 ቀን 2016 ዓ.ም

ዳኞች፡ ብርሃኑ አመነው

ረታ ቶሎሳ

በእውቀት በላይ

ቀነዓ ቂጣታ

ኑረዲን ከድር

አመልካች፡- አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ አ.ማ----------- ጠበቃ ዳዊት አወቀ ቀረበ

ተጠሪ፡- አቶ ሰጤ ፋንታዬ ----------------- አልቀረበም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

መዝገቡ ለዚህ ችሎት የቀረበው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 77806 በቀን 09/11/2013 ዓ.ም በሰጠውን ብይን ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 280788 በቀን 30/05/2014 ዓ.ም ይግባኙን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 337 መሰረት በመሰረዙ ዉሳኔዉ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል በሰበር እንዲታረም አመልካች ባቀረበዉ አቤቱታ መነሻ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ሲታይ በስር ፍ/ቤት ከሳሽ አመልካች ሲሆን ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡አመልካች በስር ፍ/ቤት በቀን 11/12/2012 ዓ.ም ባቀረበዉ ክስ የመድን ሽፋን የሰጠዉ የሰሌዳ ቁጥሩ 3-60076 አ.አ ተሽከርካሪ ሰኔ 25 ቀን 2007 ዓ.ም በጉራጌ ዞን ሶዶ

ወረዳ ኬላ ቀበሌ ንብረትነቱ የተጠሪ ከሆነዉ የሰሌዳ ቁጥሩ 1-11026 ባጃጅ ጋር ተጋጭቶ ጉዳት በመድረሱ ተሽከርካሪውን ለማስጠገን ብር 60,903.75 (ስልሳ ሺህ ዘጠኝ መቶ ሶስት ከ75/100) ወጪ ያደረኩ በመሆኑ ተጠሪ ከነወለዱ እንዲከፍሉኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪ ባቀረቡት መልስ ለክሱ መንስዔ የሆነዉ አደጋ የደረሰው ሰኔ 25 ቀን 2007 ዓ.ም ሆኖ ክሱ የቀረበው ከ5 ዓመት በኋላ በመሆኑ በይርጋ ይታገዳል፣ ፍ/ቤቱ የስረ ነገር ስልጣን ቢኖረውም የግዛት ክልል ስልጣን የጉራጌ ዞን የቡታጅራ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት ስለሆነ ክሱ ውድቅ ይደረግልኝ በማለት መከራከሩን መዝገቡ ያሣያል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የቀረቡትን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችን በመመርመር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 24(3) መሰረትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር በመ/ቁ 43912 በሰጠው አስገዳጅ ትርጉም መሰረት የግዛት ክልል ስልጣን የለውም የሚለውን መቃወሚያ ውድቅ አድርጎ ክሱ በሁለት ዓመት ይርጋ ይታገዳል የሚለውን መቃወሚያ በመቀበል መዝገቡን በብይን ዘግቶታል፡፡አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ አያስቀርብም በማለት ይግባኙን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 337 መሰረት ሰርዞታል፡፡አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረበዉ ይህንን ብይን በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘት በአጭሩ፡-የሶዶ ወረዳ ፖሊስ ጽ/ቤት በቁጥር ሶ/ወ/ፖ2577/2007 በቀን 1/11/2007 እና የሶ/ወ/ፖ3185 በቀን 26/09/2010 ዓ.ም በሰጠው የትራፊክ አደጋ ሁኔታ የተጠሪ ሹፌር የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ መንጃ ፈቃድ ሳይኖረው ያለጥንቃቄ ሲያሽከረክር የነበረ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 600/2000 አንቀጽ 21(1)(2) እና በዚሁ አዋጅ የጥፋትና ቅጣት ደንብ ሰንጠረዥ "ለ" ስር እና በደንብ ቁጥር 208/2003 አንቀጽ 85 እና በእርከን ሰንጠረዥ "ለ" ስር የሚስቀጣ ከባድ ጥፋት እንደሆነ በግልጽ ተደንግጎ እያለ እና በወንጀል ህግ አንቀጽ 572 መሰረትና በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር በመ/ቁ 117877 (ቅጽ20) በሰጠው ትርጉም መሰረት በወንጀል የሚያስቀጣ በመሆኑ ከውል ውጭ ሀላፊነት ክስ ማቅረቢያ ይርጋ ጊዜ በፍ/ብ/ህ/ቁ 2143(2) እና በወንጀል ህጉ አንቀጽ 217(1(ሠ)) መሰረት 5 ዓመት በመሆኑ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች አቤቱታ በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ በኢንሹራንስ የመዳረግ ክስ መቼ ነው የሚያቀርበው ይርጋ መቆጠር የሚጀምረው መቼ ነው? የፍ/ብ/ህ/ቁ 2143(2) … ጉዳቱ

በወንጀል የሚያስቀጣ ከሆነ... የወንጀል ይርጋ የሚወስደው ከሆነ የሚለውን ለመመርመር ሲባል መዝገቡ ለሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ታዟል፡፡ተጠሪ ባቀረቡት መልስ ለአደጋው መንስዔ የሆነውን ጥፋት ያጠፋው ማን እንደሆነ አልተረጋገጠም፤በወቅቱ የትራፊክ ፖሊስ የአደጋ ፕላን ያላነሳ በመሆኑ ጥፋተኛው ባልተረጋገጠበት የተጠሪን ባጃጅ ሹፌር በወንጀል ህግ አንቀጽ 572(1) ወንጀል የሚያቋቁም ድርጊት ባለመፈፀሙ ክስ አልተመሰረተበትም፤ ከይርጋ ጋር በተያያዘ የፍ/ብ/ህ/ቁ 2143(2) ተፈፃሚ አይሆንም፤ ተጠሪ የተከሰስኩት በሌላ ሰው ድርጊት ኃላፊ ተብዬ በመሆኑ ተፈፃሚ የሚሆነው የፍ/ብ/ህ/ቁ 2143(1) ስር የተመለከተው 2 ዓመት የይርጋ ጊዜ በመሆኑ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ይጽናልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኙ ክርክር በአጭሩ ከላይ የተገለጸዉን የሚመስል ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ዉሳኔ አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን መርምረናል፡፡እንደመረመርነዉ አመልካች በተጠሪ ላይ ክስ ያቀረበዉ ንብረትነቱ የተጠሪ የሆነ ተሽከርካሪ ከአመልካች ደንበኛ ተሽከርካሪ ጋር በመጋጨት በደረሰዉ ጉዳት መነሻ ለደንበኛዉ የከፈለዉን ካሳ ተጠሪ እንዲከፍሉት መሆኑን ክርክሩ ያሣያል፡፡ከዚህ መገንዘብ የሚቻለዉ አመልካቹ ክስ ያቀረበዉ በመድን ገቢዉ መብት በመዳረግ ወይም በመተካት መብት መሆኑን ነዉ፡፡በንግድ ህጉ አንቀጽ 683(1) ላይ እንደተደነገገዉ ኢንሹራንስ ሰጪዉ በከፈለዉ ካሳ መጠን ጉዳቱ እንዲደርስ ባደረጉት ሶስተኛ ወገኖች ላይ ክስ ለማቅረብ ኢንሹራንስ ለገባዉ ሰዉ በተከፈለዉ ገንዘብ መጠን ባሉት መብቶችና ክሶች ኢንሹራንስ ሰጪዉ ምትክ ሆኖ እንደሚገባ ተመልክቷል፡፡ይህም የመዳረግ መብቱ ከዉል ሳይሆን ከህግ የመነጨ መብት መሆኑን ያሥገነዝባል፡፡በዚህ አግባብ መድን ገቢዉና ተጠሪ ያላቸዉ ግንኙነት የተመሰረተዉ ከዉል ዉጭ በመሆኑ አመልካቹ በመድን ገቢዉ እግር ተተክቶ የሚያቀርበዉም ክስ ከዉል ዉጭ ባለዉ የህግ ማእቀፍ የሚታይ ነዉ፡፡ከዉል ዉጭ በተፈጠረ ምክንያት (ግንኙነት) የሚቀርብ ክስ በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 2143(1) መሰረት ጉዳቱ ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ እስከሁለት ዓመት ባለዉ ጊዜ ዉስጥ ካልቀረበ በይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ ተደንግጓል፡፡በእርግጥ ጉዳቱን ያስከተለዉ ድርጊት በወንጀል የሚያስቀጣ ከሆነ ይርጋ ጊዜዉ የሚታሰበዉ በወንጀል ህጉ ይርጋ መሰረት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህጉ አንቀጽ 2143(2) ድንጋጌ ይዘት ያሥገነዝባል፡፡

በዚህ ጉዳይ የስር ፍርድ ቤቶች ይርጋ ጊዜዉን የቆጠሩት ጉዳቱ ከደረሰበት (25/10/2007ዓ.ም) ወይም አመልካቹ ለደንበኛዉ ካሳ ከከፈለበት (11/02/2008ዓ.ም) ጀምሮ ክስ እስከቀረበበት (11/12/2012ዓ.ም) ያለዉ ጊዜ ሲሰላ ሁለት ዓመት ያለፈበት መሆኑን በማረጋገጥ የፍ/ብ/ህጉን

አንቀጽ 2143(1) ምርኩዝ በማድረግ ይርጋ ጊዜ አልፎበታል የሚል ድምዳሜ ላይ መድረሱን ያሣያል፡፡አመልካቹም በዚህ ጊዜ አቆጣጠር ላይ ቅሬታ የለዉም፡፡ነገር ግን የተጠሪ ተሽከርካሪ አሽከርካሪ ድርጊት በወንጀል የሚያስቀጣ ጥፋት ፈጽሚል በሚል መነሻ ጉዳዩ በወንጀል ህግ አንቀጽ 572 እና ሰበር ችሎት በመ/ቁ 117877 (ቅጽ20) በሰጠዉ ዉሳኔ መሰረት የይርጋ ጊዜው በፍ/ብ/ህ/ቁ 2143(2) እና በወንጀል ህጉ አንቀጽ 217(1(ሠ)) መሰረት 5 ዓመት ይርጋ ጊዜ መሆን ነበረበት በሚል ቅሬታዉን አቅርቧል፡፡በሰበር አጣሪ ችሎት የተያዘዉ ጭብጥ ይህንኑ ቅሬታ ነጥብ አግባብነት ለመመርመር ነዉ፡፡

በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 2143(2) ስር "…ጉዳቱ በወንጀል የሚያስቀጣ ሆኖ…" የሚለዉ አገላለጽ የተፈጸመዉ ድርጊት በወንጀል የሚያስቀጣ ከሆነ የድርጊቱ ፈጻሚ በወንጀል ቢከሰስም፤ ባይከሰስም፤ቢቀጣም፤ ባይቀጣም የይርጋ ጊዜዉ የሚወሰነዉ ድርጊቱን የወንጀል ድርጊት ለሚያደርገዉ ወንጀል ህግ ድንጋጌ በተቀመጠዉ የይርጋ ጊዜ መሰረት ይሆናል ከሚል አላማ የተቀመጠ እንደሆነ የሚያስገነዝብ ነዉ፡፡ከዚህ ጋር በተያያዘ ሰበር ችሎቱ በመ/ቁ/58920 ላይ በቀን 22/06/2003ዓ.ም (በቅጽ 11 ላይ እንደታተመዉ) በሰጠዉ አስገዳጅ ትርጉም ላይ እንደተመለከተዉ ድርጊቱን የፈጸመዉ አሽከርካሪ በወንጀል አልተከሰስኩም ወይም አልተቀጣሁም የሚል ክርክር አቅርበዉ ድርጊቱ በወንጀል ህጉ እንደወንጀል ድርጊት የተደነገገ እስከሆነ ድረስ አሽከርካሪዉ በወንጀል ባይከሰስም በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 2143(2) የተደነገገዉ የይርጋ ጊዜ ተፈጻሚ ነዉ ተብሎ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ ነዉ፡፡በተያዘዉ ጉዳይ አመልካቹ አጥበቅ የሚከራከረዉ የተጠሪ ሹፌር የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ መንጃ ፈቃድ ሳይኖረው ያለጥንቃቄ ሲያሽከረክር የነበረ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 600/2000 አንቀጽ 21(1)(2) እና በዚሁ አዋጅ የጥፋትና ቅጣት ደንብ ሰንጠረዥ "ለ" ስር እና በደንብ ቁጥር 208/2003 አንቀጽ 85 እና በእርከን ሰንጠረዥ "ለ" ስር የሚስቀጣ ከባድ ጥፋት እንደሆነ በግልጽ ተደንግጎ እያለ እና ጉዳዩ በወንጀል ህግ አንቀጽ 572 እና ሰበር ችሎት በመ/ቁ 117877 (ቅጽ20) በሰጠዉ ዉሳኔ መሰረት የይርጋ ጊዜው በፍ/ብ/ህ/ቁ 2143(2) እና በወንጀል ህጉ አንቀጽ 217(1(ሠ)) መሰረት 5 ዓመት ይርጋ ጊዜ መታየት ነበረበት በማለት ነዉ፡፡

ይሁንና ፍሬነገር የማረጋገጥ ስልጣን የተሰጠዉ የስር ፍርድ ቤት ያረጋገጠዉ ፍሬነገር የሚያሣየዉ የተጠሪ ተሽከርካሪ አሽከርካሪ መንገድ አጠቃቀም ረገድ ባደረገዉ ቸልተኝነት ከአመልካቹ ደንበኛ ተሽከርካሪ ጋር ተጋጭቶ በንብረት ላይ ጉዳት ማድረሱንና ድርጊቱም የትራፊክ ደንብ በመተላለፍ በወንጀል ህግ አንቀጽ 856 ስር የሚያስቀጣ ድርጊት ስለመፈጸሙ እንጂ ሌላ ከባድ የወንጀል ድርጊት ስለመፈጸሙ የተረጋገጠ ጉዳይ ስለመኖሩ አያሣይም፡፡ይህ

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ከሆነ ደግሞ ይርጋ ጊዜዉ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 773 ስር እንደተደነገገዉ አንድ ዓመት በመሆኑ የፍ/ብ/ህጉ አንቀጽ 2143(2) ለዚህ ጉዳይ ተፈጻሚነት የለዉም፡፡ሌላዉ አመልካቹ የጠቀሰዉ ሰበር ችሎቱ በመ/ቁ/ 117877 የሰጠዉ ዉሳኔ ይዘት ሲታይ አሽከርካሪዉ በፈጸመዉ ከባድ ቸልተኛነት በሰዉ እና በንብረት ላይ ባደረሰዉ ጉዳት በተደራራቢ የወንጀል ድርጊት ጥፋተኛ ተብሎ የተወሰነ በመሆኑ ለተያዘዉ ክርክር በፍሬነገርም ሆነ ህግ አተገባበር ረገድ ተመሳሳይነት የለዉም፡፡

ሲጠቃለል ለክርክሩ ምክንያት የሆነዉ ጉዳት ከደረሰበት ጊዜ ወይም አመልካቹ ለደንበኛዉ ክፍያ ከፈጸመበትም ጊዜ ሲታሰብ ክሱ የቀረበዉ ሁለት ዓመት ካለፈ በኋላ መሆኑን በማረጋገጥ ክሱ በይርጋ ታግዷል በማለት የስር ፍርድ ቤት የሰጠዉ ዉሳኔ በክርክሩ የተረጋገጠዉን ፍሬነገር እና አግባብነት ያለዉን ህግ ያገናዘበ ነዉ ከሚባል በስተቀር በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4) እና 10 ስር ለሰበር ችሎቱ ከተሰጠ ስልጣን ጋር ተገናዝቦ ሲታይ በዉሳኔዉ ላይ በህግ አተገባበርም ሆነ አተረጓጎም ረገድ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚያስችል ምክንያት የለም ብለናል፡፡በመሆኑም የሚከተለዉ ተወስኗል፡፡

<u>**ዉሳኔ**</u>

1ኛ/ በዚህ ጉዳይ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/77806 ላይ በቀን 09/11/2013ዓ.ም የሰጠዉን ብይን በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/280788 ላይ በቀን 30/05/2014ዓ.ም የሰጠዉ ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሠረት ጸንቷል፡ ይጻፍ፡፡

2ኛ/ክርክሩ ያስከተለዉን ዉጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ዉሳኔ ያገኘ ስለሆነ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/ተ

*ማ ሰታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም